
ETHIO
PDF
BOOKS

ETHIO
PDF
BOOK

Scanned with CamScanner




Scanned with CamScanner

## መግለቢያ

“ምንማችን ሆይ በምንሞች የምትኖር፣ ምንምህ ይቀደስ፤ ምንምህ ትምጣ፤ ምንምህ በምንም እንደሆነች እንዲሁም በምንም ትሁን። የዕለት ምንማችንን ሁሉ ዛሬ ስጠን። ምንማችንን ሁሉ ምንም በለን። እኛም ምንም ያሉንን ሁሉ ምንም እንድንል። ወደ ምንም አታግባን፤ ከምንም አድነን እንጂ። ምንም ያነተ ናትና። ምንም፡ ቅብጥርስም፡ ምንትስም። አሜን።”

ተዚህ በላይ የሰፈረችው ጠሎት ጥቂት ጨማመርኩባት እንጂ የኧርነስት ሄሚንግዌይ ገፀ ባህርይ ጠሎት ናት። ምንሞች ለምንማቸው ቢጠልይዋት መልካም ናት። እኔም ለዚህች ምንሜ መግለቢያነት የጠለይኩዋት ወድጀም አይደል። በጠሎት ተጀምራም በሆነ! የመጀመሪያ ሥራዬን ብዙ ሰዎች በጠና ይጠይቁኛል። ይህችን ምንሜን ይገፔ እንዴት እሰው ፊት ልቅረብ እያልሁ ፈራ ተባ ስል ብዙ ጊዜ ፈጀሁ። አንድ በሥነ-ፅሁፍ ብስለቱ የማላማው ወዳጄ የምታቃልላትን ያህል ቀላል ሥራ አይደለችም፤ ልታሳትማት ይገባል ሲል መከረኝ። በሰውየው ምክር ብቻ የልብልብ ሳይሰማኝ ደጋግሜ አነበብኩዋት። በዘመኑ ካሉት ሳንካዎቻችን መሀል አንዱ ላይ አነጣጥራ የተጻፈች በመሆንዋ እኔም እየተቀበልኩዋት መጣሁ። እንዲያውም ያለውን የወረወረ ፈሪ አይባልም እንዲሉ በዚህች ልቦለድ ውስጥ በተነሳው ይዘት ላይ ያለችኝን መወርወሬ ተገቢ ነው ስል ደመደምኩ። አስተየብኩዋት፤ ከሁሉም ልቦለዶቼ በፊት የተቦረቦሰች ምንሜን። እጄን የፈታችው ምንሜን። እንደ ሌሎቹ ልቦለዶችህ በትረካዋ ውስብስብ አለመሆንዋን አንባቢ ከብኩርናዋ የመጣ ብቻም ሳይሆን ከአተራረኩዋ የመነጨ እንደሆነ ይገነዘባል ሲል ምንሜ ነግሮኛል። ምንሜን እስከ ምናምኑዋ ሳቀርብ ምንማችሁ ምንም ይበለኝ። ምንም።

ይስማዕከ ወርቁ… ፳፻፲፬ ዓ.ም

# የማይነበብ

ባለፉት ሥራዎቼ ላይ ዓመተ ምህረቶችን በተለይም መጻሕፍቱ የታተሙበትን ለመጥቀስ የምጠቀማቸውን ቁጥሮች አስመልክቶ ከተለያዩ አካላት አንዳንድ አስተያየቶች ደርሰውኛል፡፡ ከፊሎቹ ባለማወቅ የተጠቀምኳቸው መስሏቸው ትክክለኛ የመሰላቸውን ቁጥር ጠቅሰው ደብዳቤ ጽፈውልኛል፡፡ ገሚሶቹ ደግሞ ሆን ብዬ እያደረኳቸው ከሆነ ከምን ተነስቼ እንደሆነ እንድገልፅላቸው ይጠይቁኛል፡፡ ምናልባትም ይህኛው መጽሐፌም የታተመበትን ዘመን "፪፻፻፬ ዓ.ም" ብዬ ስፅፍ ግራ ሳይጋቡ አይቀሩም፡፡ ይህን ቁጥር በተመለከተ ጥቂት ላብራራ ወደድሁ፡፡


ከጥንትም ጀምሮ "፻፻" የሚለው ቁጥር ብዙ ሊቃውንትን ሲያነታረክ የቆዬ ቁጥር እንደሆነ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን ሳገላብጥ አግኝቻለሁ፡፡ ጥቂቶቹ '፻፻' የሚለው ቁጥር "አንድ ሺህ" ማለት ነው ሲሉ አያሌዎቹ ግን "አሥር ሺህ" ማለት ነው ይላሉ፡፡ ምንም እንኳ "ቁጥሩን በውል የማያውቅ ህዝብ!" አስብሎ የሚያስቅብን ቢሆንም ንትርኩ ምክንያት አለው፡፡ ምክንያቱም የተለያዩ ቀደምት መጻሕፍትም ይህንን ቁጥር አዛብተው ስለሚጠቀሙት፡፡ በእርግጥም የራሱ የዘመን ቀመር ያለውና ይህንንም ለዓለም ያስተዋወቀ ህዝብ ቁጥሩ ጠፍቶበት ግራ ሲጋባ ማየት ግራ ያጋባል፡፡

ይህንን በውል የታዘብኩት የኛው "ሁለት ሺህ" ዓመተ ምህረት ሲገባ ነው፡፡ ምሁራን የሚባሉት ሳይቀሩ ሲደናገሩ ሰምተናል፡፡ አንዳንዶቹ ይኸው አዲስ ዓመት ሲገባ "እንኳን ለክልኤቱ እልፍ (፪፻፻) በሰላም አደረሳችሁ" ሲሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ "እንኳን ለእስራ ምዕት (፳፻) በሰላም አደረሳችሁ" ሲሉ ተሰምተዋል፡፡ ለመሆኑ ለየትኛው ዓመት ነው በሰላም ያደረሰን? ለ፳፻ ወይስ ለ፪፻፻? (በምልክት ደረጃ)…. ዘግየት ብዬ ደግሞ ሌላ ጉድ ተመለከትኩ፡፡ ከሁለት ሺህ ዓመተ ምህረት ወዲህ

የታተሙት የኢትዮጵያ ገንዘቦች ያስደምሙኝ ጀመር፡፡ እነዚህን ገንዘቦች ልብ ብሎ ለተመለከተ እንደኔ ግራ መጋባቱ አይቀሬ ነው፡፡

"፪ሺህ" የሚለውን እንመልከት! "፪"ን እና "ሺህ"ን እዚህ ላይ ልብ ይሏል፡፡ የለማኝ እርሻ ነው ነገሩ፡፡ ዝንቅ! አህዝና ፊደል ተደባልቆ ሲጻፍ አይተንም ሰምተንም አናውቅ፡፡ "ሳይቸግር ጤፍ ብድር" እያስብለምን? ሲያውም የአንድ ታላቅ ሀገር ገንዘብ! የአንድ "ታላቅ መንግሥት" ገንዘብ! "በስንት ጥናት የተቀረጸ ገንዘብ"..... ከዚህ በላይ በስዕል የተቀመጡትን ሳንቲሞች ለተመለከተ(ያለውም ኪሱን ቢበረብር) ነገሩን በሙሉ ለማጤን ይችላል፡፡ የሳንቲሙ ቀራጮች ራሳቸው ያለ ዕውቀት እንደቀረጹትና በዚህም አይናቸውን በጨው ካላጠቡ በቀር ፪ሺህ ብለው ከቀረፁ በሁዋላ በሌላኛው ገንዘብ ላይ ደግሞ ፳፻፪ ብለው መቅረፃቸው ብዙ ሲያነጋግራቸው አይቀርም፡፡ ለምን ይህን ያህል በዚሁ ጉዳይ ለመጻፍ ፈለግህ ትሉኝ ይሆናል፡፡ ጥቃቅን የምንላቸው እና ትኩረት የማንሰጣቸው ጉዳዮች እንዝህላል እያደረጉን ነው ስል እመልስላችኋለሁ፡፡





የአክሱም ዘመን ታሪክን የታሪክ ተመራማሪዎች ሲጽፉ በሀውልቶችና በጥንታዊ ገንዘቦች ላይ የተቀመጡ ምልክቶች(symbols) ለምርመራቸው በጠና እንደተጠቀሙባቸው ይታወቃል፡፡ [illegible] የሰራው ታሪክም ጥሏቸው በሚያልፈው ምልክቶች (ወደደም ጠላም) ይገኛል፡፡ ጥንቁቅ ትውልድ ቲጠንቅቆ ምልክቶቹን ያኖራል፡፡ በእኛ ገንዘቦች ላይ ያሉት ምልክቶችና ቁጥሮች ግን በዘፈቀደ በእንዝህላልነት እንደተቀመጡ ማስተዋል ቀላል ነው፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ፪ሺህ ብለን የጻፍንበት ሳንቲም የትም ብንወረውረው መቆየቱ [illegible]፡፡



"ሺህ"የሚለው ቄጥር (symbol) ሲ[illegible] ህዝቦች እስከ ሺህ አልቆጠሩም ነበር እንዴ? አስብሎ [illegible] (የሰይጣን ከንፈር ይገጠምና)፡፡ ይኸን ካልኩ ዘንዳ እስካሁን በየመጻሕፍቱ ያገኘኋቸውን ውርክቦች ላስፍር፡፡

እነሆ ተቃርኖ!

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ "መጽሐፈ፡ ሰዋስው ወግስ፡ወመዝገበ፡ቃላት፡ ሐዲስ፡፡" በሚለው መጽሐፋቸው በገፅ ፵፩ ላይ የግዕዝ ቁጥሮችን ሰድረው እናገኛለን፡፡ በዚህ መልክ፡፡

፩ ፪ ፫ ፬ ፭ ፮ ፯ ፰ ፱ ፲ ፳ ፴ ፵ ፶ ፷ ፸ ፹ ፺ ፻ ፲፻ ፼
(ሰረዝ የተጨመረ፡፡)

ከሰረዙ በላይ ያሉትን ፲፻ እና ፼ ያጨኗል፡፡ እንደ እርሳቸው አመጣጥ የትኛውም ቁጥር አጣማሪ የለውም ነበር፡፡ ለምሳሌ "ሃያ" (፳) ለማለት ፪፲ አላሉም፡፡ አያስኬድምና፡፡ ፻(መቶ) ካሉ በኋላ ግን ሺህ ለማለት ፲፻ ብለዋል፡፡ ይህም ማለት ፲(አሥርን) እና ፻(መቶን) አጣምረው ያመጡት ጥቅል የቁጥር ወኪል ሆነ ማለት ነው፡፡ የግዕዝ ቁጥሮችን ባህሪ ስንመለከት ግን ይህ ባህሪ የላቸውም፡፡ የአረብኛውን የቁጥር ስደራ ብንመለከት መሠረታዊ የሚባሉትን ከዜሮ እስከ ዘጠኝ ያሉትን (0—9) ቁጥሮች በመጠቀም ብቻ እስከ አሻው ይቆጥራል እንጂ ለመራሄ ቁጥሮች (ለምሳሌ ለአሥር፣....ለመቶ፣ ለሺህ ወዘተርፈ....) ራሱን የቻለ ልዩ ምልክት የለውም፡፡

የግዕዝ አቆጣጠር ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ለእያንዳንዱ መራሂ ቁጥር (ለምሳሌ ፲፣ ፳፣ ፴ ...፻ ...) የራሱ ምልክት አለው እንጂ (ከመሠረታዊ ቁጥሮች በቀር) ቁጥሮችን በማገጣጠም አይጠቀምም፡፡ ለመቶ (፻) ምልክት እንዳለው ሁሉ ለሺህም ምልክት ያበጃል እንጂ አሥርን (፲) እና መቶ(፻)ን አጣምሮ ምልክት አያበጅም፡፡ ለሺህ ምልክት ሳያበጅ ለአሥር ሺህ ምልክት ያበጃል ብሎ ማመንም አጉል ነው፡፡ እንደዛ ከሆነማ ለሃያ ሺህም ቀጥለው ላሉትም ምልክት ሊያስፈልገው ነው፡፡ ሺህን ዘሎ ለአሥር ሺህ ፼(እልፍ) የሚባል ምልክት (symbol) ያበጃል ብዬ ማመንም በግሌ ይቸግረኛል፡፡ የሚያሳምነኝም አጥቼ ትቼዋለሁ፡፡ ይልቁንስ እኔ ላሳምን፡፡ (ቀና ሲታጣ ይመለመላል ጎባጣ ብላችሁ ብታሸማጥጡኝ ቅር አይለኝም፤ልክ ናችሁ፡፡)

Scanned with CamScanner

እልፍ የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ቋንቋ "ኤልፍ" የሚባለው ነው:: በዓረብ ቋንቋ ደግሞ "እልፍ" ይባላል:: በሱርት ቋንቋ ደግሞ "አሌፍ" ይሰኛል:: በነዚህ ቋንቋዎች ሺህ ማለት ነው:: አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ራሳቸው የጻፉትን ቃል በቃል ላስቀምጥማ::

"... ዕብራይስጥና፡ ሱርት፡ ግን፡ ሺሁን፡ እልፍ፡ ብለው፡ እልፉን ሪቦ ይላሉ:: ዐረብና ትግሬም እንዲሁ ናቸው:: ..." ብለው ነገሥትን ይጠቅሳሉ-አለቃ:: "ወቀተለ፡ እምተዓይኒሆሙ ለአሦር አሰርተ፡ ወሰመንተ፡ እልፈ፡ ወሃምሳ ምዕተ::" በአማርኛ ብንተረጉመው እንግባባ ስለመሰለኝ እነሆ:: "... ከአሦራውያንም ሰፈር መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ገደለ::" (ሰረዝ የተጨመረ) መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ፲፱፥፴፭:: እዚህ ላይ እልፍ የሚለው ሺህ ተብሎ እንደተፈታ ማወቅ ቀላል ነው:: የእንግሊዝኛውን እንጨምርበት:: "... and slew a hundred and eighty five thousand in the camp of the Assyrians ..." ይለዋል::

እስኪ "ዘዳግም ፭፥፲"ን እንመልከት:: የግዕዙ መጽሐፍ ቅዱስ "እስከ እልፍ ትውልድ" የሚለውን የአማርኛው "እስከ ሺህ ትውልድ" ይለዋል፤ የእንግሊዘኛውም "... But showing steadfast love to thousand of those who love me and keep my commandments" ይላል:: ሶስቱንም ብናመሳክር ያው ነው:: እልፍ፡ ሺህ፡ ሆኖ እናገኘዋለን::

የሰሎሞንን መጽሐፍ እንመልከት:: መሐልዬ መሐልዬ ፭፥፲:: "ውሉድ እምአእላፍ" የግዕዙ መጽሐፍ ቅዱስ:: "ከእልፍ የተመረጠ ነው" የአማርኛው:: " outstanding among **ten thousand**" የእንገሊዝኛው:: እዚህ ላይ ከግዕዙ ወደ አማርኛው ሲተረጎም በራሱ እንደተዛነፈ ይስተዋላል:: የግዕዙ "አእላፍ" የሚለውን አማርኛው "እልፍ" ይለዋል:: እንግሊዝኛው ደግሞ "Ten thousand"! እዚህ ላይ "እልፍ" እና "አእላፍ" የሚሉትን ቃላት ልብ ይሏል:: በ"ሺህ" እና "በአስር ሺህ" መሃል ያለ

ልዩነት ነው፡፡ የእንግሊዝኛውም እዚህ ላይ ቃፊር ይቆማል፡፡ <u>አእላፍ</u> እንጂ <u>እልፍ</u> አስር ሺህ አለመሆኑን (ten thousand=10,000)፡፡

"ትንቢተ ዳንኤል" የሚባለውን መጽሐፍ እንመልከት፡፡ "ወየአውድዎ <u>እልፍ</u> ወትእልፊተ አእላፋት" ትንቢተ ዳንኤል ፯÷፲ የግዕዙ፡፡ "ሺህ ጊዜ ሺህ ያገለግሉት ነበር፡፡ አእላፊ አእላፋትም በፊቱ ቆመው ነበር፡፡" የአማርኛው፡፡ "Thousands upon thousands attended him, ten thousand times ten thousand stood before him" የእንግሊዝኛው፡፡

የዳዊትን መዝሙር እንመልከት፡፡
"ይወድቁ በገበኩ አሰርቱ ምዕት፡፡ <u>አእላፍ</u> በየማንከ፡፡" የግዕዙ መጽሐፍ ቅዱስ መዝሙር ፺÷፯፡፡ "አጠገብህ ሺህ፡፡ በቀኝህም <u>አሥር ሺህ</u> ይወድቃሉ፡፡" የአማርኛው፡፡ "A thousand may fall at your side, **<u>ten thousand</u>** at your right hand" የእንግሊዝኛው፡፡ ልብ እንበል፡፡ እዚህ ላይ <u>አእላፍ</u> የሚለው ቃል <u>አሥር ሺህን</u> ወክሏል፡፡ እንቀጥል፡፡

የዮሐንስ ራዕይን እንመልከት፡፡
"እለ እምውስተ ህዝበ ይሁዳ <u>፪፼ ወ፳፻</u>" ራዕይ ፯÷፭ የግዕዙ መጽሐፍ ቅዱስ፡፡ "ከይሁዳ ነገድ <u>አሥራ ሁለት ሺህ</u> ታተሙ፡፡" የአማርኛው፡፡ እንዴት እንዴት? እዚህ ላይ ከግዕዝ ወደ አማርኛ ሲተረጎም ብዙ ስህተት እንደተፈጠረ ውኸ'ንብሩም የአማረኛው ትርጉም ያመጣው እንደሆነ ልብ ያለው ልብ ይላል፡፡ እውቀቶቻችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከሰሙ እንደመጡ መገንዘብም ቀላል ነው፡፡

ኦሪትን እንመልከት፡፡
"ወይገብር ምህረተ <u>ላዕለ አእላፍ</u>" ዘፀአት ፴፬÷፯ ግዕዙ፡፡
"ቃልኪዳኔንና ምህረቴን <u>እስከ ሺህ</u> ትውልድ የምጠብቅ የታመንኩ አምላክ እኔ ነኝ፡፡" የአማርኛው፡፡ ጭራሽ አእላፍ ሺህ ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ እዚህ ላይ ደግሞ ሌላ ተቃርኖ፡፡ የአቶ አስረስ የኔሰውን

“ትቤ አክሱም መኑ አንተን”ና የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌን “መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ”ን ለተመለከተ በዚሁ የማይፈታ የ፲፻ ውዥንበር ውስጥ ማለፉ አይቀሬ ነው:: መፍትሔው ምንድን ነው? ከላይ የጠቃቀስናቸውን ጥቅሶች ስንመረምር ፲፻ የሚለው ምልክት ቃፊርነቱ ለ “ሺህ” እንደሆነ እንመለከታለን:: በመሠረቱም የግዕዝ ቁጥሮች አካሄድ ሙሉ ሙሉውን በመርገጥ ስለሆነ “፲፻” የሚወክለው “አሥር ሺህ”ን ነው ለማለት አያስደፍርም:: ፲(አሥር)፣ ፳(ሃያ)፣ ፴(ሠላሳ)፣ ፵(አርባ)፣ ሃምሳ(፶)፣ ስሳ(፷)፣ ሰባ(፸)፣ ሰማኒያ(፹)፣ ፺(ዘጠና)፣ ፻(መቶ) እያለ የሄደ የቁጥሮች ምልክት “ሺህን” (፲፻) ዘሎ ለአሥር ሺህ ምልክት (symbol) ያበጃል ማለት አያስደፍርም:: እንግዲህ ከዚህ በላይ በምን መግባባት እንችላለን? ወይስ “በምን እንግባባ” የሚለውን ዘፈን ተገባብዘን እንለያይ? ምርምራችንን በመቀጠል የጠፉብንን ምልክቶች (symbols) ማፈላለግ ካልቻልንም ያፉልጉኝ ማስታወቂያ ለጥፈን (እንደለመድነው) የአውሮጳ ምሁራን መጥተው እስኪያገኙልን መጠበቅ ከዛም “እገሌ” የሚባለው የአውሮጳ ተመራማሪ ያፀደቀውን ማስተጋባት:: ይህቺ ሀገር የጠፉባት ብዙ ቅርሶች ብቻ ሳይሆኑ፣ ብዙ ዋሻዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ ብዙ የብዙ እውቀቶች የተዳፈኑባትና የምስጢሩ መክፈቻ ቁልፍም የተሠወረባት እንደሆነች ከዚህ በላይ ማስረጃ የለም:: ምልክቶቿን ያጣ ትውልድ፣ እውቀቶቿን ያጣ ትውልድ፣ ... አያስብልም? ሳንቲሞቻችሁን ተመልከቱ:: ትደነግጣላችሁ:: እኔ በበኩሌ መጻሕፍቶቼ የታተሙበትን ዓመተ ምህረት “፲፻”ን ለአንድ ሺህ እየወከልኩ እቀጥላለሁ:: ያገኘሁት የሚያጠግበው አመክንዮ ይኸው ብቻ ነው:: እነሆ ፳፻፲፩ ዓ.ም:: እንኳን ለ፳፻፲፩ዓ.ም አደረሳችሁ:: ቂቂቂ...... ወደ ትረካው ይዣችሁ ልግባ::

ይስማዕከ ወርቁ.... ፳፻፲፩ ዓ.ም

# ኢካቦድ

“የፊንሐስም፡ ሚስት፡ ተንበርክካ፡ በወለደች፡ ጊዜ፡ የብላቴናውን፡ ስም ኢካቦድ፡ ብላ፡ ጠራችው። የእግዚአብሔር፡ ታቦት፡ ተማርካለችና፡ “ክብር፡ ከእስራኤል፡ ለቀቀ” ስትል።

መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ፬÷፳፪

Scanned with CamScanner

# ባለሜንጦዎቹ

"የኤሊም ልጆች፡ ምናምንቴዎች፡ ነበሩ። እግዚአብሔርንም፡ አያውቁም፡ ነበር። የካህናትም፡ ልማድ፡ በህዝቡ፡ ዘንድ፡ እንዲህ፡ ነበረ፥ ሰው፡ ሁሉ፡ መስዋዕት፡ ሲያቀርብ፡ ሥጋው፡ በተቀቀለ፡ ጊዜ፡ የካህኑ፡ ሎሌ፡ ይመጣ፡ ነበር። በእጁም፡ ሦስት፡ ጣት፡ ያለው፡ ሜንጦ፡ ነበረ፥ ወደ፡ ድስቱም፡ ወይም፡ ወደ፡ ምንቸቱ፡ ወይም፡ ወደ፡ አፍላሉ፡ ወይም፡ ወደ፡ ቶፋው፡ ይሰድደው፡ ነበር። ሜንጦውም፡ ያወጣውን፡ ሁሉ፡ ካህኑ፡ ለእርሱ፡ ይወስደው፡ ነበር።"

መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ፪፥፲፪

Scanned with CamScanner

# ፩

ደንገዝገዝ ብሏል፡፡ ከባህርዳር ከተማ ሰሜናዊ ምዕራብ አቅጣጫ የምትገኘዋን የገጠር ቀበሌ ጨለማ እንደ ጥቁር በርኖስ ጎፋፍኗታል፡፡ የደብረ ማርያምን ቀበሌ፡፡ ከዓሳማዎች መርቢያ መንደር ዝቅ ብላ የምትገኘዋ ደሳሳ ጎጆ ውስጥ የኩራዝ መብራት ጭል ጭል ትላለች፡፡

በዚህች ደሳሳ ጎጆ ውስጥ አራት ጣልያናውያንና ሦስት ኢትዮጵያውያን ለጥብቅ ጉዳይ ተሰባስበዋል፡፡ አንደኛው የፈረንጆቹ አስተርጓሚ ሲሆን ሁለተኛውና ዋናው ተደርዳሪ ቄስ ፀሐይ የሚባለው እውቅ ቄስ ነው፡፡ ለዚህ ድርድር ሁኔታዎችን ያመቻቸው የቀበሌው ሊቀ መንበር አቶ አዳምጠውም የተደራዳሪው ቄስ ወንድም ይሁን እንጂ ባለድርሻ እንደመሆኑ ለድርሻው ወገቡን ጠበቅ አድርጎ በመከራከር ላይ ነው፡፡

ስብሰባቸው በአካባቢው ድምፅ ታጅቧል፡፡ ያልተራከቡ ላሞችና ጥጆች ድምፅ ከወዲያ ወዲህ ያስተጋባል፡፡ የመጥባትም የመጠባትም ድምጽ አላባራም፡፡

“አይበቃኝም!” እጆቹን አወናጨፈ ቄስ ፀሐይ፡፡ “ለሶስቱ የወርቅ መስቀሎች እንዴት ይሄ ይበቃል ብላችሁ አሰባችሁ? እኔ እኮ እነዚህን ጥንታዊ መስቀሎች በጥብቅ ከሚጠበቁ ቤተ መቅደሶች እንጂ ከዱር እየለቀምኩ አላመጣቸውም፡፡”

"ይህን ያህልማ ነገሩን ዝናብ እንዳደረበት ጅራፍ አታክብደው! ደከም ያለ አንድ ኢትዮጵያዊ ቄስ ቢያንስ ሁለት መስቀል ይኖረዋል።"
"እና ሊባርክበት እንጂ አትርፎ ሊሸጠው ይመስልሃል ይዞት የሚዞር?"
"ለመንጠቅ ቀላል ነው ለማለት ፈልጌ ነው።"
"እናንተ ሰዎች የምታስቡት ሁሉ ግራ እየሆነብኝ ነው። እያመጣህ ሸጥልን ያላችሁኝ ጥንታዊ ቅርሶች ከወርቅ ወይም ከአልማዝ የተሰሩ መሆናቸው ብቻ በቂ እንዳልሆነ ነግራችሁኝ ነበር። አሁን ደግሞ ..."
"አሁንም የጠየቅንህ ሌላ ነገር አይደለም። እ ..."
"እነዚህን ሶስት የወርቅ መስቀሎች አንጠረኛ ቤት ወስጄ ባስቀጠቅጣቸው ስንት ቀለበቶችና ስንት ሀብሎች እንደሚወጧቸው አስባችሁታል? እሄን ያህልማ ጅል አታርጉኝ። ..." ሶስቱንም መስቀሎች ከጠረጴዛው ላይ አንስቶ ወደ ጃኬቱ ኪስ ሊከት ሲል አራቱ ጣልያናውያን እመሃላቸው ተቀምጦ ወደ ሚደራደረው ኢትዮጵያዊ እኩል አፈጠጡ።

"*ኪ ኮዛ ኢ ኢን ሱ?- ምን ተፈጠረ?*" አለ አንደኛው ጣልያናዊ በጣልያናዊ ቅላፄ።
"*አ ቢዞኞ ዲ ፒዩ ሶልዲ- ተጨማሪ ገንዘብ ይፈልጋል።*" አስተርጓሚው መለሰ።
"*ኳንቶ?- ምን ያህል?*" ጣልያናዊው የእጅ ቦርሳውን መሸርገጊያ እንደ ፒያኖ ቁልፍ እንሴጥሲጠ ከፈተው። በግምት ጣቶቹ መጥነው የመዘዟቸውን የዶላር ኖቶች ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ።

"እየውልህ እነሱ'ኮ ሊከፍሉኝ ነበር። የአበሻ ነገር ሆኖብህ አንተ ሆድህ ጮ'ኸ እንጂ!" ባለመስቀሉ ፊቱ እንደ ጥቢ ሰማይ እየተፈታ መስቀሎቹን ወደ ጠረጴዛው መለሰ።
"እንደዚህማ አትበል! የሽቀላህ መስመር እኔ ስለሆንኩ ይህን ማበላሸት የለብህም።"
"እነዚህን መስቀሎች የምሸጣቸው ከጎተራዬ እያወጣሁ እንዳልሆነ ታውቃለህ። ይህም ራሱ የድካሜ ዋጋ አይደለም። ሰው ሲቸግረው ...

ልብሱን፣ የቤት ዕቃውን፣ ኩላሊቱን ሳይቀር ሊሸጥ ይችላል። ህሊናውን ሲሸጥ ግን በጠና ቸግሮታል ማለት ነው።"
"ይህንንስ አትበል! ምን ቸግሮህ?! የኮሸኮሽ መንደርን ጠላ ለመኮምኮም ነው አትለኝም በአጭሩ?! ይልቅ ማታ እንዳትረሳኝ!"
"አጥብቆ ያልቸገረው ዘርና ቅርስ አይሸጥም!"
"… 'የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም' ሆኖ እንጂ ነገሩ እሱስ ልክ አይደለህም።"
"ያበሰበሰን ዝናብ አባራም አላባራም ያው ነው። ዋናው ነገር ተገቢውን ዕቃ በተገቢው ዋጋ መሸጥ ነው። … 'የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጣጣ' አሉ!"
"በጭራሽ?! መስቀሎቹን እኮ የሠራሃቸው ነው የመሰልከው! ተገቢውን ክፍያ አላገኘሁም እያልክ ነው?"
"በደንብ! አሁን የብራናው መጽሐፍ ዋጋ ልክ ነው? የታቦቱ ዋጋስ ቢሆን? …"
"ተው! ለተሠረቀ እቃ እንዲህ ዓይነት ክፍያ ተደርጎም አይታወቅ!"
"ኡኡቴ! 'ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል' አሉ! … ባለፈው ለነዛ እንግሊዞች ያንን አይጥ በልቶ የጨረሰው የብራና መጽሐፍ ስንት እንደሸጥኩላቸው ታውቅ የለ?!"
"ታድያ አይጥ የበላው ነዋ!"
"እና ብራና የሚበሉ አይጦች ማርባት አለብኝ?"
"አይ ቄስ ፀሐይ! … እናንተ ደቀ መዛሙርት ስትባሉ ደግሞ ዋጋ አይበቃችሁም። እንኳን ታቦት ኢየሱስ እንኳ የተሸጠው በሰላሳ ዲናር አይደለም እንዴ?"
"በኢየሱስ ዘመን በነበረው የዲናር ምንዛሬ እና በአሁኑ ዶላር ሽሽሬታ መካከል ያለው ልዩነት አልገባህም ማለት ነው። እኔ እኮ በኢየሱስ ዘመን የነበረን ውድ ዕቃ በአሁኑ የዶላር ምንዛሬ እያቀረብኩ …"
"እውነት ነው የምልህ ቄስ ፀሐይ ይህንን ያህል ዋጋ ፓትርያርኩ እንኳ የሚጠይቁ አይመስለኝም።"
"እሳቸው ዘንድ የሚቀንስ ዕቃ ካገኛችሁ ሞክሩ። ምናልባት ቆባቸውንም በርካሽ ይሸጡላችሁ ይሆናል።"

"እ አንከራ ቢዞኞ ዲ ፒዩ ሶልዲ? - አሁንም ተጨማሪ ገንዘብ ይፈልጋል?" ሽምገል ያለው ጣልያናዊ ጭቅጭቃቸው አሳምሮ ብሎት ጠየቀ።

"ኖ! ኖ! ኖ!... ሶሎ ስቲያሞ ዲስኩቴንዶ ሪባልታ ዴሌ ፕሮሲሜ ሚሲዮኒ-አይደለም! አይደለም! አይደለም! ... ስለ ቀጣዩ ዘመቻ በመመካከር ላይ ነን።" አስተርጓሚው ፈርጠም ብሎ መለሰ።

"ለመሆኑ የአባ ሰባጋዲስን ጉዳይ እምን ላይ ደረሰ?!" ሲል እንደገና ቄስ ፀሐይን ጠየቀ።

ቄስ ፀሐይና አዳምጠው ላፍታ ተያዩ።

"ዕቃዎቹን የሚያስቀምጡበትን ቦታ ፍንጭ ማግኘት አልተቻለም። የዋዛ ሽማግሌ አይደሉም።"

"በባሌም በቦሌም! በውድም በግድም ዕቃዎቹን ማግኘት አለብን። ቄስ ፀሐይ ስማኝ ... ይህ ህይወታችንን የሚለውጥ ጉርሻ የሚገኝበት ጉዳይ ነው።"



# ፪

አባ ሰባጋዲስ በጣና ሐይቅ ምሥራቃዊ ተራሮች አናት ላይ ቀልታ የምትጠልቀውን ጀምበር በመሸኘት ላይ ናቸው። ቀዝቃዛው የምሽቱ ነፋስ ቢጫ መጎናፀፊያቸውን ሲያርገፈግፈው ከሩቅ ላያቸው ሲበር ክንፉን የሚያማታ አሞራ ይመስላሉ። የጣና ማዕበል ከቆሙበት ቋጥኝ ስር እየተጋጨ ሲመለስ ፍንጣቂው ቢረጫቸውም ከምትጠልቀው ጀምበር ጋር የጠለቁት ጥቃቅን ዓይኖቻቸው ወደ እርሳቸው አልተመለከቱም። ላለፉት አያሌ ዓመታት ፀሐይ ስትወጣና ስትጠልቅ የማየት ልማዳቸው አልተስተጓጎለም። በእነዚህ ሁለት ቅጽበቶች ሌላ ሀሳብ ከአእምሮአቸው እንዳይሰነቀር አርገው በጥልቅ ተመስጦና ጥሞና መሆን ልማዳቸው ነበር። ዛሬ ግን በጥልቅ ተመስጦና ጥሞና ውስጥ ለመገኘት አዳግቷቸዋል። ፀሐይዋ ስትጠልቅ ያለወትሯቸው በፍርሃት ይንቀጠቀጡ ጀመር። ትናንት ሌሊት እንደ ዓይናቸው ብሌን የሚጠብቁትና በጥንታዊ ቅርሶች የተሞላው ቦታ ሲመዘበር ሲል ታላቁን ደወል በመደወልና ጥንታዊውን ቱልቱላ በመንፋት ነበር ያስጣሉት።

በዚህ የሃሳብ ቱማታ ላይ እያሉ ዓሳ አጥማጁ ይበልጣል እንደተለመደው የምሽት መረቡን ጥሎ ሲመለስ ከሩቅ ተመለከቱት። ጸሎት ላይ ይሆናሉ ብሎ ስለሚያስብ ሁሌም በዚያ ሲያልፍ በሩቅ ከአንገቱ ዝቅ ብሎ ሰላምታ ሰጥቷቸው ቢያልፍ እንጂ ጮኾ እንደማይናገር ያውቃሉ።

"አቶ ይበልጣል!" ተጣሩ። ድምፃቸው በማዕበሉ ድምጽ ተውጦ ቀረ።

“እቶ ይበልጣል!?” ከእጃቸው የማትለይ መስቀላቸውን ወደ ይበልጣል ዘረጉት።
“እቤት አባቴ! ጠሩኝ ልበል?” ይበልጣል ታንኳውን መቅዘፉን አቁሞ ዞረ።
“እንደምን ውለሃል?”
“እግዚአብሔር ይመስገን ...”

“ፈለጉኝ አባ ሰባጋዲስ?” ያለወትራቸው ሲጠሩት መገረሙ ተሳበቀበት። “እሱላ ስምኑን ብቅ አላለምሳ በደህናው ነው?” ሲሉ ጠየቁ እየቀረበ ሲመጣ። እሱላ የዓሳ አጥማጁ ይበልጣል የሥጋ ልጅ ይሁን እንጂ ያስደጉት ራሳቸው አባ ሰባጋዲስ ናቸው። ሆኖም አስኳላ ትምህርት ከጀመረ ወዲህ ውሎውና አዳሩ ባህር ዳር በመሆኑ እየመጣ የሚጎበኛቸው የሳምንቱን የእረፍት ቀናት እሁድና ቅዳሜ ብቻ ነው።
“ምናልባት ፈተና ደርሶበት ጥናት ላይ ሆኖ ይሆናል። በአስቸኳይ ፈልገውት ከሆነ ወደዛው ሄጄ አመጣዋለሁ።”
“ካላስቸገርኩህማ...”
“ኧረ ግዴለም አባቴ። ደሞ አፈር ለሚበላው ጉልበት!”
“እግዚአብሔር ይባርክህ ልጄ! በል በደህና እደር። ጠዋት እኔ ዘንድ እንዲመጣ አድርግልኝ እንግዲያውስ።”

አባ ሰባጋዲስ ለዓይን ያዝ እስኪያደርግ እዛው እቆሙበት ቋጥኝ ቆይተው። ወደ በአታቸው ተመለሱ።



# ፲

ጠዋትም ሆነ፤ በሩም ተንኳኳ።
ኳ!

“ማነው በሬን የሚያንኳኳው?”

ኳኳ!
“ማነው መስኮቴን የሚያንኳኳው?”
ኳኳኳ!
“ማነው እኔን የሚያንኳኳኝ?”
ኳኳኳኳ!
“ማነው?!”
ኳኳኳኳኳ!
“ማንም አይቀሰቅሰኝም! አስቀድሜ ነቅቻለሁ!...”
ኳኳኳኳኳኳ!
“መቼም አልከፍትም!”
ኳኳኳኳኳኳኳ!
“ሌላ በር ሄደህ አንኳኳ”
ኳኳኳኳኳኳኳኳ!
“አጥብቀህ አንኳኳ!”
ኳኳኳኳኳኳኳኳ!
“ሌላ ሰው አንኳኳ!”

ኳኳኳኳኳኳኳኳኳ!

"እጥብቀህ ባንኳኳህ ቁጥር ቢያንስ አንድ ሰው ማንቃትህ አይቀርም!"

ኳኳኳኳኳኳኳኳኳኳ!

"እንኳኳ ቢያንስ ራስህ ትነቃለህ!፡፡"

ኳኳኳኳኳኳኳኳኳኳኳ!

"ክፍት ነው ግባ" ገባ፡፡

እድሜ ጠገቡን ሳንቃ ገፋ አደረገው፡፡ ሳንቃው ኀበዝ የሙዚቃ ሊቅ እንደቀመረው ረቂቅ ሙዚቃ አፏጭቶ ተከፈተ፡፡

በሩ አስቀድሞም ክፍት እንደነበር ያውቀዋል፡፡ ነገር ግን ከመግባቱ በፊት ዘወትር ይህን ያደርጋል፡፡ እነዚህን ንግግሮች ሳይሰማ መቼም ቢሆን እንዲገባ አይፈቀድለትም፡፡

እባ ሰባጋዲስ በዚህች በእታቸው ውስጥ ላለፉት አያሌ ዓመታት ሲኖሩ ማንም ወደዚህች ጎጆ ገብቶ የሚያውቅ የለም-ከእሱላ በቀር፡፡ ማንንም ስለማያስጠጉም "እባ ለራሱ" የሚል ቅፅል ስም ወጥቶላቸዋል፡፡

"እባ ለራሱ" ራሳቸው ባቁላቸው እያሾቁ፣ የሰነፍ ቆሏቸውን እያንቀራጩ ንፁህ ውሃቸውን ችልሰው በጥሞና ስለሚኖሩ ነው-ይህ ቅጽል ስም የወጣላቸው፡፡ ሆኖም ይህን ኑሮ እንደ እርሳቸው ያጣጣመው የለም፡፡ በዚህች ጎጆ ቤት ውስጥ የተከመሩትን እድሜ ጠገብ መጻሕፍት ሲያገላብጡ ይውላሉ፤ ያድራሉ፡፡ ለማንም አላሳዩም እንጂ ራሳቸውም በብራና ላይ የሚጽፉት መጽሐፍ አለ፡፡ በየጊዜው እንደገና በተበታተኑ የብራና ገፆች ላይ የሚጽፉት መጽሐፋቸው ገና አልተደጎሰም፡፡

እሱላ በሴሊት ከባህርዳር ገስግሶ መጥቶ ሲገባ እየፃፉ ነበር ያገኛቸው፡፡ ከፊታቸው ገጾች ጥቂቶቹ የብዕር ቀለማቸው እስኪደርቅ ተበታትነው ተቀምጠዋል፡፡ እሱላ ዓይኖቹን በሥርቅታ ወርወር እያደረገ ያነባቸዋል፡፡ ከወዲያኛው ጥግ የተሰጣው አንድ ገጽ ቀልቡን ሳበው፡፡



"... የምነናዬም አጀማመር እንዲህ ነው፡፡ ምነናዬ ከታላቁ ዓባይ ወንዝ ጋር ይቆራኛል፡፡ በዓባይ ዳርቻ... በአንድ የክረምት ወራት በዓባይ ሸለቆ ውስጥ ዋሽንቴን እያንቆረቆርኩ ከብቶች ሳግድ አንዲት ቆንጆ ልጅ ስትመለከተኝ አየሁ፡፡ ዋሽንቴን አቁሜ ተመለከትኳት፡፡ እሷ ዓባይ ወዲያ ማዶ ቆማ ነበር፡፡ እኔ ደግሞ ዓባይ ወዲህ ማዶ፡፡ አየኋት፡፡ አየችኝ፡፡ ልቤ ሲሞቅ ተሰማኝ፡፡ የኔ ልብ ሙቀት እንደ አዙሪት የሳባት ይመስል እሷም ሰበር ቀለስ ሳትል ተመለከተችኝ፡፡ የአንገቷ ላይ ድሪና ግማደ መስቀል በጠዋቷ ፀሐይ ጨረሮች ያብለጨልጫሉ፡፡ የጉንጯ ደም የፊቷን ቆዳ ወጥሮታል፡፡

የዓይኖቿ ጨረሮች እኔ ላይ ተተክለው ቀሩ፡፡ የእኔም እንደዛው፡፡ ወደ እሷ ሂድ ሂድ አለኝ፡፡ ግን በየት በኩል ልሂድ? ዓባይ ከአፍ እስከ ደገፉ ጢቅ ብሎ ሞልቷል፡፡ ፈረሰኛውን ተክሎ ይጥመለመላል፡፡ ወደ እሷ ለመሄድ ቢያንስ ብዙ አውራትን መጠበቅ አለብኝ፡፡ ዓባይ እስኪጎድል ግን ትዕግስት አጣሁ፡፡ በእርግጥም መታገስ የምችል አልመሰልህ አለኝ፡፡ ድልድይ ማጣት፡፡ ድልድይ፡፡ ልጅቷ ስታየኝ እኔም ሳያት ተፋጠን ከቆየን በኋላ አፈር ብላ በጀርባዋ ያዘለችውን ሻንኩራ አውርዳ ድፍርሱን የአባይን ውሃ ወዝ በጠገበ ዋምራ ቀድታ ተሸከመች፡፡ ወንዙን ብታጎድለው ምንኛ ደስ ባለኝ?

ምንም ሳንነጋገር ጀርባዋን ሰጥታኝ ሄደች፡፡ ወገቧን እንክት አርጋ ታጥቀዋለች፡፡ አስተጣጠቋን ልብ ብሎ ላየ ወገቧ የሚሰበር ይመስለዋል፡፡ ከኋላዋ ዓይኖቼ ተከተሏት፡፡ ቀሚሷ ወዲያና ወዲህ የሚያስዘፍነው ዳሌዋ ከዓይኔ እየራቀ ሄደ፡፡ ከዛች ዕለት ጀምሬ እዛው ቦታ እንደ ጅብራ ተገትሬ መዋል ሥራዬ ሆነ፡፡ እርሷ ግን ተመልሳ አልመጣችም፡፡ 'እንደምንም ይህን ወንዝ ተሻግሬ አገሩን ላስስ? ልፈልጋት?' እያልኩ ሳውጠነጥን ሰነበትሁ፡፡ አሁንም እሷን ዓባይ ዳር ቆሜ መጠበቄን አልተውሁም፡፡ የማግዳቸው ከብቶች የሰው አዝመራ እየፈጁ አባቴን ተጉረቤት አቀያየምሁት፡፡ ሆኖም እሷን መጠበቄን ማንም ሊያስቆመኝ አልቻለም፡፡ ..." ይኸኛው ገጽ አለቀበት፡፡

አሱላ ቀጣዩን ገጽ ለማንበብ ምራቁን እየዋጠ ዓይኖቹን ቢያንከራትትም ሊያገኘው አልቻለም። ሊጠይቃቸው አስቦ መልሶ ተወው። በሌላኛው ጥግ ያለው ገጽ የበለጠ አስደነገጠው። የመጨረሻው መስመር። "ተፈፀመ ዝንቱ መጽሐፍ በዕደ ሰባጋዲስ" ይላል። 'መጽሐፉን ጨርሰውታል ማለት ነው' ሲል አሰበ።

አባ ሰባጋዲስ በቁዘማ ጥቂት ካቀረቀሩ በኋላ ወደ አሱላ ተመለከቱ። አሱላም አንዳች ነገር በመጠባበቅ ወደ እርሳቸው ዓይኖቹን ወረወረ። በአንድ ቀን ሌሊት ያረጁ ይመስል ዓይኖቻቸው ሞጨሞጨበት። ፊታቸው እንዳልተተኮሰ ሸሚዝ ተጨረማመተበት።
"አባ ... ደህናም አይደሉ እንዴ?" አሱላ ፈራ ተባ እያለ ጠየቀ።
"ስጋት ገብቶኛል ልጄ። ስጋት።" ሐሜ በረዶ የመሰለ ጢማቸውን እያፍተለተሉ መለሱለት።
"የምን ስጋት? ..."
"አስቸጋሪ ዘመን መጥቷል። ቢታሪክ እንደምናውቀው የእኛ አባቶች የውጭ ሞላጫዎችን ከሀገር ሲያባርሩ የሀገራችን አፈር እንኳ ይዘው እንዳይወጡ እግራቸውን እያስታጠቡ ነበር። አሁን ደግሞ የተገላቢጦሽ አባቶቻችን በስንት ጦርነት ያቆዩልንን ምትክ አልባ ቅርሶች የኛዎቹ ጆሉች ሽጠው ለመብላት በመቋመጥ ላይ ናቸው። ከቂሱ እስከ ጳጳሱ! ከምዕመኑ እስከ ዲያቆኑ አደራ የሚጣልበት ጠፍቷል።" አሁንም እንደገና አባ ሰባጋዲስ አንገታቸውን እንደ ከዘራ ቆልምመው ሲተክዙ ቆይተው ቀና አሉ።

"ትናንት የሆነውን የሰማህ ይመስለኛል። ትንቅንቅ ነበር። ወንበዴዎቹ እነማን እንደሆኑ ባይታወቅም ከሩቅ የመጡ አይመስለኝም። ... ድሮስ ቢሆን ወደዚህች ሀገር ወንበዴ ከሩቅ መጥቶባት ያውቃልን? ... እኛው ነን የቅርብ ጠላቶቿ! እኛው ነን የቂጥ እከኮቿ! ... ኢየሱስን እስከ ጌቴሴማኒ መርቶ ይሁዳ እንዳስያዘው፣ እኛም ምዕራባውያንን እስከ ጠጋጎችን እየመራን ስመን ኢትዮጵያን አስወረስናት። እስከመቅደላ የመራቸው ቴዎድሮስን ያስገደለው ማን ነው? እጤ ዮሐንስ አይደለምን? እጤ



ዮሐንስንስ ማን አስገደለው? አንገቱ ያለበትን ድንኳንስ ማን ጠቆመ? እኛው! እኛው!... አሁን ያስጠራሁህ... ምናልባት የሚሆነው አይታወቅምና እኔ አንድ ነገር ብሆን ብዙ ነገር ተቀብሮ እንዳይቀር..." ንግግራቸውን ሳይጨርሱ የተበታተኑትን ገጾች መሸካከፍ ጀመሩ።

አሱላ ብዙ ቢጠባበቅም ሌላ የነገሩት ነገር የለም። እስከ ረፋዱ ድረስ ገጾቹን ሲሰበስቡ ቆይተው አንድ ላይ ጠረዟቸው። ዳጎስ ያለ መጽሐፍ ወጣቸው። ሶስት መቶ ሰላሳ ገጾች ያሉት ርዕስ አልባ መጽሐፍ። መጽሐፉን ደጉሰው እንደ ጨረሱ ለአሱላ አስረከቡት።

አሱላ ህልም እንጂ እውን አልመሰለውም። ምስጢራቸውን ሁሉ እንዲያውቅ ፈቅደውለታል። ቅድም የጀመረውን ታሪክም ማንበብ እንደሚችል ሲያስብ ደስታ ሊፈነቅለው ደረሰ። ከዚህች በኋላ ወጥቶ ብቻውን ተቀምጦ እነዚህን ገጾች የሚያጣጥምበትን ጊዜ በጉጉት ተጠባበቀ። "በዚህ ማስታወሻዬ ውስጥ በቀጥታ የፃፍኩት ምስጢር እንደ ሌላ ማወቅ አለብህ። የማስጠንቅቅህ ይህ ማስታወሻ በማንም እጅ እንዳይገባ እንድትጠብቀው ነው። ቢገባ እንኳ እኔን በቅርብ ከሚያውቀኝ ሰው እጅ ካልገባ ግልብ ታሪኬን ካልሆነ በቀር ድብቅ ምስክሮቼን የሚያገኛቸው አይኖርም።"

አሱላ ከአባ ሰባጋዲስ በኋላ እንደወጣ በቀጥታ ወደባህር ዳር ሄደ። ወደ ዓማ አጥማጅ አባቱ ቤት ለመሄድ አልወደደም። የአባ ሰባጋዲስን ገጾች ለማንበብ በመጓጓቱ ብቻም ሳይሆን በአባቱ ቤት ውስጥ የምትኖረውን የእንጀራ እናቱን ዓይኖች ለማየት አልተመኘም።

# ፬

ፀጥታ፡፡ አስፈሪ ፀጥታ፡፡ በአካባቢው ረጭ ማለት የተነሳ የልብ ምትዋ ሳይቀር ይሰማታል፡፡ ዝናብ እንደመታው ከበሮ ድምፁን አለዝቦ፡፡ ‘ድፍ! ዱፍ! ... ድው! ድም! ...’ የጋመ ትንፋሽዋ እንፋሎት ወፋፍራም ከናፍሯን እየተረከከ ሰፋፊ ቀዳዳዎች ያሉት አፍንጫዋን አፎት በላቦት አወርዝቶታል፡፡ እግሯ በደመ ነፍስ ያላሰበችውን ይረግጣል፡፡ ፈርታ አታውቅም፡፡ ዛሬ ግን ያለወትሮዋ ፍርሃት በስራ አካላቷ ነግሷል፡፡ የግንቦት ወር ፀሐይ መንደሩን ሀገረ-ገሞራ አስመስላዋለች፡፡ በቀትር ነጠላዋን ተከናንባ ከቤቷ ስትወጣ ዣንጥላ መያዝ እንዳለባት የሚያስብ ልብ አልነበራትም፡፡ እግሮቿ ከጋለው ልም አፈር ላይ ሲያርፉ የጠማማ ጣቶቿ ቅርፆች መንገዱ ላይ ይቀራሉ፡፡

ቆማ ወደኋላዋ አየች፡፡ ከዱካዎችዋ በቀር የሰው ዳና የለም፡፡ የተቃጠለ እግሯን ወደ ዓባይ ውሃ ከትታ አቀዘቀዘችው የጋለን ብረት ውሃ ሲነካው እንደሚያሰማው ድምጽ ከእግሯ የሰማች መሰላት፡፡ “ትሽሽሽሹ ...” እግሯን አመድ አስመስሎት የነበረው አፈር ጥርግ ብሎ ዓባይን ተከተለ፡፡

ደብረ ማርያም ገዳም ለመድረስ ገና ይህንን ግዙፍ ወንዝ በታንኳ መሻገር አለባት፡፡ ደብረ ማርያም ከባህር ዳር ከተማ ዳርቻ የምትገኝ ደሴት ናት፡፡ አብዛኛው የደሴቷ አካል ከጣና ሐይቅ ጋር የተዋሰነ ሲሆን በደቡባዊ



ምሥራቅ ግን የዓባይ ወንዝ ተጠምጥሟት ያልፋል፡፡ የዓባይና የጣና ሐይቅ መለያያና የብዙ ቅርስ ጎተራ በመሆኗ ዘወትር ጎብኝዎች በትናንሽ ጀልባዎች ወደዚች ገዳም ይተማሉ፡፡

ወደ ማዶ አሻግራ ስታይ ባለታንኳው ተዘራ ቁሜ ትልቁ ዶቅማ ስር ተኝቷል፡፡ ጠራችው፡፡ እንደመባነን ብሎ ዓይኑን እያሻሸ ተነሳ፡፡ ሊያሻግራት ታንኳውን እየቀዘፈ መጣ፡፡ ዓባይ ደፍርሷል፡፡ በጣና ላይ መቀነት መስሎ ቁልቁል ይውዘገዘጋል፡፡ ታንኳውን ሊነጥቀው ይታገላል፡፡ ዓባይ ቁልቁል ሲጎትት ባለታንኳው ሽቅብ ይቀዝፋል፡፡ አሻገራትና ወደ ደብረ ማርያም ቤተክርስቲያን አመራች፡፡

ከደጀሰላሙ እንደደረሰች ሳትሳለም ወደ ዕቃ ቤቱ ሄደች፡፡ ያረገዘችው ሀሳብ ራሷን እንደ ዲያብሎስ እንድትቆጥር አድርጓታል፡፡ ያንን ሀሳብ እንዳረገዘች ብትሳለም ስግደቷና ፀሎቷ እንኳን ከእግዚአብሔር ደጅ ከፅዱ ዛፍ ቅጠል እንደማይደርስ አምናለች፡፡

ወደ ዕቃ ቤቱ ላይኛው በር ስትመለከት አባ ሰባጋዲስ የሉም፡፡ በቤተክርስቲያኑ ቅፅር ውስጥ ከወፎች ዝማሬ በቀር የሚሰማ የለም፡፡ ከትልቁ ፅድ ላይ ከተሰበሰቡ ዓሣ አውጭ አሞራዎች በቀር የሚታይ ነገር አጣች፡፡ የነፍስ አባቷ አባ ሰባጋዲስ የት ገቡ? ዛሬ እርሳቸውን ማግኘት አለባት፡፡ ዓይኖቿ በየዛፉ ስር ባዘኑ፡፡ የሉም፡፡

በዕቃ ቤቱ ጀርባ ሱባኤ ሲገቡ የሚዘጉባት ቤት እንዳለች ስለምትሰማ ወደዚያው አቀናች፡፡ አባ ሰባጋዲስ ዘግተው ከሆነ የዶለተችው ሁሉ ቅዠት፣ የፀነሰችው ዓላማም ጭንጋፍ ሲሆን ተሰማት፡፡ አባ ሰባጋዲስ ከዘጉ ለሰው የሚታዩት ከብዙ ጊዜ በኋላ በመሆኑ፡፡

በአሥራ አንድ ሰዓት ለነፍስ መያዣ በትንሿ መስኮት መቁነን ከሚያቀብላቸው ከዲያቆን አሉላ በቀር ወደዚህች ፀሎት ቤታቸው የሚቀርብ ማንም የለም፡፡ አሉላ ብዙ የማያውቃቸው ምስጢሮች ባይኖሩም

ለአባ የቅርብ ተላላኪና ታማኝ ዲያቆን ነው። እርሱም ቢሆን በመስኮት መቁነን ቢያቀብል እንጂ በበሩ በኩል ያለ ሰዓቱ አይገባም። "አባት ለመሆን ራስህን አዘጋጅ። ሁልጊዜ ልጅነት የለም። እኔ እየደከምኩ ዓይኖቼም ጉም እየለበሱ ነው። ልቦናዬም የዝንጋኤ ዳዋ እየዋጠው ነው። አባቶች ያወረሱንን ቅርስ ሜዳ ላይ በትኜው መሞት የለብኝም። ሰው ሁን። መፃሕፍትን መርምር። ለሌላ የማስረክበው አይሆንም። ቀጣፊ፣ ወንበዴ ነው ብዙው። እንኳን ሰጥተኸው ሸሸገህም ጉሮሮህን አንቆ ቅርስ ሸጦ ሊበላ ይጣደፋል። ስለ ነገ ይቅርና ከአንድ ደቂቃ በኋላ ለሚከሰተው ኩነት እንኳ ቆም ብሎ አያስብም...።" በማለት በዕውቀት እየኮተኮቱ አባትነትን የሚያለማምዱት አሉላን ብቻ ነው። የመጻሕፍቱን ትርጓሜ ከእርሳቸው ጠንቅቆ ተምሯል። "የፈረንጆቹን አፍ ብታጠና ስለዘመናዊው ዓለም ብታውቅ ታሪካችንን የበለጠ ልታስተዋውቅ፣ አንተም በዕውቀት ልትልቅ ትችላለህ" ብለው አባ ሰባጋዲስ ስለመከሩት ባህርዳር ከተማ አስኳላ ትምህርት ቤት ገብቶ እየተማረ ነው። በዚህ ዓመት የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የሚወስድበት ጊዜ በመሆኑ ባህርዳር ከተማ ቀበሌ አሥር አካባቢ በተከራያት ትንሽ ክፍሉ ውስጥ ከደብተሮቹ ጋር እንደ መኻገር ተጣብቆ ይውላል።

ሴትዮዋ ከአሉላ በቀር ማንም ከማይሄድባት ፀሎት ቤቷ ታዛ ጥግ ቆማ አዳመጠች። የሚያንጐራጉር ድምፅ ሰማች። አባ ሰባጋዲስ ለመሆናቸው አልተጠራጠረችም። ወደ በሩ ተጠጋች። አባ ሰባጋዲስ በሩን ከፍተው ለስው ሸክም የሚታክት ብራና መጽሐፍ ዘርግተው ያነባሉ። ቀና ብለው አይተው "ስብሐት ለአብ! ወለተ ጴጥሮስ ወደዚህ እኮ አይመጣም!" አሉ ድፍረቷ ገርሟቸው። አለማዊው ስሟ መርጊያሽ ቢሆንም እርሳቸው ግን እንደ ንስሀ አባትነታቸው የሚጠሯት በክርስትና ስሟ ነው ወለተ ጴጥሮስ እያሉ።

"ይቅርታ አባቴ የምልከው ሰው አጥቼ ነው" አለች የተከናነበችውን ነጠላ ከራሷ ላይ እያወረደችና መስቀላቸውን ልትሳለም እያጎነበሰች። መስቀል መሳለሙን ፈልጋ ሳይሆን ብዙ የሚወራላትን የፀሎት ቤታቸውን ውስጥ



ለማየት ነበር ያጎነበሰችው። ነገር ግን ስለፈራች ከፊት ለፊት ከሚታየው ከአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሥዕል በቀር ሌላ ማየት አልቻለችም።

"መጣሁ ዕቃ ቤቱ ዘንድ ጠብቂኝ" ብለው ፈጠን ብለው ተነሱ። እንኳን "በሴት" እግር 'ከቁስ' እግር እንኳ ተረግጦ የማያውቀው የፀሎት ቤታቸው ደጅ በመረገጡ በመጠኑ ተበሳጩ።

ዙሪያ ገባውን በመስቀላቸው ከባረኩ በኋላ ቢጫ ልብሰ- ምንኩስናቸውን እንደለበሱ የነሐስ መስቀላቸውን ይዘው ወጡ።

እቃ ቤቱ በር አካባቢ የተቀመጠችው መርጊያሽ አባ ሰባጋዲስ ሲመጡ ተነስታ ቆመች።
"ምን አዘለቀሽ ዛሬስ?" አሏት ወንበራቸውን ወደ ዕቃ ቤቱ በር እያስጠጉ። መርጊያሽ የነፍስ ልጃቸው ብትሆንም አንድ ቀንም እንኳ ኃጢአቷን ተናዛ አታውቅም።

"አበስኩ ገበርኩ... ንስሐ ይስጡኝ" የሚሉ ቃላት ከአፏ ወጥተው አያውቁም። ጠይም ፊቷ ይበልጥ ከሰል ስለመሰለ የኃጢአት ዕድፍ ያጠቆራት መሰላቸው። አሳዘነቻቸው። እንድትረጋጋ ብሩህ ፊት ለማሳየት ሞከሩ። ከዓለማዊ ኑሮ የተላቀቁባትን ቀን መረቋት። 'እንደመርጊያሽ መጥቆር፤ መፀፀት፤ ለመናገር ማፈር፣ መንቀጥቀጥ፤ እጅን በኃጢአት አረንቋ ነክሮ ህሊናን በቅርጭጭቱ መቁረጥ...' ይህ ሁሉ በእርሳቸው ዘንድ አለመኖሩ አስደሰታቸው። የሷን ዕድፍ ሊያፀዱ እያሰላሰሉ ሳለ "ነገ አቡዬ የኔ ስለሆኑ ትንሽ እንቡሽቡሽ መሳይ ቀምሰው ይመለሱ ብዬ ነው" አለች የነጠላዋን ዘርፍ እያጥመዘመዘች።

"ልጄ ይሄ ነበር ያስጨነቀሽ? እኔ እኮ ምን ፈተና ገጠመሽ ብዬ ፊትሽን ጠቁሮ ሳየው ደንግጬ ነበር። ለሱማ ነገ ሥዘክር መቅመሴ ይቀራል?" አሉ ቤተክርስቲያኑ ላይ ያረፈችውን ድንቅዬ ወፍ እየተመለከቱ።

ብዬ ነው" ጌጡስ ልክ ነው... ግን ዛሬስ ቢሆን ትንሽ አፍዎትን ቢያጥኑት ብዬ ነው" ለማየት እሷ ዓይኗ ከዓይናቸው ስለተገጣጠመ ማንም ቀና ብሎ ለማየት አለች ዓይኗ ከዓይናቸው ስለተገጣጠመ ማንም ቀና ብሎ ለማየት የማይደፍራቸውን የተዳፈረች መስሎ ስለተሰማት ሽምቀቅ ብላ። ወዲያው የሁለቱም ዓይኖች በደጅ ሰላሙ ወደገቡት እንግዶች አተኮሩ። አባ ሰባጋዲስ ገቢ እንግዶቹን ልሸኝና እንሄዳለን" ብለው የማጭድ ቅርፅ ያለውን የቤተክርስቲያኑን መክፈቻ እያቅጨለጨሉ ተነሱ።

አራት ፈረንጆች ከአንድ አበሻ አስተርጓሚ ጋር ሳይሳለሙ ወደ ቤተክርስቲያኑ በር ተጠጉ። ከፈረንጆቹ እጅ ሳንቲምና ከረሜላ የለመዱ ህፃናት ከኋላቸው እየተንጋጉ አብረው ወደ ቅኔ ማህሌቱ ገቡ።

"ማዳም ጊብ ሚ መኒ" አለች አንዲት ህፃን ወደ ወንዱ ፈረንጅ ከወጥ እንጨት የምትቀጥን እጇን እየዘረጋች። ፈረንጁ "ማዳም" ስላለችው ፈገግ አለ። "ኖ መኒ!" ሲል እጁን አወናጨፈ፤ የህፃናት ጨኸትና ልመና ሲበረታበት። የቤተክርስቲያኑ ጥበቃ ከምዕራብ በኩል መጥቶ ህፃናቱን ራስ-ራሳቸውን እየኮረኮመ ከግቢው ጠራርጎ አስወጣቸው።

አባ ሰባጋዲስ የማጭድ ቅርፅ ባለው ጥንታዊ መክፈቻ ትልቁን ጓጉንቸር ከፈቱና እንግዶቹ ወደ ቅድስቱ ገቡ። መቅደሱንም ከፍተው ጥንታዊ ቅርሶችን ወደ በሩ አቀረቡ። በአበሻው አስተርጓሚነት ስለገዳሟና ቅርሶቹ ለእንግዶቹ ገለፃ ማድረግ ጀመሩ። አስተርጓሚው እርሳቸውን በማግኘቱ ተደስቷ፤ ስለገዳሟ ታሪክ የሚያውቀው አንዳች ነገር የለም። አብዛኛዎቹ አስተርጓሚዎች በዘልማድ ታሪክ ሲያበላሹ፣ ያልተሠራውን ተሠራ፣ የተሠራውን አልተሠራም እያሉ፣ እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ የተሠራውን ከኢየሩሳሌም ወይም ከሌላ ሀገር የመጣ በማለት ለማዋደድ ሲሞክሩ፣ ክፍለ ዘመኑንና የነገሥታቱን ሥም ሲያደባልቁ በአንዳንድ ታሪክ አዋቂ ጎብኚዎች በጥያቄ ሲጨናነቁ፣ ነጭ ላብ ሲያልባቸው ስለሚያይ እንግዳ ይዞ ሲመጣ እንደማንኛውም አስጎብኚ አባ ሰባጋዲስን በማግኘቱ ከጎብኚዎቹ እንደ አንዱ ሆነ።



"... እግዚአብሔር እንኳን ወደዚህች ቅድስት ሥፍራ በሰላም አደረሳችሁ" አሉ አባ ሰባጋዲስ ማስጎብኘቱን ሲጀምሩ። "ይህች አሁን የምትጎበኟት ገዳም ከባህር ዳር ከተማ ሰሜናዊ ምሥራቅ አቅጣጫ በጣና ሐይቅ ዳርቻ የምትገኝ ጥንታዊት ገዳም ናት። ወደ ደሴቷ ለመግባት ከፊል ነዋሪዎቿ ዓባይ ማዶ ስለሚገኙ ዓባይን በታንኳ መሻገር አለባቸው። ይህች ታሪካዊት ገዳም የተመሠረተችው በአፄ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግሥት ከ1307-1337 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።" ፈረንጆቹ ከአስተርጓሚው የሚነገራቸውን ሰበርባራ ቃላት እያቃኑ ይመዘግባሉ። ከባለፈው ስብሰባ በኋላ በተወሰነው መሠረት ብዙ የሚዘረፉ ውድ ቅርሶች መኖራቸውን ሲያውቁ ቆጥረው ይረከቡ ይመስል አንድ በአንድ የቅርሶቹን ዓይነት ይመዘግቡ ጀመር።

"... ይህቺው ገዳም ሌላ ሁለት ስም አላት። ጉማሬዎች ስለሚበዙባት ጉማሬ ባህር፣ ከአራቱ አፍላጋት አንዱ የሆነው ግዮን፣ የዓባይ ወንዝ የጣናን ሐይቅ ውሃ ሰንጥቆ ተሻግሮ የሚወጣባትና የሚለይባት በመሆኗ ዓባይ ራስ ትባላለች።" ቀጠሉ።

አባ ሰባጋዲስ ቁንፅል ታሪክ አይወዱም። የሚያዳምጣቸው ካገኙ የታሪክ ስልቻቸውን ፈትተው "እንካችሁ ቅድስት ሀገራችሁን እወቋት፣ እነሆ ከታችኛው ጥልቅ እስከ ላይኛው ሠርቅ ያለውን ማንነታችሁን እወቁት" ይላሉ። ማስረዳቱን ቀጠሉ።

"...'ሰባቱ ከዋክብት' በሚል መጠሪያ የሚታወቁት የሃይማኖት አባቶች ከአቀኑአቸው ገዳማት አንዷ ናት። አቡነ ዘካሪያስ ደብረ ገሊላን፣ አቡነ ፍቅረ እግዚ ዮሐንስ ጣና ቂርቆስን፣ አቡነ አሳይ ምንዳባን፣ አቡነ ሂሩተ አምላክ ዳጋ እስጢፋኖስን፣ አቡነ በትረ ማርያም ዘጌን፣ አቡነ ዘዮሐንስ ክብራን ገብርኤልን ሲመሠርቱ አቡነ ታዴዎስ ደግሞ ይህችን ደብረ ማርያምን ገደሙ። አቀኑ። አቡነ ታዴዎስ ህዝቡን ደሴቷ ውስጥ በዶማ እንጂ በበሬ እንዳያርስ አዘዙ። አሁንም በሬ እዚህች ደሴት ውስጥ ተጠምዶ በጅራፍ ቆዳው እስኪላጥ አይገረፍም፤ በበሬ አይታረስም፤ በዚህች ገዳም ውስጥ ጅራፍ አይጮህም፤ እባብ አይናደፍም። አቡነ ታዴዎስ

አውግዘውታልና፡፡ ታዲያኮ እባብና ዘንዶ ሞልቷል፡፡ ግን ቢረግጡት እንኳ ቀና ብሎ አያይም፡፡" እያሉ ስለአካባቢው ገለፃ ካደረጉ በኋላ ጥንታዊ መቅረዞችን፣ መስቀሎችን፣ ንዋየ ቅድሳቱን፣ ጥንታዊ መጻሕፍትን እንደ ስንክሳር፣ ተአምረ ማርያም፣ መዝሙረ ዳዊት፣ አርባዕቱ ወንጌላትንና ሐዲስ ኪዳን የመሳሰሉትን ከትልቁ አትሮንስ ላይ እየዘረጉ አስረዷቸው፡፡ ከታሪኳ የሚበቃቸውን ያህል ጨለፉላቸው፡፡ አራቱ ጣልያናውያን በጉብኝቱ የተደሰቱ ይመስላሉ፡፡ የያዙት ካሜራ ፎቶ ማንሳቱን እስከመጨረሻው አላቆመም ነበር፡፡

አባ ሰባጋዲስ እንግዶችን ከሸኙ በኋላ መርጊያሽን ተከትለው ወደ ቤት ሄዱ፡፡ ዓባይን በተዘራ ታንኳ ተሻገሩ፡፡

* * * * * * * * * * * * *

ቤቷ ሲደርሱ ጠላ በኮልባ ዋንጫና ዳቦ በመሶበወርቅ አቀረበች፡፡ ፀሎት አድርሰው ዳቦውን ቆርሰው ከጠላው ተጎነጩ፡፡
"እስቲ ይብሉ እረ ለጋ ነገር ነው!" አለች መርጊያሽ ወደ ጓዳ እየገባች፡፡
"ተይው ከሚበስልበት ይበስላል" አሉ እየተጎነጩ፡፡ ቤቱ ቀዝቅዟል፡፡ ዳፍንት መስሏል፡፡ አልጋ ላይ ነጭ ጋቢ ለብሶ የተኛ ሰው አለ፡፡

"ማንን አሞት ነው?" አሉ ወደ አልጋው እየተመለከቱ፡፡
"የታመመ አይደለም፡፡ የኔዋ መስከረም ናት፡፡"
"ምነው በደህና ነው በቀኑ የተኛች?"

"ባህርዳር ትምህርት ሰንብታ ስለመጣች ደክሟት አሁን ነው የተኛች፡፡" አለች አሁንም ማጀት ውስጥ ጉድ ጉድ እያለች፡፡

መስከረም ከቀድሞ ባሏ የወለደቻት የመጀመሪያዋና የመጨረሻ ልጇ ናት፡፡ ከአሁኑ ባሏ ከዓሣ አጥማጁ ይበልጣል ልጅ አልወለደችም፡፡



መርጊያሽ ወደ ደብረ ማርያም የገጠር ቀበሌ ከመምጣቷ በፊት ባህርዳር ከተማ መሃል በሚገኘውና ኮሸኮሸ ተብሎ በሚታወቀው የጠላና የዳንኪራ መንደር ውስጥ ጠላ ቤት ከፍታ ነበር፡፡

የመስከረምን አባት፣ የቀድሞ ባሏን አበራን የተዋወቀችው ጠላ ቤቷ እየመጣ ሲጠጣ ነበር፡፡ ወታደር አበራን አንድ ጣሳ ጠላ ቀድታ ሁለት ጣሳ ጨዋታ ትመርቅለት ጀመር፡፡ አበራ ቅዳሜና እሁድ ከካምፕ እየሾለከ ከመርጊያሽ ጠላ ቤት አይቀርም፡፡ ጓደኞቹ ፈቃድ ሲያገኙ ወጥተው የባህር ዳር ሆቴሎችን አዳርሰው በአንድ ቀን ያለ የሌለ ገንዘባቸውን ሲበትኑ አበራ ግን መርጊያሽን በመተዋወቁ ከእርሷ ጋር ሲስቅ ሲጫወት ውሎ ወደ ካምፑ ይመለሳል፡፡

አንድ ቀን ሲጠጣና ሲጫወት ውሎ ከመሸ ለመሄድ ሲነሳ የመርጊያሽ ዓይኖች እንዲያድር ተማፀኑት፡፡ አንድ ቃል ሳይለዋወጡ በዓይን መስተጋብዕ ብቻ ለማደር ወሰነ፡፡ ከመርጊያሽ ጋር አድሮ ጠዋት ወደ ካምፕ ሲገባ አለቃው ቀኑን ሙሉ ውሃ በጀሪካን ሲያመላልስ እንዲውል በማድረግ ቀጡት፡፡ ሱሪውን ሸብሽቦ ውሃ ሲያግዝ ዋለ፡፡

እርም ሆኖት አልቀረም፤ በየሳምንቱም ወደ መርጊያሽ ጠላ ቤት ማቅናቱን አልተወም፡፡ ከአንድ ወር ቆይታ በኋላ መፅነሷን አረዳችው፡፡ ስለቸኮለች ብዙ ሴቶች እንደሚያደርጉት የገንዘብ ፍለጋ ስልት መሰለውና አስጠላችው፡፡ ስለርሷ ጥሩ ነገር ማሰብ አቆመ፡፡ ከዚያ ቀን ጀምሮ ከመርጊያሽ ጋር ተያይቶ አያውቅም፡፡ የውሃ ሽታ ሆነ፡፡ መርጊያሽ አርግዛ አልቀረችም፤ ሴት ልጅ ከነቃጭሉ ዱብ አደረገች፡፡

መስከረም ገና በጨቅላነቷ ነበር ይበልጣል የእንጀራ አባቷ የሆነው፡፡ መርጊያሽ ይበልጣልንም ያወቀችው እዛችው ጠላ ቤቷ ነበር፡፡ ዓሣ አጥማጁ ይበልጣል ዓሣውን እያዞረ ሸጦ በሮ የሚገኘው ከመርጊያሽ ጠላ ቤት ነበር፡፡

ሳትውል ሳታድር ባህርዳር ቀበሌ ስድስት የነበረችውን ጠላ ቤቷን ዘግታ ኪይበልጣል ጋር ተጠቃለለች፡፡ ደብረ ማርያም ገባች፡፡ ከከተማው ባይርቅም ትንሽ ገጠር ሆነባት፡፡ ቤታቸውን ዓባይ ዳር ሰርተው በዓሣ ማስገር መተዳደር ጀመሩ፡፡

ይበልጣል ነጋ ጠባ ከጣና ጋር ይፋጠጣል፤ መረቡን ይጥላል፤ ይኖራል፤ ያኖራል፡፡ ዓሣውን እያስገረ ፈረስ ያስጋልባል የሚባልለት ቆርቆሮ ቤት ሠርቷል፡፡ የጋራ ልጅ ስለሌላቸው መስከረምን ልክ እንደ አብራኩ ክፋይ ነው የሚያያት፡፡ መርጊያሽ ግን የርሱን ልጅ ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታት በኋላ አንቅራ ተፍታዋለች፡፡ ብዙ ጊዜ ከቤተክርስቲያን አገልግሎት የማይለየው አሉላ ግን በእንጀራ እናቱ መርጊያሽ የሚደርስበትን በደል ከመጤፍ አይቆጥረውም፡፡

"...ታዲያ አሉላ አብሮ አልመጣም?" አሉ አባ ሰባጋዲስ፡፡

"... ና ተብሎ ነበር ጥናቴ ይበልጥብኛል አልመጣም ብሎ ቀረ እንጂ!" አለች ውሽቷን፡፡

"አይ የሱ ነገር መቼም የትምህርቱ ነገር አይሆንለት! እንኳንስ ዛሬ ቀድሞም ቢሆን እንቅልፍ የለውም፡፡ ጠይቆ አይታክተውም፡፡ ሌላው ተማሪ ዓመት ሁለት ዓመት የሚፈጅበትን እርሱ በወር ካላወቅኩት አልተኛም የሚል ትጉህ ልጅ ነው፡፡" አሉ የአሉላን ትጋት ቀድሞ የመጻሕፍት ትርጓሜ ሲያስተምሩት የነበረውን ቀለም ተቀባይነት እያስታወሱ፡፡ መርጊያሽ ምንም እንኳ አሉላ የበደላት ነገር ባይኖርም የእንጀራ ልጅ በመሆኑ ብቻ ስለምትጠላው ወሬውን ለማስቀየር ብላ "ይጠጡ እንጂ!" አለች ዋንጫቸውን እየሞላች፡፡ አባ ሰባጋዲስ "አዛኟን አልጨምርም" ብለው ቢከራከሩም እጃቸውን ይዛ ቀዳችላቸው፡፡ እንኳን ሲሰክሩ የቀመሱ ያልመሰሉት አባ ሰባጋዲስ አናደዷት፡፡ ሰክረው አያውቁም፡፡ ከሰከሩ ካንገታቸው ወዝ በጠገበ ሰንሰለት ያሰሩት የቤተክርስቲያኗ ቁልፍ በወንበዴዎች እጅ ይወድቃል ብለው ይሰጋሉ፡፡ ከዚያም የገዳሟ ቅርስ



ለምልክት ሳይገኝ ይዘረፋል ብለው ስለሚያስቡ ከመጠን በላይ አይጠጡም፡፡ ለአያሌ አመታት ያህል በዚህች ገዳም ሲኖሩ ሰክረው ሲንዘላዘሉ ያገኛቸው የለም፡፡

ከግድግዳው ጥግ አፉን የከፈተውን ትልቅ ጉድጓድ አይተው

"ስብሐት ለአብ! የምን ጉድጓድ ነው?" አሉ፡፡

"ለጋን ማስቀመጫ ብዬ ነው፡፡"

"ታዲያ ይህን ያህል?"

"ጋኔ ትልቅ ነው፡፡ ለነገሩ ይህን ያህል መቆፈር አልፈለግኩም ነበር፡፡ ትንሽ ስቆፍረው ተደረመሰና ሰፊ ሆነብኝ፡፡"

"እንዲያስ ከሆነ በደንብ በቆፈርሽ!"

"እንዴት?"

"ብር ወይም ወርቅ ተቀብሮበት ቢሆንስ!"

"እረ? ማን ሊቀብርበት እዚህ ላይ!"

"አይ ልጄ አባቶቻችን'ኮ ብዙ የቀበሩልን ሀብት ነበር፡፡ ነገ ዛሬ ሲሉ ሳያሳዩን አለቁ እንጂ! ሞት ቀደማቸው! ታሪካችን፣ ማንነታችን፣ ሀብታችን ሁሉ እንደ አፅማቸው መሬት ውስጥ ሆነ፡፡ ለማን ይንገሩት? ትውልዱ ሁሉ መና ሆነባቸው፡፡ እኛማ እንኳንስ ለነገ ልንቀብር የዕለት ከርሳችን ከረጢት አልሞላ እያለን ስንዛግጥ እንውላለን፡፡ ስንታክት ኖረን ሳይሳካልን መትነን! ኧረ ወዲያልኝ!" አሉ ጭራቸውን ሽው አድርገው፡፡

"አይ አባቴ እንኳን የምንቀብረው የምንቆረጥመው አጥተን ውሃ ውሃ እያልን! እስኪ አሁን እስከ መስከረም ወፍጮው የሚከካው ሳያጣ፣ ቋቱ ዱቄት ሳይመትር የሚከርም ማን አለ? ልቅበርስ ቢባል የድሮው ወርቅ፣ ብር አልማዝ ነበር የዛሬው ወረቀት!" አለች አሁንም ከማጀት፡፡ "አይ ልጄ ትውልዱ ቅርሱ ቁርሱ ሆኖ እንጂ መች መቅበሪያ ጠፍቶ! የቀድሞው መቅበሪያ ሌላ የዛሬው መቅበሪያ ሌላ፡፡ ይገርምሻል፣ አሁን ይችን የቤተክርስቲያን ቁልፍ ላለፉት ዓመታት ስቆይ እንዴት እንዳቆየኋት መድኃኔዓለም ነው የሚያውቀው፡፡ የማይዝትብኝ የለም፡፡ እኔ ለሥጋ ልጄ አላወርሰው! ልጅ የለኝ፡፡ እኔን አንቀው ገድለው ቅርሱን ሁሉ ሽጠው

የሚቀራመቱ የሎቦች ክማና ጠልቀው ዓሣ ከሚያወጡት አሞሮች ይልቃሉ። አሁንማ ጨነቀኝ ልጄ! ሰው አለ ብዬ አምኜ ይህችን ቁልፍ የማስረክበው ሰው አጣሁ። የናንተው አሉላ ሰው ይሆናል ብዬ የምጠብቀው ልጅ ነው። ሌላውስ ሁሉም ምላጭ ነው።" ሲሉ ከማጀት ራቁን በጨርቅ የሸፈነ ሰው ወጣ። ተወርውሮ ኩርምትምት አርጎ ያዛቸው።

አልበኩናም። በግድ ካልሆነ በውድ ደማቸው ጠብ ቢል እንኳ ቁልፉን እንደማይሰጡት አረጋግጧል። ካልሰጡት ደግሞ የቀጠራቸውና በብዙ ገንዘብ ሲገዙት የተስማሙት አራቱ ጣልያናውያን ጉብኝታቸውን ጨርሰው ወደ ሀገራቸው የሚመለሱበት ቀን ቅርብ ነው።

አባ ሰባጋዲስን በራሳቸው ቅናት ከምሰሶ ጋር አስሮ በጥያቄ ያጣድፋቸው ገባ።

"አየህ ልጄ አንተ የቱንም ያክል ስቃይ ብታደርስብኝ በላይህ ላይ ያደረው የቀድሞ ጠላታችን ዲያብሎስ እንጂ አንተ አይደለህም።" አሉ ራቁት ሰውነታቸው ከወገባቸው በላይ ተጋልጦ።

"እኮ እኔ ዲያብሎስ? ዲያብሎስስ ርስዎ! ቀንሰን እናውጣ ይስጡን ስንልዎት የማይራሩት ዲያብሎስ!" አላቸው አንጀ ወገባቸውን ዠልጦ። ከዚህ በኋላ የወጧቸው ቃላት ካሳዛኝ የሰቆቃ ድምፅ ጋር የተቀላቀሉ ነበሩ፡ ፡

"ገባቶሃል? የምትጠይቀኝ እኮ እኔና አንተ ሰርተን የማንመልሰውን ቅርስ ነው! ታሪክ! ማንነት! አደራ! አ... አሻራ! ጥያቄህ ገንዘብ ከሆነ ከደመወዜ ካጠራቀምኩት ልስጥህ! አሁንም ከሱ ከኪሴ ሶስት መቶ ብር አለልህ። ታሪክ ዝረፍ ብዬ ግን አላመላክትህም! የምትገድል ሥጋዬን እንጂ ሰብዕናዬን አይደለም እኔ ደግሞ አባቶቼ ስለሥጋና ደም አልሰበኩልኝም! ያስተማሩኝ ስለማንነት ነው! ማ...ማንነት! ታሪክ!"



"አጭር ጥያቄ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ! ቁልፉ በእጄ ነው! ታቦታቱና ትልቁ የአልማዝ መስቀል ብቻ የት እንዳሉ ይነግሩኛል አይነግሩኝም?" አለ ግድግዳው ላይ የተሰቀለውን መጥረቢያ አውርዶ ስለቱን እያሳያቸው።

"ታቦታቱንና መስቀሉን ብቻ ሳይሆን ሌሎች አእላፍ ቅርሶችን ለማሳየት ዝግጁ ነበርኩ። ዛሬ ሳይሆን አስቀድሜ! ግን ሰው አጣሁ! ሰው! ኧረ የሰው ያለህ!" አሉ ቅርሱ ሁሉ ተቀብሮ ማንም ሊያገኘው ከማይችል ቦታ እስከዘለዓለሙ ተዳፍኖ መቅረቱ አሳዝኖአቸው።

"እኔ ሰው አይደለሁም?!"

"አንተማ ልጄ በአምሳለ ሰብዕ የተፈጠርክ ሌጌዎን ሆንክ! ነገ ለሚጠባ መስከረም ነገ ለሚፈስ ክረምት ቅርስ ሸጭ ካልበላሁ ብለህ የአምላክን ግንብ ልትንድ ምሳር ጨበጥክ! እስከሆድህ ብቻ አለምክ!" ብለው ሳይጨርሱ የባዕር ድምፃቸው መንደሩን እንዳይቀሰቅስ የመርጊያሽ መቀነት አፋቸው ውስጥ ተጠቀጠቀ። ወዲያው የመጥረቢያው ስለት ግንባራቸውን ለሁለት ፈረከሰው።

ነፍሳቸው መውጣቷን ሲያረጋግጡ ለጋን መትከያ ተብሎ ከተዋሸላቸው ገደል ውስጥ ቀበሯቸው። ለረጃጅም እግሮቻቸው ቦታ ስለጠበበ እየተቆማመጡ ተቀበሩ።

በልብስ ምንኩስናቸው ተጠቅልሎ በድናቸው ግብአተ መሬቱን ፈፀመ። ከረጅሙ እንጨት አልጋ ላይ ተኝታ የነበረችው የመርጊያሽ ልጅ መስከረም ከእንቅልፏ ባንና ስታይ ስቃዩ ዘግንኗት ራሷን ስለሳተች ውሃ ሲደፋባት አመሹ። ቤቱ ተጠራርጎ ድንጋይ መቃብሩ ላይ ተረብርቦ መደብ ላዩ ላይ ተሰርቶበት ቤቱ በእበት ተለቀለቀ።የማጭድ ቅርፅ ያለው ጥንታዊ ቁልፍ በነመርጊያሽ እጅ ገባ።

# ፳

ቅዳሜ ለእሁድ አጥቢያ-መንፈቀ ሌሊቱ በድምፀ ዶሮ ሳይሰበር ቄሰ ገበዙ ታላቁን ደወል ወገረው፡፡ የደወሉ ድምፅ ጣናን አንቀጠቀጠው፡፡ ደወሉ ካህናቱን ለማህሌት መጥራቱ መሆኑን የገመቱት ባላገሮች በደወሉ ድምፅ ቢነቁም ተመልሰው ተኙ፡፡ ቀሳውስቱና ካህናቱ ሻሻቸውን እየጠመጠሙ፣ ካባቸውን እየደረቡና ሽማቸውን እያስተካከሉ ማህሌቱንና ሰዓታቱን ሊቆሙ መጡ፡፡

ቤተክርስቲያኑ አልተከፈተም፡፡ ግራ የተጋቡት ካህናት በየበሩ ቆመው ነገሩ እስኪለይ ውዳሴ ማርያም መድገም ጀመሩ፡፡ ቄሰ ገበዙ አጨብጭበና ካህናቱን ሰብስቦ የአባ ሰባጋዲስን ቁልፍ እንደያዙ መጥፋት ተናገረ፡፡ ከቅዳሜ ዘጠኝ ሰአት በኋላ በግቢው ውስጥ አለመታየታቸውንም አስረዳ፡፡ "አንድ ችግር ካላጋጠማቸው በቀር ለስንት ዓመታት ሲኖሩ አንድ ቀን እንኳ ውጭ ሳያድሩ ዛሬ እንዴት ውጭ ሊያድሩ ይችላሉ?" እያሉ ሁሉም ተጨነቁ፡፡

መብራቱን በየመቅረዙ ለኩሰው፣ ቤተ መቅደሱን በንፁህ ዕጣን መአዛ አውደው፣ ከበሮና ፅናፅሉን ከቅኔ ማህሌቱ አቅርበው ማህሌቱ እስኪጀመር በጉጉት የሚጠብቁት ትጉህ አባት አባ ሰባጋዲስ የውሃ ሽታ በመሆናቸው ካህናቱ ሁሉ ግራ ተጋቡ፡፡

ሊቀ ካህናቱ ሌላ የደወል ድምፅ አሰማ፡፡ ይህኛው የደወል ድምፅ በአደጋ ጊዜ የሚሰማ፣ ቤተክርስቲያን ዘራፊ ሲመጣ የሚደወል በመሆኑ በአካባቢው የሚኖሩ ምዕመናን ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ደረስንላችሁ እያሉ ቤተክርስቲያኗን ይከቧታል፡፡ በር በሩን ይዘጋሉ፡፡ ዛሬም የደወሉ ድምፅ በደረቀው ሌሊት መንደሩን ሲያናውፀው ህፃናት ሳይቀሩ ቤተክርስቲያኑን ወረሩት፡፡ ሽማግሌዎች ወደካህናቱ ተጠግተው የአባን መጥፋት ሰሙ፡፡ አዲስ ሆነባቸው፡፡ በየጥሻው ሲፈልጉ አደሩ፡፡ አባን የበላቸው ጅብ አልጮህ አለ፡፡ ማህሌቱና ሰዓታቱ ተስተጓጎሉ፡፡

ሰማዩ የአህያ ሆድ ሲመስል ሰሞነኞች ቅዳሴ ለመግባት ዝግጅት ጀመሩ፡፡ ግን ቤተ መቅደሱ ይቅርና ቅድስተ ቅዱሳኑም ዝግ ነበር፡፡ ማንም "በሩ ተሰብሮ ይቀደስ" ብሎ ሀሳብ ያቀረበ የለም፡፡ ቁልፉ ራሱ ቅርስ ነው፣ የትም አይገኝምና፡፡ ይኸ በር ይሰበር ከተባለ በመጥረቢያና በፋስ ሲፈለጥ ማደር አለበት፡፡ ማንም አልደፈረም፡፡ ቅዳሴውም ቀረ፡፡ ሴት ወንዱ ተንጓለለ፡፡

"ቄሱም ዝም መፅሐፉም ዝም" ቆየና በኋላ እኩሌታው ወደ ባህር ዳር፣ ከፊሉ ወደ ዘጌ፣ ገሚሱ ወደ ክብራን ገብርኤል፣ እኩሉ ደግሞ ዓባይ ገንብ ለገንብ ለፍለጋ ተሰማራ፡፡ በቀን አሥራ ሁለት ሰው ቤተክርስቲያን እንዲጠብቅ ተመድቦ ህዝቡ ተበተነ፡፡

# ፯

የአቡዬ ጠበል ጣዲቅ ማህበርተኛ እሁድ አመሻሽ ላይ የነመርጊያሽን ቤት ከማጀት እስከ በር ዘግቶታል፡፡ ዋንጫውን አንጠልጥሎ ወደ ቤት የሚተመው ብዙ ነው፡፡ ከዳቦው ከጠላው እየተባለ ነው ገና፡፡ አርምሞ እንደታወጀ ሁሉ ጥግጥጉን ጎንለጎን ስለአባ ሰባጋዲስ መጥፋት በለሆሳስ ከማንሾካሾክ በቀር የህብረት ወሬ አልነበረም፡፡ የፈገግታ ብልጭታ የትኛውም ፊት ላይ አይታይም፡፡ በአባ ሰባጋዲስ ምትክ የአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ዝክርን የባረከው ቄስ ፀሐይ አባ ሰባጋዲስ ከተቀበሩበት መደብ ላይ ጀንዲና ሳምነት ተደራርቦ ተነጥፎለት ተቀምጧል፡፡ ዝምታ! ፀጥታ! ጥያቄ በሁሉም ሰው አእምሮ ውስጥ ይመላለሳል፡፡ እንደ ሌሊቱ መረዋ ያስተጋባል፡፡ እንደቃጭል ይቅጨለጨላል፡፡ እንደፀናፅል ይንሿሿል፡፡

'እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ! አባ የት ገቡ?' ይላል የሁሉም ውስተ ውሳጤ!

* * * * * * * * *

መስከረም ከሰመመኗ አልነቃችም፡፡ ትንሹን ሞት መልአከ ሞት በሌለበት ሞታለች፡፡ አባ ሰባጋዲስ ሲገደሉ ያየችው የስቃይ መድመሚት ደምሟታል፡፡ አትናገርም፤ አትጋገርም፡፡ ነገር ግን ልብሰ ምንኩስናቸው በደም ሲበሰብስ ነጭ ጢማቸው በደም ሲቀላ፣ መቀነት አፋቸው ውስጥ ተጠቅጥቆ የሚናገሩትን ወደ ውስጣቸው ሲያኾርጎደጉዱት፣ ጉም የለበሱና



እድሜ የጠገቡ ዓይኖቻቸው ገዳዮቻቸውን ሲማፀኑ እየታያት ጩኸታቸውን ልታስተጋባ "ኡ ኡ ኡ" ትላለች፡፡ እናቷ ከጮኸች ጉዴን እንዳትዘረግፈው ብላ በመስጋቷ ከጉረቤት በትንሽ ጎጆ ቤት ብቻቸውን ከሚኖሩት እሮጊት ቤት አስጠግታታለች፡፡ እማሆይ ጦቢያ ጆሮአቸው ያከራክራቸዋል እየተባለ ቢወራም አንድም ነገር አምልጧቸው አያውቅም፡፡ የመስከረም ራሷን መሳት ምክንያት ገብቷቸዋል፡፡

እማሆይ ጦቢያ እሳት ለመጫር ወደነ መርጊያሽ ቤት ሲሄዱ ቤቱ ተዘግቶ ቢያዩም የኃይለኛ ድምፅና የጦፈ ክርክር ሰምተዋል፡፡ በመዝጊያው ቀዳዳ ወደ ውስጥ አጮልቀው ሲመለከቱ ከምስሶ ጋር በሰንሰለት የታሠሩትን ሰውዬ አይተዋል፡፡ መፍለጫ ይዞ የሚያናዝዛቸውን ሰውዬም ተመልክተዋል፡፡

"መስከረሜ? የአቡነ ሐራን ጠበል ልርጭሽ?" አሏት ጠበሉን ሲያመጡ እየተነሱ፡፡

"እህል ቀምሻለሁ!" እንዳልሰሙ ትተዋት ወጡ፡፡ የአቡነ ሐራን ጠበል ከጎጆአቸው ጣራ ውጭ በተዛነቡ በቅምጫና አስቀምጠው ኖሮ አምጥተው ረጯት፡፡ ባባች፡፡ ባነነች፡፡ እምነቱን በጣታቸው ነክተው ግንባሯ ላይ ትዕምርተ መስቀል ሳሉላት፡፡ ደግነታቸው "ምነው የኔም እናት እንደርስዎ ደግ በሆነች? ምናለበት እንደርስዎ ደግ ሆና የምንበላው ባጣን! ከምድጃችን ተኮራምተን አመድ ባጠለቀን! መቼ ነው ደግነትን የምትማረው? ደግነት ይገዛ ይሆን?" አለች በህሊናዋ የናቷን ጨካኝነት እያሰላሰለች፡፡

"መስከረሜ? ተገርፈሽ ነው? ምን አጥፍተሽ ነው?" አሏት ዓይን ዓይኗን እያዩ፡፡

ኃይሏን አጠራቅማና ድምጿን ከፍ አድርጋ እንዲሰሟት "ምንም!" አለች፡፡

"እም! አይዞሽ! ቻል አርጊው... እኛም ተገርፈን፣ በአብላሊት ተለብልበን፣ በበርበሬ ታጥነን ነው ያደግነው። እንኳን አባት እናት ባልም ይቀጣል። ይገርፋል!" ሲሉ ሳያዳምጧት ሌላ በማውራታቸው ፈገግ አለች።

"ሙች ውነቴን ነው! እኔ ባሌን እግሩን እያጠብኩት አንቺ ንቀሽኝ ነው? ለምን በደንብ አታጥቢኝም? ምን ያንጠራራሻል?" ብሎ በጥፊ በርግጫ ይመታኝና የእግሩን እጣቢ ውሃ እየደበደበ ያስጠጣኝ ነበር!"

ተከዝ ብለው ቆዩና "መንገድ ላይ ወደ እናት አባቴ ተጠርተን ስንሄድ እሱ ከፊት እኔ ከኋላ ስከተል 'አንቺ! ምናባሽ ወደኋላ ትቀሪያለሽ? ማንን ቆመሽ እያየሽ ነው?' ብሎ እበት በብትሩ ዘንቁሎ ቁንዳላዬን ይቀባኝ ነበር።" መስከረም ከት ብላ ሳቀች። "አዛኝቷን! ጠባዩ ይገርም ነበር! ቅናቱ አይጣል! ፈታሁት። አስታራቂ ሽማግሌ እየላከ ሲያስቸግረኝ ይህችን የምታያትን ባሌን አገባሁ! ቆቤን! እርፍ! ይህች ቆቤ አትሰድበኝ፣ አትረግጠኝ። ሰላም። እፎይታ!" አሉ ነጭ ቆባቸውን እየነካኩ ጉራማይሌ ጥርሳቸው በፈገግታ ተሞልቶ። መስከረም ቀለላት። በእማሆይ ጤቢያ ጨዋታ ትንሽ መረጋጋትን አገኘች።

* * * * * * * * * *

የአቦው ማህበርተኛ ጠጥቶ ሞቅ ሞቅ ስላለ በረጅሙ ወሬ መለጋት ተጀምሯል። የማዶው ለማዶው፣ የጥጉ ለወዲያኛው ጥግ የአባ ሰባጋዲስን መጥፋት የት? ወዴት? እንዴት? እየተባባለ ይቀባበላል።

"ባህርዳር ከተማ ለሸርሽር ወጡ እንዴ?"

"ከመቼ ወዲህ? ሽርሽር የማያውቁበትን! ሆይ ሆይ!"

"ዕቃ ጠፍቶባቸው ፈርተው ሸሹ ይሆን?"

"እረ በአዛኙቱ! የእርሳቸው ነፍስ ሳትጠፋ እቃ አይጠፋባቸውም! ቁራጭ ሻማ ጠፍቶባቸው አያውቅም! ወንበዴ ቢያስፈራራቸው እንኳ ጥሩንባቸውን ነበር በደረቀው ሌሊት የሚነፉ ወይም ትልቁን መረዋ ሲወግሩ እንደርስላቸው ነበር።" አለ ከሁሉም በላይ ተኮፍሶ የተቀመጠው ዘካራ-ቄስ ፀሐይ።



"ልክ ነው ቄሴ! ወይ አንዱ አንቆ ገድሎ ዓባይ ከቷቸው ካልሆነ በቀር መንገድ ቢወጡ እንኳ ቤተክርስቲያኗ እንድትቀደስ እንድትወደስ ለናንተ ቁልፉን አደራ ይሰጡ ነበር!" አለ አንዱ ባላገር።

"ቁልፉን እንኳ አይሰጡም። ይልቅ ለእነዚህ ዓመታት ሙሉ ሲኖሩ ያልተከሰተ ነገር በመሆኑ ለመፍታት አስቸጋሪ ነው!" አለ የክላሽንኮብ ጠመንጃ ከኋላው ያስቀመጠው የቀበሌው ሊቀመንበር አዳምጠው ተሰማ። እስከ አሁን ምንም ሐሳብ ስላልሰነዘረ ሁሉም ወደሱ አፈጠጡ። ግን ሌላ ቃል ሳይናገር መልሶ ፀጥ አለ።

ሊቀመንበር አዳምጠው ተሰማ ፈርጣማና አፈጮሌ በመሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች አስተዳዳሪ ሆኖ ሲሾም ከተቃወሙት አንዱ አባ ሰባጋዲስ በመሆናቸው አምርሮ ይጠላቸው ነበር።

"ለቅርሳችን መጠበቅ ለደህንነታችን ዋስትና መሾም ያለበት ያወቀ የጠነቀቀ አስተዋይ ሰው መሆን አለበት" ብለው ስንቡቴ ላይ ስለተናገሩ ይጠላቸዋል። "ዝም አለ" ተብሎ እንዳይታማ ተናገረ እንጂ መናገር አልፈለገም ነበር።

ከመርጊያሽ ጋር በቅርቡ የጀመሩት ፍቅር ገሀድ እንዳይወጣ ጣራ ግድግዳው ይናገር እየመሰለው በድንጋጤ ከሊቀ መንበርነቱ በጥቂት እንሷል። ስታልፍ ስታገድም፣ ዋንጫውን ስትሞላለት ሠረቅ እያደረገ ማየቱ ባይቀርም በጥንቃቄ ነበር። ባሏ ዓሣ አስጋሪው ይበልጣል እጁን ይዞ ዋንጫውን ሲሞላለት 'መርጊያሽ የኔ! ቤቱ ያንተ! ቂቂቂ... ወደፊት ደግሞ የዓሣ መያዣ መንጠቆህን ብቻ ይዘህ ትወጣለህ! ቂቂቂ... ውልቅ! መንጠቋም! ጥፍራም!...' ይላል በልቡ እሱን ሲያይ። መርጊያሽ አንቅራ እንደተፋችው ለወደፊትም እሱን ፊታ እንደምታገባው ነግራዋለች። "እባክህ ቶሎ ተከርቸም ግባብኝ?!" ነበር ያለችው አንድ ቀን። "እገባለሁ እንጂ! ማን ከልክሎኝ?! ተከርቸም! ታያለሽ ስከረቸም!" አዳምጠውም ከህግ ሚስቱ ጋር ለጊዜው እንጂ አብሯት እንደማይኖር ለመርጊያሽ አብስሯታል።

በጣና ጉራንጉር እየተሹለከለኩ የሰሩት ፍቅር፣ ዓሣ አስጋሪው ይበልጣል መንጠቆውን ይዞ ሲወጣ አልጋው ላይ የቀበጡት ሁሉ ትዝ ሲለው ለብቻው በሀሳብ ይጠልቃል። ወዲያው ይስቃል። 'አይ ይበልጣል! መንጠቋም! ቂቂቂ...ጅል' ይላል።

"ማነህ ባለሳምንት ያቡዬ ወዳጅ ጥመድ ባስራ ሁለት። ብትዋሰኝ ዋስ አትጣ" አለ ይበልጣል ኩታውን እያጠፈ መጠጡ ሲጠናቀቅ ሲል።
"እኔ አለሁ ያቡዬ ወዳጅ" ቄስ ፀሐይ ቀጣዩ ከፋይ ለመሆን ተነሳ።
"አቡዬ አለሁ አለሁ እንዳልክ አለሁ ይበሉህ።" ፅዋውን አቀበለው። እንኑ ሲቆም "ብቅሉን ከደጋ ጌሾውን ከቆላ ይንገድልዋ።" ይበልጣል አክሎ መረቀ።
"ባገኘ ጠላ ባጣ ጥላ ይገፍ እንኘለሁ።" ቄስ ፀሐይ
"ባለአንዱንም ... ባለ ሁለቱንም ባለ ሶስቱንም አቡዬ ከወሩ ያድርሱልን። እናንተ ይዛችሁ እኛ ለመገኘት ያብቃን።" ሲቀ መንበሩ አዳምጠው ራሱን ሽማግሌ አርጎ መረቀ።
"ጠማቂም እርጥብ የነደደብሽ ደረትሽን ከውጋት ክንድሽን ከቁርጥማት ያድንሽ።" አሜን አለች መርጊያሽ ከወዲያ ጥግ ቆማ።

ባለ ተራ ከተመረቀ በኋላ ማህበሩ ተበተነ። የአባ ሰባጋዲስ ታሪክ መምጫም መመለሻም ሆነ። የሰከረው ስማቸውን ዓባይ ለዓባይ ድምፁን ከፍ አድርጎ እየጠራ ወደቤቱ እየወደቀ እየተነሳ ይጓዛል። ያቅራራል። ይሽልላል።

የስካር... የፍለጋ ቀረርቶ።
የዓባይ ዳር - የዓባይ መሀል ቀረርቶ።
የጣና ጥግ ሽለላ ስለ አባ።

"... ኧረ ጎራው... ኧረ በለው - ኧረ ወንዱ ናልኝ...
ደና ደኔ... ጥራኝ ደኑ - ጥራኝ ጫካው....
ዓባይ ግትልትሉ



ዓባይ ማደሪያ ቢስ
ዓባይ ደመ ጥቁሩ
የሰው ንብረት ዘርፎ ይላል ደህና ደሩ..."

ይላል አንዱ በቁልቁለቱ። ከብቶችን በፉጨቱ የሚነዳው ከማዶ ይቀበልና።

"...ቆየኝ ወንዱ...አለሁ ወንዱ...ገመንማኔው ገረምራሜው... ኧረ ጎራው...

ኧረ ወንዱ ናልኝ
ያባይ ዳሩ ናልኝ
ያባይ ማዶው ናብኝ
ዓባይ ቅሌን ወስዶ ቅምጫና ለመነኝ።..."

ሌለኛው ከማዶ ይቀበለዋል።

"አለሁ በለው... ኧረ ወንዱ ጥራኝ...
ገመንማኔው... ደመ ኩሩው...
ልቀቅ በለው
መልስ በለው
ይብቃ በለው
የግዮኑን ቆሌ፣
ሲጠልቅ ይፀፅታል
እንኳን ሰው አሞሌ።"

እየተባለ አምሽቶ ከብት ሲገባ ሁሉም በየበረቱ እሳት አንድዶ ዋሽንቱን ያንቀረቁራል። ቅራት ያድራል። ገሳ ይደፋል። ይነጋል ይመሻል።

# ፺

አሉላ የአባሰባጋዲስን ገጾች በማጣጣም ላይ ነው። በኒያ አዛውንት ልብ ውስጥ በዝምታ ተቀርቅረው እንደኖረ ወይን ጣፍጠው የተንቦለቦሉት ቃላት በየገጹ ላይ ጎምርተዋል። አስጎመጁት። ለእሱ የተብረከቱ ገጸ በረከቶች መሆናቸውን ሲያውቅ እንደ ሀብታምነት ተሰማው። የምንናዬ አጀማመር የሚለውን ምዕራፍ ደግሞ ደግሞ ደጋግሞ ቢያነብ አልጠግበው ብሏል። አሁንም እንደገና ይህንኑ ምዕራፍ ከመድገሙ በፊት የአባ ሰባጋዲስን መጽሐፍ ርዕስ መስጠት እንዳለበት ወሰነ። ርዕሱንም "የአባ ሰባጋዲስ ገጾች" ሲል ሰየመው። ሆኖም የግዕዙ ስያሜ የበለጠ ተውህቦ አለው ብሎ ስላመነ "ገፀ ሰባጋዲስ" አለው። ነገር ግን ይኸኛው የግዕዙ ርዕስ ጠቅለል ብሎ ጠለቅ ያለ ቢመስልም ትርጉሙ "የሰባጋዲስ መልክ" ሆኖ ስለመጣበት በሀሳቡ ለመጽናት ተቸገረ።

'ልክ ነው! ይህ መጽሐፍ የራሳቸው መልክ በመሆኑ 'ገፀ ሰባጋዲስ' መባል አለበት። አዎ! ሊያውም የእርሳቸው ውስጣዊ ገጽ!' በግዕዙ ስያሜ ከሀሳቡ ጋር ተስማምቶ ንባቡን ቀጥሏል። "የምንናዬ አጀማመር"ን።

"… ሁለት ወር ጠበቅኳት። አልመጣችም። ዓባይም አልጎደለም። እንዲያውም ክረምቱ እያየለ ወንዙም አጥብቆ እየሞላ የመጣ መሰለኝ። የሰማያት መስኮት ተከፍተው ጀገጀግ ዝናብ ይንዠቀዠቅ ጀመር። የዓባይ ሸለቆዎች እንደ ባዘቶ በሚጎተት ጉም ተለጎሙ። የዓባይ ዳር ቅጠሎች የተንቆረዘዘ የዝናብ ጠብታ አልለያቸው አለ። የእኔም ዓይኖች እንደ ቅጠሎቹ የእንባ ጠብታ አንቆረዘዙ። አይሆንም! … አይደረግም! … የወንዝ ዳር ጋኔን መታኝ ይሆን? ምን ዓይነት ቁጣ ወረደብኝ? ለመሆኑ ሰው ናት? ወይስ ሰይጣን በሴት አምሳል መጣችብኝ? እያልኩ እጨነቅ ጀመር።

"… እንዲህ እንዲህ ስል ፍልሰታ ደረሰች። አሸከሩ ሁሉ የሚቆርብበት ወቅት መጣ። የመንደራችን ልጃገረዶችና እረኞች የእናት የአባቶቻቸውን ኩታ እየነጠቁ ሲቆርቡ ሲሄዱ እኔ ግን እምቢ አልኩ። 'አላልኳችሁም? ተናግሬ ነበር! ልጄን እወንዝ ዳር ሰይጣን መቶታል ብል ማን ይሰማኝ?' ሲል አባቴ ነገሩን አባብሶት እርፍ አለ። ይጠመቅ ተብዬ ጠበል ተወሰድኩ። እኔም የእውነት ሰይጣን የመታኝ መስሎኝ ስጠመቅ ያየሁትን ለፈለፍኩ። 'አባይ ወዲያ ማዶ አየኋት። ውበቷ ያስደነግጣል። ሻንኩራ አዝላ ነበር። አጥብቃ አየችኝ። ውሃ ቀድታ ስትሄድ ፈዝዤ እያየኋት ቆምኩ። እስካሁን እዛው ሥፍራ እየቆምኩ ብጠብቃት አልመጣችም።' እያልኩ ለፈለፍኩ። የበለጠ ሶስት ሰባት እንድጠመቅ ታዘዘልኝ። ስጠመቅ ቄሱ በፀበሉ ብለው ብለው አልሆን ሲላቸው በመቁጠሪያቸው ወገቤን እየሸነቆጡ ያስለፈልፉኝ ገቡ።

'ልቀቅ! እወንዝ ዳር የለከፍከው ሰይጣን! በእግዚአብሔር ስም ልቀቅ!' እያሉ ይገሾልጡኝ ጀመር።

'እሺ እለቃለሁ!' አልኩ ዱላው ቢጠናብኝ። 'እለቃለሁ!'

'ውጣ! በኢየሱስ ስም! ውጣ!'

''እሺ እለቃለሁ!'

'ጩኸኽ ውጣ!'

'ኡኡኡኡኡኡኡ …' ጩኸቴን ለቀኩት። አንጓራሁ።

'ሁለተኛ አትደርስበትም?!'

'አልደርስበትም!'

'ገብርኤል ይቆማምጠኝ በል?!'

'ገብርኤል ይቆማምጠኝ!'

'ምስህን ተናገር?!'

'አመድ! አመድ! አመድ!' ሲባል የሰማሁትን ሁሉ አልኩ። በሰንሰለት ወገቤ ታስሮ አመድ ፈልጌ እንድቅምና እንድንከባለል ተላኩ። አመድ ፍለጋ ጓሮ ለጓሮ ስባዝን አባቴ፣ እናቴና እህቴ እያለቀሱ ይከተሉኝ ነበር። ከምር

ሰይጣን ይዞኝ ቢሆን ኖሮ አመድ ያለበትን ለማወቅ ይህን ያህል ባልደከምኩ። ስንት ዳክሬ አመድ ከአንድ ገበሬ ጓሮ አገኘሁ። ሮጬ እንደ አህያ ተንከባለልኩበት። በመጨረሻም አመዱን ሸመሸምኩት። አመድ አቃቃሜ ለራሴ እንኳ አስደነገጠኝ መንተ እፍረቴን አመዴን ቅሜ ገላዬን ተለቃልቄ ወደ ትውልድ ቀዬዬ ተመለስኩ። ...” አሉላ መጽሐፉን አጥፎ ስለ አባ ሰባጋዲስ ያስላስል ጀመር፤ እየተገረመ፤ እየተደመመ። ‘ታዲያ... እዚህ ውስጥ ከፍቅር ታሪክ በስተቀር ምን ምስጢር ተቀምጦበታል?’

# ፫

መስከረም ገና በጠዋቱ ጉዞዋን ወደ ባህር ዳር ጀምራለች። ከሁለት የስንቅ አገልግሎች ሌላ የያዘችው የለም። ውርጩ ያደነዘዛቸውን እጆቿን ወደ ደረቷ አስጠግታ ብብቷ ውስጥ ወሽቃቸዋለች። ጭስ የመሰለ ጭጋግ ቀዬውን ለጉሞታል።

አንድ ዛፍ ሥር ሁለቱንም አገልግሎች ከፍታ አየችና ህቅ! ህቅ! ብላ አለቀሰች። ለአሉላ ስጭው ተብላ የያዘችው ስንቅ ሳምንት ሙሉ አልጋስር በቅርጫት ዝንብ ሲወረው የነበር ኮቸሮ ነበር። ከመሸብረሩ በተጨማሪ የፀጉር ባለሙያ ያላየው የሽማግሌ ሸበቶ ራስ መስሏል። ሸቷል። እንኳን ሰው ውሻ አሽትቶ የሚተወው ዓይነት ነው።

“... አሁን ይሄ ለአሉላ?! አሁን ይሄ ለሰው ልጅ?! ቆይ ምን አድርጌት ነው? እንኳን ሰው እንስሳ ገላምጦ የማያይ ልጅ! እሁሁሁ...” ብላ ስቅ ስቅ ብላ አለቀሰች። አብረው ባንድ ቤት እንዳይኖሩ የተደረገው ለዚህ እንደሆነ ገባት። መርጊያሽ አሉላንና መስከረምን አንድ ላይ አኑራ “ለግድቃን የወረደ ለኃጥአን” እያለ እንዳልፈለገች ተረዳች።

አንድ ቀን ይበልጣል “... ለምን... ለምን አብረው አንድ ቤት አይከራዩም ለምን በየቦታው ኪራይ መክፈል አስፈለገ?...” ቢል “የኛ ባለጎረምሳ ልጅን ለጎረምሳህ እንድድርልህ ነው የፈለግከው?” ብላ ቅስሙን ሰበረችው።

“ተይ መርጊያሽ አሉላን እንደማታውቂው ይህን መናገር ነበረብሽ? እሱ መስከረምም ብትሆን ሀገሩን ሁሉ የሚያስተምር መንፈሳዊ ልጅ ነው።

ከእህቱ አትለይም። እህቱ ናት። ልጅሽ ቢሆን ለየብቻ ይኑሩ ትይ ነበር?..." ሲላት "ሰውዬ! መጓት ከሆነ ችሎት ጠብቀኝ!" ስላለችው ያንን ጉዳይ ዳግመኛ አንስቶት አያውቅም።

አሉላን በምግብ እንደምትጎዳው ግን አቤቱታ አቅርቦላት አያውቅም። ረሀቡን የሚያውቁለት አባ ሰባጋዲስ ነበሩ። እርሳቸው በሚሰጡት ገንዘብ ነበር ጥሬ ሽንብራ ቆርጥሞ የሚማረው። ደህና ስንቅ ይላክልኛል ብሎ ጠብቆ አያውቅም። እንደተላከለት ሰው ሳያየው ይደፋዋል። ጥቂት የተሻለ ከሆነም ለውሻ ይሰጠዋል። የተከራየበት የግቢ ውሾች የሚወዱትና ሲገባ ጅራታቸውን የሚቆሉለት ለዚህ ነው። መርጊያሽንም ቢሆን "በደልሽኝ" ብሏት አያውቅም። ዝም ነው። በሆድ ለሆድ አምላክ ማመልከት ብቻ።

መስከረም የተበላሸውን ስንቅ ደፍታ ከራሷ አገልግል ስንቅ ቀንሳ ለአሉላ ቋጠረችለትና ዕንባዋን አባብሳ መንገዷን ቀጠለች።

መስከረም አሉላ ከተከራየበት ግቢ እንደገባች ወደ ትንሿ ክፍሉ አመራች። በሩ እስከላንቃው ተከፍቷል። መሬት ላይ ከተነጠፈው የማዳበሪያ ፍራሽ ላይ "ጧ" ብሎ ተኝቷል። ከጎኑ የተደጎሰ መፅሐፍ ስለነበር ሲያነብ በዚያው እንቅልፍ እንደወሰደው ገመተች።

ሁለቱን አገልግሎች ወለሉ ላይ አስቀምጣ ከፍራሹ ጠርዝ ላይ ተቀመጠች። ወዲያው ከዓይኗ ዕንባ ዝርግፍ አለ።

"ምን ሆነሻል?"
"ምንም!"
"ንገሪኝ . . ."

"... እኔ በቅቤ ሽሮ የተቀባ ጤፍ እንጀራ፣ አንዳንዴም የኑግ ጭብጦ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ዳቦ ቆሎ፣ ሰነፍ ቆሎ፣ ሌላም ሌላም በአገልግሌ ሲላክልኝ ላንተ



ግን... የኖረ ድቁስ መሀሉ ላይ የተለጠፈበት የተበላሸ ዳጉሣ እንጀራ ይላክልሀል!... ለምንድን ነው?"

"ቆይ... ስለኔ ስንቅ ማን ነገረሽ?"
"ፊትቼ አይቼው!"
"የት?"
"አድርሽለት ስባል።"
"ግን'ኮ አንዳንድ ቀን ያልጠበኳቸውን ጥሩ ጥሩ ምግቦች አገኛለሁ"
"አዎ... እነሱ ደግሞ ከቤት የተላኩልህ አይደሉም።"
"ታዲያ ከየት መጡ?"

"ለኔ ከተላከልኝ ላይ ቀንሼ ባንተ አገልግል አስርልህ ነበር።"

አንገቱን ደፍቶ ተከዘ። ስለ እንጀራ እናቱ አረመኔነት መናገር አይፈልግም። የእናቷን ማንነት ለልጂቱ ማስረዳት አልፈለገም።

"ምን ይደረጋል! ደግነት ተበጥብጦ አይጋት!" መስከረም ከንፈሯን መጠጠች።

ከብዙ የፀጥታ ጊዜ በኋላ

"እኔ ካንተ ጋር እንድኖር በሙሉ ድምፅ ተወስኗል።" አለች መስከረም ቀና ብላ።

"ማነው ባለሙሉ ድምፁ?"
"እኔ!"
"ለምን?"
"በቃ! ብሔራዊ ፈተናም ስለደረሰ ታስጠናኛለህ... እኔንም በጣም ቸግሮኛል..."
"ምንድን ነው የቸገረሽ?"

"ከኔ ጋር ተዳብለው የሚኖሩት ሁለቱ ሴቶች ጎረምሳ ማንጋጋት ጀምረዋል። በዚህ ደግሞ ከነርሱ ጋር የሚመጣ አንድ ጎረምሳ እያስቸገረኝ ነው። በዚህ በፈተና ወቅት መዘናጋት አልፈልግም። ባይሆን ከወንድሜ ጋር ነው

Scanned with CamScanner

የምትኖረው ሲባል ይፈራ ይሆናል። እንዲያውም ሁለት ቀን እነሱ በሌሉበት መጥቶ ሊያስገድደኝ ሞክሮ 'እጮሃለሁ' እያልኩ ሳስፈራራው ነው የሄደልኝ። በየቀኑ ሲመጣ ደብዳቤ እየፃፈ ቦርሳዬ ውስጥ ሳላየው ይከታል። እንግዲህ እንደምታደርግ አድርገኝ።" ብላ አቀረቀረች።

"እና... እናትሽ..."

"እናትሽ አትበል..." አለች ቃሉ ሲጠራ ቀፏት። ግን ደግሞ ንዴቷ እንደ ከብት ዝንብ በርግጋ ከግንባሯ ላይ ስትነሳ ታወቀቻት።

"... አሉላ... አስጠላሃለሁ?"

"እንዴ... ምን ዓይነት ጥያቄ ነው?"

"ካልጠላኸኝ የቀሩትን ትንሽ ሳምንታት አብረን አጥንተን ራሳችንን ለብሔራዊ ፈተና እናዘጋጅ። እርሷ የምትለውን ትበል። ከተፈተንከው ፈተና አይበልጥም። እህት ከወንድሟ ጋር ብትኖር ምን ክፋት አለው? ብደፈር አይቆረቁርህም ማለት ነው?" ብላ ዓይኑ ውስጥ ጠልቃ አየችው።

"ለምን!? ለምን አይቆረቁረኝም?!" አለ ልክ የተደፈረች ያህል ጮክ ብሎ።

"በቃ ና...ና እንሂድና ጓዜን ይዘን እንምጣ።"

እጇን ይዛ ጎተተችው። ተነሳ። ተያይዘው ወጡ።



# ፱

ዓሣ አስጋሪው ይበልጣል መረቡን ለመጣል ወደ ጣና ሲወርድ ያየው ሊቀመንበር አዳምጠው ገና መርጊያሽ ሳትነሳ ከች አለ።

"ደህና አደርሽልኝ?" አለ አልጋዋ ላይ እንደተኛች ጉንጯን ሳም ሳም አድርጎ።

"አንተ? ሸለምጥማጥ ማን ነገረህ?" አለች ፈገግ እያለች። ትላልቅ ዓይኖቿ በደስታ አንቋለጡ።

"ሸለምጥማጥ የዶሮ ክንፍ እንቅስቃሴ በሩቅ እንደሚሰማው አታውቂም?"

"አሁን ዕቃ ረሣሁ ብሎ ተመልሶ ቢመጣስ?"

"ቢመጣሳ! መንጠቋም በይው! ምኑን ዕቃ ይረሣውና? እንደኛ የሰው መዝገብ... ማመልከቻ... ማስታወሻ እስክርቢቶ አይጠፋበት! የእሱ ዕቃዎች ሶስት ናቸው። አጭር ዱላ፣ መረብና መንጠቆ። አራተኛው ደግሞ ጣና ዳር ተዘፍዝፎ የሚኖር ታንኳ፤ በቃ! የውስጥ ሱሪውን ረስቶ ሂዶ እንደሆን አላውቅም።" አለ የለበጣ ሳቅ እየሳቀ።

"የውስጥ ሱሪውን መቼ አውልቆት ያውቅና!"

"አሁን ዛሬ አብራችሁ አላደራችሁም?!"

"አብረን ከተኛን ስንት ዘመናችን!"

"እስኪ አንቺ ማይ!" እጇን ለጋና ምት ዘረጋላት።

"ሙት! ያንተን ሥጋ ያስበላኝ! ካንተ ጋር ከተገናኘን ጀምሬ ጭኑን ከፍቼለት አላውቅም።" ብላ መዳፏን ከመዳፉ አጋጨች።

"ቂቂቂ... ሙትቻ እኮ ነው! ሙትቻ! መንጠቋም! እኔስ ሰጋሁ። ሙች ሰጋሁ!" አለ ኮቱን አውልቆ ወደ ጓዳዋ እየገባ።

"የምን ስጋት ነው?" አለች ቀሚሷን ወደ ላይ እየገለበች። እንደተለመደው ለማውለቅ።

"እንደው... ሌላ ወዶ ከሆነስ?"

"አይ አንተ! ሰው ብለኸው እኮ ነው! እሱ ነው ወንድ የሚወጣው? እሱ ደፍሮ ሴት ሲጠይቅ... ሲያሽኮረምም..."

"እሱስ ልክ ነሽ ሀሞት የለውም!" አለ የማጣጣል ምልክት ፊቱ ላይ ተክሎ።

"ያንተይቱስ እንዴት ናት?"

"እሷን ተያት!"

"እስኪ ሙች በለኝ አሁን! እንደኔ ጣል አርገሀታል?"

"በእውነት ነው ምልሽ... ዛሬ ማታ አብራኝ ልትተኛ ፈልጋ ስትሽኮረመም ነበር ያመሸች። አሳዘነችኝ።"

"እናማ አዘንክላትና አብራ አደረች። አይደለም?"

"ልሙትልሽ! ጋቢዬን ነጥቄ ዓይኔን እያጉረጠረጥኩ ተነስቼ ስሄድ...ስቅስቅ ብላ አለቀሰች...እንዲህ ያስለቅሳል ለካ?................ እናቷ ብትሞት እንዲህ የምታለቅስ አይመስለኝም። ህቅ ህቅ እያለች ለቅሶዋን አስነካችው።"

"ጨካኝ!"

"ግን ባንቺ መጨከን አልቻልኩም። ሲያንሰፈስፈኝ ነው ያደረ።"

"ጠጋ በለኝ ይልቅ ብርድ ነው። አሙቀኝ ..." በቃል መነጋገር ቁሞ በሥጋ መመታተር ተጀመረ። እጆቿ ወገቡን ጨምድደው ያዙ። ሁለቱ እግሮቿ ተመናቀሩ።

ሲያበቁ ፀጉር ያጠለቀው ደረቱ ላይ ተለጥፋ

"አይ አንዳንድ ቀን!" አለች።

"እንዴት?" አላት በረጅሙ ተንፍሶ።

"ሙት አንዳንዱ ቀንስ ጠማማ ነው!"

"የቱ ቀን?"



"ይበልጣልን ያገባሁበት!"

"እርሱ ግን'ኮ ነፍሱ ጥልጥል እስኪምትል ነው የሚወድሽ!" አለ በፌዝ ቃል።

"ኧረ አንዳች ያንጠልጥለው! ሴታ ሴት እኮ ነው። እኔማ ሴት ያገባሁ ይመስለኛል።"

"እኔ የምለው?!"

"እህ?"

"ሃያ ዓመት ሙሉ ልጅ ሳትወልዱ የቀራችሁበት ምክንያት ምን ይሆን?"

"ልጅ መውለድ ይፈራል። በመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት እኔ ከሱ ልጅ መውለድ ፈልጌ ነበር። በኋላ 'ቆይ ለእኛም ለልጁም ጥሪት እንያዝና እንወልዳለን' ይለኝ ስለነበር እኔም እየተደበቅሁ መድኃኒት መውሰድ ጀመርኩ። ይገርምሀል ከቀድሞዋ ባለቤቱ እንኳን አሉላን ብቻ ነው ወልዶ የቀረ። ለምን? ስትለው 'ምን ላበላው ምን ላወርሰው?' ይላል።

"በተገናኘን በአሥር ዓመታችን አረገዝኩ። ጤናው እምቢ ሲለኝ ወደ አንድ አዋቂ ቤት ሄድኩ። ገና ስገባ፣ ...'አንቺ ልጅ እንዳትገቢ!' አሉኝ ጠንቋዩ።

'ምነው ጌታዬ ምን አጠፋሁ ምን አጉደልኩ' ብላቸው፤ 'መቀነትሽን ፈተሽ ግቢ!' አሉኝ። ፈትቼ ገባሁ።

'በሆድሽ ውስጥ ጥቁር ቡችላ ይታየኛል። ከወለድሽው ያጠፋሻል። ካስወረድሽው ይጠቅምሻል' አሉኝ።

'ጌታዬ ያሉኝ አልተገለጠልኝም' አልኳቸው።

'ሂጂና ይህችን ቅጠል በጥብጠሽ ጠጪና ሲያስወርድሽ ከትልቁ ዋርካ ሥር ደሙን ድፊው። እዛ ዋርካ ዙሪያ የባልሽ አያት የቀበሩበት ጋን ሙሉ ብርና የወርቅ ቡችላ አለልሽ' አሉኝ። ብወልደው ካልጠቀመኝ ምን ዋጋ ሊኖረው ስለዚህ ብሬን ላውጣና ቀን ይውጣልኝ ብዬ አስወረድኩትና ደሙን በዋርካው ዙሪያ ረጨሁት። ከዛ በኋላ አስር ዓመት ሙሉ በየምክንያቱ እየቆፈርኩ ብኖርም ላገኘው አልቻልኩም። በዚህ ምክንያት ሳልወልድ ቆየሁ። አሁን ከሁለት ዓመት በፊት ይበልጣል ዓሣ ለማስገር

በሌሊቱ ተነስቶ ይሄዳል፡፡ ጉማሬዎች ያገኙትና ከታንኳው ላይ ተገልብጠ በዋና ሊያመልጥ ቢል አልሆንለት ብሎ ይረጋግጡ ይጎዱትና ሰዎች ተሰብስበው ነፍሱን ያተርፉታል፡፡ ሐኪም ቤት ታክሞ ከተመለሰ ወዲህ እምቢ አለው፡፡"

"ምኑ ነው እምቢ ያለው?" አላት፡፡

"ከዛ ወዲህ ግንኙነት አድርገን አናውቅም፡፡ እንኳን ልጅ መውለድ የወጉን እንኳ አድርገን አናውቅም፡፡"

"እና ሁለት ዓመት ሙሉ ዝም ብለሽ ኖርሽ?"

"ይኸው አንተን አገኘሁ፡፡"

"አሁን ምን ወሰንሽ?"

"እንዲሁ ካንተ ጋር የምንቀጥል ከሆነ..." ብላ ሳትጨርስ

"ስለመቀጠላችንማ ጥርጥር የለውም፡፡ የዋርካውን ዙሪያም በደንብ ማስቆፈር አለብን፡፡ ለዚህ ደግሞ ከአሁኑ ጀምሬ አዋቂ እፈልጋለሁ፡፡ ግን የምንቆፍርበት ሰዓት ነው የሚያሳስበኝ" አላት፡፡

"ለእርሱ አታስብ፡፡ ይህን ሴታ ሴት ድራሹን አጠፋዋለሁ፡፡ ከዛም ዋርካውም ጓሮውም የግሌ ይሆናል፡፡"

"ከዛ በኋላ ደግሞ ከኔ ጋር ሚዜ በሌለበት እኔና አንቺ ሚዜና ሙሽራ እንሆናለን፡፡ ግን እንዴት እሱን ማባረር ትችያለሽ?"

"ይህማ ቀላል ነው፡፡ ቁስሉን መንካት ብቻ፡፡ ወይም ቁስሌን አዋርሰዋለሁ፡፡"

"የምን ቁስል?"

"እሱን ከሆነ በኋላ ታየዋለህ፡፡ ጭንሸው የማይሄድን አህያ ቁስሉን መንካት ነው መድኃኒቱ፡፡" ብላ ያዘጋጀችውን የቅቤ ዙር ልታጠጣው ከአልጋ መቀነቷን ታጥቃ ስትወርድ በሩ ተንኳኳ፡፡

አዳምጠው ሱሪው አልጋው ሥር ስለወደቀበት ከአልጋ ሥር ሱሪውን መፈለግ ጀመረ፡፡ መርጊያሽ የተተኮሰባት መሰለች፡፡ መቀነቷን እንደነገሩ



አሰረችና ራሷን በሻሽ ቢጤ ሸብ አድርጋ እንደታመመ ሰው እየተንቀረሰሰች ልትከፍት ሄደች፡፡ አዳምጠው መደቡ ላይ ደንግጦ ተቀመጠ፡፡ ምን መላ እንደምትዘይድ አልገባውም፡፡

የተተኮሰበት ድርጭት መስሎ ተቀመጠ፡፡ ፍርሃት ቆንጠጥ ቢያደርገውም የያዘውን ክላሽንኮቭ ዞሮ ሲያይ የልብልብ ተሰማው፡፡

"ምነው በቀን በሩን ዘጋሽው?" አለ ይበልጣል በቅርጫት ሞልቶ የተሸከመውን ዓሣ እያስቀመጠ፡፡ ከውጭ ስለገባ ወደ ውስጥ አልታየውም፡፡

"በጧቱ ተነሳብኝ!"

"ምኑ?"

"ሞኝ ባገኝ የሚሉት በሽታ ተጠናውቶኝ አይደል! በጧቱ ራሴን ሲያፈርሰኝ ጊዜ የሚበጣኝ ሰው ፍለጋ መንገድ መንገዱን ሳይ እርሳቸውን አገኘኋቸው፡፡ 'እባክዎን ድፍረት ባይሆንብኝ ሰውየው ስለወጣብኝ ይብጡኝ' አልኳቸው፡፡ እግዜር ይስጣቸውና መጥተው በጧቱ አፈሰሱልኝ፡፡" አለች በእጇ ወደ አዳምጠው በዝግታ እያመለከተች፡፡ ይበልጣል ዓይኑ ላይ ውሃው ሲፈልቅበት ስለቆየ ወደ ቤት ውስጥ በደንብ ማየት አቅቶት አላየውም ነበርና "አይ የኔ ነገር ከውጭ ስገባ ቶሎ አላይ! እንደምን አረፈድክ" ብሎ አዳምጠውን ሰላም አለው፡፡

"ኧረ ክፉ በሽታ ነው! ተጠቅተው እኮ ነው የደረስኩ፡፡ ይገርምሀል የኔን ባለቤትም ይኸው 'ሞኝ ባገኝ' የሚሉት በሽታ ደሟን ሊጨርሰው ነው፡፡" አለ ነገሩን በነጋ በጠባ ደም ማፍሰስ - ነጋ ጠባ ዋገምት መትከል ሆነ፡፡ ጥሩ መደበቂያ ሆኖ ስላገኘው፡፡

"እንደው በናንተ በመንግሥቱ መድኃኒት አልተገኘለትም?" አለ ይበልጣል፡፡

"ምን ይገኝለታል፡፡ 'ለሞኝ ባገኝ' መድኃኒቱ ሞኝ አለመሆን ነው፡፡ ራስን ሲያነሆልል፣ እጅን ሲያዝል መበጣት ነው መድኃኒቱ፡፡" አለ አዳምጠው አዋቂ ለመምሰል ድምጹን እየጎተተ፡፡

Scanned with CamScanner

"እና ትንሽ ቅዝቃዜ መጣይ የሰጠም መርጊያሽን ስጠየሁን በዲራቅ..." "መርጊያሽ ክበር" ታዲያ ወም አትሜ አትርዘምበሳሁ..." አለች በዲስመ ድምፅ።

"ግድ የለም እኔ አቀርዘምበሁ ቁም ቦት እንዳለ አላፀኝ።" "ካሌ እንግዲያውስ ስትንሽ ግድ ቀስ አድርገህ አስተውለህ ቅቁ። ከሉ ከሌል ድግም የገደምን ክፍናህ እሶት እሌ።" አለች በንቀት ዓይናኗ ቁምሳሟን እያየችፍ። ...

እዳምጠው የቀረበለትን የቡድ ዓይን የመሰለ ጠላ ጠጥቶ ከላሸንክፋትን እየጠጠጠ ወደ ሰለበሰው አመራ።

መርጊያሽ ተነስታ አሌጋዋ ላይ ወጥታ ተኛች። እንዲያናግራት አልፈለገችም።

"ዓለዩ ስጠሜ ደህና አልነበርሽም?" አለ ይበልጣል አሌጋው ጫፍ ተቀምጦ።

"ደህና ልሁን አልሁን ምን ገዶህ አንተ!"

"እንዴት አይገደኝም?"

"ልሁን እታድርቶኝ ልተኝበት"

"ቆይ ምነው አንች ሰው እንዲህ እንደጠላትሽ አየሽኝ...እረ ተይ መርጊያሽ?"

"እኔ እንደጠላት ካየሁህ እንደጠላኜ የምታይህን ይዘህ ከተፍ!"

"ምናለ ቀና ቀናውን ብናስብ?"

"ልሁን ድሮ ቀረ። በእድህ አመግባቱ በፊት ታሽፈግድልኝ እንዳልነበር ዛሬ..."

"እህ... ዛሬስ ቢሆን ምን አጠፋሁ?"

"ምን አጠፋሁ?"



"እንደ ዓደኞቼ መሸታ ቤት አላመሽ። በሚት ወጥቼ በብርድ እየተቆላሁ እንደ ጋኔን ከውሃ ጋር አታገላለሁ። ከዚህ ውጭ ሌላ..."

"ሌላ እንዲየምርህ ሌላዋን አምጣ።"

"ተይ እንጂ መርጊያሽ! ያለምንም ምክንያት ለምን ቁጣ ቁጣ ይልሻል?!"

"ቢቃኝ እንደዉም ቢቃኝ! የምትሆንህን የማትቆጣዋን አምጣ። እኔ አባቴን አመጣና ያለኝን ተካፍዬ እሄድልሃለሁ።" ስትለው ብልጭ አለበትና፤

"ሂጂ ታዲያ! አምጫቸው። መንገዱ ጠፍቶሽ ከሆነ አሳይሻለሁ። አልበዛም? ያለአንዳች ምክንያት መንጣጣት ምን ይባላል? ነው አባት እንዳለሽ ልትነግሪኝ ነው? አዎ። እኔ እናት አባቴን ጨርሼ ባድማ ጠባቂ ሆኜ ቀርቻለሁ። ዘመድ የለኝም። ወንድም የለኝም። አባቴ ከተከላቸው ዛፎች በቀር የቀረኝ ጥሪት የለም። አንቺ ባለብዙ ዘመድ ባለብዙ ወገን ነሽ እቴ! እኔ ማን አለኝ! ሂጂ ያውልሽ አውራ ጎዳናው" አላት።

ውጭ ሲላት ታምሜአለሁ ብላ ያመካኘችው ተረሳትና "አንተ! ገሬድህ መስልኩህ እንዲህ አመናጭቀህ ውጭ የምትለኝ?"

"እና ዘለዓለም አንችን ስለምን ልኑር? አሁንማ አበዛሽው። ያለአንዳች በደል ያለ አንዳች ምክንያት ምን ያህል አሳሬን እንዳበላሽኝ ታውቂያለሽ። እኔ ትዳር የያዝኩ መስሎኝ ዓሳ ተሸክሜ ከተማ ለከተማ እየዞርኩ ስሸጥ እንባዛ በሮጠበት እየዋኘሁ የምኖረውኮ ትዳር እና ቤት ያለኝ መስሎኝ ነው።" አለ በንዴት ሲዪፍ አንጀቱ እየተመተረ።

ዓሣ ሻጩ ይበልጣል ምንም እንኳን ዕድሜው ወደ ስልሳው ቢጠጋም አክብሮ እርስዎ የሚለው የለም። እንዲያውም መንደር ለመንደር ዓሣና እንባዛውን በትከሻው ተሸክሞ ስለሚዞር ሕፃናቱ ሁሉ የሚጠሩት "እንባዛው" እያሉ ነው። እርሱ ግን ሳቅ እያለ ያልፋል። 'የሕፃናት አፍ አይስቀይምም' የሚል እምነት አለው።

ከመርጊያሽ ጋር ስፍር ቁጥር የሌለው የንዝንዝና የጭቅጭቅ ጊዜያት አሳልፏል። ብዙ ጊዜ ለፍች ቀርበው ሽማግሌ ገላግሏቸዋል። አሁን ግን ከልቡ ቆርጧል። ሽማግሌዎች ሳይኖሩም ቢሆን ለመፋታት ወሰነ።

"ከነገ ጀምሮ ከዚህ ቤት እንዳላይሽ!" አለ በአጭር ዱላው መሬቱን እየቆረቆረ።

"አንተ ነህ እኔ ከቤት የምንወጣው?!"
"ብለሽ ብለሽ ደግሞ ያባቴን ባድማ አስለቅቂኝ እንጂ! 'አባት አለኝ ባድማ አለኝ' አላልሽም? ሂጂ እንጂ! አንቺ ባለባድማ ነሽ እቴ! የትኛው ልጃችን መሬት ስጡኝ ብሎ እንዳያስቸግረን ነው?"
"ልጅ ባልወልድስ! ድፍን ሃያ አመት ያለማሁት ባያ ማ አይደለም?"
"እስኪ በሞቴ የተከልሽውን ዛፍ አሳይኝ? አንቺ ደግሞ ወሬ ከማበካት ሌላ ምን ሠርተሻል? በቤታችን እንኳ ከድሮዋ ባለቤቱ ጎታዎች በቀር እህል እንኳ መያዣ የለም። ጎታ እንኳን! ጭቃ! ጎታ! አይ..." አለና ተነስቶ ወጣ። መርጊያሽ እንደሁልጊዜው ይለማመጠኛል ብላ ያነሳቸው ነገር እንዲህ ተካሮ እዚህ ይደርሳል ብላ አላሰበችም ነበር። ጭንቅላቷን በሁለት እጇ ይዛ ተቀመጠች።

"የድሮዋ ባለቤቱ የሠራችው ጎታ..." የሚለው ጆሮዋ ላይ ደጋግሞ አቃጨለ። ቤቱን ከግድግዳ እስከጣራው በአንክሮ ተመለከተችው። እውነትም ካንድ የጠላ መጥመቂያ ጋን ውጭ የእርሷ የምትለው የረባ ዕቃ የለም። ከሌላ ሰው ቤት የተቀመጠች እንግዳ እንደሆነች ተሰማት።

እንኳን ሃያ ዓመት አንድ ቀን ያደረችበት ቤት አልመስልሽ አላት። እሷነቷን የሚያሳይ አንድም ዕቃ የለም። ከወደጥግ ያገኘችውን ዱላ አንስታ ዕቃዎቹን ማነካከት ጀመረች። ቤቱ አዲስ እብድ የገባበት መሰለ። ጎታው ተናደ። መሰበወርቆች በእሳት ጋዩ። ማድጋ፣ ኩስኩሶት፣ ጀበናው፣ ገንቦው፣ ማሰሮው ተሰባብሮ ማጀቱን ሞላው።



# ፲

መርጊያሽ ጆሮዋ የጥይት ሩምታና ጩኸት ወደሰማበት አቅጣጫ

እንደ ቀንድ ቆመ። ምንም ጊዜ ሳታጠፋ ነጠላዋን ነጥቃ ወደዚያው ሮጠች። የዓባይ ዳር በሰው ተጥለቅልቋል። ወደ ደብረ ማርያም ቤተክርስቲያን የሚተመው ሕዝብ የመሻገሪያ ታንኳ ወረፋ አልደርሰው ብሎ ወዲህ ማዶ ተከምሯል። ጩኸቱን የሰማው ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያኑ እስከሚደርስ ጓጉቷል።

ወደ ደጀ ሰላሙ ስትገባ አዳምጠው ከቤተክርስቲያኑ ዓውደ ምህረት ላይ ከፍ ብሎ ቆሟል። ቅጥር ግቢው ተጨናንቋል። ህዝቡ ዙሪያውን አሰፍስፎ ቆሟል። ጫጫታውን ለማርገብ የሚያጨበጭቡ እጆች ስለበረከቱ እነርሱም የጫጫታው አንዱ አካል ሆነዋል።

ጩኸቱ ጋብ ሲል አዳምጠው ትልቅ ወረቀት ገልጦ ማንበብ ጀመረ። ድምፁን ከፍ አድርጎ ሲያነብ አንገቱ ላይ ያሉት የደም ቧንቧዎች ይገተራሉ። በፊቱ ላይ ላብ በስሱ ቸፍ ብሏል።

"... በቅድሚያ ለደብረ ማርያምና ለአካባቢዋ ነዋሪዎች ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ባደረጋችሁት ጥብቅ ጥበቃ ምን ያህል ለቅርሳችን ተቆርቋሪ መሆናችሁን ያሳያችሁበት ምስክር መሆኑን ልገልፅላችሁ እወዳለሁ። በዚህም መንግሥት የተሰማውን ደስታ ለመግለፅ ያቅተኛል። መንግሥት የሕዝቡን ሰላምና ፀጥታ አስፍኖ ልማትን ከማፋጠን ጎን ለጎን ቅርሶቻችን የቱሪስት መስህቦች እንዲሆኑ ልዩ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል።" ቀና ብሎ የተሰበሰበውን ህዝብ አስተዋለ።

መርጊያሽ ህዝቡን እያመሰች እየገፈታተረች ወደፊት ስትጠጋ ተመልክቶ ንግግሩን ቀጠለ።

"ስለ ደብረ ማርያም መዚጋት ሀዘን ያልገባው የለም ለማለት እደፍራለሁ። የአባታችን የአባ ስባጋዲስ መጥፋት ሳያንስ ቁልፉም በመጥፋቱ ሀገሬው ብዙ ብዙ ሲያወራ ቆይቷል። የቁልፉ ከጎባይ ወንዝ ምስራቃዊ ዳርቻ ገነቡ አካባቢ መገኘት እርሳቸው በውሃው ተበልተው እንደሞቱ ባስከተለው ጥርጣሬ አስከሬናቸውን ለማውጣት የተደረገው የዋናተኞች ጥረት ከንቱ ቢሆንም ቄስ ፀሐይ ለእውቅ ዋናተኞች በሰጡት የገንዘብ ድጋፍ ምስጋናዬን የማቀርበው በሕዝቡና በራሴ ስም ነው።" ብሎ ወደ ቄስ ፀሐይ ዞር አለ። ሕዝቡ ጭብጨባውን ከዳር እዳር አስነካው።

ቄስ ፀሐይ የአዳምጠው ወንድም በመሆኑ ለሥጋው በማስጨብጨቡ አንዳንዶች አጉረመረሙ። ሌት ተቀን የዓባይን ጉራንጉር ሲያስሱ የሰነበቱት ዋናተኛ ከበሌዎች ምስጋና ስላልተቸራቸው ማጨብጨባቸውን አቆሙ። ስንት የደከመ ማቅ ለብሶ ያለቀስ እያለ ቄስ ፀሐይ ቁልፉን እንዲይዝ ፈልጎ መሆኑን ለአንዳንዶቹ ካህናት ግልፅ ነበር። ጉርምርምታው ስለበዛ ከዛ በኋላ ለተናገራቸው ነገሮች ጭብጨባው አልደመቀም። እንደውም ገንዘቡን ለዋናተኞች የሰጠው እሱ ሆኖ ወንድሙን ለማስወደድ እርሳቸው ናቸው የሰጡት ማለቱ ገርሟቸዋል። በዛ ላይ ትልቅ ለማስመሰል እንቱ ማለቱ ብዙዎችን አስገርሟል።

ማጉረምረሙና ጫጫታው ሲበርድ ጉሮሮውን ጠራርጎ ቀጠለ።

"... እንግዲህ መቼም ከመንግሥት ቀድመን ለራሳችን መገኘት ያለብን ራሳችን ነን። እ - እ ቁልፉ የሕዝብ ነው። ሰው ቢሞት ሰው ይተካል።" ብሎ ሳይጨርስ አንዲት እመበለት ከፍ ባለ ድምፅ እየጮሁ "ሰው ቢሞት ሰው ቢተካም እንደ አባ ስባጋዲስ ያለ አይገኝም። ሁሉም ቀጣፊ ሌባ ነው። አሁንም ታቦታችን አደጋ ላይ ናት። ፅዮንን ማን ይጠብቃት?! እስኪ ማነው ታምኖ ቁልፉ የሚሰጠው? መቀበሪያችን፣ የስንት ቅርስ ባለቤት



የሆነችው ደብራችን ስትጠፋ እየታየኝ ነው..." ሲሉ ሁሉም "ልክ ናቸው! እማሆይ ልክ ናቸው" አሉ።

"እንደማመጥ!" አለ አዳምጠው ከንፈሩን በምላሱ እያረጠበ።

"እንደማመጥ! እስኪ ካህናት ወደዚህ ወደ ዓውደ ምህረቱ ቅረቡልን?!" ሲል በየሕዝቡ መሀል ጠምጥመው የቆሙት ካህናትና ደባትሩ ወደ ዓውደ ምህረቱ ወጡ።

"ዋናው ነገር ቁልፉ መገኘቱ ነው። በእኔ በኩል ሰው ካለፈ በኋላ ብዙ ማለት አይገባኝም። እርሳቸው ለምን ወደ ወንዙ እንደገቡ ባይገባንም በነገሩ ጥልቅ ሀዘን እንደተሰማን ገልጫለሁ። አሁን ካህናቱና ሽማግሌዎች ባላችሁበት ሁነኛ ሰው በሕዝቡ ፊት ይመረጥና ቁልፉን ይረከብ። እኔ ጨርሻለሁ መድረኩን መናገር ለምትፈልጉ እለቃለሁ።" ብሎ ቁልፉን ከፍ አድርጎ ለሕዝቡ አሣየ።

ቄስ ፀሐይ ወደ መድረኩ እየወጣ መናገር ጀመረ። "የደብረ ማርያም ሕዝብ ሆይ እግዚአብሔር ያጥናህ። ትልቅ አባት አጣን። መተኪያ የሌላቸው ሊቀ ሊቃውንት፣ የቅኔ፣ የመፅሐፍ፣ የአቋቋም፣ የድጓ መምህር። ዕድሜ ልካቸውን ሲማሩ ኖረው ሲያስተምሩ የኖሩ። ዕቃ ቤት ጠብቀው ፍም አፍመው የቤተክርስቲያኗን ግቢ አፅድተው ያለፉ ግን ለዘለአለም ሕያው ሆነው የሚኖሩ አባት አጣን። ሰባኬ ትህትና፣ ሰባኬ ወንጌል አባታችንን መተካት ባንችልም ፈለጋቸውን ለመከተል ዝግጁ ነን።" አለና ሳይጨርስ ሕዝቡ ማጉረምረም አበዛ። "ፈለጋቸውን ለመከተል ዝግጁ ነን" ማለት የስልጣን ፍለጋ ምልክት መሆኑ ግልፅ ሆነላቸው።

አንድ ሽማግሌ ጭራቸውን ወደ ላይ ገትረው "እንግዲህ ሁሉም የተሰማውን ብሏል። እኔስ ስለ አባ መሞት እርግጠኛ መሆን ስላልቻልኩ መናገርም አልችል...." ሲሉ የለቅሶ ጩኸት ተሰማ። እመበለቶች ደረታቸውን መድቃታቸውን ቀጠሉ። ሽማግሌው ግን አላቆሙም።

Scanned with CamScanner

"ተው እባካችሁ! የእኛ ለቅሶአችን መች በዚህ ያበቃል፡፡ ዘለአለም ስናለቅስ እንኖራለን እንጂ! ይልቅ መናገር የፈለግኩት የቁልፉን ጉዳይ ነው፡፡ ቁልፉን መረከብ ያለበት አሉላ ብቻ ነው፡፡ በእውቀቱም በሥነ ምግባሩም እንደርሳቸው ለመሆን የሚጥር ልጅ ያየሁ እርሱን ብቻ ነው፡፡ እርሳቸውም ብዙ ምስጢር የሚነግሩት ለእርሱ ነው፡፡ ለማንም የማያሳዩአቸውን ምስጢራት እንደሚያውቅ ነው የሚሰማኝ፡፡ ስለዚህ ቁልፉን አሉላ ይያዝ፡፡" ብለው ጭራቸውን ሽው አድርገው በራ ራሳቸው ላይ አድርገው ዝም አሉ፡፡

"አይሆንም! የማይሆነውን!? ልጅ አስኳላ ትምህርቱን ለመጨረስ ነው ፍላጎት ያለው፡፡ ደግሞ ተቆጥሮ ያልተረከበውን ዕቃ ይዞ ለእርሱ መስናክል እንዲሆን አልፈልግም፡፡ ልጅ መማር ነው የሚፈልግ፡፡ እዚህ ተቀምጦ ዕቃ ቤት ጠባቂ መሆን አይፈልግም፡፡ ደብረ ማርያምን ከትምህርቱ ጎን ለጎን ያገለግላል እንጂ ይህን ታላቅ ሸክም እንዲሸከም አልፈቅድለትም፡፡ አሁንም ፈተና እየተፈተነ ስለሆነ የአባ ሰባጋዲስን የቀለም አባቱን መጥፋት አልሰማም፡፡ የእርሳቸውን መጥፋት ከሰማ ደግሞ ከሀዘኑ ብዛት የተነሳ ምን እንደሚሆን አላውቅም፡፡ ልጅ አሉላ ከኔ ከአባቱ አብልጦ እንደሚወዳቸው አውቃለሁ፡፡" አለ ይበልጣል ድምፁን ከፍ አድርጎ ጋቢውን ትከሻው ላይ እየከመረ፡፡ የክት ኩታ ያለችው ይህች ብቻ ብትሆንም አደባባይ ለብሷት ሲወጣ የተብደለች አትመስልም፡፡ እንዴ ለብሶ በአባይ ውሃ ሙሽልቅ አርጎ ሳያጥብ አያስቀምጣትም፡፡

"እንግዲህ መቼስ ሰው ጠፋ ተብሎ ቁልፉን ከዛፍ ላይ አናንጠለጥለው! በእውነቱ ከኛ ከዚህ ሁሉ ሰው ቁልፍ የሚይዝ ሰው ጠፋ ተብሎ ሲነገር በጣም የሚያሳዝን ነው፡፡ ሰው ሲሞት ሰው አይተካም ለካ!... መቼስ ታዲያ ምን ይሆናል? እኔ የምለው? ቄስ ፀሐይ ጥንቁቅ ሰው ስለሆነ ለእርሱ ቢሰጥስ ነው፡፡" ብለው ዝም አሉ አንድ ሽማግሌ፡፡ ከአዳምጠው ጎን ቆመው፡፡ ሕዝቡ ቢያጉረመርምም ለቄስ ፀሐይ ቁልፉ ተሰጠው፡፡
ቄስ ፀሐይም ለይስሙላ ያህል "እያችሁ ወገኖቼ የሰጣችሁኝ ከባድ ሸክም ነው፡፡ በዚህ ላይ አሳሳቢው ነገር ንዋዬ ቅድሳቱንና ቅርሱን ሁሉ ቆጥሬ



አስመረክቤ ነው፡፡ ራሴን አደጋ ውስጥ እያስገባሁ መሆኑ ቢገባኝም ለእመብርሃን ሁሉን ነገር ሰጥቼ በሥራዬ ሁሉ አጋሬ እንድትሆን እየፀለይኩ ነው የምረከባችሁ፡፡" ብሎ የማጭድ ቅርፅ ያለውን ጥንታዊና ዕድሜጌ ጠገቡን ቁልፍ ተረክቦ ከእጅ መስቀሉ ጎን አንገቱ ላይ አንጠለጠለው፡፡

ቁልፉ ከወንዙ ዳር በመገኘቱ ህዝቡ አባን የበላቸው ውሃ ነው ብሎ እንዲያምን አደረገው፡፡

አገሬው ሲበተን እያወራ የሄደው የአባ ሰባጋዲስን ነገር ነው፡፡

"እንዲያው ታቦቱን ሲዘርፉ አስበው ገድለው ጥለዋቸው ነው እንጂ እሳቸውማ ምን ከፍቷቸው ራሳቸውን ወደ ውሃ ይወረውራሉ?"

"ወንበዴ ይሆናል" አለ አንዱ እርግጠኛ ባልሆነ ስሜት፡፡

"የለም ወንበዴም አይደል፡፡ ወንበዴማ ቢሆን ቁልፉን እንዴት ወንዝ ዳር ይጥለዋል?"

"አዳምጠው እንዲያ ዋናተኛ መሆኑን አላውቅም ነበርኮ ጃል!"
"እኛ ስንዛግጥ ውለን እሱ ማግኘቱ ማርያም ፈቅዳለት እኮ ነው፡፡"

"እና ግን ለቄስ ፀሐይ ቁልፉን ማስረከቡ ገርሞኛል፡፡ ቄስ ፀሐይ እኮ አፈ ጮሌ መሆኑ እንጂ አያምርበትም፡፡ ትምህርቱም ወሸክ ያለች ናት መሰለኝ ብዙ ጊዜ አይቀድስም፡፡ ስንት ሊቅ ሞልቶ እርሱ መያዝ የለበትም ነበር፡፡"
"እሪ ከተማ ለከተማ ሲያንዛርጥ ነው የማየው!"
"ማንም ይያዘው ማን ዋናው ቁልፉ መገኘቱ ነው፡፡"
"እሱስ ባልከፋ ካልሆነ ሰው እጅ ወድቆ ቅርሳችንን ሁሉ እንዳይዘርፉት እንጂ፡፡" እየተባባለ እየተሻገረ ሄደ፡፡

"ተው እባካችሁ! የእኛ ለቅሶአችን መች በዚህ ያበቃል፡፡ ዘለአለም ስናለቅስ እንኖራለን እንዴ! ይልቅ መናገር የፈለግኩት የቁልፉን ጉዳይ ነው፡፡ ቁልፉን መረከብ ያለበት አሉላ ብቻ ነው፡፡ በእውቀቱም በሥነ ምግባሩም እንደርሳቸው ለመሆን የሚጥር ልጅ ያየሁ እርሱን ብቻ ነው፡፡ እርሳቸውም ብዙ ምስጢር የሚነግሩት ለእርሱ ነው፡፡ ለማንም የማያሳዩአቸውን ምስጢራት እንደሚያውቅ ነው የሚሰማኝ፡፡ ስለዚህ ቁልፉን አሉላ ይያዝ፡፡" ብለው ጭራቸውን ሽው አድርገው በራ ራሳቸው ላይ አድርገው ዝም አሉ፡፡

"አይሆንም! የማይሆነውን!? ልጁ አስኳላ ትምህርቱን ለመጨረስ ነው ፍላጎት ያለው፡፡ ደግሞ ተቆጥሮ ያልተረከበውን ዕቃ ይዞ ለእርሱ መሰናክል እንዲሆን አልፈልግም፡፡ ልጄ መማር ነው የሚፈልግ፡፡ እዚህ ተቀምጦ ዕቃ ቤት ጠባቂ መሆን አይፈልግም፡፡ ደብረ ማርያምን ከትምህርቱ ጎን ለጎን ያገለግላል እንጂ ይህን ታላቅ ሸክም እንዲሸከም አልፈቅድለትም፡፡ አሁንም ፈተና እየተፈተነ ስለሆነ የአባ ሰባጋዲስን የቀለም አባቱን መጥፋት አልሰማም፡፡ የእርሳቸውን መጥፋት ከሰማ ደግሞ ከሀዘኑ ብዛት የተነሳ ምን እንደሚሆን አላውቅም፡፡ ልጄ አሉላ ከኔ ከአባቱ አብልጦ እንደሚወዳቸው አውቃለሁ፡፡" አለ ይበልጣል ድምፁን ከፍ አድርጎ ጋቢውን ትከሻው ላይ እየከመረ፡፡ የክት ኩታ ያለችው ይህች ብቻ ብትሆንም አደባባይ ለብሷት ሲወጣ የተበደለች አትመስልም፡፡ አንዴ ለብሶ በአባይ ውሃ ሙሽልቅ አርጎ ሳያጥብ አያስቀምጣትም፡፡

"እንግዲህ መቼስ ሰው ጠፋ ተብሎ ቁልፉን ከዛፍ ላይ አናንጠለጥለው! በእውነቱ ከኛ ከዚህ ሁሉ ሰው ቁልፍ የሚይዝ ሰው ጠፋ ተብሎ ሲነገር በጣም የሚያሳዝን ነው፡፡ ሰው ሲሞት ሰው አይተካም ለካ!... መቼስ ታዲያ ምን ይሆናል? እኔ የምለው? ቄስ ፀሐይ ጥንቁቅ ሰው ስለሆነ ለእርሱ ቢሰጥስ ነው፡፡" ብለው ዝም አሉ አንድ ሽማግሌ፡፡ ከአዳምጠው ጎን ቆመው፡፡ ሕዝቡ ቢያጉረመርምም ለቄስ ፀሐይ ቁልፉ ተሰጠው፡፡
ቄስ ፀሐይም ለይስሙላ ያህል "እያችሁ ወገኖቼ የሰጣችሁኝ ከባድ ሸክም ነው፡፡ በዚህ ላይ አሳሳቢው ነገር ንዋዬ ቅድሳቱንና ቅርሱን ሁሉ ቆጥሬ



አለመረከቤ ነው፡፡ ራሴን አደጋ ውስጥ እያስገባሁ መሆኑ ቢገባኝም ለእመብርሃን ሁሉን ነገር ሰጥቼ በሥራዬ ሁሉ አጋሬ እንድትሆን እየፀለይኩ ነው የምረከባችሁ፡፡" ብሎ የማጭድ ቅርፅ ያለውን ጥንታዊና ዕድሜ ጠገቡን ቁልፍ ተረክቦ ከእጅ መስቀሉ ጎን አንገቱ ላይ አንጠለጠለው፡፡

ቁልፉ ከወንዙ ዳር በመገኘቱ ህዝቡ አባን የበላቸው ውሃ ነው ብሎ እንዲያምን አደረገው፡፡

አገሬው ሲበተን እያወራ የሄደው የአባ ሰባጋዲስን ነገር ነው፡፡

"እንዲያው ታቦቱን ሲዘርፉ አስበው ገድለው ጥለዋቸው ነው እንጂ እሳቸውማ ምን ከፍቷቸው ራሳቸውን ወደ ውሃ ይወረውራሉ?"

"ወንበዴ ይሆናል" አለ አንዱ እርግጠኛ ባልሆነ ስሜት፡፡

"የለም ወንበዴም አይደል፡፡ ወንበዴማ ቢሆን ቁልፉን እንዴት ወንዝ ዳር ይጥለዋል?"

"አዳምጠው እንዲያ ዋናተኛ መሆኑን አላውቅም ነበር'ኮ ጃል!"
"እኛ ስንዛግጥ ውለን እሱ ማግኘቱ ማርያም ፈቅዳለት እኮ ነው፡፡"

"እና ግን ለቄስ ፀሐይ ቁልፉን ማስረከቡ ገርሞኛል፡፡ ቄስ ፀሐይ እኮ አፈ ጮሌ መሆኑ እንጂ አያምርበትም፡፡ ትምህርቱም ወሽክ ያለች ናት መሰለኝ ብዙ ጊዜ አይቀድስም፡፡ ስንት ሊቅ ሞልቶ እርሱ መያዝ የለበትም ነበር፡፡"
"ኧረ ኩተማ ለከተማ ሲያንዛርጥ ነው የማየው!"
"ማንንም ይያዘው ማን ዋናው ቁልፉ መገኘቱ ነው፡፡"
"እሱስ ባልከፋ ካልሆነ ሰው እጅ ወድቆ ቅርሳችንን ሁሉ እንዳይዘርፉት እንጂ፡፡" እየተባባለ እየተሻገረ ሄደ፡፡

# ፲፩

አሉላና መስከረም በአንዲት ጣራ ስር መኖር ከጀመሩ ቀናት አለፉ፡፡ በአንደኛው የግድግዳ ጥግ የአሉላ ፍራሽ በሌላኛው ጥግ ደግሞ የመስከረም ፍራሽ መሬት ላይ ተነጥፈዋል፡፡ ሌትም ቀንም ዓይኖቹ ከመፅሐፍ ላይ የማይነሱትን አሉላን ከወዲያኛው ጥግ ሆና ዓይኖቿን ተክላ ታየዋለች መስከረም፡፡ ሲሰማት የኖረው ስሜት እንደቡግንጅ የሚፈርጥበትን ቀን ብትጠባበቅም ከእሱ በኩል ምንም ዓይነት ምልክት አላገኘችም፡፡ እንደወደደችው ገብቷታል፡፡ እንደተመኘችው እርግጠኛ ናት፡፡

"አሉ? አሉላ! ምነው ተከርቼምነቴ አልተስማማህም እንዴ?" አለች ወሬ ለመቀስቀስ፡፡

"ኧረ ለምን? ደግሞኮ ጥሩ ተከርቸም ብቻ አይደለሽም ጥሩ ደባልም እንጂ! ስትተኚ አታንኮራፊ፣ እኔ ደግሞ የሚያንኮራፋ ሰው ያስጠላኛል! ውይ ውይ ሰው ተኝቶ ካንኮራፋ ወይ እንቅልፍ አይወስደኝ ወይ አላነብ ዝም ብዬ የእንኩርፊያውን ምት ነው እንደሙዚቃ የማዳምጥ! ሌላ ደግሞ የማልወደው ምን መሰለሽ? የጫማ ሽታ!"

"ይኼ ሁሉ ከሌለብኝ እንዴት ዕድለኛ ደባል ነኝ፡፡"

"ግን አንቺ ደባሌ ሳትሆኝ እህቴ ነሽ ራስሽን ከደባልነት አውርጂ" ብሏት ንባቡን ቀጠለ፡፡ የአባ ሰባጋዲስን ገጾች፡፡ "ገጸ ሰባጋዲስ"ን፡፡

"ከጠበል ወደ ቀዬዬ ከመመለሴ ወደ ተሰከፍኩበት ሥፍራ ወደ አባይ በርሬ ወረድኩ፡፡ ተራሮችና ኮረብቶች በአደይ አበባ ተሞሽረዋል፡፡ ሸለቆዎች በልዩ ልዩ አዝመራዎች ተንቆጥቁጠዋል፡፡ የገብስ እሸቱ ቃሙኝ ቃሙኝ ይላል፡፡



ስብል ጠባቂዎች ማማ ሰርተው ዋሽንታቸውን ያንቆረቁሩታል፡፡ በወንጭፋቸው የሚተኩሱት ሻፊ ድንጋይ እያፏጨ ሰማዩን ይገምሰዋል፡፡ አረሞች የከብቶችን ቁስል ይቆጠቁጣሉ፡፡ ንቦች ሽታቸው የሚያውድ አበቦችን እየቀሰሙ ልዩ ዝማሬ ያሰማሉ፡፡ አባይ ግን ሳይጎድል ቆየኝ፡፡

ይኼኔ ውሃ ልትቀዳ ተመላልሳ ይሆናል፡፡ ምነው ጠበል ባልወሰዱኝ! ... አትል ሳይለቀኝ አስመለጡኝ፡፡ ይኼኔ እሷም ፈልጋ አታኝ ይሆናል፡፡ እያልኩ እሷን ቆማ ያየሁበትን ቦታ ይወልዳት ይመስል በዓይኔ እጠባው ጀመር፡፡ በዚህ ጊዜ አንዲት ኮረዳ እየዘፈነች ቢዶ ማድጋዋን በዋምራዋ እያንኳኳች ከማዶ ስትመጣ አየሁ፡፡ ያቺ ልጅ በመጣችበት መንገድ፡፡ ልቤ ዳንኪራውን ይረግጥ ጀመር፡፡ ድምጿ እየቀረበኝ አካሏም እየተጠጋኝ መጣ፡፡ እስክትደርስ አላስችል ብሎኝ ባውራ ጣቴ ቆምኩ፡፡ ..."

"አሉላ! ምነው እቴ?! አልራበህም እንዴ? እንብላ እንጂ?" ስትል መስከረም ከንባቡ አናጠበችው፡፡ አሉላ ከስጠመበት ዓለም ተመንጥቆ ሲወጣ እንደመደንገጥ አለ፡፡

"ምነው?" አለች መስከረም ያገልግሉን ምግብ በሌማት ቀንሳ እያቀረበች፡፡ "ምን እያነበብክ ነው? እሄን ያህል የሚመስጥ ነገር ምን ተገኝቶ ነው? 'ፍቅር እስከመቃብር'ን የምታነብ እኮ ነው ያስመሰለብህ!"

"ኧረ እንዲያውም!"

"ልቦለድ ነው ከምር?!"

"ልቦለድስ አይደለም!"

"እንግዲያ ሌላ ምን ተገኝ እንዲህ የሚመስጥ ነገር?!" መቼም አንተ ያንን 'አደፍርስ' የሚባለውን ልቦለድ ስታነብ ነው እንዲህ የሚያረግህ፡፡ ደሞ ጀመርከው እንዴ?"

"አይደለም የሆነ ሰው የህይወት ታሪክ ነው፡፡"

"የሚፃፍ ታሪክ እንዳለው ሰው የሚያስቀናኝ የለም፡፡ ... በል ጉረስ ... ንባቡን ትደርስበታለህ፡፡"

እየተሟሟቀ ሲመጣ አሉላ አንዳች ደስታ ተሰማው። እስከ ዛሬ ብቻውን በጨለማ ክፍል ውስጥ በወጉ ሳይሆን ያሳለፋቸው ዓመታት በእስር ቤት ያሳለፋቸው ዓመታት እንደሆኑ ተሰማው።

“እስከዛሬ ለየብቻችን መኖር ያልነበረብንን ነው የኖርነው።” አለ የጎረሰውን እያላመጠ።

“እማዬ ለምን ይህን እንደወሰነች አልገባኝም። አባዬ ግን አብረን እንድንኖር የሚፈልግ ይመስለኛል።”

“በርግጥም ለኔና ላንቺ ለየብቻ ለቤት ኪራይና ለቀለብ ከሚከፍሉ አብረን ብንኖር ኖሮ ወጪው ይቀንስላቸው ነበር።”

“እኔን እኮ ነው የገረመኝ ግን! እስኪ በነዚህ ቀናት ውስጥ ስንት ነገር አስጠናኸኝ! ስንት ነገር አወቅሁ! እስከ ዛሬ እንደዚህ አጥንቼ ቢሆን ኖሮ የት እደርስ ነበር።”

“ቢሆንም ጎበዝ ነሽ። ካሉት የክፍልሽ ሴቶች የላቀ ውጤት የምታመጭ አንቺ ነሽ።”

“ከወንዶችም ጋር እወዳደር ነበራ!”
“እሱማ ቢሆን ጊዜው ገና ነው። ከርሞ ከምትመደቢበት ዩኒቨርሲቲ ልትበልጫቸው ትችያለሽ። ዋናው መበርታት ነው። ከኖርነው መቶ ዓመት ያልኖርነው አንድ ቀን ይበልጣል። አሁንም ነገሮች በእጅሽ ናቸው። ሁሉንም ነገር ከልብሽ ከመነጨ ትጋት ከያዝሽው ከቁጥጥርሽ አይወጣም።”

“እሱ ነው ግን አእምሮዬ ባዶ እንደሆነ ይሰማኛል።”

“እንደሱማ አታስቢ! ባዶ አእምሮ የለም።” አለ ሲያጎርሳት ያዘጋጀውን ወደ አፏ እያስጠጋ። ሲያጎርሳት እስከአሁን አንድ ቀንም ጎርሳ የማታውቅ



መሰላት። በራሷ እጅ ዘጠና ጊዜ ከምትጎርስ በእርሱ እጅ አንድ ጊዜ መጉረሱን መረጠች።

“በቀደም ‘አዳም ከሔዋን ጋር ከኖራቸው ረጅም ዘመናት ብቻውን የኖራቸው ጥቂት ቀናት እጥፍ ይመረጣሉ’ ያልከኝን ሃሳብ ዛሬም አልቀየርከውም?” አለች ወተት የመሰሉ ጥርሶቿን በፈገግታ ሞልታ።

“ለምን ጠየቅሽኝ?”
“እንደው! አብረን መኖር ስንጀምር የተሰማህን ለማወቅ ፈልጌ!”
“ሔዋን ለአዳም ባለቤቱ፣ መስከረም ለአሉላ እህቱ ማወዳደር ይቻላል?”
“አይ... የአብሮ መኖርን መልካምነት ለመግለፅ ፈልጌ እንጂ...”
“አዳምና ሔዋን'ኮ ታዲያ አብረው ሲኖሩ ከደስታው ስቃዩ ይበዛ ነበር። እኔና አንቺ ግን የበዛ ደስታም ያነሰ ሀዘንም አላየንም።”
“አሁንም ሔዋንን ለስቃያቸው ተጠያቂ እያደረግህ ነው አይደል?”
“እና ማነው ተጠያቂ?”
“ራሱ እግዚአብሔር!”
“ስእሲ ሲነ ቅድስት! ምንነካሽ! ለምን ተጠያቂ ይሆናል?”
“መጀመሪያ በዛች ባማረች፣ በአበቦች መአዛ በታወደች፣ ሲቀምሷቸው በጣዕም ብዛት ነፍስን ከሥጋ የሚለዩ ፍራፍሬዎች ባበቀለባት ገነት መሀል ለምን ያችን የተረገመች ዕፀ በለስ መትከል አስፈለገው?”
“እና ያለሕግ መኖር ነበረብን ነው የምትይ?”
“ጥፋት በሌለበት ጥፋት ስለማይኖር አናጠፋም ነበር።”

ምግቡን አቁሞ በአንክሮ ተከታተላት። ይህን ያህል ጠልቃ ማሰብ መጀመሯ ገረመው።

“ቆይ... እንዲህ እያሰብሽ ነው ትምህርት ከበደኝ የምትይኝ?”

“ለምን መሰለህ... የትምህርት መፃሕፍት አንዳንዴ የእውነት መደበቂያ ዋሻ መስለው ይታዩኛል:: ማስተማር ያለባቸውን ትተው የሌለባቸውን ሲዘባርቁ ታያለህ:: ያዘጋጁዋቸው ሰዎች ደግሞ ወይ ዕውቀት ጎሏቸዋል ወይም ትውልዱን ሊቀብሩ ቆርጠው የተነሱ ይመስሉኛል:: አሰልቺ ናቸው:: ስለዚህ እነሱን ወርውሬ ከትምህርት ውጭ የሆኑ መጻሕፍትን አነባለሁ:: እያደረቅሁህ ምግቡን መብላት አስተውኩህ አይደል?” ብላ በረጃጅም አለንጋ ጣቶቿ አዘጋጅታ አጎረሰችው::

ጣቶቿ ለስላሳ ውብ ከንፈሮቹን ሲነኩት ነዘራት:: ፍዝዝ ብላ ከንፈሩን አየች:: ደግማ ስታጎርሰው በትንሽ ጣቷ ዳበስ አደረገቻቸው:: ልትገምጣቸው ጓጓች:: ‘እንዴ... ወንድሜን?...ግን'ኮ አብረን አደግን እንጂ ካንድ ማህፀን አልወጣን:: አንድ ጡት አልጠባን:: ከአንድ ማህፀን አንድ እትብት አልጎተትን በአንድ እንሽርት ውሃ አልዋኘን!' እና ብስመውስ... እቅፍ ባደርገውስ ‘አንቺ ባለጌ ወንድምሽ'ኮ ነኝ! አንቺ እብድ ክህነት'ኮ አለኝ:: ዲያቆን እኮ ነኝ!' ብሎ በጥፊ ቢጠፈጥፈኝስ እያለች በውስጧ ተብሰለሰለች:: የበሉበትን ዕቃ አጥቦ አስቀመጠና እጇን ሊያስታጥባት ውሃ ይዞ አጎነበሰ::

“ማነው አስታጣቢው?”
“እኔ!”
“እንዴ እኔ ነኝ እንጂ!”
“ምን ችግር አለው ባስታጥብሽ?”
“በል ባይሆን ተነስቼ ልታጠብ...”

“ተቀመጭ ባክሽ! ሁለታችንም ከቆምን ደሀ እንሆናለን:: እንደዚህ የሚባል ልማድ አለ አይደል?” ብሎ እንደቆመ ጣቶቿ ላይ ውሃ ጨመረላት:: ታጥባ ስትጨርስ ፊቱ ላይ ረጨችበት:: ዓይኑን ጨፍኖ ሲከፍት ደገመችው:: እሱም ረጨባት:: አስቀምጦ በእፍኙ ሞልቶ ሲረጭባት ሲል ከቤቱ ጥግ ተሸጉጣ ተማፀነችው:: ግን ፊቷን በውሃ አለበሰው:: የውሃ ነጠብጣብ ፊቷ ላይ ቁጥር ቁጥር እንዳለ ወገቡን ጥምጥም አድርጋ ይዛ ግድግዳው ጋር ለተመችው:: “ለካ ጨካኝ ነህ!” ብላ አፏን አስጠግታ ዓይኗን እያስለመለመች ስትናገር መልካም መአዛ ያዘለ ትንፋሿ ገረፈው::



ሰውነቱን ያሞቀው ትንፋሿ የልቡን ምት አፈጠነው:: የማያውቀው ስሜት ወረረው:: ዓይኖቿን ጨፍና በኃይል ከንፈሮቿን ከንፈሮቹ ላይ አሳረፈቻቸው::

የበሩ መንኳኳት ከገቡበት አዲስ ዓለም በፍጥነት መነጠቃቸው:: በድንጋጤ ተላቀቁ::

በሩን ከፍታ ስትወጣ ህፃን ልጅ ከደጅ ቆሟል:: በነጭ ፖስታ የታሸገ ደብዳቤ ይዟል:: ሰላሳ እጆቹን ዘረጋላት::

ይዛው ስትገባ “የምን ደብዳቤ ነው?” አላት:: “የላኪው አድራሻ የለም ግን በተቀባይ አድራሻ ላይ ስሜን የፃፈውን ብዕር አውቀዋለሁ::”

“የማን ነው?”
“ምነው ቸኮልክ?”
“አይ... ከቤተሰብ የተላከ ከሆነ ጤንነቱን ቶሎ ለማረጋገጥ ፈልጌ ነው::”
“ጤናማስ አይደለም፤ ግን ከቤተሰብ አልተላከም::” ብላ ፖስታውን ከፍታ ማንበብ ጀመረች::

ከደብዳቤው መግቢያ ላይ በመጥረቢያ የተገመሰ የልብ ምስልና የእንቡጥ አበባ ምስል አለበት::

“እስኪ ዛሬስ ሳንብብለት!” አለችና ድምጿን ከፍ አድርጋ ለእሱ ሳም እያሰማች ማንበብ ቀጠለች::

“... መስኪ.... መስከረም! የኔ የመስከረም አደይ አበባ! ይህ ስንተኛው ደብዳቤ ነበር? ረስቼዋለሁ:: ውድ ፍቅሬ ልቤን ስንት ጊዜ በጦር ወግቼ ስዩ በሰጠሁሽ ደብዳቤዎች ላይ አንዳች ምላሽ በማጣቴ ዛሬ ደግሞ በመጥረቢያ ቀረጥኩት:: አንቺን ለመሰለች ቆንጆ ይህ ቢያንስ እንጂ

አይበዛም፡፡ መስሲ እንቺን ማፍቀር የሚያሳፍር አይደለም፡፡ ውስጥሽ እንደ መስከረም አደይ ተፈጥሮ በልዩ ጊዜ ያበቀበችው እንዲ በቀላሉ ለመጎዳል የመጣ አይደለም፡፡ ተሸርተሽን እንደ ታቦት ድንኳን የወጠረት ዘንዶዉ ጡቶችሽ ለዚህ ምሥክር ናቸው፡፡ ከንፈሮችሽ እንደ እንጆሪ ግመጡኝ ግመጡኝ ይላሉ፡፡ መች ይቀርላቸዋል? ስሚ! የተመኘሁትን ለማቹ የምኖር ይመስልሻል? አላረገውም፡፡ አባቴም አላረገውም፡፡ እንዲገባ እቢ፡፡

መስከ... መስከዬ... ምነው ምን ሰራሁ? ምነው ማፍቀሬን እንደ በደል ቆጠርሽብኝ? ለምን ለፍቅሬ ምላሽ ነፈግሽኝ? ምግብ አልበላልህ ብሎኝ ውሃ ግን ጠጣ ጠጣ ይለኛል፡፡ ይህም ልቤ በፍቅርሽ መቃጠሉን የሚያመለክት መሆኑን ደርሼበታለሁ፡፡ ውሃ መጠጣት ስለበዛሁ ቤተሰቦቼና ጓደኞቼ "ታንከሩ" ብለው ቅፅል ስም አውጥተውልኛል፡፡ በእርግጥም የውሃ ታንከር ሆኛለሁ፡፡

ቆይ ልበጅ? ምን ይሰራልሻል? ቆይ እንደት ብዬ? እርዝ ሲዘንብ የመስከ ፀጉርሽን፤ እንደመንገድ መብራቶች እያንፀባረቁ ፍቅርን የሚረጩ ዓይኖችሽን፤ ምንጃላ ጻሊሽን... ያዩ እንኳንና እኔ ያረቀርቡሽ የሰሙሽ አይሳሳላቸውም? ከዚህ በላይ ግን አልታገስሽም፡፡ ስሞኑን ደግሞ ጭራሽ ለጎይኔ ረሀብ ልትሆኚ ከዛ መካከሉ ወንድምሽ ጋር ለመናር ቤት መቀየርሽን መጥቼ ሳጣሽ ከጎደኞችሽ ተረዳሁ፡፡ ካሁን በኋላ ለፍቅር ያልታደለውን ልቤን ለበቀል አዶቼን ለእርምጃ እንዳትጋብዣቸው፡፡ ለዛን መልስ እፈልጋለሁ፡፡ ፍቅር ወይም ሞት! አፍቃሪሽ ዘውዱ፡፡" ብዬ ሳትጨርስ፤

"ዘውዱ ተሰማ?" አለ አሉላ ደንግጦ፡፡

"ታውቀዋለህ?"

"የአጻምጠው ወንድም አይደለም?"

"አዎን ነው፡፡"

"የት ነው አሁን የሚኖር?"

"የባህዳር ማረሚያ ቤት ዘበኛ ነው!"

"ፖሊስ ሆኗላ!"

"አዎ፤ የወህኒ ቤት ዘበኛ ነው፡፡"

[illegible]

ንግልናዬን ጠብቄ በንፅሕናና በቅድስና እግዚአብሔርን አገለግለዋለሁ
የልኩ የሥጋ ፍላጐቴን በመንፈሳዊ ህይወቴ አፍኜ ኖርኩ።"

"አሉላ? እኔም እኮ ድንግል ነኝ። ድንግል ድንግልን ያረክሰዋል?"

"እህቴ ነሻ!"

"እርግጠኛ ነህ?"

"አይደለሽም እንዴ?"

ነረ በእግዚአብሔር ነፍሴን አታስጨንቃት! እኔ ግን እህትህም ልሁን
ንምህ እወድሃለሁ!" ተፋጠው ተያዩ።

# ፲፪

ስድስት ሽማግሌዎች ከደጅ ሳምነትና አጎዛ ተነጥፎላቸው ተቀምጠዋል። ጠዋት በመሆኑ ሁሉም ጋቢ ለብሰዋል። የጠዋቱ ብርድና ነፋስ ራሳቸውን ጠቅ ስላደረጋቸው ተከናንበዋል። የመርጊያሽ አባት ብላታ ቁሜ በነጭ ሻሽ ራሳቸውን አስረው ከመሀል ተቀምጠዋል። በራቸው ከሻሹ ድግል መሀል ይታያል።

ከፊት ለፊታቸው ከይበልጣል ፊንጠር ብላ የተቀመጠችው መርጊያሽ ቆመችና ክንብንቧን አውርዳ "አባቶቼ በጧቱ ያስቸገርኳችሁ ጉዳዬ ሳይገባችሁ አይቀርም። ትዳር የያዝኩ መስሎኝ ደፋ ቀና እያልኩ በምኖርበት ቤት ወጥቶ ገብቶ ከኔ ጋር ንትርክና ጭቅጭቅ አበዛ። ከአሁን በፊት እንደምታስታውሱት ብዙ ጊዜ እንድታፋቱኝ አስቸግሬያችሁ ትዳር የያዝኩ መስሏችሁ አስማምታችሁኝ ቃላችሁን ጠብቄ እየኖርኩ እያለ እንደሚስቱ ሳይሆን እንደ ገረዱ ስላየኝ ያለኝን ንብረቴን እንድታካፍሉኝ እማጠናችኋለሁ።" ብላ ስትቀመጥ ይበልጣል ዱላውን ጥሎ ክንብንቡን አወረደና፣

"አባቶቼ ይታያችሁ… እኔ ለማኝ እሷ ተለማኝ ሆነን እስከዛሬ አንድ ቀን እንኳ ትዳር ያለኝ ሳይመስለኝ በገዛ ቤቴ እንግዳ ሆኜ በተቀመጥኩ ውሃ ለውሃ እንደተማሬ ስማስን ውዬ ቀብሌ ለቀበሌ ዓሣ ተሸክሜ ዞሬ ሸጬ በገባሁ ከቤት እግሯን ዘርግታ ነገር ስትሰበስብ ወሬ ስታደራ ትውልና ማታ ስገባ ገና ከበር መወረፍ ትጀምረኛለች። እስኪ ይታያችሁ ለደከመና ለማስነ ሰው ይህ ነበር ዋጋው? ደግሞስ ይሁን አንድ ቀን ልብ ትገዛለች

Scanned with CamScanner

በዬ ሃያ ዓመት ሙሉ ኖሬ ትናንት ራሷ ባነሳችው ጭቅጭቅ ብንጋጭ ዕቃውን ሁሉ ሰባብራ ጎታውን አፈራርሳ ስልቻዎችንና አቁማዳዎችን አቃጥላ ቤቱ ጣራና ግድግዳው ብቻ ቀርቷል። ያቃጠለችው ደግሞ የራሷን ዕቃ አይደለም። የቀድሞ ባለቤቴ የሰፋችውን የስፌት ዕቃ፣ የሠራችውን ጎታ እና የጠጅ መጣያዋን ማሰሮና ጋኖች ሁሉ ነው።

"እርሷማ ወሬ ከማራገብ በቀር ሃያ ዓመት ሙሉ አንድ ወስከምቢያ እንኳ አልሰፋችም። በዚህ ራሷን ዞር ብላ ብትገመግመው ይሻላት ነበር። ይታያችሁ! ያ ግድግዳውን ተደግፎ የምታዩት አከንባሎ ከዛሬ ሃያ ዓመት በፊት የዱሮ ባለቤቴ የሠራችው ነው። አሁን ደግሞ 'አካፍሉኝ ንብሬቴን' ስትል ትንሽ እንኳ አታፍርም። ምኑን ነው የምንካፈል? ምን ጥሪት ኖሮን? ንብረቴ የጣና ሐይቅ ዓሣ ነው። ዓሣ ከሆነ መካፈል የፈለገች ያውላት ሐይቁ። ያውላት ጣናው።" ሲል የምትመልሰውን አጣች።

ከሽማግሌዎች አንዱ ሆኖ የመጣው አዳምጠው፣ ይበልጣል አፏን ስለአስያዛት ብሽቅ ብሏል። የሚናገረው ባይኖረውም ሲናገር ጉሮሮውን ጠራረገ። "እያችሁ... መቼም አብሮ መኖር ቀላል አይደለም። አለመግባባት ይኖራል። ጉልቻና ጉልቻ እንኳ ይጋጫል። በዚህ ደግሞ ሴቶች በብዛት ይጎዳሉ። ንብረታቸውን ተካፍለው የሚሄዱ ጥቂቶቹ ናቸው። ብዙዎቹ እንኳን ሃብት ንብረት ቀርቶ ነጠላ እንኳ ሳይደርቡ ራሳቸውን በሁለት እጃቸው ይዘው እያለቀሱ ይሄዳሉ...ይሄ ባለፈው የቀበሌ ገበሬ ማህበራችን ስብሰባ ላይ ተነስቶ ብዙ የተወያየንበት ጉዳይ ነው። እኛም እንደ መንግስት..." ብሎ ሳይጨርስ፣ "እኔ ግን ምንም አላደረግኋትም። ወንዱ እንደሴት ሆኜ እግሯን አጥቤ፣ ቢያማት ተንከራትቼ አስታምሜ ነው! አንድ ቀን እንኳ እንደወንዶች አፍ እላፊ አልሰደብኳትም። እንኳን ዱላ እንኳን ቅሚያ። እና አቶ አዳምጠው ያቀረብከው ምሳሌ ለእኔና ለመርጊያሽ አይሆንም። በዚህች ቤት ውስጥ ያለው ግን በእኔ በወንዱ ላይ የተፈፀመ በደል እንጂ በሴቷ ላይ የተደረገ ጭቆና አይደለም" ብሎ ይበልጣል የአዳምጠውን ድጋፍ አከሸፈበት።



ከመሀል የተቀመጡት ሽማግሌ ነጭ ጭራቸውን ከግራ ወደ ቀኝ ሸው እያደረጉ ምክር ጀመሩ።

"ይህች በጧት ሙቀቷን ስትለግስን ጀርባችንን አጉብጠን ደረታችንን ገልብጠን የስጠናት ፀሐይ ስትበረታ ሲረፋፍድ ስታቃጥለን ጥላችንን እንዘረጋባታለን። ቀትሩ አልፎ ስትዘቀዘቅ መሽብን ብለን እንጣደፋለን። ቀኗን ጨርሳ ጨለማ ሲተካ በተራራዎች ገመገም ከአድማሱ ዳርቻ ስትገባና በመስኮቷ በኩል ስትጠልቅ በጣና አፋፍ ቆመን በስስት እንሰናበታታለን። የእኛም ነገር እንደዚሁ ነው። ስንገናኝ እንዋደዳለን። እንፋቀራለን። እኔ ይቅርብኝ ላንቺ እኔ ይቅርብኝ ላንተ እንባባላለን። ነገር እንደነፋስ መግቢያ እያጣምና አሉባልታ ሲገባ እንደቀትሩ እንቅልቅል ያቃጠለን ፍቅራችን ላይ ውሃ እንከልስበታለን። ከሞቀ ትዳራችንና ፍቅራችን ላይ ውሃ በመከለሳችን ፍቅራችን የውሻ አፍንጫ ይሆናል። ያችን ቀትር ያችን ነዳዳ ስሜት ብናልፋት ግን አብረን እናመሽ ነበር። መቼም መቀዳደም አይቀርም አንዱን ሞት ቢነጥቀው እንደ ምሽቷ ጀንበር በስስት እንሰየዋለን። ደረታችንን እንደቃለን። ማቅ እንለብሳለን። ለጠሉት ወዳጅ ግን ማቅ አይለበስም። ቢሞት አይቆረቆርም። ልጆቼ እናንተም ይህችን ቀትር እለፏት። እሳትና ገለባ አትሁኑ። አንዱ እሳት ሲሆን ሌላው ጭድ መሆን ሳይሆን ያለበት ውሃ ነው። አብራችሁ ስለማምሸት እንጂ ስለመለያየት ለምን ታስባላችሁ? ይቅር ተባባሉ ልጆቼ። ነገራችሁን ሁሉ ሰማነው። በኔ በኩል ለፍቺ የሚያበቃ ነገር አላገኘሁም። ያለ ምክንያት ትዳር አፍርሱ ብዬ ንብረት ባካፍል እግዚአብሔር ነፍሴን ይጠይቃታል።" ብለው ዝም አሉ።

"ምክንያትማ አለ እንጂ! ከጭቅጭቅ በላይ ከንትርክ የበለጠ ምክንያት አለ እንዴ? ልብ ለልብ ካልተገናኘን አንዱ ገዢ ሌላው ተገዢ አንዱ ጌታ ሌላው ባሪያ የሆነበት ትዳር ይሰምራል? እኩል እናስብ እንከባበር ብላት አሻፈረኝ አለችኝ። ከሰው ፊት አዋረደችኝ። ውሻ ላይ እንኳ የማይደረገውን እጣቢ ደፋችብኝ። ከዚህ ወዲያ ምክንያት አለ አባቶቼ?" አለ ይበልጣል መሬት መሬቱን እያየ።

ሌላኛው ሽማግሌ መሬቱን በእጃቸው ተመርኩዘው ከተቀመጡበት ተነሱ፡፡
"ተዉ እንጂ ልጆቼ! የሽማግሌ ቃልማ መስማት ያስፈልጋል፡፡ እኛንም አታዋርዱን፡፡ ልናስታርቅ እንጂ ልናጣላችሁ አልመጣንም፡፡ ድሮ ድሮ የሽማግሌ ቃል ይሰማ ነበር፡፡ እኛም እዚህ ደርሰን ሁለት ፀጉር ያበቀልነው የአባቶቻችን ቃል ሰምተን ነው፡፡

"ዛሬ ዛሬ እርጥቡ ነደደ፡፡ ውሃው ሸቅብ ፈሰሰ፡፡ የማይማገደውን ቀንጠፋንና ጉመሮን እንጀራ ጋግረን በላንበት፡፡ የአባቶቻችን ምርቃት እርግማን ሆኖ መሬት ባዶዋን ቀረች፡፡ ድንጋዮች ብቻ ገጠጡ፡፡ ትልቅ ሰው ጠፋ፡፡ ትልቅ ዛፍ እንኳ ጠፋ፡፡ የዝናብ ማባሪያ የነፋስና የወጀቦ ማገጃ አጣን፡፡ ብዙዎች አባቶቻችን እየረገሙን ሞቱ፡፡ እያወገዙን ወደ መቃብር ወረዱ፡፡ እርግማናቸውን ጋቢያችንን ዘርግተን ተቀበልነው፡፡ ከዛ ወዲህ የሽማግሌን ምክርና የእናቶችን ተግሣፅ የሚያዳምጥ ጆሮ ጠፋ፡፡ ልጆች በጎልማሳነታቸው ሞቱ፡፡ ሽማግሌ ጠፋ፡፡ እስኪ አሁን አርጅቶ፣ አጎንብሶ፣ ምርኩዝ ጨብጦ የሚሄድ ሰው መንገድ ያጋጥማችኋል? ተዉ ልጆቼ ቃላችንን ስሙ፡፡ ዘመኑ ወራቱ ቡቃያዎች የበቀሉበት ጉልጓሎ እርሻ የሚካሄድበት ሳለ የዘራችሁት ሳያሸት ምኑን አካፍለን እናለያያችሁ? ክረምቱ ጨለማው ሲመጣ መፋታት ምን ይሉታል? ታናናሾቻችሁ ጎጆ ሲወጡ እናንተ ቤት ልታፈርሱ?
"ባይሆን ክረምቱ ይፍሰስላችሁና በመኸሩ አዝመራችሁን ሸክፋችሁ-ያነዜ ካልሆነ ንብረታችሁን እናካፍላለን፡፡" ብለው ዝም ሲሉ የመርጊያሽ አባት መር ብለው ተነሱ፡፡

"ልጄ ትናንት ማታ በጨለማ መጥታ ስቅስቅ ብላ እያለቀሰች ነግራኛለች፡፡ ከልጄ ሰንብ የተረዳሁት እንዳንገበገባትና እንዳንገሸገሻት ነው፡፡ እኔ አባቷ እንኳን ሰሷ ሰልጄ ለማንም አተርፉለሁ"
"እኔ ግን አላውቅም፡፡ ይትረፍዎት አይትረፍዎት ማጫ ሰጥተው አልዳሯትም፡፡ እሱን ባህርዳር ቀበሌ ስድስት ሄደው ይጠይቁ፡፡ ጠላ ቤቱን አስትቼ 'ሬታን ጋለሞታዋን አገባ' እያለ አዳሜ ሲስቅብኝ ጆሮ ዳባ



ልበስ ብዬ ሰው ባደረግኳት ዛሬ ደግሞ ሰጥተው እንደዳሯት ዕቃ ሊካፈሉ አህያና በቅሎ ጭነው መምጣትዎ ያሳፍራል፡፡" አለ ይበልጣል ምርር ብሎት ተነስቶ፡፡

"እኮ አንተ! ወይኔ ብላታ! አንተ?! ክፍት ባደረ አፍህ እኔን እንዲህ ታዋርደኛ? ማን ነው ያሳደገህ ባክህ!"

"አዎ፡፡ እኔን እንደርስዎ ልጅ ብላታ ወይም ፊታውራሪ አላሳደገኝም፡፡ ራሴ ጥሬ ግሬ የረካባ ጥጃ ጠብቄ ነው ያደግሁት፡፡ ግን አልሰርቅም አልቀጥፍም፡፡ ትልቅ ስም የለኝም፡፡ የጉደፈ ርካሽ ስምም አላገኘሁም፡፡ አዎ አባቴም እንደኔ ዓሣ አስጋሪ ነበር፡፡ እንደርስዎ ሸማ ለባሽ አልነበረም፡፡ ልጅዎን ግን ካሁን በኋላ ለሀብታምና ጥሩ ዝና ላለው መዳር ይችላሉ፡፡"

"እኮ አንተ! እባክህ ልጄን ያዝልኝ አልኩህ? አንተ ቅርናታም!" ብለው ከዘራቸውን ወደ አናቱ ሲልኩ ሽማግሌዎች በመቋሚያቸው መክተው አዳኑት፡፡

"ልብ አድርጉ አባቶች፡፡ ልብ በሉ፡፡ የተገፋሁ እቅም አንሶኝ አይደለም፡፡ የመረረኝ ደሀ ነኝ፡፡ መሮኛል ራስዎን እንዳልፈረክስልዎት! ተከብረው ቢቀመጡ ይሻልዎታል፡፡"

"አንተ ግማታም! የማንን አባት ነው የምትፈረክስ፡፡ አንተ ሙትቻ ጥንብ! እንኳን አባቴን እኔንም አትችል፡፡" ብላ መርጊያሽ የሙቀጫ ልጅ አንስታ ልትማታ ተገለገለች፡፡ ሽማግሌዎች ሁለቱንም ጎራ ይዘው መገላገል ቢጀምሩም ከሁለቱ ጎራ የሚወጡት የስድብ ቃላት ጠቡን አባብሰውት የመንደሩ ሰው ተሰበሰበ፡፡

"አንቺ ስካራም ወንዶ! እስከ ዛሬ እንደባሪያ አንገቴን ደፍቼ ብገዛልሽ ልብ የሌለኝ፣ የማይመረኝ ድንጋይ መሰልኩሽ"
"እንደኮሶ ይምረርሃ!"

"ደህን እንደክሶ ሲመረው እንቆቆ ይሆናል!" ብሎ ሲገስገል "ልብ በሉ! ልብ አድርጉ! አባቴን ሲገለው ነው። አባ ሰባጋዲስን ገሎ መደብ ውስጥ እንደቀበራቸው ደግሞ አባቴን ሊቀብረው ነው! ኡኡ!" ብላ መርጊያሽ አገሩን በእሪታ አደባለቀችው።

ሁሉም ሽማግሌዎች ራሳቸውን ያዙ። ክው ብለው ቆሙ። የሰሙትን ማመን አቃታቸው።

"አንተ ጉዳም! ጉድህን ደብቄልህ በኖርኩ አፍህን ከፍተህ አባቴን ታዋርደው? አባቴን ልትገለው! ትገዛት? አባ ሰባጋዲስን ከትክቶ የቀበረውን እጅህን አባቴ ላይ ትዘረጋው። አንት ከሃዲ! አንት ነፍስ ገዳይ! አንተ ሰው በላ!" ስትል አልገባህ አለው። ተንቀጠቀጠ። ተርበደበደ። ምላሱ ተሳሰረ። መልስ አጣ።

አዳምጠው መሣሪያውን አቀባብሎ ወደ ሰማይ አንድ ጥይት ሲተኩስ መንደሩ ሁሉ በሩጫ ከደጃፍ ተሰበሰበ። እሪታ ቀለጠ። የአባ ሰባጋዲስ ነገር ያንገበገበው ሁሉ ዱላውን እየመዠለጠ መጣ። ይበልጣልን ውሃ ሳይል መሀል እናቱን ብሎ ሊገድል አሰፈሰፈ። ሽማግሌዎች ወጣቶችን እየገሰገሱ 'ተረጋጉ' ቢሉም የሚሰማቸው አጡ።

ይበልጣል በሩን ከፍቶ ገብቶ ቤቱ ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን አድዋማ አውርዶ ትልቁን መደብ መቆፈር ጀመረ። አዲሱን መደብ! "ሰሜን ልታጠፉ እንጂ አባ ሰባጋዲስን አልገደልኩም!" እያለ ሲቆፍ ባዶ ገደል ያገኝ መስሎት ነበር። ከውጭ የከበበው ሰው መሳሪያ ይዞ ወጥቶ ይፈጀናል ብሎ ስለሰጋ ጥግ ጥግ ይዞ ቆመ። አሮጊቶች ደረታቸውን እየደቁ ነጠላቸውን እየዘቀዘቁ የአባ ሰባጋዲስን ስም እየጠሩ ማልቀስ ጀመሩ። ፊታቸውን የነጩም አሉ። አዳምጠው "ኑ ጉድ እዩ!" ብሎ ህዝቡን እየመራ ወደ ቤት ሲገባ ይበልጣል መደቡን እየቆፈረ ነበር። ቤቱ ጠጠር መጣያ እስኪታጣ በሰው ተሞላ። ከበሩ ላይ የሚገፋው አንዱ በአንዱ ትከሻ ላይ አንገቱን እያዘለቀ ሲያይ አጭር መግቢያ አጥቶ ከሥር አዳምጠው መሳሪያውን



ከይበልጣል ጀሮ ላይ ደግና ሲቆፍር ይከታተለዋል። ወደቡ እንደተደረመሰ የቤቱ ግማት ሰውን ወደ ውጭ ሲያባርረው ቢመጣም ከጥቂቱ በቀር ማንም አልወጣም። ጉዱን ለማየት አዳሜ በጋቢው አፍንጫውን ይዞ ቆመ።

መጀመሪያ መጥረቢያ ከአፈር ጋር ተደባልቆ ብቅ አለ። ከዚያ በኋላ ግን እጁ መቆፈር አልቻለም። ነጭ ሸበት ላይ በደረቀ ደም የጠገበ ጭንቅላት ታየው። ተዝለፍልፎ ወደቀ።

"ና - የደብረ ማርያም ህዝብ ጉድህን እይ! ና... ተአምር ተመልከት። ና ይህን ወንጀል መስክረህ አጋልጥ። አባትህ እዚህ አሉ። የአባታችን አፅም እንደተራ ዕቃ እዚህ መደብ ሥር አለልህ። ና - ጉድ በል አገሬ" እያለ አዳምጠው ለፈለፈ። ህዝቡ አሰፍስፎ ገባ። አንዳንዶች ሌላ ነገር ሲተናነቃቸው ሆዳቸውን እየደገፉ ወጡ። ያዩትን ሰቆቃ መቋቋም ያቃታቸው ራሳቸውን ስተው ሲወድቁ የበረታው እየተሸከመ ወደጓሮ ወስዶ ውሃ ይደፋባቸዋል።

ይበልጣልን እንደ አበደ ውሻ ሁሉም ቀጠቀጠው። ልብሱን እየሳበ ትንሽ ትልቁ ባገኘው ሁሉ ወገረው። ያጠለቃት ጥብቆ ተቀዳዳ እርቃኑን ሆነ። ጥርሱ ደም ጎረሰ። ፊቱ ደም ለበሰ። ደሙ በጢሙ እየተንጠባጠበ ቁምጣውን አጨቀየው።

የአካባቢው ሚሊሻዎች የጥይቱን ተኩስ ሲሰሙ መሣሪያቸውን እየነጠቁ እነሱም በማዶው እየተኮሱ መጡ። የሰማው ላልሰማው እያዳረሰ ይህ ጉድ ዓባይ ማዶ ደረስ ተሰማ። የሕዝቡ ብዛት የአንድ ገቢያ ያህል ሆነ።

ሚሊሻዎች ይበልጣልን እየደበደቡ በአዳምጠው ጥብቅ ትዕዛዝ ነፍሱ እንዳትጠፋ አድርገው እንዲቀጠቅጡት ስለታዘዙ እየደበደቡ ከቤት አወጡት። በድኑን በጀንዲ ጠፍሮ እንዲሸከም አደረጉት።

የአባ ሰባጋዲስን በድን አሸክመው ወደ ጣቢያ ሲነዱት ካህናቱ ከፊት ቆመው አሳሳልፍ አሉ።

“የአባታችን በድን ክቡር ነው፤ ቅዱስ ነው። ተሰርቆ እንደተገኘ ሸቀጥ ይዛችሁት ከተማ ለከተማ አትዞሩም። ስጡን።” ብለው አመፁ።

“ከፈለጋችሁ ገዳያቸውን ከሕግ አድርሱልን እሳቸውን ግን ቆሞስ ናቸውና በድናቸውን የመንካት ስልጣን የላችሁም፤ አስከሬናቸው በቃለ እግዚአብሔር ይከብራል እንጂ” አሉ።

ካህናቱ አስከሬናቸውን ተረክበው ወደ ቤተክርስቲያን ከሕዝቡ ጋር በለቅሶ በዋይታ ሲሄዱ ከፊሉ ሕዝብ ይበልጣልን እየደበደበና በድንጋይ እየወገረ ተከተለ።

ከሲቀመንበር አዳምጠው ግቢ ሲገባ ሚሊሻዎች ከበሩ ላይ ሕዝቡን መለሱት። አዳምጠው ወደ ጠባቧ ማጎሪያ ቤት አስገብተው እንዲደበድቡት አዘዙ። ትንሿ ማጎሪያ ውስጥ ውሃ እየተደፋበት በፍልጥ ሲደበደብ ውሎ ፀሐይ ሲገባ ደከመ። አዳምጠውም ቤቱ ውስጥ ሕይወቱ እንዳያልፍ ስለሰጋ ሚሊሻዎች በቃሬዛ ተሸክመው ፖሊስ ጣቢያ ወሰዱት-ባህር ዳር።



# ፲፫

አሉላና መስከረም የብሔራዊ ፈተና ያጠናቀቁባትን ምሽት ቤታቸው ውስጥ ሞቅ ደመቅ አድርገዋታል። እናቷ ለሻይ መጠጫ ብላ የሰጠቻት ገንዘብ ገፋ ያለች ስለነበረች ይህችን ምሽት አድምቃላቸዋለች። ከጓደኞቻቸው ጋር ፊልም ሞልተው ፎቶ ሲነሱና ሲዝናኑ ውለው ከተበተኑ በኋላ ወደ ቤታቸው ገብተው ሌላ አዲስ መዝናኛ ከፍተዋል።

“በእውነት አሉላ እንደዛሬ ስትጫወት አይቼህ አላውቅም። እንዲህ ስትስቅና ስትጫወት እንዴት ያምርብሀል መሰለህ?”

“በይ አትቀልጂብኝ እባክሽ፣ እኔ ስቆ ማሳቁን አላውቅበትም። እንዴት አላየሽም ጨዋታውን ወደ ቁምነገር እየቀየርኩባቸው ወሬ ሳቆረፍድ?”

“በእውነት ለኔ ነግረውኛል። ጎበዙ ወንድምሽ እንዲህ ሲጫወት አይተነው አናውቅም እስከዛሬ ምን ሆኖ ነው ባክሽ? በእውነት ጎድቶን ነበር። ለነገሩ ጎበዝ ተማሪዎች ጨዋታውንም ቁም ነገሩንም ያውቁበታል። አውቀው እያደፈጡ እንጂ ነው ሲሉኝ የነበር።”

“ሲያጋንኑ ነው እባክሽ! ሲያላግጡብኝ ነው።”

“ባይገርምህ እናንተ ክፍል ያለችው ሰገነት የሚሏት ያች ቆንጆየዋ ልጅ እንደወደደችህ ገብቶኛል። በቃ'ኮ ዓይኗ ካንተ ላይ አይነቀልም! ምን እንዳለች ታውቃለህ? ሙሉ ሰው አሉላ ብቻ ነው። ሌላው ጎደሎ ነው። እሱ'ኮ ከእውቀቱም ከፀባዩም ከውበቱም ያልነፈገው ነው አለች።”

Scanned with CamScanner

ኔ ደግሞ እንዲህ ዓይነት ከንቱ ውዳሴ ነው የማይገባኝ። ሙሉ ሰው የሚባል የለም። ሁሉም ሰው በጎደሉና በሙሉ መካከል የሚዋልል ነው። ጎደሉውን ሲሞላ ይባክናል። ምሉዕ ሲሆን መስሳሉን ይወጣል። የመስሳሏን የመጨረሻ እንጩት ግን የረገጠ በዚህች ዓለም ላይ የለም። ለመሆኑ ፈተናውን በደንብ ሠርተሸዋል አይደል?"

"ውጤቱን እግዚአብሔር ይባርከው እንጂ እኔ ያቅሜን ሠርቻለሁ።"

"እግዚአብሔር ደግሞ የሚፈቅደው የዘራሽዉን እንድታጭጂ ብቻ ነው..."

"ነገ ለራሷ ትጨነቅ። ብቻ ዛሬ መፅናናቱ ነው ዋናው።"

"ብይ ድክም ብሎኛል ልተኛ።"

"ተኛ በል እኔም ወደ ፍራሼ ላዝግም።" ብላ ከራሷ ፍራሽ ላይ እጆቿን አመናቅራ ተኛች። እንቅልፍ ግን እምቢ አሳት።

ጨለማ የነገሰበት ሌሊት የእንቅልፍ መላእክት ስለእንቅልፍ በሚዘምሩበት ምሽት ፅልመት የዋጠው ሰማይ የደመና በርኖሱን ደረበ። ጥቋቁር ደመናዎች ሰማዩን ወረሩት። ቁርና ብርድ የብርድ ልብሷን ጥሰው አንሶላዋን አልፈው ወደ ውስጧ ዘለቁ።

ሰማዩ ከሉን ለብሶ በመብረቅ ሲታረስና በነጐድጓድ ሲንቀጠቀጥ ያኔ መስከረም ወደ አሉላ ጉያ ሽጉጥ ማለት አማራት። ግን ቀን ከንፈሩን ከመሳም ውጭ ጨለማው ሌሊት ሲመጣ አያስቀርባትም። ልዩ ፍጡር መስሎ ይታያታል፤ የፍቅር ጦር የማይወጋው የአድማስ ጥግ ድንጋይ።

ያለ የሌለ ኃይሏን አጠራቅማ ደፈረች። በዛ ድደን ሌሊት መስከረም የእንቅልፍ መላእክት የከበቡትን አሉላን ፍለጋ ተነሳች። አንሶላው ውስጥ ገብታ ፈርጣማ አካሉን ዳበሰች። ፀጉሯን እንደካባ በጀርባው ደፋችለት። እንደባህር ዳር ጨፌ በፊቱ ላይ ነሰነሰችው። ያኔ ፍቅሯ ነቃ። "ወንድሟ" ባነነ። እንዳይናገራት አፉን በአፏ ዘጋችው። ትንፋሿን ወደ ሳንባው ላከች፤



፡ በሹል ጡቶቿ ደረቱን ወግታ መናገሪያ አንደበቱን ከለከለችው። "ሌሊቱን ሰማው፤ ይጮሃል። ቁሩ አጥንት በረዶ ያደርጋል። ወጀቡ ጣራችንን ሊፈነቅለው ነው። መጣሁ። ተጠጋሁህ። እቅፍ ብቻ አድርገኝና እንቅልፍ ይውሰደኝ።" አለችው። ሌሊቱ እንደምንም አለፈ።

ሲነጋ ግን ተጨነቀች። ጭንቀቱም በመንጋቱ አልነበረም፣ ፈተናውን እስኪፈተን የደበቀችውን ሀዘን በጧቱ ማርዳት ግድ ሆነባት።

"አሉላ?... እስኪ ንቃ!" አለች ጭንቀት ባዘለ ድምፅ።

"ዛሬማ ፈተና ጨርሰን አይደል? ትንሽ ልተኛ እንጂ።"

"የለም የምነግርህ ነገር ስላለኝ ነው።"

"የምን ነገር?"

"የአባ ሰባጋዲስን ነገር ሰምተሃል?"

"ኧረ የለም!"

"ጠፍተው ሀገር እየተንጓለለ አይደል እንዴ? እኔ'ኮ እስከዛሬ የደበቅሁህ በፈተና ጊዜ መናገሩን ጠልቸው ነው።"

"ምንድን ነው የምታወሪው!"

"እየቀለድኩ አይደለም።" ብላ በጥልቀት አሰበች። "ጠፉ" ብቻ ሳይሆን "ሞቱ" ማለት ፈለገች። ግን ፈራች። ምስጢር ዘክዝካ እናቷን ወህኒ ማውረድ አልመረጠችም። አሟሟታቸውን ለአሉላ መንገር እንዳለባት ግን ራሷን አሳመነች።

"በያ ንገሪኝ እንዴት ሊጠፉ ቻሉ?" አለ ተነስቶ እየተቁነጠነጠ።

"አሉላ... አባ የጠፉት ላይመለሱ ነው።"

"የት እንደሄዱ ታውቂያለሽ?"

"አውቃለሁ። ግን መንገርን እፈራለሁ።"

"በፈጠረሽ መስኪ..."

"ተቀመጥና ተረጋግተህ ስማኝ ይህን ጉድ ልንገርህ። ምስጢሩን ግን አጥብቀህ ልትይዘው ማልልኝ።"

"እመብርሃንን! አንቺ ሙች! ምስጢርሽ ምስጢሬ ነው።" ብሎ ዓይኑን አፍጦ አንገቱን አስግጎ ከአፏ የሚወጣውን በጉጉት ጠበቀ።

"እየውልህ... ባለፈው ያቡዬ ዋዜማ'ለት ካንተ ተለይቼ ቤት እንደሄድኩ ከባድ እንቅልፍ ጥሎኝ ነበር። በግምት ለአንድ ሰዓት ያህል ተኝቼ ስነቃ ፊቱን በጭንብል የሸፈነ ሰው አባ ሰባጋዲስን ከምስሶው ጋር አስሮ በመጥረቢያ ሲከተክታቸው አየሁ።"

"ኧረ በስመአብ በይ! ቅዠት ነው የምትነግሪኝ?" በድንጋጤ ክው አለ።
"ህልምም ቅዠትም አይደለም እውነት ነው። ይልቅ ተረጋግተህ ስማኝ። ብቻዬን የማልችለው ሰቆቃ ስለሆነ ነው የምነግርህ። የቤተሰቦቻችን ጉድ!"
"መስኪ ተይ እንጂ አታባቢኝ! እንደዚህ ያለ ቀልድማ አልቃለድም!"
"ቀልድ ሳይሆን ቁም ነገር... አባን በመጥረቢያ ሲከተክቷቸው እንዳይናገሩ አፋቸው ውስጥ ጨርቅ ጠቅጥቆ ነፍሳቸው ከወጣች በኋላ ደግሞ ቤት ውስጥ ሲቀብሩ አየሁ። ራሴን ስቼ ከተኛሁበት ዘልዬ ስታኘር እናቴ ዓይኔን ሸፍና ውሃ ደፋችብኝ። ከዛ በኋላ የነቃሁት ከእማሆይ ጦቢያ ቤት ወስዳ ጥላኝ ከዋልኩ በኋላ ነው። ..."

ቀጥላ የተናገረችውን አላዳመጣትም። ወጥቶ ተፈተለከ። እየተጣራች ተከተለችው።

• • • • • • • • • • • • • • •

ቤት ሲደርሱ ማንም አልነበረም። ሆጥታ በመንደሩ ሰፍኗል። ወደ ቤት ገቡ። ትልቁ የቤት ውስጥ መቃብር አፉን ከፍቷል። ሽታው ወደ ውጪ ገፈተራቸው። ብጣሽ ልብስ-ምንኩስና ከአፈሩ ውስጥ ተወሽቶ ስላየ ሳብ አድርጎ አየው። አዎን የአባ ሰባጋዲስ ልብስ- ምንኩስና ቁራጭ ነው። ቁራጩን ልብስ ጨምድዶ ያለቅስ ጀመር።

ቤቱን ለቀው ወደ ቤተክርስቲያኑ ሲሮጡ ከወደፊታቸው የሚመጣ አንድ ባላገር አገኙት።

"አባትህ አረፉ እንዴ?" አለው ባላገሩ ደንገጥ ብሎ።



"ማንኛው አባቴ"
"እቶ ይበልጣል ነዋ!"
"ምን ሆኖ?"
"እኔ እኮ በትናንትናው ድብደባ ያረፈ መስሎኝ ነው።"
"የምን ድብደባ?" አለ አሉላ የልብ ምቱ እየፈጠነ። ባላገሩ ከመጀመሪያው ጀምሮ የተፈፀመውን ሁሉ ዘርዝሮ ነገረው። ሕዝበ አዳሙ ሁሉ በዱላና በድንጋይ እንደወረደበትና ሚሊሻዎች ተረክበው ወደ አዳምጠው ግቢ እንዳስገቡት፣ በዚያም ውስጥ በድብደባ እንደዋሉበት ከሰማው ወሬ አክሎ ነገራቸው። ሰውዬውን ጥለውት ወደ ማዶ ተሻገሩ ወደ ቤተክርስቲያኑ።

ማህሌቱ ያሬድ ማህሌታይ ያለበት ይመስል ያረግዳል። የአባ ሰባጋዲስ አስከሬን በቤተክርስቲያን አልባሳት ደምቆ ከመሀል ተቀምጧል። ከዳጋ እስጢፋኖስ፣ ከኩበራን ገብርኤልና ከዘጌ ገዳማት የመጡ ደናግልና መነኮሳት ሀናዕል እና አብረቅራቂ ዣንጥላ ይዘው እያጠኑ ከበውታል። በአራቱም አቅጣጫ ባሉት መቅረዞች ላይ ሻማዎች ተለኩሰዋል። የባህርዳር ሊቃውንት፣ የዓባይ ማዶ ካህናትና ዲያቆናት፣ የደራ መምህራንና ምሁራን ሁሉ እየተላከባቸው ተሰብስበዋል።
ቅኔ ዘራፊዎች መወድሱን ያወርዱታል። የጎጃምና የበጌ ምድር ሊቃውንት ጥልቅ ሰምና ወርቅ ያለው ቅኔ ለመዝረፍ ይሽቀዳደማሉ፡ ፡ አንዱ ሲጀምር ሌላው ነጥቆ ይጨርስበታል። በቅኔ ላይ ቅኔ ፈሰሰ። ካህናቱና መዘምራኑ የሚጨብጡትን አጥተው ቆመው ማዳመጥ ጀመሩ። የቅኔው ባላባት ለሚባሉት አባ ሰባጋዲስ የሚበቃ ቅኔ ጠፋ።

የጎጃሙ ሲዘርፍ ጎጃሜው "ይበል! ይበል ነው!" ይላል። የበጌምድሩ ሲዘርፍ በጌምድሬው "ይበል ነው! እፁብ ነው!" ይላል። አሉላ ዙሪያውን የከበበውን ለቀስተኛና ካህናት እየገፈታተረ፣ እየጮኸ ገባ።

ከማህሌቱ መሀል ገብቶ ከአባ ሰባጋዲስ አስከሬን ስር ተንከባለለ። ተነስቶ የአስከሬኑን ልብስ ገፎ ሊያይ ሲል እጁን ተረባርበው ያዙት። "አባቴ... አባ... ለእርስዎ መጥረቢያ! ለእርስዎ ሞት! ወይኔ! ኧረ ተውኝ! አልሞቱም

አሉ! በፍፁም አይሞቱም! እርሳቸው ሞት አይነካቸውም! አትም የለውም! ኡኡኡ... እምቢ አይሞቱም! እምቢ..." እያለ በዕንባ እየታጠበ ሲያቸ ለማኙ ሲያስቸግር ዕንባ ያልመጣቸው ዓይናቸው ወረጨ። አልቅሰው የደከማቸው ዕንባቸው እንደገና በዓይናቸው ተቸለሰ።

ፀሎተ ፍትሐቱና ሥርአተ ቀብሩ ከተፈፀመ በኋላ ለቀስተኛውና ለየአድባራቱ አልባሳት ይዞ የመጣው ካህን ዓባይን በታንኳ እየተሻገረ ሙንዝ ጀመረ-በአባ ሰባጋዲስ አሟሟት እየተገረመ።



# ፲፩

ማዕከላዊ ባህርዳር። ምሽቱ በመግፋት ላይ ነው። በታዋቂ ዳንኪራ ቤቶች ውስጥ አስረሽ ምቺው ቀልጧል። ጣራና ግድግዳው ይርገፈገፋል።

አራቱ ጣልያናውያንና ሶስቱ ኢትዮጵያን ከአንዱ ቤት አንዱ ቤት በመዝለል ላይ ናቸው። ቄስ ፀሐይ ቀይ ሱሪና ባለ ኮፍያ ሰማያዊ ጃኬት በመልበሱ ማንም እንደማይለየው እርግጠኛ ሆኗል። የጃኬቱን ኮፍያ እስከቅንድቡ ስቦ ደፍቶታል። ቁልፉ በእጁ በመግባቱ ሁሉም ጮቤ በመርገጥ ላይ ናቸው። አዳምጠው እስክስታውን ያስነካዋል። ቄስ ፀሐይንም የሚችለው ጠፍቷል። አራቱ ፈረንጆች ከአስተርጓሚው ጋር ያገሬውን እስክስታ በመለማመድ ላይ ናቸው። ሰሌን ቆራጣ፤ ትከሻቸውን ወደታች ወደታች ይመነጭቁታል። በየገቡበት በቢራ የሚሞሉት ጠረጴዛ ሲነቃነቅ ጠርሙስ ሲሰበር የሚሰማው ኳኳታ ሌላ ነው። የዳንኪራ ቤቱ ወለል ሁሉ አሸወይና ሲሆን አመሸ።

የቄስ ፀሐይ ሆድ ያባውን በብቅሉ ማውጣት ጀምሯል። "ያንን ጫጩት አላቀውም!" እያለ ይለፈልፋል። "ለአሉላ ብቻ ነው ሊያሳዩት የሚችሉ። ስንት ነገር የቀረቀሩበትን ጉድጓድ ከእሱ በቀር ለማንም አያሳዩም። ሰማችሁኝ? አላቀውም። ትርምቦውን ይገፍ እገባግቢቱ ገብቼ እንዲያሳየኝ አደርጋለሁ። ማርያምን አላቀውም! ... እሱ ሆድ ውስጥ ያን ሁሉ ሀብት ቀብረውት ከሆነም ሆዱን ከመቅደድ ወደኋላ አልልም!" እያለ ሲፎክርላቸው ሌሊቱ ተጋምሷል።

# ፲፫

አሉላ መሰንበቻውን እንደ እብድ ሲያረገው ቆይቷል። በአንድ በኩል አባቱ በአባ ሰባጋዲስ ግድያ እንዴት ሊሳተፍ እንደቻለ አልገባህ አለው። ይበልጣል በአባ ሰባጋዲስ ዘንድ እንደ ትሁት የሚታይ ሰው እንደሆነ ያውቃል። እርሱም ቢሆን ክፉ ያስብባቸዋል የሚል እምነት አልነበረውም። በሌላ በኩል በይበልጣል ላይ የተወሰነው የፍርድ ውሳኔ መፍጠኑ አጠራጥሮታል። ነገሩ ግራ ቀኝ ሳይጣራ ደንበኛ ወንጀል መርማሪ ጉዳዩን በውል ሳይመረምር በዚህ ፍጥነት በአባቱ ላይ የዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት መበየኑ በአባቱ ላይ የተደፈደፈ ነገር እንዳለ እንዲገምት አርጎታል።

ገና በጠዋት ተነስቶ ወደ ወህኒ ቤት ጉዞ የጀመረውም ለዚህ ነው። በብስጭት እስከአሁን ያልጠየቀውን አባቱን ለመጠየቅ ብቻም ሳይሆን ስለጉዳዩ ከእሱ ለመስማት ነው።

እሥረኛ ጠያቂዎች ረጅም ሰልፍ ሰርተዋል። የጠያቂ ቦኖ ካገኘ በኋላ ወደ አንድ ግርግም ሄዶ ተቀመጠ። ብዙም ሳይቆይ አባቱ በፖሊስ ታጅቦ መጣ።

“ልጄ አለህ?... እንኳንም ሳልሞት ዓይንህን አየሁ! ልጄ!... ልጄ! ሰው አጣሁ። ያለ በደሌ ያለ ኅጢአቴ በግፈኞች ሴራ ተፈረደብኝ። አየህ ልጄ ሰው ከሌለህ አፍህ ብቻ ዋጋ የለውም። ዓይኔ እያየ አንደበቴ መናገር እየቻለ አንደበተኞች በሐሰት ረቱኝ። እጄን ያለኃጢአቱ ለእጀ ሙቅ



ሰጠሁት።” አለ ይበልጣል የዕንባ ሳግ እየተናነቀው። የደቀቀ ሞራሉ ዳግም የሚጠገን አይመስልም። ስሜቱ ቀዝቀዝ ብሏል።

“አባባ... ስለወላዲተ አምላክ ሳትደብቅ ንገረኝ... በግድያው...”

“ልጄ...? አንተም እንደሌሎች ነፍስ ገዳይ አልከኝ? አይ ጉድ! ልጄ እኔኮ እንኳን በሰው ላይ በዶሮ ላይ የሚጨክን እጅ የለኝም። እባክህ ልጄ ባይሆን አንተ ወንጀለኛ አለመሆኔን እመነኝ። እኔ'ኮ ያቃጠለኝ ፍርድ መዛባቱ ብቻ አይደለም። በዚህች ምድር ላይ በግድያው እንደሌለሁበት የሚያምነኝ አንድም ፍጡር ማጣቴ ነው። ልጄ፣ ግደሉኝ አልኳቸው፣ ግን አይኔ እያየ የሚዘገንን ስቃይ ፈረዱብኝ። ዕርቃኔ ሥጋዬን በፍልጥና በስለት ሲተፈትፉኝ አደሩ። ይህን ሁሉ ግን...”

“ቆይ አባዬ... ወንጀሉን ማን እንደፈፀመውስ አታውቅም?”

“ባውቅማ መልካም ነበር። አንዷ ወንጀለኛ ግን ያች ሰይጣን ናት። መቀበሩንም ያወቅሁት... ጉዴንም የሰማሁት ከእርሷ ነው።” አለና እንባውን ማንገዋቅገዋቅ ቀጠለ።

“ልጄ አደራ የምልህ ግን፤ ያች ሰይጣን ባድማዬን ሸጣው እንዳትሄድ ሄደህ ያላወቅህ ያልሰማህ መስለህ ባድማዬን ጠብቅ። አደራ ይሁንብህ ልጄ።” ብሎ ማተቡን ያዘው። ፖሊሱ ሰዓት ደርሷል ይበቃል ብሎ ሲወስደው ጉንጩን ሳም አድርጎ ተለየው።

አሉላ የሰው ረሀብተኛ የሆነውን አባቱን በዓይኑ ሲሸኘው ዕንባው በረጅም አፍንጫው ላይ ተንኳሎ ወደ አንደኛው ቀዳዳ ገባ።

የእስር ቤቱን ቦኖ ሰጥቶ ሲመለስ አንድ ግራጫ ፍሬም ያለው መነፅር ያረገና ቡኒ ጃኬት የለበሰ ሰው ተከትሎ እንደሚፈልገው ነገረውና አስቆመው። በሰላሳዎቹ መጀመሪያ ላይ ያለ ጎልማሳ ነው።

“የአቶ ይበልጣል ልጅ ነህ፤ አይደል?” አለው መነፅሩን ከዝርጥ ጥቁር አፍንጫው ላይ እያስተካከለ።

Scanned with CamScanner

"አልተሳሳቱም" ጌታዬ" አለ አሉላ።

"የአባትህ ጠበቃ ነኝ። ተበጀ እባላለሁ። በአንዳንድ ጉዳዮች ዙሪያ እንድንነጋገር ፈቃደኛ ነህ?"

"መነጋገር እንችላለን።" አሉላ ለአባቱ ማን ጠበቃ ሲቀጥርለት እንደቻለ ሳላላወቀ ግር አለው።

"እንግዲያውስ ሻይ ቡና እያልን ብናወራ ይመረጣል።" አለና ወደ አንዲት ትንሽ ካፌ ሄደው ውጭ ወንበር አስወጥተው ተቀመጡ።

"አባትህ ይበልጣል እንዴት ያለ ሰው እንደሆነ በደንብ ታውቀዋለህ?" አለ እግሩን እግሩ ላይ አነባብሮ።

"ጥሩ ሰው ይመስለኝ ነበር። ይህን ያረገዋል ብዬ ማመን ይቸግረኛል። ጥጋበኛና ጋጠወጥ ሰው አልነበረም። ድህነቱን በመረቦቹ ሲሟገት የሚኖር ዓሣ አጥማጅ ነው።..."

"እና አባትህን ወደ ወንጀሉ የገፋፋው ማጣት ነው?"

"እኔ ማጣት ብቻውን ወንጀለኛ ያደርጋል ብዬ አላምንም። ለመኖር ይሠራል እንጂ ይህን ያህል የገንዘብ ፍቅር የለውም። ያገኛትን ለእኛ ለልጆቹ አካፍሎ ተመስገን ብሎ ይተኛል።"

"ሌላ ወደ ወንጀል የሚገፋፋው ነገር ያለ ይመስልሃል?"

"አባቴ ወንጀሉን ለመፈፀም የሚያበቃ ምንም ምክንያት የለውም። እንደውም አባ ሰባጋዲስን በጣም ይወዳቸው ነበር። የእኔም የቀለም አባቴ በመሆናቸው ከእርሱ እኩል እንደምወዳቸው ያውቃል። አባቴ አባቴን ሊገድል እጁን ያነሳል ብዬ አላስብም።"

"ግን አደረገው። አፅማቸውን አውጥቶ ሲጥል ሲል እጅ ከፍንጅ በሊቀ መንበሩ ተያዘ። በአደባባይ ወንጀለኛነቱን ራሱ በሠራው ስህተት አረጋገጠ።"

"ፍርዱ ግን..."



"የፍርድ ውሳኔው ለምን እንደፈጠነ አላወቅሁም። የመከላከያ ምስክር ማቅረብ አልቻልንም። ወደፊት የመከላከያ ምስክር የምናገኝ ከሆነ ይግባኝ የመጠየቅ እድል ይኖረናል።"

"ለመሆኑ ..." አለ አሉላ። "አባቴ ጠበቃ ከወዴት ሊያመጣ ቻለ?"

"ጥሩ ጥያቄ ነው። እኔ ይህን ሥራ የምሠራው በነፃ ነው።"

"እንዴት በነፃ ልትረዳው ፈለግህ?"

"ይኸኛውም ጥሩ ጥያቄ ነው። እንደማንኛውም ተቆርቋሪ ኢትዮጵያዊ በቅርስ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በቸልታ ማለፍ አልፈልግም። ሆኖም በዚህ ጉዳይ ላይ ቸልተኛ እንዲሆን አልፈልግም። የአባትህ ጉዳይ በዚህ ጉዳይ ላይ ስለሆነ በግል ቀርቤ ጠይቄዋለሁ። ልረዳው ተነሳሽነቴ የጨመረውም ይህ ጉዳይ ተድበስብሶ መታለፍ ስለሌለበት ነው። ሻምበል ዶሬ የተባሉ ወንጀል መርማሪም ጉዳዩን በጥብቅ እየተከታተሉ እንደሆነ ደርሼበታለሁ። እኔም ከዚህ ወንጀል ጀርባ ያሉ ስውር ወንጀለኞች ተገቢው ቅጣት እንዲጣልባቸው ካለኝ የግል ተነሳሽነት እንጂ ከአባትህ ሽራፊ ሳንቲም ፈልጌ አይምሰልህ። ይልቅስ ቤቱን ላሳይህና የመከላከያ ምስክሮች ይሆኑናል ብለህ የምታስባቸውን ሰዎች ትጠቁመኛለህ። የተለየ ጉዳይ ስታገኝም እየመጣህ ትነግረኛለህ። በመሆኑም መረጃዎችን አጠረቃቅመን በከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ እንጠይቃለን።"

"ደግ እንጂ። እኔማ ደስ ይለኛል።" አሉላ ጠበቃ ተበጀን ተከትሎ አድራሻውን አይቶ አመሻሽ ላይ ወደ ደብረ ማርያም ተመለሰ።

Scanned with CamScanner

# ፲፯

ሰ

Scanned with CamScanner

"እሱ ሰው ደግሞ ደስ አላለኝም። ወንድሙ መስከረምን ካላገባሁ ታንቄ እሞታለሁ' ብሎ ትናንት 'እናቱ ሽማግሌ ተላከ' ብላ ነገረችኝ። እኔስ የሱ ሰው ነገር እኳ'ኳንም አላማረኝም። ከእማዬ ጋር ትናንት ቤት አገኘሁትና ሲወጣ 'ወንድሙ አንችን ሊያገባ ስለፈለገ ሽማግሌ ሆኖ መጥቶ ነው' አለችኝ።" አለች ውሃውን በእግሮቿ እያንቦራጨቀች መስከረም።

"ካልሽስ ትናንት ልቤን ካጨሰው አንዱ የለበሰው ኮት የአባቴ ስለመሰለኝ ነው። በጣም ስለተናደድኩ ሳላስበው እንዴት አባቴ ታስሮ አንቺ እንዲህ ትቀብጫለሽ? አልኳት። ከዛ ያለችውን ሳልሰማ ወጥቼ ሄድኩ።"

"ከእርሱ ጋር መቅበጥ ለመጀመሯ እርግጠኛ ነህ?" አለችው ግንቦሯን ቋጥራ።

"እርግጠኛ ባልሆንም አንዳንድ ነገሮች እንድጠራጠር አድርገውኛል። መስኪ... እናትሽን ግን ትወጃታለሽ?" አላት ለይሉኝታ ብላ እናቷን እያጣጣለች እንዳይሆን ሰግቶ።

"ውስጧ ያለው ቋጥቋጦ ቢነቀል ልወዳት እችላለሁ።" አለች ትክዝ ብላ።

"እንዴት ያለ ቋጥቋጦ?"

"ውስጧ ትልቅ የተንኮል ቋጥቋጦ እንዳለ ይሰማኛል።" አለች። "እባክህ ለአንድ ደቂቃ እንኳ ስለቤተሰቦቻችን ረስተን ይህችን የምትጠልቅ ቀይ ጀንበር በአንባ ሳይሆን በሳቅ እንሸኛት?" ብላ ሐይቁን ደም አስመስላ የምትጠልቀውን ፀሐይ እያየች እጁን ሳበችው።

"እንዴት ብዬ መሳቅ እችላለሁ?"

"እዚህ ሐይቅ ውስጥ ያለውን ሰይጣን ደስ እንዳይለው ለሁለት እንሳቅበት!" አለች ዝም ብላ መሳቅ ያልፈለገችውን ሳቅ እየሳቀች።



"እዚህ ሐይቅ ውስጥ ሰይጣን እንዳለ ታምኛለሽ?"

"አለ እንጂ! እሱ ስላለ አይደል እንዴ ውሃው ስንጠጣው የሚጣላን!? ለአትክልቱ ስናጠጣው የሚያደርቅብን!? ስንዋኝበት የሚያሰጥመን!? ይልቅ አሁን ስለአስጨናቂዎቹ አታንሣብኝ... ና ወደዚህ..." ብላ ፊቱን በውሃ ረጨችው። ቀና የቀዘቀዘ ከንፈሩ ላይ የሞቀ ከንፈሯ አረፈበት።

መስከረም ጠፍጣፋው አለት ላይ ቆማ ከተንጠራራች በኋላ ቀሚሷን አወለቀችው። አሉላ ግራ ተጋባ።

"ምን እየሆንሽ ነው መስኪ?"

መስከረም ወደ እሱ ዙራ ተንከትክታ ሳቀችበት።

"አይዞህ አትፍራ።" አለች አሁንም ሳታፍረው ወደ እሱ እንደዞረች። ሊፈርጡ የደረሱ የሚመስሉ ጡቶቿን በሁለቱም መዳፎቿ ከሥር ያዘቻቸው። በግራ በኩል ያለው ጡቷን የፀሐይዋ ቀያይ ጨረሮች አርፈውበት በቀኝ በኩል ካለው የበለጠ የቀላ እንኮይ አስመሰሉት። ዞማ ፀጉሯ በጀርዋ በኩል አልፎ እንደጨፌ ብትን ብሎበታል። አጠቃላይ የገላዋ ቆዳ ከእግር እስከ ራሷ ያለ አካሏን ጭርንቅ አርጎ ይዟት ሲያይ የጠበባት መሰለው። የወጣትነቷ ትኩስ ደምና ስሜት በቆዳዋ ውስጥ ሲራወጥ የሚያይ መሰለው። አሉላን የማያውቀው አዲስ ስሜት ወረረው።

"ና እንጂ እንዋኝ?!... እንደማታውቀኝ አፍጥጠህ ታየኛለህ እንዴ?..."

አሉላን እስከ ልብሱ ወደ ሐይቁ ገፋችው። ልብሱን ለማውለቅም ሆነ ለመቃወም ጊዜ አልነበረውም። መለመላዋን ቆማ እጆችዋን ወደ ግራ ቀኝ ዳሌዎቿ አሳጥቃ ወደ ሐይቁ ተወረወረች። ውሃው ውስጥ ደፍቃ ትንፋሽ አሳጥታው ብቅ ሲል ትንፋሽ እስኪያጥረው ሳመችው።

እንደ ሳር ክዳን ቁልቁል የተደፋ ዞማ ፀጉሯን ጨምድዶ ይዞ እሱም በተራው ደፈቃት። ትንፋሽ አጥሯት ብቅ ስትልም ከመሳም አልዳነም።

"ኧረግ! ኧረግ!..." የሚል ጎርናና ሻካራ ድምፅ የሁለቱንም ጆሮዎች አቆማቸው። "ምናባህ እያደረካት ነው አንተ?!" ከንፈራቸውን አላቀው ድምፁን ወደሰሙበት ሲዞሩ የቀበሌው ሊቀ መንበር አዳምጠው መሳሪያውን ዘቅዝቆ የሚያረጉትን ሁሉ እየተመለከታቸው ነበር።

Scanned with CamScanner

"የኛ ዲያቆን!...እ?...ጉድ! ጉድ! አገር ጉድ ይበል እንገግዶህ!...ይህንን ማን ያምናል?... አንተ እርኩስ! ያውም እህትህን!?..." አዳምጠው ሌላ ሳይናገር ወደመጣበት ተመልሶ ሄደ። ከነሱ እስከርቅ የሚናገረው ሁሉ ያሰማቸው ነበር። "ጉድ ነው!... የጉድም ጉድ!...ጉድ በል ይብረ ማርያም እንገግዶህ! ጉድ!...ጉድ!..."

አሉላና መስከረም ደንገዘው ቀሩ። አፋቸው ተሳሰረ።

"የመከራው ዘገር!" አለች መስከረም ወጥታ ቀሚሷን እያጠለቀች። አሉላም ልብሱን አውልቆ ጨምቆ እስኪለብስ በደመነፍስ ውስጥ ነበር። "እኔ ነኝ አሉላ! እኔ ነኝ! ከዚህ ጉድ የከተትኩህ! አሳርፍ ብዬ..." መስከረም ትብሰከሰክ ጀመር። አሉላ ምንም መናገር አልቻለም።

ሁለታቸውም እንደደነዘዙ ፀሐይ በተራራዎቹ አናት ጠልቃ ድንግዝግዝ ብሎ ነበር። ወደ ቤት በዝምታ ጉዟቸውን ቀጠሉ። እረኞች ዋሽንታቸውን እያንቆረቆሩ ከብቶቻቸውን ወደ በረቶቻቸው እየነዱ ያፏጫሉ።

ቤት ሲደርሱ መርጊያሽ የምድጃውን እሳት እያንገረገረች ስትሞቅ አገኟት። ጎራዳዋን ገለብ አርጋ ሁለመናዋን ለሳቱ ሰጥታ ተቀምጣለች። አሉላና መስከረም ጥልቅ ሲሉ ሳመል ያህል ጭኖቿን ጠመም አርጋ ነገሯን ደበቀች። ያለ ሁል ጊዜዋ አንዳችም ቃል አልተናገረችም። መስከረም ቀጥታ ወደ አልጋው ወጥታ ተኛች። አሉላ መደቡ ላይ ተቀምጦ ዓይኖቹን ወለሉ ላይ ተከለ።

"ራት አትበላም?" አለች መርጊያሽ ለአሉላ ያዘጋጀችውን ምግብ እያቀረበች።

"ቢቀርብኝ ይሻላል። ተይው አልበላም።" አለ አሉላ መሬት መሬቱን እያዩ።

"ምን ሆነሃል ደሞ..."
"ምንም አልሆንሁ።"



ገበል ለሁሉም ራትህን ብላ፣ ልትተኛ ነው" አለች በሌማት እራቱን ወደፊቱ እያገፋች። ያለሁልጊዜዋ ራትህን ብላ ማለቷ ገረመው። ከዚያ ቀን ድረስ 'ብላ' ብላው አታውቅም። ሳትጠይቅ ምናምንቷ ነገር ፊቱ ላይ ወርወር አድርጋለት፣ ከበላ ይበላል ካልበላ ይተዋል እንጂ።

ዛሬ ያለወትሮዋ 'ብላ' ብላ ስትንተባተብ ምክንያቱ ባይገባውም የቀረበለትን መብላት ጀመረ። ወጡ በዘይት የበሰለ ነው። እንጀራው ያ የሻገተ እንጀራ ሳይሆን ምንዱባ የጤፍ እንጀራ ነው። ብሉኝ ብሉኝ ይላል። ዋጡኝ ዋጡኝ የሚል ዘፈሪታ የጤፍ እንጀራ ከመርጊያሽ ሲቀርብለት የመጀመሪያ ጊዜው ነው። ያደረገችው ሁሉ ለሰዷት ጥሩ ሰው ለመሆን ጉዞ የጀመረች ስለመሰለው "እመብርሃን ሆይ ከዚህ ለልጂ ምህረቱን ላኪላት!" አለ በልቡ።

"አንቺ መስከረም!" አለቻት አልጋ ላይ የተጋደመችውን ልጇን።

"እመት?" አለች ራሷን ቀና አድርጋ። "ሂጂና እማሆይ ጦቢያ ቤት እንጥፍጣፊ ላምባ እባክዎትን ይላኩልኝ ብላለች ብለሽ በዚያች ኩራዝ አምጭልኝ" ብላ መስከረምን ላከቻት።

አሉላ በልቶ ከጨረሰ በኋላ እጆቹን ታጥቦ ሲመለስ ተዝለፍልፎ ወደቀ። እጆቹ ሽባ ባለቤት አጡ። ዓይኖቹ ተስለምልመው ሽቅብ ወደ ቅንድቡ ተሰነጡ። የበላበት አፉ እንደተከፈተ ቀረ።

"ዋኛ አማች? አማቼ! የልጄ ባል? አትሰማም? አንተ ስለሌሎች ነፍስ ትሰብክ ነበር። የኛ ዲያቆን? ራስክን ለምን አትረዳም? ወይ... እየየየ..." ብላ መርጊያሽ ተሳለቀችና አዝላ እያንዘላዘለች ወደ ዓባይ ወሰደችው።

ገንቡ ላይ ቆማ ቁልቁል ወደሚጥመለመለው ውሃ ጣለችው። ጨለማው ዓይን ቢደነቆል ስለማያማይ እየተደናበረች ወደ ቤቷ ተመለሰች።

Scanned with CamScanner

መስከረም ከእማሆይ ጦቢያ ቤት ስትመለስ እናቷ ሰው ተሸክማ ወደ አባይ ስትወርድ አይታት ኖሮ ከኋላ-ኋላዋ ተከትላ ጥላው ስትመለስ ወዲያው ልብሷንና ጫማዋን አወላልቃ ወደ ዓባይ ዘለላ ገባች። በጨለማው ውስጥ እየዋኘች 'ከጆጆባው' ውስጥ የተወሸቀውን በድን መጎተት ጀመረች። አንድ አካሉን ጎትታ ስታወጣ ሌላኛው አካሉ ወደ ወንዙ እየተዝለፈለፈ ይገባል።

በውሃው ዳርቻ ከሚንጫጩት የዓባይ ዳር እንቁራሪቶች በቀር የሚሰማ ድምፅ የለም። በእርግጥ የሌላ ሰው ድምፅ መስማት አልፈለገችም። ሰው ቢያስፈልጋትም የሰውን መምጣት አልፈለገችም። ቢመጣ ይጨርስብኛል እንጂ ያግዘኛል ብላ አላሰበችም። ከወንዙ ማውጣት አልቻለችም።

አፏን ከአፉ ገጥማ አሽተተችው። ትንፋሹ የመርዝ ጠረን። ልቡን ስትነካው ለአመል ያህል ትር - ትር ይላል።

"አምላኬ ሆይ... አሉ!... አሉላ! ..." ተጣራች አልመለሰላትም። ሌላ መላ ታያት።

ሁለቱን ጣቶቿን ወደ አፉ አስገብታ ወደ እንጥሉ ገፋቻቸው። ያሰበችው ሆነ። ወዲያውኑ አስመለሰው። ትንፋሿን በአፍንጫው ለገሠችው። በእርሷ አተነፋፈስ ቁልቁል ወደ ሳንባው አየር ልካ መልሳ ራሷ ትተነፍስለታለች። ደረቱን ደገፍ አድርጋ ጫን ጫን ማረጓን ቀጠለች። ደጋግሞ እንዲያስታውከው ጣቶቿን ወደ ጉሮሮው ሳከች። መላልሶ አስመለሰው። በአፍንጫው የምህረት እስትንፋስ ሸው አለች። ከልቡ የህይወት ትርታ ተሰማች። ጥቂት እረፍት እስኪያደርግ ጠበቀችው ከቆይታ በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ጥርሷን ነክሳ ጎትታ አነሳችው።

ጊዜ ሳታጠፋ ደጋግፋው ወደ እማሆይ ጦቢያ ቤት መሄድ ጀመረች።

በላብ ባህር ተዘፍቃ ከእማሆይ ጦቢያ ቤት ደረሰች። ትንሿ መደብ ላይ እንደዳስተኛችው እማሆይ ጦቢያ የተበጠበጠ ነገር በ 'ዋምራ' ቅል



አምጥተው አጠጡት። እማሆይ ጦቢያ ደረታቸውን እየደቁ ያለቅሱ ጀመር።

"አይ ይህቺ ባድማ! አይ... እንዴት በአንድ ወራት በአንድ ወቅት ይህን ያህል ስቃይ ይህን ያህል መከራ? እስኪ አሁን ይህ ቅዱስ ይህ የማርያም አገልጋይ ምን አደረጋት? በእውነት እመቤቱ ከመንበርሽ ካለሽ ለምን ይህን ሁሉ በደል ይህን ሁሉ መከራ አታይም? ለምን ሰው ያለ ኃጢአቱ ሲገፋ አትፈርጅም?" አሉ እማሆይ ጦቢያ ወደ ጣርያው ጠቋሚ ጣታቸውን ቀሰረው።

መስከረም እንባዋ እንደ ዓባይ ወንዝ ቁልቁል በደረቷ ይንገዋገዋ ጀመር።

"እማሆይ በቃ ሞተ? በቃ እኔ ብቻዬን ልቀር ነው? ወይኔ... አሉላ! አሉ... ሆይ! እረ እባክህ አትጨክንብኝ ንቃ? ብቻዬን ለማን ጥለኸኝ ነው? ብቻዬን ቀረሁብህ'ኮ።..." አለች መስከረም አንገቱን ጥምጥም አድርጋ ይዛ የተጨፈኑ ዓይኖቹን እየተማፀነች።

"አይዞሽ ልጄ የሰጠሁት ነገር መርዙን ያረክሰዋል። ቆይ ረጋ በይ እንጂ ልጄ... መቼስ እኛ ተጣርተን አንመልሰው... እሱ የአባቶቻችን አምላክ ይመልስልን እንጂ!"

"እማሆይ በቃ'ኮ ትንፋሹ ፀጥ አለች። ልቡ መምታት አቆመ'ኮ። እረ ከምን ልግባ? እረ የሰው ያለህ! እረ ያዳኝ ያለህ..."

"ተይ ቀስ በይ ምንም አይሆንም! መድኃኒቱ ያረክስለታል ስልሽ ይኸው ሙቀት አለው። ተይው ይልቅ ልቀቂው፤ ቆይማ እኔ ድግፍ ላድርገው" ሲወድቁ ሲነሱ አምሽተው ትንሽ መረጋጋት ጀመሩ። በደንብ ባይሆንም ትንሽ ትንሽ መተንፈስና እና የልብ ምቱም ለአመል ያህል መምታት ጀመረች።

መርጊያሽ መስከረም ስለቀረችባት አጭር ዱላዋን ይዛ ለፍለጋ ስትወጣ መዝነብ የጀመረው ከባድ ዝናብ አላስወጣት አለ። መስከረም የቆየችው ዝናቡ አላስኬዳት ብሎ ነው ብላ ስለገመተች ተመልሳ ተቀመጠች።

በመስከረም ፊት ላይ የተስፋ ጭላንጭል ብልጭ አለ። ዓይኖቿ የዓይኖቹን መከፈት ጓጉተዋል። እማሆይ ጦቢያ ከወለሉ ላይ መንበርከካቸውን ሳያውቁት እግራቸው እስኪደነዝዝ ቆይተዋል።

"እ...እ...እእ..." አለ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ሳያሳይ።
"አሉላ! አሉ... እባክህን... እባክህን አለሁ በለኝ።" አለች።

ዓይኖቹን ለአፍታ ገለጠ መልሶ ዘጋቸው። እውነት አልመስለሽ አላት። መልአከ ሞት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናበታት ብሎት የተሰናበታት መሰላት። ፍርሃት ፍርሃት አላት። ዓይኖቹ ተመልሰው ተከፈቱ። ቅላታቸው ሲጠጣ ያደረ ሰካራም አስመስለውታል። አያት። ዓይኖቹ በተስፋ የሚንከባለሉ ዓይኖቿ ላይ አረፉ።

አሉላ ያለበትን ማወቅ ተሳነው። ግን በሕይወት ለመሆኑ ምልክት የሆነችውን ሴት አያት-መስከረምን።

ትንሿ መደብ ላይ የበግ አጎዛና የእማሆይ ጦቢያ ቀሚስ ተነጥፎለት አስተኙት። ትንሽ እንቅልፍ ሸለብ ሲያደርገው ከመደቡ ጎን ተቀምጣ ስታየው ቆይታ ወደ ቤት ሄደች መስከረም።

"አንቺ እስከአሁን የት አባሽ ቆይተሽ ነው?" አለቻት ገና ከበሩ ስትገባ።

"እንዴ? በዝናብ መምጣት ነበረብኝ?" አለች መስከረም በዝናቡ አመካኝታ።

"ያ... እከካም የት ሄዶ ነው?"



"እኔ የት አየሁት... ቤት አልነበር እንዴ?" አለች አሉላን መሆኑ ስለገባት።

"ቆይ... አልሰማሁ መስሎሻል! ባንቺ ቤት አልታወቀብሽም!"
"ምኑ?"
"ተይ እንጂ ደግሞ ልታደናቁሪ መሞከርሽ ነው። እ? እከከ..."
"ምኑን ነው የማደናቁርሽ?"
"ከዛ ተራ የለሽ ዲቃላ ጋር ምን ስታደርጊ ነበር?"
"ምን አደረኩ?"
"አንቺ ግም! እኔ ተራ ይኖርሻል ብዬ ለማንም ተራ ባላገር አልድርም ልጄን ብዬ ስንቱ በገበያ በድንጋዩ ሲያስቸግረኝ አሻፈረኝ ብዬ አንቺ ከዲቃላ ጋር መማገጥ ጀመርሽ?" ብላ ስትንፈቀፈቅባት ዝም ከማለት በቀር የመለሰችላት የለም።

"እኮ በይ እንጂ መልሽልኝ! አንቺ ወራዳ ታዋርጂኝ!? በያ መልስ ስጪ!"
ለዚህም ዝም ማለትን መረጠች። መልስ ሳትመልስላት ስትቀር የናቀቻት መሰሏት ባሰባት። ዘነዘናዋን አንስታ ይዛ "በዚህ ራስሽን ሳልፈጠፍጥሽ የምጠይቅሽን መልሽልኝ! በያ!"
"አሁን ምንድን ነው የምትጠይቂኝ!"
"ያ... ዲቃላ አስረግዞሻል?"
አልመለሰችላትም። መርጊያሽ ዓይኗ በርበሬ መሰለ። ከንፈሯ ተንቀጠቀጠ።
"ይህችን ጥያቄ ካልመለስሽ አለቅሽ! እናቴ ተንበርክካ አላማጠችኝም! እጄን ሳታስችኝ እውነቱን ንገሪኝ!" ብላ ተሸክማ ጎታ ውስጥ ጨመረቻት። ሰሞኑን ከሰራችው አዲስ ጎታ።

በትልቅ ገል የእሳት ረመጥ አፍሳ "ይህን ረመጥ ፊትሽ ላይ ሳልበትነው ተናገሪ! እዚህ ጎታ ውስጥ እንዳለሽ ሳላጋይሽ ንገሪኝ!" አለች አንገቷን ቁልቁል በጎታው አፍ ዘቅዝቃ። መስከረም ደንግጣ ወጥመድ ውስጥ እንደገባች አይጥ ተቁለጨለጨች።

Scanned with CamScanner

"ቆይ የምን እርግዝና ነው?"

"አላረገዝሽም?"

"ወንድሜ ጋር መዋል፣ መሳቅ መጫወት አልችልም?" አለች እዚያው ጎታው ውስጥ ቆማ፡፡

"ማን ነው ወንድምሽ? ያ... ዲቃላ! ያ...እከካም ነው ወንድምሽ? አፍሽን ሞልተሽ ወንድሜ ስትይ አታፍሪም?"

"ባረግዝስ የሚከለክለኝ አለ? ወንድሜ ካልሆነ ምን ጨነቀሽ?" አለች የእርሷም ንዴት ፊቷ ላይ ጫር ብላ፡፡

"ያ ዲቃላ ምን እንዳደረገሽ ንገሪኝ! እኮ በይ!"

"ዲቃላስ እኔ... በስካር የተወለድኩ የጠላ ቤት ውዳቂ... እሱ ዲቃላ አይደለም፡፡"

"እኮ አንቺ ምጥሟጣ... ለካስ ይህን ያህል ተደርሶልኝ ኖሯል? እ?... ጉድ! ጉድ! ኧረ በሞትኩ... ኧረ ውርደቴ!"

"እኔ ግን አላዋረድኩሽም፡፡ እንኳን ማርገዝ..." ብላ ሳትጨርስ አለማርገዟን የተረዳች ያህል በትልቅ ገል የያዘችውን የእሳት ፍም ረመጥ እንደያዘች ሾከክ ብላ ተቀመጠች፡፡ "አርግዣለሁ!" ብትላት ኖሮ የወጠነችው ሁሉ በውጥን ይቀር ነበር፡፡ ለቀበሌ አስተዳዳሪው ወንድም ለዘውዱ ልትድራት ተስማምታለች፡፡ ዘውዱም እሷን ካላገባሁ አልኖርም ብሎ ስመጥር የሀገር ሽማግሌዎችን እየላከ መርጊያሽን በጥቅማ ጥቅም መደለል ጀምሯል፡፡ መርጊያሽ የአዳምጠውን ፍቅር ላለማኮላሸት ጭምር ጥያቄውን ሳታቅማማ ነበር የተቀበለችው፡፡



# ፲፯

ባለፉት ሁለት ቀናት ታደርግ እንደነበረው በጧት ሹልክ ብላ ከእማሆይ ጦቢያ ቤት የተኛውን አሉላን ደህና ማደሩን ልታይ ሄደች፡፡ ጤንነቱ ወደነበረበት ባይመለስም ቀስ እያለ ያወራት ነበር፡፡ እማሆይ ጦቢያ የድሮ አስቂኝ ተረቶች እየነገሩ ለሳቅ ያልተፈጠሩ የሚመስሉ ጥርሶቹን ፈገግ ሲያደርገው መስከረም ደስታ ይፈነቅላት ነበር፡፡ ነገር ግን ወዲያው የዚህች ለቅሶ የበዛባት መንደር ወሬ ሲነሳ ህመሙና ራስ ምታቱ ይነሳል፡፡

ዛሬም ንጋቱ በወፎች ዝማሬ ሲበሰር "ግብር ውሃ" ልውጣ ብላ አመካኝታ 'መገበሪያዋን' እንደያዘች ተሹለክለካ ከእማሆይ ጦቢያ ጎጆ ቤት ገባች፡፡ ጎጆ ቤቷ በጢስ ተከባላች፡፡ ጢሱ በጣራዋ የሳር ክዳን ውስጥ አልፎ ይትጎለጎላል፡፡

እማሆይ ጦቢያ ከምድጃው ዳር ተቀምጠው እሳት እየሞቁ ነበር፡፡ እማሆይ ጦቢያ ከምድጃው ዳር ተቀምጠው እሳት እየሞቁ በውስጧ ያሉ የተደበቁ ተባዮችን ቆባቸውን አውልቀው እሳት እያሞቁ በውስጧ ያሉ የተደበቁ ተባዮችን እያሳደዱ፡፡ ራሳቸው ጥጥ የተከመረበት ይመስላል፡፡ የሸበተች ፀጉራቸው በዓመት አንዴ በሰኔ ብቻ ነው የምትላጨው ፀጉራቸውን እንደተላጩ ይቀብሩታል፡፡ ጥፍራቸውንም ሲቆረጡ ከደጃቸው ካለው ትልቅ ጠፍጣፋ ድንጋይ ሥር ይቀብሩታል፡፡ መስከረም ድሮ ከእርሳቸው ጋር ልትቃለድ ስትፈልግ "እማሆይ ይህን ድንጋይ ፈንቅዬ ፀጉርዎን ወዲያ ልጥለው ነው!" ትላቸዋለች፡፡

"ተይ! አይጣልም ብየሽ የል? ጌታችን ፈጣሪያችን በምፅአት ጊዜ ሲመጣ ከተፈጠርን ጊዜ ጀምሮ ያለው አካላችን ይሰበስባል። ጅብ የበላው፣ ውሃ የወሰደው ሁሉ ይነሳል። እነዚህ ፀጉሮቼም ይሰበሰባሉ" ይላሉ።

"ለምሳሌ ሶስት ጅቦች የበሉት ሰው ቢኖርና ሁለቱ ጅቦች ጎጃሜዎች ቢሆኑ አንዱ ጅብ ደግሞ ጎንደሬ ሆኖ ወደ ሰሜን ተራራ ቢሄድ የዚህ ሰው አካል በነዚህ ጅቦች ተበታትኖ እንዴት ሊገናኝ ይችላል?" ስትላቸው።

"እየሽ ይሄ ለማርያም ልጅ አይሳነውም። በነፋሳቱ ይሰበስበዋል። የኑግ ፍሬ ተዘርቶ የበቆሎ ምርት ይሰጣል? ልክ እንደዛ የእኔን አካል ቅንጣት ከሌላ ሳይደባልቅ ለኔ ይገጣጥምልኛል። ያን ጊዜ ታዲያ የጥፍጥሬ ቁራጭ አትቀርም። ትሰበሰባለች። በየግድሙ ከጣልኳት ታስጠይቀኛለች።" ሲሉ "እና እስከ ዛሬ የቆረጡት ጥፍር ሲቀጣጠል አይረዝምም? የግዮን ቆሌ ጥፍር አይመስልም?" ትላቸዋለች።

"አይ! ተይ አንቺ ልጅ የማይረባ ጥያቄ አታምጪ! የየቱን ከየት ገጠምሽው? አሁን የግዮኑን ቆሌ ጥፍር አይተሻል?"

"እኔ ባላየው ሲያወሩ እሰማለሁ። እዛው ጣና መሃል ተቀምጦ በጣም ረጅም እጁን ከፈለገው ቤት እየሰደደ ይበላል። የጣና ጥልቀት አያሳስበውም ከውሃ ውስጥ ተቀምጦ ስለማያሰጥመው ከሥር ባሉት ትልልቅ ድንጋዮች "ቅልሞሽ" ይጫወታል። ቅልሞሽ የሚጫወትበት ድንጋይ ታዲያ ተሰባብሮ አንድ ቤት የሚሰራ ነው። በዚያ ቅልሞሽ ሲጫወት አምልጦት ሲወድቅ ከህይቁ ይደነቦቃል። ህይቁን ሲደነቡቀው ማዕበል ይነሳል። ማዕበሉ ግድግዳ መስሎ ይመጣና ከዳር ሲጋጭ በአካባቢው ያለውን መሬት ያጠጣዋል። የውሃው ፍንጣቂ እስከኛ ቤት ይደርሳል'ኮ።" እያለች ስለምታጫውታቸው ይወዷታል። ትምህርት ቤት ስትሄድ እስከምትመጣ ይናፍቃሉ።

ዛሬ ግን ትክዝ ብለዋል። ፊታቸው ላይ ከባድ ሀዘን ይነበባል።

"አሉላ የት ሄደ?" አለቻቸው ገና ከበሩ ስትገባ። እንባቸው በአራት ዘለላ ወረደ።

"ምነው? የት ሂዶ ነው?" አለች ግንባሯን ቋጥራ።

"ሄደ።"

"ወዴት?"

"ገና በመንፈቅ ሌሊት ተነስቶ ሳምባ ለኩሶ ተቀምጦ ሲፅፍ ቆይቶ የፃፈውን አስቀመጠና ተነስቶ ወደኔ መጣ። ከተኛሁበት ሳልነሳ 'እማሆይ ላደረጉልኝ ሁሉ ኢየሱስ በአባቱ ፊት መልካሙን ዋጋ ይክፈልልኝ። መስከረም ጠዋት ከመጣች ይህችን ወረቀት ይስጡልኝ ይሳሙልኝ! ደህና ሁኑ' ብሎ ይህችን ወረቀት ሰጥቶኝ ገና ዶሮ እንደጮኸ ወጥቶ ሄደ።" ብለው የያዙትን ደብዳቤ ወረቀት ሰጧት። ደብዳቤውን ተቻኩላ ማንበብ ጀመረች።

"መስኪ... ይህን ውሳኔ ስወስን በግብታዊነት አይደለም። የኔ ከዚህ መዋል ማደር ያንችን ሥቃይ ከማበርከት ሌላ ዋጋ እንደሌለው ገብቶኛ ነው።

ለምን በእኔ ምክንያት ትሰቃያለሽ? አሜከላሽ ሆኜ በእያንዳንዱ እርምጃሽ ከምወጋሽ ሳንቺ ራሴን አሜከላሽን ነቅያለሁ።

እማሆይ ጦቢያ ትናንት ማለዳ ኪዳን ሊያደርሱ ወደ ቤተክርስቲያን ሄደው ነበር። ሰምተው የመጡት ግን ኪዳንና ፀሎት ሳይሆን የእኔና የአንቺን የሐሜት ኪዳን ነበር። የእኔና የአንቺ መፋቀር የአደባባይ ምስጢር ሆኗል።

እኔማ ከጣናና ከዓባይ ውሃ በቀር ከነዛ ነጫጭ አሞሮች ሌላ የሰማን ያለ አይመስለኝም ነበር። ከነዛ ረጃጅም የዶቅማ ቅጠሎች ሌላ ያየን ያለ አይመስለኝም ነበር።

ካህናቱ ኪዳኑን አቋርጠው የእኔን መርከስ አነበነቡ። ከአሁን በኋላ እንኳን ቅዳሴ ገብቼ ልቀድስ ቀርቶ የደብሩን ዕድ መደገፍ እንኳ አልዳፈርም።

Scanned with CamScanner

እንጥሉ እስኪንጠለጠል በቀደስኩበት መቅደስ፣ ጉሮሮዬ እስኪዘጋ በሰበክሁበት ዓውደ ምህረት ለሌሎች መሰናክል መሆንን አልመርጥም።

የላይኛው አምላክ በሚያውቀው ከንፈርሽን እንጂ ሌላ የሚያረክስ ነገር አልፈፀምኩም ነበር። ነገር ግን ልጅም ወልደን እንደጣልን ተወራ። እኔማ ከማርያም በቀር ድንግል አይወልድም ይመስለኝ ነበር። ለካስ እኔና አንቺም በድንግልና ወልደን ኖሯል! አንቺን ትቶ ለመሄድ ልቤ አልቆርጥ ብሎኝ ነበር። ነገር ግን ከዚህ ገሀነም መንደር ሂድ ሂድ ጥሩ ጥሩ ስላለኝ ነው። ሌላ አማራጭ አጣሁ። እንኳን መዋልና ማደር እዚህ መንደር አንድ ደቂቃ ዓመት ሆነብኝ። ለጊዜው እኔም ወደ የት እንደምሄድ አላውቅም። ስለዚህ ፍለጋ ብለሽ እንዳትሞክሪ። መቼም ቢሆን ተለያይተን እንደማንቀር ተስፋ አለኝ። ነገር ግን በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ መማርም ስለማልችል መስደድን መርጫለሁ።

አባቴ እንደአበደ ውሻ ተደብድቦ ደሙ በፈሰሰበት ቤት እህል የቀመስኩት እውነቱን ለማወቅ ፈልጌ ነበር። ግን አልቻልኩም። መስኪ ሁልጊዜም ካንቺ ጋር ነኝ። የአባቴን ነገር አደራሽን! እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ እንገናኛለን። የሚመጣ ሰው ካገኘሁ ደብዳቤ እልክብሻለሁ። መልካሙን ሁሉ እመኝልሻለሁ።

ያንቺው አሉላ ይበልጣል።"

እንብባ ስትጨርስ ቆፈን እንደያዘው ኩርትምትም ብላ ተቀመጠች። እማሆይ ጦቢያም በአይበሉባቸው ዓይናቸውን ጠራርገው መስከረምን ማፅናናት ጀመሩ።

"ተይው ዝም በይ።" አሏት እንደጨቅላ እያባበሉ።

"እንዴት ልተወው? እንዴት ዝም ልበል? እማማ... ነፋስ ጨብጬ ቀረሁኮ። የት አገኘዋለሁ አሁን?"



ሰውን ሰው ፈልጎ አያገኘውም። ልጄ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። አንድዬ አብራችሁ እንድትኖሩ ስላልፈቀደ ነው። በጎ ነው ያደረገው። አውርተው አውርተው እስከሚሰለቹ መሸሸጉ ጥሩ ነው። እዚህ አንድ ቀን መዋል የለበትም።"

"መሸሹንማ መቼ ጠላሁት። ከእሱ ተለይቼ አንድ ቀን ማደር አለመቻሌ ነው እንጂ። ... እሱ ምን ያርግ? ስቃዩ በዛ! ሀዘኑ በዛ! ሁለት አባቶቹን አጣ! ለዚህ ሁሉ እናቴ ናት! ግድ የለም..."

"ልጄ፣ መሄዱማ ጥሩ ነው ይገድሉት ነበር። ለክሬኑ ምን ይሰራልሻል?" ብለው ሳይጨርሱ መርጊያሽ እየተጣራች መጣች።

# ፲፰

"የጣና ነሽ" የተባለችው ትልቅዋ የባህር ትራንዚት መርከብ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ላይ የጥሩባዋን ጩኸት አስተጋባች። የጉዞ ማመልከቻ ደወሉ ሲሰማ እንቅልፍ ያስረፈደባቸው ተጓዦች ሻንጣቸውን እግተልትለው የመርከቧ መልህቅ ሳይነቀል ልብሳቸውን እያውለበለቡና እየተጋፉ ወደ መርከቧ ገቡ። አሮጊቶች እጃቸውን ተይዘው የህልም ጉዞ ሆኖባቸው እየተንጓቹ ይመጣሉ።

የመርከቡ ካፒቴን ትልቁን መሪ ተደግፎ የመርከቡ ሠራተኞች ሥራ መጠናቀቁን ይጠባበቃል። ዕቃውን ጭነው እንደጨረሱ የእጅ ምልክት አሳዩት።

መርከቧ ወዲያው ሞተሯን አሟሙቃ በሾለ አፍንጫዋ የጣናን ባህር ለሁለት እየከፈለች ጉዞዋን ወደ ደቅ ደሴቶች አደረገች።

ከላይኛው የመርከቧ ክፍል በላይ የተቦጫጨቀው የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ሽው በሚለው የጠዋት ነፋስ ይውለበለባል። እንደ ቡሄ ጅራፍ ይጮሃል። ከመርከቡ የሚንቆረቆረው ጥዑም ሀገራዊ ዜማ ከባህሩ ተነስቶ በቅዝቃዜ ሰውነትን ዳበስ አድርጎ ከሚያልፈው ቀዝቃዛ ነፋስ ጋር ተዋህዶ ልብን በተመስጦ ሰማየ ሰማያት ያመጥቃል። ጋራ ተራራውን ያስቃኛል። ውሃው ላይ ተንሳፈው የሚዋኙት አሞሮች ለመርከቧ መንገድ ይለቃሉ።



አንዳንድ ተጓዦች በመርከቡ ጠርዝ ላይ ተቀምጠው እግራቸውን ወደ ውሃ አንጠልጥለው የደረ ጋዜጣ ያነባሉ።

ሌሎች ከምግብ ቤቱ የደራ ጨዋታ ይዘዋል። የቀሩት በተመስጦ በሐይቁ ተደምመው ከጣና ሐይቅ መሀል አልፎ አልፎ ጉብ ጉብ ያሉትን ደሴቶች ይቃኛሉ።

እሷ ከመርከቡ ጫፍ ላይ ተቀምጣ በስተ ምሥራቅ የምትወጣውን ፀሐ... አይኗ በደሴቶቹ ሙሉ በመመልከት ላይ ነው።

"ወንድም!" አለው አንድ ጎርነን ያለ ድምፅ ከኋላው።

"አቤት!" አለው በቅፅበት ዞሮ ትኩር ብሎ የጠራውን ሰውዬ [illegible] ሊያስታውሰው አልሆነለትም። የት እንደሚያውቀው ግር አለው። ቢጫ የመነኩሴ ልብስ ለብሷል። ቆብ ግን አልደፋም።

[illegible] መቁጠሪያ አንጠልጥሏል። እግሮቹ ጫማ አልተጫሙም። [illegible] ጠይም ፊቱ ላይ ትንሽ ፈገግታ ብትን ብላለች። በአንክሮ [illegible] ሲያስተውለው አየውና "አንተ... አሱላ አይደለህም?" አለው ካልሆነ [illegible] የጥርጣሬ ምልክት እያሳየ።

"ትክክል ነህ ጌታዬ!" አለው አሱላ ፈልገህ አምጣው ተብሎ የተላከ መልክት።

"ዶክተር ጌታው ተመሳስለህብኝ ነው ማለት ነው።"
"ምንም አይደል!" አለው እንደገና ፊቱን ወደ ሀይቁ መልሶ።
"ዶክተር ጌታው... እ... አሱላ የሚባል አንተን የሚመስል ጓደኛ ነበረኝ። በርግጥ ዘመኑ ሩቅ ነው።" አለ እንደገና ሰውዬው ጥቂት ጠብቆ።
"ስንት ይሆናል?"

Scanned with CamScanner

ሶስት ዓመት ያህል ይሆናል፡፡ እንዴው ዘመድህ "በግምት አንድ አሥራ ሶስት ዓመት ያህል ይሆናል፡፡ እንዴው ዘመድህ ከሆነም ልታውቀው ትችላለህ፡፡ አንዳንድ የቆሎ ተማሪዎች ስማቸውን ስለሚቀይሩ ወይ የሀገሩ መጠሪያ ተቀይሮ ይሆናል፡፡ መልኩ ግን ቁርጥ አንተን ይመስል ነበር፡፡"

"ፈጣሪ ተሳስቶ ድጋሚ ፈጥሮ ይሆናል፡፡"

"ይቅርታ አልገባኝም፡፡"

"ማለቴ በተለያየ ቦታ ተመሳሳይ ሰዎችን ፈጥሮ ይሆናል፡፡"

"ሆኖ ያውቃል?"

"ሁለት የተለያዩ ነፍሳትን ተመሳሳይ ሥጋ አልብሶ በተለያዩ ማህፀኖች ፈጥሯቸው ይሆናል፡፡ እና እኔ አሉላን ከመሰልኩህ እንግዲህ አሉላም የኔን ዓይነት ቆዳ የለበሰ ሌላ ነፍስ በሌላ ቀዬ ያደገ ሰው ነው ማለት ነው፡፡"

"የአሉላ አገርማ ያች እዛ ማዶ ያለችው ደሴት... ያች ትንሽ ኮብቦ ብላ የምትታየን ደሴት ናት፡፡ ደብረ ማርያም ገዳም ናት፡፡ በዛች ደብር ስር ካሉ መንደሮች ባንዷ ትንሽ መንደር እንደተወለደ ያኔ ድሮ ቆሎ ትምህርት ቤት ሳለን አውቅ ነበር፡፡ እንዴት ያለ ሊቅ መሰለህ! ቅኔ እንደውሃ ነበር የሚያወርደው፡፡ ተለያየን ታዲያ፡፡ እኔ ቅኔ አምቢ አለኝ፡፡ እሱ ቅኔውን ዘርፎ ሲሄድ እኔ እዛው በወድቅ ብንሳ አልገባኝ ብሉ ሲደክመኝ ተውኩትና ዜማ ቤት ገባሁ፡፡ አይ አሉላ..." እያለ አሻግሮ ገዳሚን እያየ ብዙ ተናገረ፡፡

"ለመሆኑ አንተ ማነህ?"

"እኔማ 'ይስሐቅ' እባላለሁ፡፡ ግን ብዙ ተማሪዎች በቅፅል ስሜ ነው የሚጠሩኝ፡፡ 'ጃቢር' ይሉኛል፡፡ ጃቢር ብለው ሲጠሩኝ ዝም እላለሁ፡፡ ቂቂቂ... እየሰማሁ እኮ ነው ዝም የምለው፡፡ 'ጃቢር! ጃቢር! ጃቢር' እያሉ ሶስቴ ከጠሩኝ በኋላ ሲመረኝ 'አቤት!' እላለሁ፡፡ በኋላ ለመድኩትና ሲጠሩኝ ሳላስብ አቤት ማለትን ለመድሁ፡፡ ጃቢር የሚሉኝ አኮፋዳዬን ይዤ አገር ስለማካልል ነው፡፡ ይገባሃል? ላይገባህ ይችላል ግዴለም፡፡" አለ አሉላ አለመሆኑን ፍፁም አምኖ፡፡



ይስሐቅ ብዙ ጊዜ ካንድ ትምህርት ቤት ተቀምጦ የማይማር ተማሪ ነበር፡፡ ረሀብ አይችልም፡፡ በደጋው ረሃብ ሲጠና ወደ ቆላው ይወርዳል፡፡ በቆላው ካልደላው ወደ ወይና ደጋው ይሄዳል፡፡

ጎጃም ረሃብ ሲሆን ጎንደር፣ ጎንደር ምንዳቤ ሲጠናበት ትግራይ ይሄዳል፡፡ የማያውቀው መምህር የለም፡፡ እዚህ ቦታ አዲስ መርጌታ ወንበር ተክለ ሲባል አኮፋዳውን ይዞ ወደዚያው ይሄዳል፡፡ ሄዶ ሶስት ቀን ያየውና ካልጣመው ወደ ሌላው ይንዛል፡፡ ከሌላው ካልተመቸው ደግሞ ቀድሞ ወደ ነበረበት ይመለሳል፡፡ ጃቢር፡፡

ጃቢር መሐሪና ዝክር አያመልጠውም ነበር፡፡ በአሥራ ሁለት የሚካኤል ዝክር ቤተክርስቲያን አይቀርም፡፡ በሃያ አንድ የማርያም ታቦት ታቦት ካለበት ደብር ቅምጫናውን ለቅልቆ ከች ይላል፡፡ በየዝክሩ እየዞረ ካለችበት ቅምጫናውን በጠላ፣ አኮፋዳውን በቁራሽ ይሞላና እያዜመ እያንጎራጎረ ወደ ቤተ ጉባኤው ይመለሳል፡፡ ግራም ይንፈስ ቀኝ ጃቢርን ረሃብ ንክች አድርጎት አያውቅም፡፡ ሌላው የአብነት ተማሪ በረሀብና በእከክ እየተሰቃየ ሲማር ጃቢር 'እምን ረሀብ ይሄደስ ኩይናት' የምትል የተለመደች ብሂሉን እየተናገረ ዳባውን አንግቶውን ጠቅልሉ ይንዛል፡፡

"እኔ ደግሞ አሉላ እባላለሁ፡፡" አለ ፈገግ ብሎ እሱን ፍለጋ የተሳከ አለመሆኑን ካረጋገጠ በኋላ፡፡

"ጉዴ! ይህን ያህል ታስወሸክተኛ? አረ ጣዋንቷ እኔኮ አይደለሁም ስትለኝ አገኘሁህ ብዬ የተደሰትኩትን ያህል ከፍቶኝ ነበር፡፡" አለና ተቃቅፈው ተሳሳሙ፡፡ የቀድሞ ትዝታቸው ትዝ ትዝ ውል ውል አላቸው፡፡

"ጉዴ! ምንው ታዲያ..." አለው እንደነገሩ ለብሶ ሊያብድ አንድ ሐሙስ የቀረው መስሎ ስላየው፡፡ እስከ ዛሬ የቅኔ ወይም የመጻሕፍት ትርጓሜ መምህር ይሆናል ብሎ ያስብ ነበር፡፡

"ምን ይደረግ ብለህ ነው? 'አምላክ ሲጣላ ብትር አይቆርጥም' ይባል የል" አለው።

"ምነው ታዲያ ይህን ያህል ከእግዚአብሔር ጋር ዱላ የሚያማዝዝ ነገር..."
ታሪኩ ብዙ ነው ተወው። ለመሆኑ... አንተ የምትኖረው የት ነው?"
"ጓዴ! የኔን ነገርማ ታውቀው የለ! ... ያው መዞር ነው። አሁን ግን እርትም አርጌ ሁሉን ነገር ትቻለሁ። የአብነት ትምህርቱንም ትቸዋለሁ።"
"ምነዋ?"
"እምቢ አለኝ። ምስጢሩ አልገለፅልኝ አለ። አንድ ቀን የኔታ መንክር የሚባሉትን መምህር አታውቃቸውም? ወደ ደንቢያ ናቸው። እባክዎትን ምስጢሩ ተደበቀብኝ ሆሣዕና ይስጡኝ ብዬ የትምህርት መድኃኒት እንዲያጠጡኝ ከጫማቸው ወድቄ ለመንኳቸው፤ ሲጠናብኝ። 'እኔ ያለኝ ዘኢያገድፍ ነው። ቅኔ የሚያዘርፍ መድኃኒት ከሰጠሁህ በዚያው ልታብድብኝ ስለምትችል አልሰጥህም' አሉኝ።

'ይሁንብኝ ሲሆን ሲሆን አዛኝቱ ትጠብቀኝ ይሆናል። ካልሆነም በኋላዬ ፊደል የቆጠሩ ሁሉ መሪጌታ ሲሆኑ እኔ የጓደኛ መሳቂያ ሆኜ ከምቀር ይስጡኝና ልበድ። ጨርቄን ልጣል ግዴለም' ብላቸው እሺ በጎ አልለኝ አሉ። በዚያ ምክንያት ከቤተ ጉባኤ ወጥቼ ሄድኩ። አንድ አልፎ ሂያጅ እንደኔ ጎላላ ቢጤ ተማሪ አግኝቼ ሆሣዕና አጠጣሀለሁ ብሎ ከእርሱ ጋር ሲያዞረኝ ከርሞ በእስጢፋኖስ ማር በጥብጦ ቢያጠጣኝ እንኳንስ ቅኔ ሊያዘርፈኝ ይበልጥ ደነዝ አደረገኝ። እኔም ዕድሌን እያማረርኩ ትቼው ገዳም ገባሁ።" ብሎ ወደ ዳጋ ደሴት ተመለከተ።

"የት ገዳም?"
"ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም።" አለው ከርቀት ከሚታዩት ደሴቶች ቅልቁን በእጁ እያመለከተው። ለረጅም ጊዜ በፀጥታ ውስጥ ቆዩ። የተንጣለለው ሐይቅ ላይ ዓይኖቻቸውን ጥለው።



"ወደዚህ መርከብ ስገባ ወደየት እንደምሄድ አላውቅም ነበር። ለምን የሚገኝ መስሎኝ ነው። አብሬህ ወደዛው ብንዝ ምን ይመስልሀል?" አለው አሉላ ድንገት።

"ለምን ጓዴ!" አለ ደንገጥ ብሎ።
"ምነው ደነገጥክ?"
"አንተማ ጓዴ! ሊቅ ነህ። ቅኔህን አስመሥክረህ ለምን ወንበር አትተክልም?"
"ገዳም ውስጥ ሊቅ አይገባም እንዴ?" አለው አሉላ የተናገረው ፈገግ አስኝቶት።

"እረ ብዙ ሊቅ ሊቃውንት አሉ። ዳጋ እስጢፋኖስ ውስጥ እንኳ እኔ የማውቃቸው ብዙ ምሁራን አባቶች አሉ። በአለማዊ ትምህርት ዶክተር የሆኑ ግን ዓለምን ንቀው የመነኑ ሞልተዋል። እነ አባ ገብረ መስቀል፣ እነ አባ ወልደ ጊዮርጊስ ሁሉ ቀድሞ ዶክተር የነበሩ በኋላ ዓለምን ንቀው የመጡ መነኩሳት ናቸው።" አለ ጀቢር በገዳሙ ውስጥ ያሉ ምሁራን መነኩሳትን እየዘረዘረ።

"እኔ እንኳን አለምን ንቄያት ሳይሆን ዓለም ራሷ ንቃ ያባረረችኝ ነኝ።" አለና አሉላ የደረሰበትን ሁሉ ዘርዝሮ አጫወተው። ጀቢር በጣም አዘኑ። እያንዳንዱን ታሪክ ሲሰማ ከንፈሩን ይመጣል። ታሪኩን ዘርዝሮለት እንደጨረሰ ለጥቂት ደቂቃ በዝምታ ውስጥ ሆኑ።

"ጓዴ... ታዲያ አንተስ እንዴት ነህ?" አለ አሉላ ነገሩን ለመለወጥ ያህል ወደ ጀቢር ዞሮ።
"ይገርምሀል!... መቼስ እግዚአብሔር የፈረደብኝ አይደለሁ!"
"እንዴት?"
"ያን ያህል ዓመት በቆሎ ትምህርት ቤት ስባዝን ክህነት አላመጣሁም ነበር። እናቱ ደግሞ ዲያቆን ሆኜ ቀድሼ እንዳቆርባት ትሻል ነበር። እኔ

ግን ስዞር ኖሬ ቁመቱ ከገረዘዘ በኋላ ክህነት ልቀበል ብዬ ወደ ጳጳሱ ዘንድ ስቀር።

"አንተ እስከዛሬ የት ነበርክ? ለመሆኑ ምን ምን ታውቃለህ?" አሉኝ አቡነ ቀሲሱ። ዜማ ዘልቄያለሁ አልኳቸው ፈርቼ።

"እድሜህ ስንት ነው?" ሲሉኝ አሥራ ስድስት። አልኳቸው ታድያኮ 23 ዓመቴ ነበር ያንዜ። ትኩር ብለው አዩኝና በሳቅ ሞቱ። እኔም ሳቅ አልኩ። እንዲያ ገርጅፌ ሲያዩኝ ከሴት ጋር ግንኙነት ያደረኩ መሰላቸው መሰለኝ። 'ከዚህ ግቢ ዞር ብለህ ሳታይ ውጣ' አሉኝ። ምነው እኔኮ... ብዬ ሳልጨርስ 'ሂድ ከዚህ' ብለው እንጥሌ እስኪወርድ በኩርኩም አቅልጠው የጳጳሱ አቡነ ቀሲስ አባረሩኝ። እኔ ግን እንኳን ከሴት ጋር ልገናኝ በህፃንነቴ የናቴን ጡት ስጠባ ከናቴ ጋር ካደርኩት በቀር አብሬ ተኝቼ እንኳ አላውቅም።

"በዚህም ጭምር ተማርሬ ነው ገዳም የገባሁ። እዚሁ ከሚታየን ገዳም ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም። እዚህ ደግሞ አበምኔቱን ያመንኩሱኝ ብላቸው። 'ቆይ ልጄ ጉልበትህ ሳይደክም ክንድህ ሳይዝል ቆብ ብትደፋ ምን ያደርግልሀል? ያሩ ይበዛብሃል፤ ሰይጣን ይፈትንሃል። ይህች ቆብ አክሊለ ሶክ ናት። እንዲህ ስክተናት ስንሄድ ስታምርብን ቀላል አትምሰልህ። ቀስ ብለህ እስክትመነኩስ በአመክሮ ኑር' አሉኝ። እየውልህ እስከ አሁን ገዳሙ ውስጥ ኖሬ ቆብ አልደፋሁም። እልሀለሁ።" ብሎ ጥቂት ዝም አለና ቀጠለ።

"እኔ ስፈጠር ጀምሮ ዕድሌ ጠማማ ነው። ለምንም በቅቼ አላውቅም። አሁን ዝም ብዬ የገዳሙ ተላላኪ ነኝ። ሲልኩኝ ባህዳር እመጣና የገበያ እቃ ገዝቼ እሄዳለሁ። በቃ። አንተ ግን የተማርክ ስለሆንክ ቶሎ ያመነኩሱህ ይሆናል።" አለ።

"ለመሆኑ ገዳሙ እንዴት ነው?"



"ይመቻል ማለትህ ነው? ገዳም እየሄድክ ስለምኞት መጠየቅ የለብህም። ስቃዩ ግን ያምራል። በዚያ ክፉ ነገር አትሰማም። ፀሎት፣መዝሙር፣ ሰአታት፣ ቅዳሴ ነው የምትሰማው። የሚሸትህ ዕጣን ነው። የምታየው ቆብ የደፉ መነኩሴ ነው። የምትነካው የጫካውን ቅጠል ብቻ ነው። በቃ።" እያለ ከፊታቸው የቀረበውን ደሴት በአንክሮ እየተመለከተ ነገረው። ፀሐይ ከረር ብላ ቀትር እየመጣ ነው።

ካፒቴኑ መርከብዋን አስተካክሎ ለማቆም እየታገለ ነው። የመርከብዋ ሠራተኞች ደግሞ የመርከብዋን ማሰሪያ ገመድ ወደ ወደቡ ወርውረው ወደቡ ላይ ካለው ችካል ጋር በማሰር ላይ ናቸው። ሌሎች መልህቋን ልትጥል ቲጧን ወደ ወደቡ አዞረች። መርከብዋ ሰው እየተርመሰመሰ ይወርድ ጀመር። አሱላና ጆቢርም ወርደው ወደ ኮረብታው ወጡ።

የጣና ነሽ መርከብ ወደ ዳጋ የምትመጣ ወይ "የሀገርህን እወቅ" ጉዞ ሲኖር ወይም ብዛት ያላቸው ጎብኝዎች ሲመጡ እነሱን እሷ ብቻ ስለምትችል ነው። ዛሬ የመጣችውም በአንድ ላይ አያሌ ጎብኝዎች በመምጣታቸው እነሱን ይዛ ነው።

በቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ አካባቢ ሎሚ ሙዝና ሌሎች አትክልቶችና እፅዋት እጅብ ብለው ይታያሉ። የጠጅ ሳሩ መአዛና የቤተክርስቲያኑ ጉልላት አጨዌዎች ሿሿቴ የአሉላን ነፍስ አጫወቷት። በጭንቀት ተቋጥሮ የነበረ ግንባሩ ተፈታ። ደፍርሶ የነበረ ዓይኑ ጠራ። ከስሞ የነበረ ፊገግታው በመልካም ገፅታው ላይ ፍንትው አለ። ገነት ውስጥ ያለ መሰለው። ቀልቡ ከቤተክርስቲያኑ ጉልላት ላይ እንደተቀመጡት ርግቦች ስብስብ አለ። በዝና የሚያውቀው ዳጋ እስጢፋኖስ ከሰማው በላይ እጅግ ልቆ አገኘው።

"እፁብ ነው!" አለ አንጋጦ የቤተክርስቲያኑን ጣሪያ እያየ።

ግና ምን አየህና! መጀመሪያ የቤተክርስቲያኑን ቅርፅ በደምብ እየው:: በመርከብ ቅርፅ የተሠራበት ምሳሌ በጥፋት ውሃ ዘመን የሰው ዘር በኖህ መርከብ አማካይነት መዳኑን ለማመልከት ነው::" ብሎ ጀቢር አሉላን ቀጭም ብሎ ተመለከተው:: አስኳላ ትምህርት መማሩን ስለነገረው ይህ እውቀቱ እንደማይረባው ለመንገር ፈለገ:: እንዲረሳው ፈለገ::

"ፈረንጆቹ አገር አየር በፊኛ ይሸጣል፣ ውሃ በላስቲክ ይቸበቸባል እዚህ ግን ሁሉ ነገር በነጣ ነው ይህን ንፁህ አየር ያለ ክፍያ ማግ እንግዲህ!"

"ብቻ... ከሌለን ያለን ይልቅ ነበር:: የያዝነውን እየረጋገጥን የሰው አንጋጠን ስናይ እየመሸብን ነው እንጂ::" አለ አሉላ ወደ በዕቃ ቤቱ ወርደው ሌላ የሚያስደንቅ ትዕይንት እያዩ:: ፈረንጆቹ ይራኮቱበታል እቃ ቤቱን::

ደሳሳ ጎጆ በሆነ ዕቃ ቤት ውስጥ የሚገኙት ንዋየ ቅድሳት እና ቅርሶች ዓይን ያፈዛሉ::

በቁጥር በርከት ያሉና በመጠናቸው ግዙፍ የሆኑ በጥንት ጊዜ የነበሩ ቅዱሳን አበው ቀለም በጥብጠው ብራና ዳምጠው በግዕዝ ቋንቋ የጻፍዋቸው የብራና መጻሕፍትን ሲያይ ዓይኑን ታከተው:: ምሉዕነት ተሰማው:: ነገር ግን እሱ ምንም ነገር ሳይሰራ በትንሽ ሐሜት ስደት መጀመሩ የቀድሞ አባቶችን ጥንካሬና የላቀ አስተሳሰብ ሲያይ ባዶነት ተሰማው::

"እየውልህ ይስሐቅ... እኔ ደግሞ ከነዚህ ትላልቅ መጻሕፍት አንዱን ተርጉሜ ለአለም ህዝብ ዕንቁ ታሪካችንን አስተዋውቃለሁ::" አለ በደስታ ሰክሮ::

"ያማ ወንድ ወጣህ ነበር" አለው በግብታዊነት የተናገረው መሆኑ ቢገባውም ደስ ሲለው እሱም ደስ ብሎት::



እነዚህ የምታያቸውን ረጅም ዘመን ያስቆጠሩ ንዋየ ቅድሳት፣ ሁሉ በየቀን እየመጣሁ ሳይ ለዛሬ መዋል አቅቶኝ ተስፋ ቆርጬ የነበርኩት ተመልሼ ስለነገ እስባለሁ:: ፅናትን አማርባቸዋለሁ:: በዚህ ገዳም ውስጥ ስቆይ ብዙ ጊዜ ለመሔድ ጓዜን እጠቀልለና በዚህ ሳልፍ ይህን ሁሉ ሳይ እንደገና ፅናት አግኝቼ እመለሳለሁ:: አሁን አሁን ይህ ችግር የለብኝም:: ሂድ ሂድ የሚለኝ መንፈስ ራሱ ሂዷል:: አባ ተወልደ መድህን የሚባሉ አባት የሥዕል ጥበብ ስላስተማሩኝ ስዕል እየሳልኩ እውላለሁ::" አለ ጀቢር ዕቃ ቤቱን ካሳየው በኋላ ወደ ገዳሙ ግቢ እየወሰደው::

አሉላ ከገዳሙ ግቢ ሲገባ ልዩ የሆነ መንፈስ ወረረው:: ድሮ ከሚያውቀው የቆሎ ትምህርት ቤት ህይወት ትዝታ ተነከረ:: እንግዳ ሲመጣ እኔ እግሩን ልጠብ እኔ እግሩን ልጠብ እየተባባሉ ውሃ በቅምጫና ይዘው የእንግዳውን እግር ለስብስብ ይዘው ሲሚገቱ፣ እንግዳው አይገባኝም፣ ራሴ እታጠባለሁ ብሎ ሲያስቸግር የሚታየው ግርግር ዛሬ ሲታየው እንደገና ወደ ነበረበት ህይወቱ ተመለሰ::

መነኮሳቱ አሉላን ለማስተናገድ ሲሯሯጡ ገረመው:: አንድ ቆብ የደፉ መነኩሴ እግሩን ለማጠብ ሲጎነበሱ ቱር ብሎ ተነሳ:: ግን በግድ አጠቡት:: ጀቢር ከጎጆዋ ውስጥ ገብቶ ቢጫ አቡጀዲ አውጥቶ በጀርባው በኩል አጣጥፎ ጣል አረገለት:: የደስታ ሙቀት ትከሻውን ሞቀው::

# ፲፱

መስከረም ጣና ዳር ቁጭ ብላ እንድ ለክረምት ማሳለፊያ የተዋሰችውን አሮጌ የሩሲያ ልቦለድ መጽሐፍ ስታነብ ውላ ወደ ቤት እንደተመለሰች ውሃ ለመጠጣት መጥለቂያዋን ይዛ ወደ ማጀት ገባች፡፡ አዲስ ማጀት መሰሳት፡፡ የማታውቃቸው አዳዲስ ዕቃዎች ተደርድረዋል፡፡ ቀልቧን የሳቧት ግን ሶስቱ ሳጥኖች ናቸው፡፡ ቀርባ በአትኩሮት ተመለከተች፡፡ ተቆልፈዋል፡፡ ብዙ ቁልፎች በአንድ የቁልፍ መያገ ተሰክተው ከአንደኛው ሳጥን ላይ ተቀምጠዋል፡፡ እንደ ተረሱ ገመተች፡፡ ሳጥኖቹን በተለያዩ ቁልፎች ለመክፈት ሞከረች፡፡ አንደኛው ሳጥን ተከፈተ፡፡ በውስጡ ያየችውን ማመን አቃታት፡፡ አንድ የወርቅ ዕዋ እና ሁለት እድሜ የጠገቡ የብራና መጻሕፍት ሳጥኑ ውስጥ ተቀምጠዋል፡፡ ሌሎችን መክፈት አልፈለገችም፡፡ እንደዚሁ የቤተክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት የያዙ መሆናቸው ገምታ መልሳ ሳጥኑን እንደነበር አድርጋ ከማጀት ወጣች፡፡

ጠፍሩ አልጋ አልተነጠፈም፡፡ እብድ ያደረበት መስሏል፡፡ ጆንዲው ተንሸራቶ መሬት ሊነካ ደርሷል፡፡ ልታነጥፈው ጆንዲውን ስትስብ ሁለት የክላሽንኮብ ጥይቶችና የቀበሌው ማህተም በጨርቅ ተጠቅልለው መሬት ላይ ወደቁ፡፡ እነዚህን አንስታ ደበቀቻቸው፡፡ ጆንዲው ላይ ያሉትን አንዳንድ ምልክቶች አይታ ወሲብ የተፈፀመ መሆኑን አመነች፡፡ የልብ ምቷ ፈጠነ፡፡ ብርክ ያዛት፡፡ እስከአሁን የገመተችው ሁሉ እውን እንደሆነ ገባት፡፡ አንገቷን ደፍታ መደቡ ላይ ተቀምጣ ስታሰላስል መርጊያሽ እያንጎራጎረች ገባች፡፡ እንጉርጉሮው የዘፈን ይሁን የሀዘን አይለይም፡፡ ስክር ብላለች፡፡

“ምን ሆነሽ ነው አንገትሽን የደፋሽ?” አለች ሽክር ባለ ድምጿ-ገና ከመግባቷ፡፡



“ምንም አልሆንኩ፡፡” አለች መስከረም ያቀረቀረ አንገቷን እቃንታ፡፡

አይ አለመታደል? አይ አለማወቅ! ከዚህ ሁሉ እሱን አግብተሽ ለወግ ለማረግ ብታበቂኝ ምን ነበረበት? ኧረ ተይ እንቺ ልጅ ኧረ ተይ?! ዘውዱን የመሠለ ቀዘባ ወለባ ሺጋ ጎበዝ! አይ ጠባይ! አይ ጨዋነት! ይገርምሻል ገበያ ልውል በወህኒ ቤቱ በኩል ሳልፍ አይቶኝ... እየተብከነከነ መጥቶ ጉልበቴን ሳም ሳም አድርጎ... ‘እናቴ ምን ልርዳዎት?’ አለኝ፡፡

‘ልጄ ግዴለም የምትረዳኝ ነገር የለም፡፡ ትንሽ ገበያ አድርጌ ልመለስ ነው’ ብለው አንቆ ይዞ ወስዶ ውቴል ቤት... ሥጋው...ቁርጡ... ኧረ ምኑ ቅጡ ልጄ! እንኳንም ያን ዲቃላ እግዜር አላቀቀሽ! እግዜር እንደማይሆንሽ ስለሚያውቅ'ኮ ነው በጨለማ ያቀረብኩለትን ራት በልቶ ሳይጨርስ ውልቅ ብሎ የጠፋው፡፡” አለች ገድላ ወደዓባይ ውሃ የጣለችው አሉላ ዳግም እንደማይመለስ አምና፡፡ የዓባይ አንባዛዎች ሆዱን ቀደው ሲሯሯጡ፣ ጉማሬዎች ሲረጋግጡት፣ አዞዎች ሲቧጨቁትና ሲውጡት በአይነ ህሊናዋ ታያት፡፡

“ባል ባል የሚሆነው ወደውት መርጠውት ሲገኝ ነው እንጂ እንደፋሲካ በግ አንቆ ሲወስድ ነው እንዴ?”

“ማንነው አንቆ የሚወስድሽ! ወደሽው ለምደሽው ትሄጃለሽ ግዴለም፡፡ ልጅ መስሎሽ እኮ ነው! ደግሞም የምስለኔ ተሰማ ልጅ ነው፡፡ የምስለኔ ልጅ! ወንድሙ አዳምጠው ቢሆንስ! እ?! ዛሬ የሕዝብ አዳሙን ጉዳይ የሚያስጨርስ ህዝብ በሁለት እጁ አጨብጭቦ የመረጠው አስተዳዳሪ ነው! የጥሩ ሰው ዘር ነው፡፡ ታዲያ ምኑን ጠላሽው? እ?!”

“ሌላ የምትይው የለሽም በቃ?” መስከረም ከቤት ወጥታ ቁልቁል ወደ ጣና ወረደች፡፡

“ከዚህ የበለጠ?” መርጊያሽ ሳንቃውን ይዛ አሾካካች፡፡ “ኡኡቴ! ያ ቅማላም ውሎብሽ የለ! አዎ ምናምኑን ቀብቶሽ ነው፡፡”

# ፳

ከወደ ማታ ጀምሮ የጣናና የዓባይ ዳር ነፋሻ አየር በጆሮዋ ሲያፏጭ ደስ ይላታል። የንፋሱ ሹክሹክታ ሙዚቃዋ ነው። ህይወትን ያድሳል። በዚህ ሰዓት ከጣና ሐይቅ ዳርቻ ባሉ ትላልቅ ቋጥኞች ላይ ተቀምጣ ማዕበሉ ውሃውን ከገንቡ አጋጭቶ ትልቅ አረፋ ሲፈጥር ማየት ይማርካታል።

መስከረም ከዶቅማው ዛፍ ስር ካለ ጠፍጣፋ አለት ላይ እንደወትሮዋ ተቀምጣ ታንጎራጉራለች። የተስፋዬ ወርቅነህ ዜማ ሳታስበው ካፏ ገባ። ግጥሙን ከራሷ ግጥምጥሞሽ ጋር እያያዘች አንጎራጎረችው።

ደራ ነው መሬ ነው አዳሬ
ልገለቀው ዓባይ ጣናን ዞሬ
በል ዓባይ በል ጣና ፍረደኝ
ከሄደ እኔን ላማር ጥሎኝ
"ጽዕ!" የራሷን ግጥም ትቀላቅልበት ጀመር።
በል ዓባይ በል ጣና ፍረደኝ
ወደ ፍቅሬ እኔንም ውሰደኝ
"አይ..."
በል ዓባይ በል ጣና ፍረደኝ
እንደአፈሩ እኔንም ውሰደኝ
"አዬ..."
በል ዓባይ በል ጣና አንድ በለኝ
ወይ አሉላን መልስ ወይ እኔን ውሰደኝ
"ኧረ ወዲያልኝ!"
ዓባይ ጉደል ጉደል



ቀጭን መንገድ አውጣ
የጠፋኝ ወዳጄ
ተሻግሮ እንዲመጣ
ዓባይና ጣና በአንድ ላይ ሲሄዱ
አይተዋወቁም እንግዲህ ፍረዱ!"

እያለች እንጉርጉሮዋን በእንባዋ ስታርስ አነስ ያለች ጀልባ ከማዶ ሞተርዋን አቀዠቅዛ ቆመች። በውስጧ የነበሩበት ሰዎች ከጀልባዋ ወርደው ወደ ደብረ ማርያም ገዳም ሲገቡ አንዱ ግን ዓባይን በታንኳ ተሻግሮ ወደ እሷ መጣ።

ቢጫ አቡጀዲ ለብሷል። ትዕምርተ መስቀል ጫፉ ላይ ባለበት የብረት መቋሚያ ቅምጫና እና አኮፋዳ ሰክቶ በኋላው በትከሻው አቆንድሿል። ፊቱ በፀጉር ተሞልቷል። ራሱ ምላጭ ከዞረው ቆይቷል። ወደእሷ ቀጥታ ሲመጣ ተቁነጠነጠች። ፈራች። ዜማዋን አቋርጣ እንገቷን አቀረቀረች።

"ጤና ይስጥልኝ!" አለ ሰገድ ብሎ።
"እግዚአብሔር ይመስገን!" ብላ ከተቀመጠችበት ተነሳች።
"እባክዎን የኔ እመቤት እዚህ አካባቢ ከሆኑ ሰው ልጠይቅዎት ፈልጌ ነበር።"
"አዎን እዚህ አካባቢ ነኝ። የማውቀው ከሆነ እነግሮታለሁ" አለች ጉሮሮዋን ጠራርጋ።
"አቶ ይበልጣል በላይ የሚባል ሰው ያውቃሉ?"
"አዎን። አውቃለሁ ግን..."
"አውቃለሁ እሱ የለም። ቤቱን ካወቁ ብቻ ያሳዩኝ።"
"ለምን ፈልገውት ነው?"
"ለክፉም አይደል ለበጎ ነው አይደብቁኝ እባክዎትን!"
"እኔ'ኮ ልጅ ነኝ። አንቱታ አያስፈልገኝም"
"አይ... ሰው መቼስ ደርሶ ተንጠልጥሎ አይጠራ!"
"ግዴለም አንቺ እያሉ ያናግሩኝ!"
"አይ እሱስ ይከብደኛል።"
"ግን ለምን እንደፈለጉት ለነግሩኝ ይችላሉ?"

Scanned with CamScanner

"አይ...እሱን አልፈለኩትም እኔ፡፡ እንዴት የእንጀራ ልጁ ነበረች፡፡ ካለች አሷን ነው የፈለኳት፡፡ ከሩቅ አገር መልእክት ይገ፤ ስለመጣሁ ነው፡፡ ለክፉ አይደለም የፈለኳት፡፡ ወይ የማያውቁት ከሆነ ሳይመሽ እንድጠያይቅ ያሰናብቱኝ እባክዎ! እ..." ብሎ ድንጋዩ ላይ ጓዙን ሳያወርድ ተቀመጠ፡፡

መልእክት ይገ፤ ስለመጣሁ ስላለ ሰፍ ብላ "እኔ ነኝ፡፡ የ... የይበልጣል የእንጀራ ልጅ እኔ ነኝ፡፡" አለች፡፡

"እውነት?"

"እውነቴን ነው እኔ ነኝ፡፡ ይመኑኝ የፈለጉትን ምልክት ይጠይቁኝ፡፡ እባክዎትን መ... መልክቱ ለኔ ከሆነ ይንገሩኝ!"

"ምን የሚነግሩኝ ምልክት ይኖራል?"

"አሉላ የሚባል ወንድም ጠፍቶኛል፡፡ እሱም ፊቱ ላይ ማርያም የሳመችው ምልክት አለው፡፡ ቀይ ነው፡፡"

"ይኼ በቂ አይደለም፡፡" አለ ሳቅ ብሎ፡፡

"ሌላው ምስጢር ስለሆነ መዘርዘር አያስፈልግም ይመስለኛል፡፡ በሕይወት መኖሩን የምናውቅ እኔና እማሆይ ጦቢያ የሚባሉ መነኩሲት ነን፡፡ እሳቸውም ለማንም አይናገሩም፡፡ ብቸኛ ናቸው፡፡ ልጅም የላቸው ለልጃቸው እንዳይነግሩ! ሌላ ማንም አያውቅም፡፡ በሕይወት መኖሩን ማወቁ አይበቃም?"

"ወንድምዎት ነው እንዴ ታዲያ?"

"ወንድሜም..." ሰው መኖር አለመኖሩን ዞር ዞር ብላ ወደ ዱሩ አይታ፡፡

"ወንድሜም..." ስትል እውነተኛዋ መስከረም መሆኗን ሲረዳ፤ "ወንድምዎትም ወዳጅዎትም ነበር፡፡"

"አሁንም ነው፡፡ ምነው ሞተብኝ እንዴት?" ብላ ራሷን ያዘች፡፡

"አዎን ሞቷል፡፡" ሲላት ተንከባላ ከድንጋይ ላይ ስትወድቅ እጇ ተላጠ፡፡ በሮ ሄዶ አነሳትና፡፡

"ሞቷል ማለቴ በሥጋ ነው እንጂ በነፍስ አይደለም፡፡"

"እ... እባክዎትን... እ...እ...አ...አልገባኝም"



"ማለቴ... አሉላ የሚኖረው ገዳም ውስጥ ነው፡፡ ገዳማዊ ማለት ደግሞ ሥጋውን ገድሎ በነፍሱ ውስጥ ብቻ የሚኖር ማለት ነው፡፡ ለዚህ ነው ሞቷል ያልኩዎት እንጂ በህይወት-ሥጋ ውስጥ በነፍስ አለ፡፡ እውነቴን ነው ይመኑኝ፤ አሉላ አለ፡፡"

"እ... እውነት?"

"አዎን እውነቴን ነው፡፡ ከእርሱ የተላከ ደብዳቤ ይገ፤ ስለመጣሁ ነው፡፡ ለመሆኑ ስምዎ ማነው?"

"መስከረም ይበልጣል፡፡"

"አይደሉም ማለት ነው፡፡ በጣም አዝናለሁ፡፡ ይህን ያህል ያስመሹኝ? ወይ ወላዲተ አምላክ?..." ብሎ ተነሳ፡፡

"እንዴት ምነው?"

"እኔ ስጥ የተባልኩት...መስከረም አ - በ - ራ ለተባለች ልጅ ነው፡፡ በርግጥ ሌሎቹ ምልክቶች ልክ ነበሩ ግን የስም ልዩነት አለ፡፡"

"መስከረም አበራ - ም እባላለሁ፡፡ አበራ ወላጅ አባቴ ነው፡፡ ይበልጣል ደግሞ የእንጀራ አባቴ ነው፡፡ ስለዚህ የወለደኝን ስለማላውቀው ያሳደገኝን አባቴን መጠሪያዬ እንዲሆን መረጥኩ፡፡ ሰው ሲፈልግ መስከረም አበራ ሳይፈልግ መስከረም ይበልጣል ይለኛል፡፡"

"እንዲያ ከሆነ ጥሩ!" ብሎ ከዳዊት ማህደር ውስጥ በዝግታ አውጥቶ በአንቦልክ ያልታሸገ ደብዳቤ አውጥቶ ሰጣት፡፡ ደብዳቤው ቁልጥምጥም ብሎ እንዳይፈታ ተደርጎ በሶስት ጎን ቅርጽ ታጥፏል፡፡ አስተጣጠፉን ታውቀዋለች፡፡ የአሉላ ደብዳቤ አስተጣጠፍ እንዲህ ነው፡፡ አድራሻ አልተፃፈበትም፡፡

ድምጿን ሳታሰማ ደብዳቤውን አነበበች፡፡ እንባዋ በተገጠመ ከንፈሯ ላይ አልፎ ደብዳቤው ላይ ጠብ አለ፡፡

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

መስከረም ጀቢር የተናገራቸውን ቃላት እንደገና በአእምሮዋ ከለሰቻቸው።

'ወይ እሱ እንዲመጣ ወይ ወደቡ ድረስ ወርዶ እንዲያነጋግረዎት!' "የትኛው ባለወደብ ገዳም ውስጥ ይሆን ያለው?" አለች።

"ክብራን ገብርኤል? ጣና ቂርቆስ? ዳጋ እስጢፋኖስ?" ግምቷን አስቀመጠች። ጀቢር የሚመለስባት ቀን እንደሰማይ ራቀቻት።



# ፳፬

ዳጋ። አሉላ የአባ ሰባጋዲስን መጽሐፍ ከረጅም ጊዜ በኋላ ከፈተው።

ባለፈው ያቆመበትን ገጽ በጽጌረዳ አበባ አልቦት ስለነበር ወዲያው አገኘው። ከመሰንበቱ የተነሳ የጽጌረዳ አበባው ክሽሽ ብሎ ደርቋል። በጣቶቹ ቆንጥጦ ከገጾቹ መሃል መዞ አሽተተው መአዛው እጅጉን ስምሯል። መልሶ ወደ ገጾቹ መሃል ሊያስገባው ሲል ድቅቅ ብሎ ተሰባበረበት። የደቀቀውንም አልጣለውም በሰባጋዲስ መጽሐፍ ገጾች ውስጥ በተነው። የመጽሐፉ መአዛ የጽጌረዳውን ጠረን ይዟል። ካቆመበት ጀመረ።

"... ውሃ ቀጂዋ ያችኛዋ አልነበረችም። ይህቺኛዋ ሌላይቱ ናት። እኔን ስታይ አፍራ ዘፈኗን አቋማ ውሃዋን ጠልቃ ተመለሰች።

ይህም ሆኖ እውነተኛዋን ያቺኛዋን ልጅ በተስፋ ጠበኳት። እውነት ለመናገር እሷን አለመጠበቅ አልችልም። በግዴ እዛው ቦታ እየሄድሁ ዓይኔ ያቡሀይፈስ እስኪመስል ስጠብቃት ከረምኩ።

'ዘፀንአ ዴዴሃ ይበልዕ ፍሬሃ' የሚባለው ብሂል ሀሰት አይደለምና ዓባይ ሞልቶ አሰስ ገሰሱን ይዞ ቁልቁል በሚጥመለመልባት አንዲት ቀን ዓይኖቼ እንደገና ያችን ልጅ ሊያይዋት ተቃረቡ። ተሲአት ኃይለኛ ዝናብ ለቆት ፈተት ሲል እንደልማዴ እየተንደረደርኩ አባይ ዳር ከተፍ አልኩ። ጠብቄ ጠብቄ ሲሰለቸኝ ዋሽንቴን አንቆረቁረው ጀመር። የአባይ ፈረሰኛ የሚያስንፍጠውን ግፋፎና ምናምንቴ እያየሁ ዋሽንቴን ስጫወት ቆይቼ ቀና ስል ስጠብቃት የኖርኳት ልጅ ያኔ ስታይኝ እንደነበረው ኢየቸኝ ተገጣጠምን። ተንቀጠቀጥኩ።"

"አሉላ ሰው ይፈልግሃል!" አንድ መነኩሴ ሲጠሩት የአባ ሰባጋዲስን መፅሐፍ ለመዝጋት እያልጓጓ ተነሳ።

# ፳፱

"ኧረ ተይ እማዬ፤ ኧረ ተይ ሰው ሳቀብሽ!" አለች መስከረም መርጊያሽ አዳምጠውን ሸኝታ ቤት ስትገባ።

"ዝምበይ አንቺ! አንቺን ደግሞ ማነው አማካሪ ያደረገሽ!" አለች መርጊያሽ ንዴቷ ብልጭ ብሎ።

"ተይ እማ ተይ! አሁን ምን ይቀርብሻል አርፈሽ ብትቀመጭ! ገና የሄደበት ዱካ ሳይጠፋ! ደሙ ሳይደርቅ ይህ ሰው ለጊዜው ነው እንጂ አያዛልቅሽም"

"አንቺ ዝምበይ ነው ምልሽ!"

"እኔ'ኮ እናቱ ስምሽ ሲጠሩ እየከፋኝ'ኮ ነው። 'ባሏን ሳትፈታ በላዩ ላይ ወሸመች። ብሎ ብሎ ተከርቸም ገባባት።' እየተባለ አዳሜ የቡና መጠጫ እንዳደረገሽ እየሰማሁ ነው። እሱም ሚስቱን ፈትቶ ልጆቹ እየተላቀሱ ነው። እማይዬ! እባክሽ ይቅርብሽ።"

"ገና ነው። አልገባሽም ልጄ። መበደሌን የማውቅ እኔ ነኝ። በማታውቂው ነገር አትዘባርቂ። የእንጀራ አባትሽንም ቢሆን በሰማንያ አላገባሁትም። የተባፈ ቁራጭ ብጣሽ ወረቀት የለም። ዝም ብለን በቃል ብቻ ተስማማን መጥቼ ገባሁ። እኔም ተከርቸም ነበርሁ ተከርቸም አገባሁ በቃ! ምን ይጠበስ?" አለች እየተቀመጠች።

"እኮ! ከሰማንያ ቃል ኪዳን አይበልጥም? ወረቀት ይቀደዳል ቃል ግን ዘለዓለማዊ ነው።"



"ቃልም" ይፈርሳል። ሲሽቆጠቆጥልኝ እንዳልነበር አሁን በአደባባይ ስሜን አረከሰው። እኔ ደግሞ ሴት እንዳልሆንኩ አሳየሁት። ቀመሰኝ። እንዲህ ነኝ እናትሽ። ከልኩ አስገባሁት። አሁን እዛ ወህኒ ውስጥ ከቅማል ጋር ይላፋ። ቁንጫ ይዝለልበት። አንቺ ግን አርፈሽ ተቀመጭ። የማደርገውን እኔ አውቃለሁ። ቤቴን መቃብር አደረገው። ሰው ገድሎ እንደቀበረ አባቴ ላይም" ሲዝትበት የምታገሰው መስሎት ነበር። ተይኝ! የእሱን ነገር ተይኝ..." አለች መርጊያሽ እጇን እያርገፈገፈች።

***************************

አዳምጠው ትዳሩን ፈትቶ ልጆቹን በትኖ ተከርቸም ስለገባ ሀገሬው ሁሉ ጉድ አለ። የይበልጣልን ኮት ለብሶ ለቅሶ ሲወጣ ያዩ እረኞች በየመልካው ከብት እያገዱ እንካሰላንቲውንና አለሉሉውን ይገጥሙበታል።

"እንካ ሰላንቲያ"

"በምንቲያ"

"በመቸም"

"ምን አለ በመቸም"

"አዳምጠው ጠቅሎ ገባ አሉ ተከርቸም!"

ሌላው ይቀበልና

"እንካ ሰላንቲያ"

"በምንቲያ"

"በቅምጫና"

"ምናል በቅምጫና?"

"መርጊያሽ ለተከርቸም ሰጠችው አሉ አጥና!"

አንደኛው ገሳ የደፋ ተንከለኛ እረኛማ ሥራው ይኼ ብቻ ሆኗል።

"እንካ ሰላንቲያ"

"በምንቲያ"

"በጥልጣል"

"ምናለ በጥልጣል"

"በርሀን ዘጋጋ ተከርቸም ይመጣል"

Scanned with CamScanner

........................

ጓንካ ሰላንቲያ
ዝምንቲያ
ዝንባ
ምናለ በነባ
"ትኩስ ሽሮ በልቶ ተከርችም እንባ"

........................

"እሰሩሉ እሰሩሉ ይበልጣል ተከርችም ይመጣል"

........................

"እሰሩሉ እሰሩሉ አንምጠው ውጡን ስለቀጠው"

........................

ዚፈን አውጭዎችም አለቀቁትም

"... ሽረ ተው ተከርችም የሴቱሁን ብላ!
ትደበደባለህ እንደኛ ቡችላ።"
ይላል አንዱ ከአዝማቹ መሀል ዋሽንቱን ይዞ ከሚጓዘ።
"እስኪ እንደተከርችም ግን አለ ፈጣጣ!
ቆምጣ ሰብሶ ንብቶ በላሊ እርጎ ወጣ።"
ይላል ሌላው ከሚደው ሆኖ።

........................

መስከረም ትምህርት ቤት ተመርተናል ብላ ዋሺታ ይበልጣልን ልትጠይቅ ወደ ወህኒ ቤት ገና በማለዳ ነበር የደረሰችው። የደብረ ማርያም ነፃ አስኪታልፍ የእረኞች ሽሙጥ እላላልፋት ብሉ ነበር። የተከርችም አሰሉሉ እና እንካስላንቲያ።



እስር ቤቱ በር ላይ ስትደርስ ዘውዱን አየችው። ሆኖም ሳያያት ወደ ስልቱ የተላከ ቦታ አገኘች።

ይበልጣል ገና ሲያያት የተዘበራረቀ ስሜት ተሰማው። አላምጦ እየዋጠ ሃሳቦን ኪታስረ ወዲህ እስካሁን መጥታ ሳትጠይቀው መቅረቷ አሳዝኗት ነበር። በሌላ በኩል የእናቷ ተፅዕኖ ስላለባት 'አልፈርድባትም' አለ።

ገና ሲታየው "አባዬ!..." አለች ሆድን በሚያባውስ ድምፅ።

"ሊፈ... ናፍቆቴ...ባልወልድሽ እንኳን... ምነው ልጄ አልናፍቅሽ መሰሉሽ ነው? እናፍቃለሁ ኮ ልጄ... ምነው እስከዛሬ ጨከንሽብኝ?" አለ ይበልጣል ነገሩን እቅፍ አድርጎ።

"ልቤ ብሉኝ ነው እንጂ ሁሌጊዜ አስብሃለሁ አባዬ! አሁን... ጤንነትህ እንዴት ነው?"
"ምን ጤና አለኝ ብለሽ ነው?"
"ምንከን ነው አባዬ?"
"ልጄ ቅር እንዳይልሽ... እናትሽ በጣም በደለችኝ። ባልዋልኩበት ነገር ወነጀለችኝ። ፍርድ ተጣመመብኝ። ሳልበድል በደለኛ ተባልኩ። ከዚህ ወዲ ምን ህመም አለ? ከዚህ በላይ ምን በሽታ አለ? ዓይኔ እያየ ሞትኩ። ነውሉ ከሁሉ ለፍርድ ሳልቀርብ ግንም መንገደኛ እንደአበደ ውሻ ደበደቡኝ። አስተዳዳሪ ተብዬው ለእናትሽ አዳልቶ አሰቃየኝ። ያኮረሰው እጄን በሱቱና ነገር ቀጠቀጠው። እየውልሽ ጀርባዬ እየውልሽ እግሬ እጄ... አየሽው? ከዚህ ሁሉ ግን የውስጤ ቁስል ይበልጣል።" አለ የተላላበ ሰውነቱን ገልጦ እያሳያት። ለምጡ ሲዘገንናት እንባዋን መቆጣጠር አቃታት።

"አሁን እኔ ልረዳህ የምችለው ምንድን ነው አባዬ?" ፖሊሶቹ ጊዜውት ሳይጨርሱ ቶሎ ቶሎ ትጠይቀው ጀመር። ይበልጣል ትንሽ አቀርቅሮ አሰበና ቀና አለ።

"ብቻ እየመጣሽ ከጠየቅሽኝ ይበቃኛል። ሌላ ምን ማድረግ ትችያለሽ? ይልቅ ስትመጪ እነዛ መናጢዎች እንዳያዩሽ ተጠንቀቂ። እናትሽም ብትሆን ካየችሽ ትጠላሻለች። ለኔማ መጥተሽ ከጠየቅሽኝ ትልቅ ነገር ነው። ሌላማ ተማሪ ነሽ! ይልቅ አሉላ የት ሄዶ ነው ብቅ ብሎ የማያየኝ? ነውስ እንደሌሎች ወንጀለኛ መስየው ትቶኝ ነው?" ከፉ ጥያቄ ነበር የጠየቃት። 'እናቱ ገደለችው' ትበል ወይስ 'ጠፋ' ትበል? ሁለቱም መልሶች ልክ ቢሆኑም የመጀመሪያውን ማርዳት ግን አልፈለገችም። ለመልስ ስለዘገየች፡ "እሱንም አስሩት እንዴ?" አለ ይበልጣል።

"አይ... መታሰርስ አልታሰረም። ጠፍቶ ሰንብቶ ነበር ዛሬ ካልታወቀ ቦታ ሆኖ ደብዳቤ ፅፎልኛል።"

"ውይ! ውይ! አስረውት ነው እንጂ ታዲያ! አይ ዕድሌ!" አለ እራሱን ይዞ።

"እንዳላሰሩት እርግጠኛ ነኝ። መልእክተኛው እንዳለኝ ገዳም ውስጥ ነው የሚኖረው።"

"አይ የእሱ ነገር... ቤተክርስቲያን ባየበት እንደዞረ ነው መቼም!"

"ቦታውን ባውቀው ጥሩ ነበር። ነገር ግን መልእክተኛው ሊነግረኝ አልቻለም።" ብላ ወሬ ልትቀጥል ስትል አጅቦት የመጣው ፖሊስ አስነስቶ ይዞት ሄደ።

እስር ቤቱን ለቃ ስትወጣ ዘውዱ የደንብ ልብሱን ቀይሮ ሽክ ብሎ ለብሶ ተከተላት። መከተሉን ብታውቅም እንዳላወቀች ፈጧን ሳታዞር መንገዷን ቀጠለች።

"መስከረም!" አላት ጎርነን ባለ ድምፁ። ዝም አለችው። እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጎ መራመድና መናገር ጀመረ። እጁን አሽቀንጥራ "አንተ ሰው ብታርፍ አይሻልህም? ክብርህን ብትጠብቅ አይሻልህም? ቅሌታም! ለፖሊስም ፖሊስ እንዳለው እወቅ!" አለችው ያስፈራራች መስሏት።

"ትዕግሥቴ አልቋል ከአሁን በኋላ!"

"ጊዜ ሳታጠፋ ጓደኛህን ብትፈልግ ይሻልሃል!" ብላው ፍጥነቷን ጨመረች። እጇን በግራ እጁ ሳብ አርጎ አስቆማትና ዞር ስትል የቀኝ እጁን ለቦክስ ጨብጦ አሳያት።

"እሱ እንዳተ ሳለ ባለጌ የሚገባ ነው። የምትፈራዋን ልጅ አግኝተሃል። ሰው መሳይ!" አለች። ምንም ዓይነት ድንጋጤ አላሳየችውም። ጥላው ሄደች። ባለበት ቆሞ ጥርሱን ነክሶ ተመለከታት።

የቂት ራቅ እንዳለች እንዳታየው እየተሸሸገ ይከተላት ጀመር። ወደ ደብረ ማርያም የገጠር ቀበሌ የሚወስደውን የኮረኮንች መንገድ ስትይዝም ከሩቅ እያየት ነበር።

መስከረም ገና ባላዘረዘሩት የበቆሎ አዝመራዎች መሃል ባለችው ቀጭን መንገድ አሳብራ ፈጠን ፈጠን እያለች ስትራመድ የሚራመድ ሰው ዳና ከኋላዋ ሰማች። ዞረች። የሚራመደው ሰው ግን የለም። ተራመደች። አብሮ የሚራመደውን ኮቴ እንደገና ሰማች። ቆማ ፊቷን ሳታዞር አዳመጠች። ወዲያው ከኋላዋ የመጣ አንድ ጠንካራ መዳፍ አፏን ከረቸመው። ሌላኛው መዳፍ ወፍራም ካልሲ አፏ ውስጥ ጎደጎደባት። ወዲያው ተሸክሟት ወደ በቆለው አዝመራ ይዟት ገባ። ከመንገዱ ገባ ብሎ በቂ ርቀት ላይ ጣላትና በፈርጣማ ክንዱ አፏን እንዳፈነ። በሌላኛው እጁ ከመቅዕበት ቀበቶውን ፈታው። ጉርዷን ቁልቁል ስቦ ሲያወልቀው የሚንፈራገጡ እግሮቿ አላስቀሩትም። የሸሚዟን አንድ ጎን ይዞ ሲስበው አዝራሮቹ ግራና ቀኝ ተበታተኑ። የሾሉ ጡቶቿን ቁልቁል የሚጎመጁ ዓይኖቹን ተከለባቸው። ቁልቁል ዓይኖቹን አወረዳቸው ቀይ የውስጥ ሱሪዋን በኃይል ስቦ አውልቆ በሚያቃጥሉ ጭኖቿ መሃል ገባ።

# ፳፫

እንዴት አስስተኛ ጀልባ ከባህር ዳር ከተማ ተነስታ ጣናን እየሰነጠቀች ከሰዓት በኋላ ዳጋ ደሴት ወደብ መልህቋን ጥላለች፡፡ ጀልባዋ አራት ጣሊያናውያንና ስስት ኢትዮጵያንን አሳፍራ ነበር፡፡ አራቱን ፈረንጆች የጣሊያናውያኑ አስተርጓሚ እየመራቸው ኮረብታው ላይ ወዳለው የእስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ሲወስዳቸው ሁለቱ ግን ወደ ገዳሙ ቅፅረ ግቢ ገብተው አሉላን ሲያጠያይቁ ቆይተው አስጠሩት፡፡

አሉላ የአባ ሰባጋዲስን መጽሐፍ በጣቶቹ አልቦ እንደያዘ ወደአስጠሩት ሰዎች ሲመጣ ያየውን ማመን አልቻለም፡፡
'እዚህ መኖሬን እንዴት ሊያውቁ ቻሉ?' አሉላ ከንፈሩ ደረቀበት፡፡ በደመነፍስ እጁን ለሰላምታ ዘረጋላቸው፡፡
"ሞተሃል ተብሉ ነበር፡፡" አለው አዳምጠው በምፀት ድምፀት፡፡ "እንደ ክርስቶስ መቃብር ፈንቅለህ ወጣህ?"
"እዚህ መሆኔን ማን ነገራችሁ?"
"ከአንተ ልብ ሩቅ ሄደህ መደበቅህ ነበር፡፡ ቂቂቂ ..." ቄስ ፀሐይ ድምፁን ቀንሶ ተመፃደቀበት፡፡ "ነገሩ ጥሩ ቦታ መርጠሃል፡፡ ለሰራኸው ኃጢአትህ እዎ እዚህ ንስሀ መግባት ያሻህ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያናን አዋርደህ ሥልጣነ ክህነትህን ጥለህ፡፡ ሊያውም ተራ መሃይም እንኳ የማይደፍረውን እህትህን አጨማልቀህ ... ሌላው ይቅር አባትህ እኒያን አዛውንት ገሎ ሲቀብራቸው ሳይናዘዙ የሞቱትን የቤተ ክርስቲያኒቱን ሀብት ውድማ ውጦት እንዲቀር አርገህ ... ለዚህ ሁሉ ኃጢአትህ ንስሀ የሚበቃህ አይመስለኝም፡፡"
"እና ይኼን ልትነግሩኝ ነው አመጣጣችሁ?"



ገ... ከስግደቱ ልናግዝህ ነው እንጂ! ...ሃሃሃ ..." አዳምጠው ሳያስበው ርምቀ ወጣበት፡፡
ሉት... ቀስ ..." ቄስ ፀሐይ ድምጽ እንዲቀነስ ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ "ወደ ቁም ነሩ እንግባ!" ሲልም ቀጠለ፡፡ "ቅድም እንደገለፅኩት ሽማግሌው ብዙ የቤተ ክርስቲያኗን ቅርሶች ቀብረው እንደሞቱ ይታወቃል፡፡ የእርሳቸው አፋሽና አንጓሽ አንተ ነህ፡፡ በአጭሩ አንተ የእሳቸው ከዳሚ ነበርክ ማለት ይቻላል፡፡"
ቅርሶች? አሁን እንዲህ ይባላል? ከካህን አፍ ይህ ቃል መውጣት ነበረበት?" አሉላ ግንባሩን በሀፍረት ከሰከሰው፡፡
ሌላውን ንትርክ ተወውና አሁን የምንጠይቅህን ብቻ መልስልን!" ሲል አዳምጠው ዓይኖቹን አሉላ ላይ አንቦገቦገ፡፡
"ምንድን ነው ከእኔ የምትፈልጉት?"
"ቅርሶቹን የት እንደቀረቀሯቸው እንድትነግረን ብቻ ነው የምንፈልግ፡፡" ቄስ ፀሐይ ቃላቱን አንድ በአንድ ረገጥ እያረገ ተናገረ፡፡
"የማውቀው ነገር የለም፡፡ እኔ ደግሞ መናገር የምችለው ይህን ብቻ ነው፡፡"
እርስ በእርስ ተፋጠው ቆዩ፡፡

"ቆይ ቆይ ቆይ ..." ቄስ ፀሐይ አሉላ ወደያዘው መጽሐፍ ጠቋሚ ጣቱን በቀስታ ቀሰረ፡፡ "አሃ ... ገፀ ሰባጋዲስ? ለካ እዛች ጉረኖ ውስጥ ተደብቀው ይህን ሲፅፉ ነበረ የኖሩት?"
አዳምጠውና ቄስ ፀሐይ ተያዩ፡፡

በዚሁ ቅጽበት አሉላ ፈትለክ ብሎ ወደ ጫካው ገባ፡፡ ቄስ ፀሐይና አዳምጠው ተከትለውት ወደ ጫካው ተወረወሩ፡፡
ዱካውን እየተከታተሉ በየጥሻው ያስሱት ጀመር፡፡

'እረ ለመሆኑ እዚህ መሆኔን ማን ጠቆማቸው?' ሲል አሰበ-አሉላ፡፡
'ከይሲዎች!'

ጆቢር ለመስከረም ከአሉላ የተነከውን ደብዳቤ ሲሰጣት እንደተለመደው አዳምጠው ተደብቆ እየተመለከተ ነበር። የተባባሉት ሁሉ ጥርት ብሎ ይሰማው ነበር። ጆቢር ለመስከረም ደብዳቤውን ሰጥቶ የደብረ ማርያምን ቀበሌ ሳይለቅ ከአዳምጠው እጅ አላመለጠም። በአንድ የበቆሎ አዝመራ ውስጥ ጠብቆ፣ አፉን ለጉሞ ሲያስለፈልፈው አምሽቶ ነበር ያውጣጣው። ጆቢር ዱላው ሲጠናበት የአሉላን መገኛ መደበቅ አቃተው።

ጆቢር ምንም እንኳ ዱላው ነሰባብረውም እያጠለቀሰ መንፈሳዊ ጉዞውን አላቆመም። በቆሎው ውስጥ ተሰባብሮ ካደረ በኋላ ነበር ወደ ክርስቶስ ሰምራ ጉዞውን የቀጠለ። "ይህ የሰይጣን ፈተና ነው! አልቀርም!" እያለ።

አሉላ ይሄ ሁሉ ነገር ሳይገባው እየተገረመ እዛው ዛፉ ላይ ለረጅም ደቂቃዎች ቆይቶ ቁልቁል ተመለከተ። የጫካውን ውስጥ እዚህ ከፍታ ላይ ሆኖ መረመረው። ከዛፉ ላይ የአባ ሰባጋዲስን መጽሐፍ በብብቱ አጣብቆ እየተንፏቀቀ ወርዶ ወደ ገዳሙ ጉዞውን ቀጠለ። በጉዞው ላይ ግን አንደ ነገር አይቶ ቆመ። ነጭ የሻሸ ጥምጣም ጥቅጥቅ ባለው ጫካ ውስጥ ከሾህ ተሰክቶ ተመለከተ። ወደ ሻሹ ቀረበ። ፈገግ አለ። የቄስ ፀሐይ ጥምጣም እንደሆነ ተረዳ። "ክብረ ቢስ!" ሲል ሻሹን ከሾሁ ላይ መዥርጦ አውርዶ ረጋገጠው። በጫካው ውስጥ ጥቁር ጭቃ ላይ እስኪበቃው ረጋግጦ እንደገና ቁልቁል ተመለከተው። የተቸገረው ተፀዳድቶ የጣለው ሰገራ ያዳከረው መሰለው። ምራቁን ለጉደበት ተራመደ።



# ፳፬

መስከረም ዓይኖቿን ቀስ በቀስ ገለጠቻቸው። የዋለችበት የሰመመን ዓለም የህልም እንጂ የእውን አልመስላት አለ።

ጆርቃኗን ናት። ቀሚሷ ከእግሮቿ በታች ተመናቅሮ ተቀምጧል። ሸሚዟ በስተግራዋ አንድ የታጠፈ በቆሎ ላይ ተዘርሯል። የውስጥ ሱሪዋ በጭቃ ጭቃ ተረጋግጦ በወዲያ በኩል አለ።

እንገቷን ቀና ለማድረግ ሞከረች። እንደጠወለገ የአበባ አንገት ራሷን ቀና ማድረግ አቃተው። መሬት ተከፍቶ ቢውጣት መረጠች። ድንጋጤ፣ ሀፍረት፣ ውርደት ... ተንዘፈዘፈች። እንደምንም ለመቆም ሞከረች። እግሮቿ ሰውነቷን መሸከም አቅቷቸው ተወጫመዱ። ተንፈርክካ ቁልቁል ተመለከተች። እርጥቡ መሬት ላይ መቀመጫዋ ያረፈበትን ቅርፅ አየች። ዞራ ስትመለከት አጠቃላይ የራሷ ቅርፅ ጭቃው ውስጥ ተንጋሏል።

እየተንቀጠቀጠች ጥርሷን ነክሳ ልብሶቿን ትለብስ ጀመር። ለብሳ እስክትጨርስ ዓመት ሆነባት። እንደሰካራም ግራ ቀኝ እየረገጠች መንገዷን ጀመረች።

የሆነው ሁሉ አንድ በአንድ ይታወሳት ጀመር። ጠንካራ መዳፍ ሲያፍናት። ጠንካራ ክንዶች ቁልጥምጥም አርገው ሲጥሏት። ኃይለኛ ህመም ጭኖቿ መሃል ሲሰማት በጭካኔ የተሞላ ፊት በዓይኖቿ ትይዩ ጎንበስ ቀና ሲል። በመጨረሻም 'ይህ ነው ዘውዱ! ... ሃሃሃሃ ...' የሚል ድምጽ ... እንባዋ ጉንጮቿን አጨቀያቸው።

# ፳፫

እየመሸ ነው፡፡ ጉርምርምታ፡፡ በጥቋቁር ደመናዎች የተጎፋፈነው ሰማይ ምጥ ይዞታል፡፡

አሉላ ጣና የአበምኔቱንና የሌላ መነኮሳትን ልብስ እያጠበ ነው፡፡ አጠባውን ሳይጨርስ መሽቷል፡፡ በዚሁ ቅፅበት አንድ የመሸበት ጀልባ እሱ ካለበት ወደብ ሞተሩን አቀዝቅዞ መልህቁን ጣለ፡፡ ገመዶቹ ከወደቡ ችካሎች ጋር ታሰሩ፡፡ ጥቂት ሰዎች ከወረዱ በኋላ ጀልባው እንደገና ሞተሩን አስነስቶ ወደ ደቅ ደሴት በሹል አፍንጫው ባህሩን እየከፈለ ከኋላው በመቅዘፊያው ውሃውን እያንቦጫረቀ ጉዞውን ቀጠለ፡፡

ከጀልባው ከወረዱት ሰዎች ጋር ተደባልቃ የወረደች እንስት ወደ አሉላ ስትመጣ ተመለከተ፡፡ በነጠላ ራሷን ተከናንባለች፡፡

“ጤና ይስጥልኝ፡፡” አለች እሱ ዘንድ ስትደርስ ክንብንቧን እያወረደች፡፡ አሉላ ልቡ ከሁለት ፍርክስ ያለ መሰለው፡፡ ሆዱ ከላይ እስከታች የተቀረደደ ያህል፡፡ እንደሁልጊዜው በሀሳቡ የምትመጣበት እንጂ እውነተኛዋ መስከረም አልመሰለው አለች፡፡ ሮጣ መጥታ ስትጠመጠምበት ሁሉ ማመን አቃተው፡፡ የሚናገረው አጣ፡፡ የሚያውቀው አንድ ቃል እንኳ ያለ አልመሰለው አለ፡፡

“አሉ… አሉላ! ምን በደልኩህ? ምን ሠራሁህ?”
“አ… አይ… እ… እ…”
“አሉላ እንዲህ የሚጨክን ልብ አለህ ለካ?”



ጣስኪ ይህ ጭካኔ አይደለም፡፡ ጥሩ ውሳኔ መስሎ ስለታየኝ ነው፡፡ እዛ ተተምጨ ላንቺ ሰቀቀን ከምሆን መሰደዴ የተሻለ ነበር፡፡ ልቀመጥ ብልስ የት እቀመጥ ነበር? የእማሆይ ጦቢያ የጉሽጉሻ ዱቄት አልቃ ነበር፡፡ ውጣት ጡረተኛ ሆኜ እንድቀመጥ ፈለግሽ? በዛ ላይ መንደሩ፣ ደብሩ ሁሉ በለሜት ቢላዋ እየዘለዘለን እንዴት ብዬ ልቀመጥ? ከዚህ በላይ ብዙ ያስጨነቀኝ እናታችን ተሸክማኝ እንደጥንብ ልትጥለኝ ወደ ዓባይ ስትወስደኝ የሰማሁት ነው፡፡ እሱን አልነግርሽም፡፡ ቢቀርብሽ ይሻላል፡፡…” እንዴት እንደመጣች ግርም አለው፡፡ “የላኩት ሰው እዚህ መሆኔን ነግሮሽ ነው?” አላት፡፡

“አልነገረኝም፡፡ ነገር ግን በንግግራችን ውስጥ አንድ ጠቋሚ ቃል ስላገኘሁ ያችን አንድ ቃል ተከትዬ ፍለጋ ጀመርኩ፡፡”

“የምን ቃል?”

“ወደብ ያለው ገዳም እንደሆነ ጠቋሚ ቃል አገኘሁ፡፡ የመጣውም በጀልባ ስለሆነ ከጣና ገዳማት በአንዱ እንደምትኖር አሰብኩ፡፡”

“እና… ጣና ውስጥ ያሉ ገዳማትን ሁሉ አሰስኳቸው እንዳትዪኝ!”

“ያልሄድኩበት የለም፡፡ የቀሩኝ የደቅ ገዳማት ናቸው እንጂ ሌሎችን አዳርሻቸዋለሁ፡፡” አለች ዓይን ዓይኑን እያየች፡፡ ፊቱ የፀጉር ጫካ ለብሷል፡፡ ጢሙ ጎፍሯል፡፡ የራስ ፀጉሩ አድጎ አርበኛ አስመስሎታል፡፡

ቆመው ለረጅም ሰዓታት ሲያወሩ ጨለማ በርኖሱን ደርቦ መጣ፡፡ የብርሃን ፍንጣቂ ሲያልቅ መተያየት አቆሙ፡፡ ዝናቡም ልምጣ ልምጣ እያለ ነው፡፡

“ምን ይሻላል?” አለ አሉላ ፊቱን ጭንቀት እንደጉንዳን እየወረረው፡፡
“እንዴት?” አለች መስከረም የጭንቀቱ ምክንያት ሳይገባት፡፡

"ዱጋ እስጢፋኖስ የወንዶች ብቻ ገዳም ነው። ከዚህች ከተቀመጥንባት ወደብ አልፈን ወደ ደሴቱ እኔና አንቺ መግባት አንችልም።"

"ምን ይሻላል?" አለች መልሳ።

"ሴት አትገባም። ውግዝ ነው። አማራጫችን እዚሁ ወደቡ አካባቢ ማደር ብቻ ነው።"

"ሌላ አማራጭ ከሌለ ለእኔ በጣም ደስ የሚለኝ ነው የሚሆነው።" አለች መስከረም።

"ከአንተ ጋር ነብር ከጫካው ቢወጣ፣ አዞዎችና ጉማሬዎች ከሐይቁ ቢወጡ አልፈራም"

አሉላ የመነኮሳቱን ልብስ ከቁጥቋጦዎች ላይ አንስቶ "ጠብቂኝ መጣሁ" ብሎ ወደ ገዳሙ ሽቅብ ሮጠ።

ስለተከሰተው ሁኔታ አበምኔቱን ሊያነጋግራቸው ቢፈልግም ፀሎት ላይ ስለሆኑ ጊዜ ማጥፋት አልፈለገም። ቢያማክራቸውም የሚለወጥ ነገር እንደሌለ አሰበ።

"መቼስ የዛሬን ሴት ይግባ ብለው ውግዘት አይሽሩ!" ብሎ እሳት በገል ይዞ ወደ ወደቡ ተመልሶ ሄደ።

ከዚያው ካቅራቢያው ጫካ እንጨት ሰብሮ ያነደደው እሳት የአካባቢውን የጨለማ ምርጊት ገላለጠው። የዛፉ ሥር በብርሃን ደመቀ። ጨለማው ጥቁር መጋረጃ መስሎ ዙሪያቸውን ከበባቸው።

"መስኪ... እንግዲህ ጦምሽን ማደርሽ ነው። በገዳሙ ውስጥ ያለው ምግብም ለሴት አይፈቀድም። ዳቤው ለእኛ ብቻ የተፈቀደ ነው።"



"እኔም መንገደኛ ስለሆንኩ ያለ ስንቅ አልወጣሁም።" ብላ የያዘችትን አነስተኛ ሰማያዊ ሻንጣ ፈትታ የሚበላ ነገር አቀረበች።

"የእኛስ ለእናንተ ይፈቀዳል?" አለች። በቀልድ መልክ።

"በዓለሙ ውስጥ ያሉ ነገሮች ሁሉ አያስፈልጉንም።" አላት ፈርጠም ብሎ።

"በእውነት?" አለች 'አልበላም' የሚል መስሏት።

"እውነት።"

"አሁን አብረህ አታባላኝም ታዲያ?"

"አዎን።" ልታጎርሰው ያዘጋጀችውን ወደ ቦታው መልሳ በእሳቱ ወላፈን መሀል አየችው። ከእርሷ አርባ ክንድ የራቃት ያህል ተሰማት። አብራው ተቀምጣ ብቸኝነት ከበባት። 'ከእንግዲህ በቃ የእኔ አይደለም እኔ የጋገርኩትን አይበላም። ያጎረስኩትን አይውጥም። ገላውን መንካት አልችልም። በእኔና በእሱ መካከል ትልቅ ተራራ አለ።' ስትል አሰበች።

"የተናገርኩትን ነገር ላሻሽለው?" አለ። ጭንቀቷን ፊቷ ላይ አንብቦ።

"...'በዓለሙ ውስጥ ያሉ ክፉ ነገሮች አያስፈልጉኝም።' ብልስ ይስማማሻል?" አላት።

"እንደዛማ ከሆነ... እኔም በዓለሙ ውስጥ ያሉ ክፉ ነገሮችን አልፈልጋቸውም።" አለች።

መከፋቷን አይቶ የያዘችውን የዳቦ ቆሎ አብሮ መቆርጠም ጀመረ። አብረው ሲኖሩ አውርተውት አውርተውት የማያልቀው ወሬ ተራርቀው ከርመው ሲገናኙ ለየብቻቸው ሲያስቡት የነበረው ወሬ ጠፋባቸው።

"ብቻዬን ሳወራ እንዳልነበር አሁን ሳገኝሽ ጥፍት አለብኝ!" አላት።

"እኔስ ብሆን!"

"ቆይ... የአባዬ ነገር እንዴት ሆነ?"

"ምን ለውጥ አለው ብለህ ነው!"

"ጠይቀሽው ታውቂያለሽ?"

"አዎን።"

"ከስቷል?"

"መክሳት ብቻ! ከሰውነት ተራ ወጥቶ ጠቁሮ የፊቱ አጥንት እንደሚዋጋ ቀንድ ወጥቶ..."

ቀየውን ከለቀቀ ጊዜ ጀምሮ የተከሰቱ አዳዲስ ነገሮችን ከሥር እስከጫፍ ተረከችለት። ያልነገረችው ነገር ቢኖር የመደፈሯን ታሪክ ብቻ ነው። ለሶስት ሳምንት ያህል ጥርሷን ነክሳ ቻል አርጋው ሰንብታለች ይህ ሲሆን መርጊያሽ እንኳ አላወቀችም።

ጨለማው እየከበደ ሌሊቱ እየገፋ መጣ። እያነፈነፈ የቆየው ሰማይ ማንፍረቅ ጀመረ። የዳጋ ኮረብታ የሰማዩን እንባ ተቀብሎ እያንቆረቆረ ወደ ጣና መጨመር ጀመረ።

ያነደዱት እሳት ጠፍቶ። አመዱ ውሃ ቋጠረ። ከሰሉ ተንሳፈፈ። የተጠጉበት ዛፍ በወጀቡ እስከ ሥሩ ተነቃነቀ። የተቀመጡበት መሬት በጎርፍ ተጥለቀለቀ። በዝናብ የበሰበሰ ልብሳቸው ከሰውነታቸው ጋር ተጣበቀ። ዱባ ዱባ የሚያክለው የመስከረም ዝናብ መስከረም ፊት ላይ ሲነጥብ አንዱ ጠብታ ብቻ ፊቷን ያለብሰዋል።

ከዳጋ ኮረብታ ቁልቁል የሚጣደፈው ጐርፍ እግራቸውን አጠለቀው። ከንፈራቸው ያለ ትዕዛዝ በራሱ ፈቃድ በብርድ ይንቀጠቀጣል። ጥርሳቸው 'ሽጭ 'ሽጭ' ይላል።

"መስኪ... ለምን! ለምን መጣሽ?"

"አሁን ነው የምትጠይቀኝ?"

"ስቃይሽን አበዛሁት'ኮ መስኪ።"

"ከኔ ስቃይማ ያንተ ስቃይ እጥፍ ድርብ ይበዛል። ተወው እባክህ! የዛሬውስ ደስ የሚል ነው። ስለበረደኝ እንድጠጋ ትፈቅድልኛለህ?" ብላ ደረቱ ላይ ተለጠፈች።



"ተጠጊ!..." አቀፋት።

"አብረን እንሂድም?" አለችው ተላጣጥቀው ሙቀት ሲነጣጠቁ ቆይተው።

"ምን ልሠራ?" ብዙ ዝምታ ሰፈነ።

ቆፈኑን አልቻሉትም። መስከረም የሚንቀጠቀጥ ከንፈሯን ከአሉላ ከንፈር ላይ በኃይል አሳረፈችው። ሊከለክላት አልፈለገም። እሱም በብርድ የሚንዘፈዘፍ ከንፈሩ እስኪሞቅ ይስማት ጀመር። በጎርፍ የጠለመ እግራቸው ሳይቀር የሞቀ መሰላቸው። የሌሊቱን ብርድ እንዲህ ሲቋቋሙት አደሩ።

መስከረም የደከመ አካሏ ስለዛለ ምን ሰዓት እንቅልፍ እንደወሰዳት ባታውቅም ስትነቃ ራሷን ከአሉላ ደረት ተጠግቶ ስታገኘው ፍፁም ደስታ ተሰማት። አሉላ ግን በመብረቁ ብልጭታና በብልጭታው ውስጥ በሚታየው የዛፎች ውዝዋዜ ተመስጦ ሳያስበው እያሌ ሰዓታት አልፈዋል።

ጎርፉ ወርዶ አልቋል። የመብረቁ ብልጭታና የሰማዩ ነጎድጓድ ጋብ ብሏል። ሰማዩ የአህያ ሆድ መስሎ ንጋቱ በአእዋፋቱ ዝማሬ ሲበሰር ከኮረብታማው ቤተክርስቲያን የደወል ድምፅ ተሰማ። የኪዳን ፀሎት ደወል ነው።

አሉላ በሀሳብ ይብሰለሰል ጀመረ። እሱን ብላ ስቃይ የምታየውን መስከረምን "አልሄድም" ሲላት ምን እንደሚሰማት ያውቃል።

"እንደምንሄድ ወሰንክ?"

"እባክሽን ስለመሄድ አታንሽብኝ"

"አንድ ነገር እንድታውቅልኝ እፈልጋለሁ። ብቻዬን መመለስ እንደማልችል ልነግርህ እወዳለሁ።"

"አበምኔቱ ዘንድ ደርሼ ልምጣ፤ ጠብቂኝ" ብሏት ወደ ገዳሙ ሄደ፡፡

ገዳሙ ውስጥ እንደገባ መነኮሳቱ ሁሉ ከማህበር ፀሎት ቤቱ ተሰብስበዋል፡፡ ወደማህበር ፀሎት ቤቱ በር ሊገባ ሲል ከመሀል ቆመው የሚመሩት አበምኔቱ ከበር እንዲቆም ምልክት ሰጡት፡፡

ሲነጋገሩ ከቆዩ በኋላ አበምኔቱ እጁን ይዘው ወደ ግል የፀሎት ቤታቸው ወሰዱት፡፡ "እግዚአብሔር የሚጠላው ኃጢአተኛን ሳይሆን ኃጢአትን ነው" የሚባለውን ባያምኑ ኖሮ ወደፀሎት ቤታቸው መግባት ባልቻለ ነበር፡፡

"የት ነው ያደርከው?" አሉ ቆጣ ብለው፡፡ መልስ ሊመልስ ጎረሮውን ሲጠራርግ፡፡

"ተወው! የት እንዳደርክ አውቃለሁ፡፡ ሁሉም ነገሮች በዝርዝር ደርሰውኛል፡፡ እንደ ገዳሙ አበምኔትነቴ እነዚህን ነገሮች የመፍታት ሀላፊነት አለብኝ፡፡ አሁን ተሰብስበን ስንወያይ የቆየነው ስለአንተ ጉዳይ ነው፡፡ እሳት በደሴቱ ወደብ አካባቢ ከሚገኝ ዛፍ ስር ሲነድ አይተው ሄደው ከማን ጋር እንደነበርክ አይተዋል፡፡ ሴት ረግጦት የማያውቀውን ገዳም በማስደፈርህ ትልቅ ቁጣ አስነስቷል፡፡ ዳር መሆኑ ጥሩ እንጂ ወደ ላይ ወደ ደብሩ አካባቢ ቢሆን ኖሮ ልጅቷንም ልታስቀስፋት ትችል ነበር፡፡ በመነኮሳቱ የተቀሰቀሰውን ቁጣ ለማብረድ ብዙ ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ ቢሆንም ገዳሙን ለቀህ እንድትወጣ ተወስኗል፡፡ ቀድሞም ነግሬህ ነበር፡፡ በዓለም ውስጥ ልብህን የሚጎትት ነገር እያለ ገዳማዊ መሆን እንደማትችል ነግሬህ ነበር፡፡"

"ምህረት አይደረግልኝም ታዲያ?" አለ ደንግጦ፡፡



"ይህ ሰብዙ መነኮሳት መሰናክል የሚሆን ጥፋት በመሆኑ ይቅርታ የለውም፡፡ ደግሞ እያወቅህ ነው ያጠፋኸው፡፡ የገዳሙን ሥርዓትና ደንብ በደንብ ለማስረዳት ሞክሬ ነበር፡፡ አላዳመጥከኝም ነበር?"

"እሪ በሚገባ አዳምጨዎት ነበር፡፡ ነገር ግን የመጣችው ከመሸ ስለሆነና መመለሻ ጀልባም ስላልነበር የመጨረሻ አማራጭ መስሉ ስለታየኝ ነው እንዲህ ያደረኩት፡፡"

"እኔን እንኳ ማማከር አልፈለክም፡፡ ምክንያት ለአዳምና ለሄዋንም አላዋጣቸው፡፡ የምነግርህ የእኔን ውሳኔ ብቻ ሳይሆን የገዳማዊያኑን ውሳኔ ነው፡፡ ልረዳህ የምችለው አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ አሁን የጀልባ መምጫ ሰአት ስላልሆነ ሳስፍርህ እችላለሁ፡፡ እስከዛ ግን ወደ ጫካው ገባ ብላችሁ ተደበቁልን፡፡ ጎብኚ እንግዳ ከመጣ ሴት እያሳደሩ ተብለን ስማችን ይጠፋል፡፡" ብለው ወጥተው ሄዱ፡፡ አገጩን በሁለት እጆቹ አስደግፎ እንደያዘ አሉላ ሳያስበው እንባው ወረደ፡፡ የለበሰውን ቢጫ አቡጀዲ ከአራት አጣጥፎ አልጋው ላይ ጥሎ ወደ ወደቡ ወረደ፡፡

አጠር ያሉ ወጣት መነኩሴ የጀልባዋን ሞተር አስነስተው አሉላና መስከረምን ጭነው ወደ ባህርዳር ጉዞ ጀመሩ፡፡

አሉላ ባህር ዳር እንደደረሰ በቀጥታ ያመራው ወደ ጠበቃ ተበጀ ቤት ነበር፡፡ የሆነውን ሁሉ በዝርዝር ከጨዋታው በኋላ በይበልጣል ጉዳይ ይግባኝ ለመጠየቅ የሚያስችል መረጃዎችን ሁሉ ያጠናቅሩ ጀመር፡፡ ጠበቃ ተበጀ በግቢው ውስጥ ያለችውን አራት በአራት ክፍል ቤት ለአሉላ መጠጊያነት ሰጠው፡፡ መስከረም ግን ወደ ደብረ ማርያም ሄዳ ነገሩን በቅርበት እየተከታተለች መረጃ ታመላልስ ጀመር፡፡

Scanned with CamScanner

# ፳፪

መስከረም ከደብረማርያም ተነስታ ወደ ወህኒ ቤት በመገስገስ ላይ ናት። ጆርባዋን ከበዳት። ሁለት ጊዜ ለመዞር ቃጥታ ተወችው። እርምጃው እየቀረባት መጣ። ከመቅፅበት ተሽከርክራ ወደ ኋላዋ ዞረች።
"አንተ እእእ! እንኳ አይባልም?!" አለች የጭንቀት ትንፋሿን ለቃ።
"እንዴት ቀልቤን እንደገፈፍከው ኡሁሁ ..."

ከኋላዋ ተዘራ የሚባለው የመንደራቸው ጅል ነበር የደረሰባት። በአገልግል ስንቅ ነገር አንጠልጥሏል። ሲራመድ መሬቱን ያነጋንገዋል። ጭቃና ደረቅ አይመርጥም።

"መስከረም ነሽ? እኔ'ኮ ሌላ ሰው መስለሽኝ አልፌሽ ልሄድ ነበር። እንደምን አደርሽ?" አለ በጎርናና ድምፁ።

"እግዚአበሔር ይመስገን"

ተዘራ በመንደሩ አሉ ከሚባሉ ሞኝ ሰዎች አንዱ ነው። "አውቆ ሞኝ ይመስላል እንጂ እንደእርሱ ብስል የለም" የሚሉም አሉ። ዓባይን በታንኳ እየቀዘፈ ለብዙ ዓመታት ሰው ሲያሻግር ሲኖር አንድም ሰው ውሃ አስበልቶ አያውቅም። አባይን በማሻገር በሚያገኛት ሳንቲም ጠላ ቤት ሄዶ ይጠጣል። ምግብ ብዙ አይበላም። የኮረፌ ጠላ ነገር ሞቱ ነው። ከታንኳ ቀዘፋ በተጨማሪ ተላላኪም በመሆኑ የአንድ ጣሳ ጠላ ዋጋ ከፍለው እሱን የትም መላክ ቀላል ነው። ሰው አይመርጥም - የሚጠጣበት አንድ ሽልንግ ካገኘ ህፃን ቢልከው ሽማግሌ ግድ የለውም።



ዶፍዷፉ ፊቱ ወጣ ገባ የበዛበት መልክአ ምድር ቢመስልም አንድ ቀን ከፍቶት አያውቅም። ታንኳውን ከዓባይ ዳር አስጠግቶ ዶቅማው ሥር ተኝቶ የሚሻገር ሰው ሲጠብቅ በዚያው እንቅልፍ ይወስደዋል። ሲነቃ ታንኳውን ያጠዋል። ዓባይ እስከ መቅዘፊያው ይዞበት ይሄዳል። ይህን የዓባይን ተንኮል ለምዶታል። ዓባይን ለመስደብ በውስጡ ያሉትን ጅኖችና ጋኔኖች ስለሚፈራ ዝም ይላል። ሌላ ታንኳ ከደንገል ሠርቶ ሥራውን ይቀጥላል። ሰዎች "ዓባይ እንዴት ተጣልቶህ ነው ሁሌ ታንኳህን የሚወስድብህ?" ብለው ሲቀልዱ "ዓባይ ዘዋሪ በመሆኑ እስከዛሬ የወሰደብኝን ታንኳዎች መልሶ በላይ ያመጣልኛል። ዓባይ እንኳን ታንኳ ዶሮ እንኳ ይመልሳል።" ይላል ሊያስቅ። ለዓባይ ወንዝ የሚሳሉ ሰዎች ለዓባይ ነጭ ዶሮ ያርዱና ወደ ውሃው ይጥሉታል። አዙሪቱ መልሶ የታረደውን ዶሮ ወደ ገንቡ ያመጣዋል። ደሙ በውሃው ታጥቦ ይሄዳል። ነገር ግን የአባይ ቆሌዎችና ጂኒዎች ደሙን መጠው መስዋዕትነቱን ተቀብሎ አመጡት ስለሚባል እልልታው ይቀልጣል። ተዘራ ግን ለዓባይ ዶሮ አርዶለት አያውቅም። ታንኳውን ግን ይገብራል፤ ሳይፈልግ።

ተዘራ ስንቅ ይዞ የት እንደሚሄድ ያልገባት መስከረም "ወደየት እየሄድክ ነው?" ስትል ጠየቀችው።

"ተልኬ እየሄድኩ ነው። ሁለት ሽልንግ በጧቱ አገኘሁ። ትናንት ማታ ያሳደርኳት አንዲት ሌላ ሽልንግ አለችኝ። ሁለት ጆግ ኮረፌ ጠላ እጠጣና፣ አንድ ፊልተር ጠላ ላዩ ላይ እከልስበትና እያቅራራሁ..." አለ የቀን ውሎውን እያሰላሰለ።

"እኔ'ኮ ያልኩህ 'ወደየት እየሄድክ ነው?' ነው።"
"እኔም ተልኬ አልኩሽ።"
"ማን ልኮህ ነው?"
"ማንም! አትናገር ተብያለሁ'ኮ።"
"ወደየት ነው የተላከው?"
"ስንቅ ላደርስ ነዋ!"

"ለማን?"

"ለወህኒ ቤት!"

"ወህኒ ቤት ለማን ስጥ ተብለህ ነው?"

"ለይበልጣል። ለዛ ለሌባው - አባ ሰባጋዲስን ገድሎ ወለሉ ውስጥ ቀብሮ ለተያዘው። ለእንጀራ አባትሽ። ተከትዬ ወገቡን በዱላ እንጉብጨዋለሁ'ኮ - ተይዞ ሳል። እህ! አባ ሰባጋዲስ'ኮ ስንት ሽልንግ ሰጥተውኝ ነበር። ደሞ እሰጥሃለሁ ብለውኝ ነበር። ሲርበኝ ወደ ዕቃ ቤቱ ስሄድ ንፍሮ ይሰጡኛል። አቤት የባቄላ ሹቃቸውን! አይጨክኑብኝም። እህ! እሳቸውን ገሎ እንኳን በዱላ በአካፋ ብመታው አልጠግብም ነበር። ግን የያዝኩት ጠማማ ዝግጣ ስለነበር እስኪሰበር ወገቡን እነጠጥኩት። 'እ - እ - እ' ብሎ ዝም ሲል ሳቁ መጣኝ። ያን ያህል እንደአህያ ሲዠለጥ ዝም፣ ጭጭ፣ ኢያለቅስም። ጉማሬ እየረጋገጠ አለማምዶት'ኮ ነው።" አለ በጅላንፎ ቃል አወጣጥ ነገር መደበቅ አይሆንለትም።

"ማን አድርስለት ብሎህ ነው?" አለችው ለይበልጣል ማንም ስንቅ ይልክለታል ብላ ስለማትገምት።

"እናትሽ ናታ! ውይ! ግን'ኮ ለማንም አትናገር ተብዬአለሁ። ገና ደግሞ ሽልጌን አልሰጠችኝም። አድርሰህ ስትመጣ ነው ያለችኝ። እባክሽን አትናገሪብኝ?" አለ ፈርቶ። ተዘራ ደራም ቢልኩት ፎገራ ሁሌ ከአፉ የሚወጣው ሽልንግ ነው። በዚህ የተነሳ የመንደሩ ልጆች 'ሽልንጉ' እያሉ ነው የሚጠሩት።

"አልናገርብህም።" አለች ሌላም ነገር ከእርሱ መስማት ስለፈለገች።

"መርጊያሽ ስትልከኝ... 'መርጊያሽ ልካልህ ነው አትበል፤ እማሆይ ጦቢያ ናቸው የላኩልህ ብለህ ስጠው።' ሌላ ደግሞ..."

"ሌላስ ምን አለችህ?"



"ሌላ... ሌላ... 'ለማንም አትስጥ! እንዳትፈታው! ማንም ቢጠይቅህ የእኔን ስም አትጥራ ስሜን ካልተናገርክና በደንብ አድርሰህ ከመጣህ ተጨማሪ ሁለት ሽልንግ እሰጥሀለሁ' አለችኝ።" መቼም ልጇ ናት ብሎ ምስጢር እንዳላወጣ ገምቷል።

ይህን ሲነጋገሩ ከወህኒ ቤቱ አካባቢ ደረሱ። "ለምን እኔ አላደርስለትም?" አለች መስከረም።

"እኔስ?" አለ ተዘራ።

"አንተ ሂድና የታንኳ ሥራህን ሥራ። ዛሬ ብዙ ተሻጋሪ ይኖራል። እኔ ይበልጣልን ልጠይቅ ልገባ ስለሆነ እግር መንገዴን ይገፍልህ ልሂድ።"

"አይ... ዛሬ የታንኳ ሥራ አልሠራም። ብዙ ሽልንግ ይዣለሁ አላልኩሽም? በዚሁ ጠላ ቤት እገባለሁ። ለማንም አትስጥ ተብያለሁ። ሙች አልሰጥሽም!" አለ ወደ እስር ቤቱ በር እየመራ።

በዚሁ ቅጽበት ከወህኒ ቤቱ ጠባቂ ከዘውዱ ጋር ዓይን ለዓይን ተገጫጩ። ሰውነቷን አንዳች ነገር ወረራት። አንዘፈዘፋት። ይባስ ብሎ ለማባሸቅ ምንጭሩን ዘረጋባት። ልቧ የቋጥኝ ያህል ከበዳት። ሲደፍራት የነበረው ሁኔታ ሁሉ አንድ በአንድ አዕምሮዋ ውስጥ ተመላለሰ። የመጠቃት፣ ሰው የማጣት፣ የአቅመቢስነት ስሜት ሲራወጥባት ዕንባዋ ኩልል እያለ ፈሰሰ። የመጣችበት ተግባር መልሶ ትዝ ሲላት በረጅም ደቂቃዎች ፈዛ ከቆመችበት ሁኔታ ባተተች።

ስትሮጥ ፍተሻው ላይ ደረሰች። ተዘራ ግን ከፍተሻው ውስጥ የለም። ግራ ተጋባች። ራሷን እንደ 'ጉርና' አዞራት። 'ክው' ብላ ራሷን ይዛ ቆመች። 'ቦኖ' ይዛ ይበልጣልን ብታስጠራም 'አሁን ሊወጣ አይችልም' ብለው ስላሰናበቷት የምታደርገው አጣች። ወደ ማረሚያ ቤቱ በር ስታመራ

'ጠቆር ረዘም' ያለ' ፖሊስ መጥቶ መታወቂያውን አሳይቶ አስቆማት። ጎረሮሮውን ጠራረገና "ሳነጋግርሽ እፈልጋለሁ ወይዘሪት መስከረም" አላት።

"አመጣጤ እኮ ..."

"አመጣጥሽ ይገባኛል። ሆኖም ..." ወደ አስር ቤቱ መውጫ በር እየተራመደ እንድትከተለው ጋበዛት።

ተዘራ የት እንደገባ ማወቅ ብትፈልግም ከዚህች ሰዓት ጀምሮ ተጠያቂ እንጂ ጠያቂ መሆን እንደማትችል ተነገራት።



# ፳፯

ሻምበል ዶሬ የወንጀል ምርመራ ክፍል ሹም ነው። ምንም ያህል እልህ አስጨራሽ ነገር ቢገጥመው አይበሳጭም። ረጋ ብሎ የሚናገር አስተዋይ ሰው ነው። የመስከረም መደናገጥ እንዲሰክን ችሎታውን በከፊል ተጠቅሞታል።

ዘወትር እንደሚያደርገው ለምርመራ የሚያስፈልጉትን ሰዎች መሠረታዊ ጥያቄዎች ከመጠየቅ ይጀምራል። በዚህ ሁኔታ መጀመር ዋናውን ጉዳይ ሳያውቁት እንዲዘረዝሩ ያረጋቸዋል ሲል ያምናል።

"ስም?"

"መስከረም አበራ።"

"የቁልምጫ ስም?"

"መስኪ።"

"አድራሻ?"

"ደብረ ማርያም።"

"ፆታ?" መስከረም ከት ብላ ሳቀች። "እያየኸኝ?"

"በማየት ፆታን መለየት ይቻላል?" ፈገግ ብሎ መለሰላት

"እሺ ... ሴት"

"ብሔር?"

"ከወንጀሉ ጋር ይገናኛል?"

"እነዚህ ጥያቄዎች መሠረታዊ ናቸው ወይዘሪት መስከረም።"

"በእናቴ አማራ ሳልሆን አልቀርም። በአባቴ ግን ምን እንደሆንኩ አላውቀም። ወታደር ነበር። ከእናቴ ጋርም የአጭር ጊዜ ትውውቅ ብቻ ስለነበራቸው በውል አይተዋወቁም።"

"እሺ ... ዜግነት?"

"ኢትዮጵያዊት።"

"ሥራ?"

"ተማሪ።"

"እድሜ?"

"ሃያ አንድ ዓመቴን ል ..."

"ቁመት?"

"ተለክቼ አላውቅም፤ በግምት ግን ሜትር ከስልሳ ሳልሆን አልቀርም።"

"ክብደትስ?"

"ይህንንም ተለክቼ አላውቅም..... ያው በግምት ሃምሳ ኪሎ ግራም ሳልሆን እቀራለሁ?"

"ቁመና?"

"አልገባኝም።"

"ማለት ... ትክክለኛ? ጉባጣ? ... መጻጉዕ?"

"እንደሚያዩኝ ነኝ።"

"ፀጉር?"

"ዞማ"

"የዓይን ቀለም?"

"ቡኒ።"

"የቅንድብ ዓይነት?"

መስከረም ሳቋ አፈናት። "ምን ዓይነት አለው ደግሞ ይሄ?"

"ፀጉሩ የበነነ ቅንድብ? ደጋን የመሰለ ቅንድብ? ፀጉር የበዛበት ቅንድብ? ቀጥ ያለ ቅንድብ?"

"በመጠኑ ቀጥ ያለ ቅንድብ መሰለኝ ያለኝ።"

"አገጭ?"

"በመጠኑ ክብ።"

"ጆሮ?"



"መካከለኛ።"

"ምንም ዓይነት የአእምሮ ችግር የለብሽም?"

"እግዚአብሔር ይመስገን የለብኝም።"

"መልካም!" ሻምበል ዶሬ ብዕሩን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ ሲጋራውን ለኮሰ። በሲጋራው ጢስ ውስጥ መስከረምን እየተመለከተ ጥቂት እረፍት እንድታደርግ ተዋት። ሲጋራውን እንደጨረሰ ብዕሩን ከንፈሩ ላይ አርጎ ወደ ዋናው ጥያቄ ገባ።

"አባትሽና...ማለት የእንጀራ አባትሽና እናትሽ ሌላ ጠብ ነበራቸው?"

"እኔ እስከማውቀው ድረስ የለም።"

"የእንጀራ አባትሽ ይህን ወንጀል ለመፈፀም የሚያበቃው ነገር ይኖራል ብለሽ የምትገምችው የለም?"

"እኔ የምለው?! ለምን እስከዛሬ ዝም ብላችሁ ቆይታችሁ አሁን እንደአዲስ ነገር ማጣራት ፈለጋችሁ?"

"እየጠየኩሽ መሰለኝ! ወይዘሪት መስከረም! ለጥያቄዎቹ በቂ መልስ ልትሰጭኝ ይገባል። ይህን ወንጀል ያጣራ የነበረው መርማሪ ቡድን ለሥራው በቂ ስላለሆነ በቦታው ላይ እኔ ተወክዬ እንደገና እንዲጣራ በማድረግ ላይ ነኝ።" አለ በእርሱ አምና ቃሏን እንድትሰጠው። ለማረጋጋት ያህል። "ለዚህ ሥራዬ መሳካት ብቸኛዋ ሰው አንቺ ነሽ። ስለእውነት በእውነት ብቻ የምታውቂውን ንገሪኝ።"

"እሺ ለምን ስንቅ ሊያደርስ የመጣው ተዘራ የት እንደገባ ልትነግረኝ አልፈለክም?"

"ቀላል ነው። ተዘራ የያዘው ስንቅ የተመረዘ ስለነበር ተዘራም ስንቁም በቁጥጥር ስር ውለው እየተጣሩ ነው። ስንቁን የላከችው እናትሽ መሆንዋ ተረጋግጧል። ወደ ቦታውም አንድ የወንጀል አጣሪ ቡድን ልኬያለሁ። የእንጀራ ወንድምሽ አሉላም ወንጀሉን ለማጣራት ያመችን ዘንድ..."

"እና አሠራችሁት?"

"ምነው ደነገጥሽ?"

"ምንም!"

"ለመሆኑ ወንጀሉ ሲፈፀም አንቺ የት ነበርሽ?"

"የትም!" አለች ድምጿን በማርገብገብ፡፡

"እንዴት!? እየቀለድሽ ነው?"

"በእንቅልፍ ዓለም ውስጥ ነበርኩ፡፡"

"ቤት ውስጥ ተኝተሽ ነበር፡፡"

"ተኝቼ ነበር፡፡ መተኛት ብቻ አይደለም ከባድ እንቅልፍ ውስጥ ነበርኩ፡፡"

"እንዴት ከባድ እንቅልፍ ሊወስድሽ ቻለ? የሰቆቃ ድምጽ እየሰማሽ?"

መስከረም ምንም መልስ አልመለሰችለትም፡፡

"እናትሽና የእንጀራ አባትሽ ከዚህ ቀደም ግንኙነታቸው ምን ይመስላል?

"እሱ ብዙ ጊዜ ቤት አይውልም እናቴ በርግጥ በእሱ ላይ አስቸጋሪ ባህሪ ነበራት፡፡"

"የሻከረ ግንኙነት ነበራቸው?"

"አንዳንዴ ይጨቃጨቃሉ፡፡"

ረዥም የዝምታ ጊዜ አለፈ፡፡

"እናትሽ የእንጀራ አባትሽን ለምን መግደል እንደፈለገች ታውቂያለሽ?"

"ለምን እንደፈለገች አላውቅም፡፡ የግድያ ሙከራ ማድረጓንም የነገርከኝ አንተ ነህ፡፡"

"ዛሬ ለምን የእንጀራ አባትሽን ልትጠይቂው መጣሽ?"

"እንደሁልጊዜው ነው፡፡ ዛሬ ልጠይቀው አመጣጤ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ አይደለም፡፡ ያው ደህንነቱን ለማወቅ ያህል ነው፡፡ እሱ ከአባቴ ይበልጣል፡፡ አባቴን አላውቀውም፡፡ እሱ እየፈተፈተ፣ በአፉ በቆሎ ጥሬ አድቅቆ እያገጠገጠ ነው ያሳደገኝ፡፡ እሱ ሲታሠር ካልጠየኩት እግዚአብሔር ነፍሴን በሰማይ ቤት ይጠይቃታል፡፡ ከዚህም ሌላ አሉላን የመሠለ ልጅ አባት ነው፡፡"

"ማለት..."



"አባትነቱ ቀርቶም የአሉላ አባት ስለሆነ ብቻ ቢሆንልኝ ወይም ብችል እንኳን መጠየቅ ልብሴን አውልቄ ሰጥቼው ብሄድ ደስ ባለኝ፡፡"

እነዚህንና ሌሎች ጥያቄዎችን ሲጠይቃት ከቆየ በኋላ አመስግኖ አሰናበታት፡፡

# ፳፰

በ፲ አለቃ ጀምበሩ የሚመራው መርማሪ ፖሊስ ወደ ቦታው ተልኮ ሲደርስ የመርጊያሽ ቤት ዝግ ነበር። ሻምበል ዶሬ የተዘራና የመስከረም ጉዳይ ተደራርቦ ባይዘው ኑሮ ይህን ቡድን አስከትሎ በሄደም ነበር። ነገር ግን መቶ አለቃ ጀምበሩም የዋዛ ሰው እንዳልሆነ ያውቃል። የቡድኑ መሪ ሆኖ ሲሄድ ያገኘውን ሁሉ ቃርሞ እንደሚያመጣም ብቻ ሳይሆን የራሱን ብሩህ አእምሮ ተጠቅሞ የሚወስንና በመረጃ አያያዝ ረገድም የሚተማመንበት ሰው ነው። "ደፋር፣ ጥንቁቅ፣ አስተዋይ ..." ሲል ያሞካሽዋል።

መቶ አለቃ ጀምበሩ አንኳኳ። ከውጭ ያልተዘጋ ስለነበር ከውስጥ ሰው እንደሚኖር እርግጠኛ ሆነ። አብረውት የመጡት ፖሊሶች የቤቱን ግቢ ዙሪያውን ከበዋል። ከመቶ አለቃ ጀምበሩ ኋላ አንድ ሌላ ጠይም ፖሊስ መሳሪያውን አቀባብሎ ቆሟል።

ሶስቴ ቤቱ ቢንኳኳም ከፋች ስላጣ በሩን በመሳሪያው ገፋ አደረገው። ከውስጥ አልተሸገጠም። 'ዘው' ብሎ ሲገባ ሰው አጣ። ከውጭ ስለገባ ዓይኑ ቶሎ አላየም። ጥግ ይዞ ጥቂት እንደቆየ ወደ አልጋው አማተረ። ሱሪ የሚታጠቅ ሰው ሲውደፈደፍ ተመለከተ።

"እንዳትንቀሳቀስ!" ሲል ባረቀበት። መሳሪያውን በተጠንቀቅ ይዞ ተጠጋው። ሶስት ፖሊሶች ተከታትለው ገቡ። ሱሪውን እስከግማሽ አጥልቆ በእጁ



የሱሪውን ወገብ ጭኑ ላይ ይዞ አልጋው ላይ ኀንበስ ብሎ ቆመ። መርጊያሽ መቀነቷን ሳትታጠቅ ቀሚሷን አንቦርስሳ ቆመች።

የ፲ አለቃ ጀምበሩ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ እና ንብረት መበርበሪያ ማዘዣ አውጥቶ አሳየውና "ምርመራችንን እስክንጨርስ መንቀሳቀስ አይቻልም። ልብስህን ብቻ ለብሰህ መጨረስ ትችላለህ!" አለ ወገቡን ከፈተሸው በኋላ። ከአልጋው ራስጌ ያገኘውን ክላሽንኮቭ ጠመንጃ አንስቶ በትከሻው አንጠለጠለው። በኤግዚቢትነት።

ሁለቱ ፖሊሶች ጓዳ ጎድጓዳውን እየፈተሹ ነው። ከማጀት ያገኙዋቸውን ሶስት ሳጥኖች አልተቆለፉም ነበር። በውስጣቸው የታጨቁት የቤተክርስቲያን ቅርሶች እስከሳጥናቸው በኤግዚቢትነት ተያዙ። ጥንታዊ መፃሕፍት፣ ፅዋዎች፣ የወርቅ፣ የነሐስና የብረት መስቀሎች ... ሌሎች በቤት ውስጥ የተገኙ ወንጀሉን ለማጣራት አስፈላጊ ናቸው የተባሉ ቁሳቁሶችም ተያዙ።

መንደርተኛው 'የነመርጊያሽ ቤት በፖሊስ ታጠረ' ሲባል ከየቤቱ እየወጣ ደጁን ሞላው። ከብዙ ደቂቃዎች በኋላ የአዳምጠውና የመርጊያሽ እጆች በካቴና ተጠንፍረው ከሳጥኖቹ ጋር ሲነዱ ህዝቡ ጉድ አለ። የሚያየውን ማመን አቃተው።

ከህዝቡ ጋር ቆሞ ወሬ ሲቃርም የነበረው ቄስ ፀሐይም ተጠቁሞበት በፖሊሶች እጅ እንዲገባ ተደረገ።

ህዝቡ በሆታ ነው የምንሸኛቸው ብሎ ተከተለ። ሽመሉን ወደ ላይ አቃንቶ "ሽቦ ሎጋው ሽቦ" ብሎ ያስጀመረም አልታጣ።

Scanned with CamScanner

# ፳፱

የሁድን መሬው ፫ አለቃ ጀምበሩና ፲ አለቃ ገዛኸኝ ለውይይት ከሻምበል ዶሬ ቢሮ ተሰብስበዋል። ሻምበል ዶሬ ሲጋራውን ለኩሶ ሁለቱ ከማገ በኋላ አገጩን በሁለት እጆቹ አስደግፎ ስለደረሱበት የክትትል ውጤት ጠየቃቸው።

"ሊቀ መንበር አዳምጠውንና የወይዘሮ መርጊያሽን ግንኙነት ከወንጀሉ ጋር ለማያያዝ በቂ ማስረጃ አላገኘንም። ወይዘሮ መርጊያሽ በሰጡት የእምነት ክህደት ቃል፣ ሳጥኖቹን በቤታቸው ውስጥ የሚያውቋቸው ከአቶ ይበልጣል መታሰር ትንሽ ቀናት ቀደም ብሎ እንደሆነና ድንገት አቶ ይበልጣል አምጥተው እንዳስቀመጧቸው ነው የተናገሩት።" ሲል ሙቶ አለቃ ጀምበሩ ተናገረ።

"ማስተባበያውን ተቀበልከው?" ሲል ሻምበል ዶሬ መልሶ ጠየቀው።

"በቂ ማስተባበያ አይደለም። ሊቀ መንበሩ አቶ አዳምጠው ከአቶ ይበልጣል መታሰር በፊትም ቅርርብ እንደነበራቸው ታውቋል። በዚህም ቤት ውስጥ ያለውን ምስጢር ማወቃቸው አይቀርም ተብሎ ይገመታል። ለዛውም ይህን ከባድ ዕቃ! የቤተክርስቲያን አስፈላጊ ቅርሶች የሞሉበት ሳጥንኮ ነው።" ሲል ሙቶ አለቃ ጀምበሩ መለሰ።

"አንዳንድ ሰዎችን በመጠየቅ እንደተረዳሁት አቶ አዳምጠው ቁልፉ ከተገኘ በኋላ ለቄስ ፀሐይ መስጠቱ ጥርጣሬውን እንደሚያጎላውም ከግንዛቤ ውስጥ



ማስገባት አለብን። ቄስ ፀሐይ የቅርሱን መዘረፍ ለሕዝቡ አለማሳወቁም በሁለቱ ዘመዳሞች ስምምነት የተደበቀና የተሰረቀ ለመሆኑ ፍንጭ የሚሰጥ ይመስለኛል። በተጨማሪም እኒሁ ተጠርጣሪ አቶ አዳምጠው ከቄስ ጋር ሆነው ከአራት ፈረንጆች ጋር ከተማ ውስጥ ሲጠጡ መታየታቸው ከሰዎች ጋር ያገናኛቸው አንድ ድብቅ ምስጢር እንዳለ ያሳያል። እኒሁ ፈረንጆች በተደጋጋሚ ለጉብኝት በሚል ሰበብ በአካባቢው መታየታቸውም ጥርጣሬውን ያጎላዋል።" አለ የ፲ አለቃ ገዛኸኝ።

"ራሱ አቶ አዳምጠው በሰጠው ቃል 'ሁሉም ሰው እንደሚያደርገው ከመርጊያሽ ጋር ተዋደናል። አዲስ ነገር አላደረኩም። ከዚህ ውጭ ግን የማውቀው ነገር የለም' ነው ያለው።" ሲል የ፲ አለቃ ገዛኸኝ አከለ።

"በዚህ ዙሪያ ያለህ አስተያየት ምንድን ነው?" ሲል ሻምበል ዶሬ እንደገና ጠየቀው።

"ሰውዬው በወሲብ ቅሌት ከመጠርጠሩ በተጨማሪ በትክክል እጅ ከፍንጅ ተይዟል። ከአንዳንድ የአካባቢው ነዋሪዎች በደረሰን መረጃም ሊቀመንበሩ ከሴትዮዋ ተከርቸም ገብቷል። በእርግጥ ዝም ተብሎ የሚታይ ነገር ሳይሆን በጥንቃቄ መመርመር ያለበት ነገር ነው።" ብሎ በረጅሙ ተንፍሶ ጨረሰ።

"የአራቱ ጣልያናውያን መያዝ ለምርመራችን ትልቅ ፋይዳ ያለው ነገር ነው። የሚሸጥላቸውን ነገሮች በእጃቸው ከማስረከቡ በፊት ገፋ ያለ ገንዘብ እንደተቀበለ በተዘዋዋሪ አውቀናል። ለዚህ ወንጀል መፈፀሚያ የመረጠው የመደበቂያ ቤት የአቶ ይበልጣል ቤት እንዴት ሊመረጥ እንደቻለ ያወቅነው ነገር የለም። በራሱ ቤት ውስጥ የመደበቅ አማራጭን ለም
እንዳልተጠቀመ አልተደረሰበትም። ቤቱን ገብተን ፈትሸናል። ነገር ግ
ያገኘነው ጥንታዊ የቤተክርስቲያን ዕቃ የለም።" ሲል የ፱ አለቃ ጀንበ
አብራርቶ ተናገረ ይህ ማለት ደግሞ ከመርጊያሽ ጋር ተከርቸም መግባቱ የእቃዎቹ እሷ ዘንድ መገኘታቸው ...።"

"ተከርቸምነቱ ከወንጀሉ ጋር ምን ግንኙነት ይኖረዋል?" ሲል ሻምበል ዶሬ ጠየቀ።

"ተከርቸም መግባቱ ምንአልባት የመርጊያሽን ቤት እንደ ማከማቺያ ለመጠቀምና ለዚህም ሲሉ አቶ ይበልጣልን በመወንጀል የዚህ ሁሉ ስርቆት ፈፃሚ እንደሆነ ለማስመሰልም ይሆናል።" ... ለሃያ ደቂቃዎች ያህል በወንጀሉ ዙሪያ ሲነጋገሩ ቆይተው ለተጨማሪ የማጣራት ሥራዎች ዕቅድ አውጥተው ተለያዩ።

እነዚህና ሌሎችንም የተጣሩ ውጤቶች የይበልጣልን የግድያ ወንጀል እያይዞ ለመመርመር የተመደበው በሻምበል ዶሬ የሚመራው የምርመራ ክፍል ሥራውን በአግባቡ ለማጠናቀቅ ደፋ ቀና ሲል ውሎ አደረ። ለወንጀሉ ማጣራት አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን ሰዎች ከደብረ ማርያምና ከአካባቢዋ ያሉ ሰዎችን ሲመረምር ሰነበተ።

# ፴

ዳኛው ከችሎት ወንበር ላይ ከመሰየማቸው አስቀድሞ የፍርድ ቤቱ አዳራሽ በሕዝብ ታጭቋል። የወንጀሉን ታሪክ የሰማ ሁሉ ወደፍርድ ቤቱ በር ለመድረስ ጊዜ አልፈጀም። ብዙው የአዳራሹ ወንበሮች የተያዙት በደብረ ማርያም አካባቢ ሰዎች ነው። ጫጫታውን ለማስታገሥ ከወዲያ ወዲህ የሚሯሯጠው ሥነ-ሥርዓት አስከባሪ ከአቅሙ በላይ ስለሆነበት ተናዷል። "እሽ!" ሲል ምንም አልቀረውም። በሹክሹክታ የሚወራው ወሬ ደርቷል፤ ከውጭ ግርግሩና ሁካታው የፍርድ ቤቱን አካባቢ የሞቀ ገበያ አስመስሎታል።

"ዳኞች ሊገቡ ስለሆነ ቆማችሁ ጠብቁ" ሥነ-ሥርዓት አስከባሪው ጮኾ ተናገረ። ሁሉም የዳኞችን መግቢያ ያይ ጀመር።

ጥቁርና ቀይ ቀለም ያለው ካባቸውን የተጎናፀፉት የመሃል ዳኛ የግራና የቀኙን ዳኛ አስከትለው የመስቀል ወፍ መስለው ገቡ። ዳኛው ሲቀመጡ ሁሉም ተቀመጡ። ዳኛው ከተሰየሙበት ፊት ለፊት በስተግራ የተከሳሹ ጠበቃ አለፍ ብለው ተቀምጠዋል፤ አቃቤ ሕጉ በስተቀኝ ተሰይመዋል። ዳኛው ትልቅ መነፀራቸውን ሰክተው መዝገቡን ካገላበጡ በኋላ ተከሳሽ እንዲገባ አዘዙ-የመዝገቡን ስም ጠርተው።

ተከሳሹ ይበልጣል በፖሊሶች ታጅቦ ገባ። በአዳራሹ የተትረፈረፈው ህዝብ ሁሉ ዓይን ወደ እሱ ተተኮሰ።

Scanned with CamScanner

አዳምጠው የልብ ምቱ እንደከበሮ ለራሱ ይሰማው ጀመር:: አፍንጫው ላይ ላብ ጨርርር ሲልበት በሸሚዙ ጫፍ አፍንጫውን ወለወለ:: የመርጊያሽ ብብትም በላብ ተነከረ::

"ተከሳሽ አቶ ይበልጣል!... የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን ትቃወማለህ?" ሲሉ ዳኛው ጠየቁ ከረኸርም ፀጥታ በኋላ::

"አዎ ክቡር ዳኛ::" ብሎ ዝም አለ:: በዚህ ቅፅበት ጠበቃ ተበጀ ተነስቶ ቆመ::

"ደንበኛዬን ነፃ ሊያወጡልኝ የሚያስችሉ የመከላከያ ምስክሮችን እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ::" የይበልጣል ጠበቃ አቶ ተበጀ ጠየቀ::

"የተከሳሽ ጠበቃ ምስክሮቹ ሊያስይዙት የሚችሉትን ጭብጥ አቅርብ::"

"አቶ ይበልጣል ወንጀሉ ሲፈፀም በሰዓቱ እንዳልነበሩ፣ ወ/ሮ መርጊያሽና አባ ሰባጋዲስ አብረው ወጥተው እንዳልተመለሱ፣ ወንጀሉ በተፈፀመበት ሰዓት የነበረና ማን እንደፈፀመው የሚያውቅ የዓይን ምስክር አለኝ:: ምስክሮቼም እነዚህን ጭብጦች ያስረዱልኛል::" ሲል ጭብጡን ጠቅለል አድርጎ አቀረበ:: ምስክሮቹ ቃለ-መሃላ እንዲፈፅሙ ዳኛው ሲያዙ ሁሉም ምስክሮች ተኮለኮሉ::

"በእውነት ለመመስከር፣ በሀሰት ላለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ቃል እገባለሁ::" ሲሉ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ቀኝ እጃቸውን አስቀምጠው ማሉ:: ሌሎቹም ምስክሮች ወጥተው አንደኛው ምስክር ቀረበ::

የመጀመሪያው የመከላከያ ምስክር ተዘራ ቁሜ ነው:: ስንቁን ሊያደርስ እንደመጣ ለፖሊሱ በየዋህነት የለፈለፋቸው ቃላት እስከ ስንቁ ለእስር ዳርገውታል:: ስንቁን ስለማድረስ እንጂ ስለስንቁ የማውቀው ጉዳይ የለም ቢልም ፖሊስ ባደረበት ጥርጣሬ እስር ቤት እንዲቆይ አርጎታል:: እንዳይፈራ በተሰጠው የማደፋፈሪያ ምክር የተፅናና ቢመስልም ከምስክር መሰየሚያው ወንበር ላይ ሲወጣ መንቀጥቀጥ ጀመረ::



"አቶ ተዘራ" ሲሉ ዳኛው መነፅራቸውን እያስተካከሉ ጠየቁት::
"አቤት" ተዘራ አንገቱን እንደበገና ደርዳሪ አሰገገ::
"ይግባኝ ባይን ታውቀዋለህ?"
"ማን ነው ይግባኝ ባዩ?"
"አቶ ይበልጣልን"
"በደንብ እንጂ"
"ፀብ ዝምድና አለህ?"
"እረ በፍጡም!"
"ለእውነት ቃል ስለገባህ ያየኸውን የሰማኸውን ተናገር::"
"አቶ ተዘራ ግንቦት አራት ቀን አንተ የት ነበርክ" አለ:: ለመጀመሪያ ጊዜ 'አቶ' ሲባል ስለሰማ ክብር ተሰማው:: አንድም ሳይደብቅ ለመናገር ቆረጠ::

"ከጠዋት እስከማታ እዛው ዓባይ ነው የዋልኩ:: ያን ቀን በታንኳ ተሻጋሪ ሰው ስላጣሁና ሽልንግ ስለሌለኝ የትም አልሄድኩም"::"

"በዚያ ቀን አባ ሰባጋዲስን ምን ሲያረጉ ነው ያየሀቸው?"

"መጀመሪያ ወይዘሮ መርጊያሽ ከደቅማው ሥር እንቅልፍ ወስደኝ ሳለ ጠሩኝና ተነሣሁ:: ስነቃ እባክህ ና አሻግረኝ አሉኝ ከማዶ ሆነው:: በታንኳ እየቀዘፍኩ ሄጄ አሻገርኳቸው:: ወደ ደብረ ማርያም ሄደው ገቡ:: ከዛ ደግሞ እንቅልፍ ወሰደኝ:: ሽልንጌን ሳይሰጡኝ እንዳይሄዱ ብዬ ሁለት ጊዜ ባንኜ ብነቃም አልመጡም:: ቆይተው ከአባ ሰባጋዲስ ጋር እያወሩ መጡ:: የሚያወሩትን አልሰማሁም:: አሻገርኳቸውና ሶስት ሽልንግ ሰጡኝ:: አብረው ወደነመርጊያሽ ቤት ሄዱ:: እኔ ግን ከዛ በኋላ አባ ሰባጋዲስን አላሻገርኳቸውም! አልተመለሱም ይኸው እስከዛሬም አላሻገርኳቸውም::"

"እስከ ስንት ሰዓት ቆይተህ ነበር አንተ እዛ ዓባይ ዳር" ሲል ተበጀ ጠየቀው::

"ሰዓት አልይዝም:: መቁጠርም አልችልም:: ግን... ደንገዝገዝ ብሎ ለዓይን እስከሚይዝ እዚያው ነበርኩ::"

"ከዚያ በኋላ ስለአባ ሰባጋዲስ የምታውቀው ምንድን ነው?"

Scanned with CamScanner

"ምንም አላውቅም። በበነጋታው አባ ስባጋዲስ ጠፉ ሲባል ሰማሁ። እንደሁሉም ሰው አዘንኩ። ሌላ ጊዜ ደግሞ ከነወይዘሮ መርጊያሽ ቤት አፅማቸው ተገኘ ተብሎ ሰው ሲሰበሰብ አብሬ ተሰበሰብኩ። አቶ ይበልጣል አጥንታቸውን ተሸክሞ ሲደበደብ አየሁ።"

"ማነው የደበደበው?!" ሲል ጠየቀ አቶ ተበጀ ለዚህ ጥያቄ አፅንኦት መስጠት ፈልጉ።

"ሊቀ መንበር አዳምጠው። በዱላ፣ በጠመንጃ ሰደፍ እየመታው በአፉ በአፍንጫው ደሙ ሲዥረገረግ ነበር። አልዋሽም እኔም በያዝኩት ብትር ዘብጨዋለሁ። ያን ቀን ያልመታው ሰው የለም። ትልቁ ትንሹ ሲደበድበው ነው የዋለ። አስመሞቱ ገርሞኛል። እኔ ብሆን ገና ሰው ሲመጣ ነበር የምሞተው። በእውነት እሱ ዘጠኝ ነፍስ ነው መሰለኝ የያዘው።"

"አንተ ለምን መታሃው?"
"አባ ስባጋዲስ'ኮ ደግ ናቸው። ንፍሮ ይሰጡኛል። ሲርበኝ ያበሉኛል። አንተ ልጅ ጠላ መጠጣት ይቅርብህ ሽልንግ ስታገኝ እንጀራ በሽሮ ብላ። አትስከር። ሲርብህ ከኔ-ና (ጵፅ!) ይሉኝ ነበር።" ብሎ ከልቡ አዘነ።

"አቶ ይበልጣል በግድያው አለበት ብለህ ታምናለህ?"
"አየዋ ይበልጣል በእውነት ከሆነ አናከብረውም። ትንሽ ትልቁ 'አንባዛው!' ሲለው ሳቅ ብሎ አንገቱን ደፍቶ ነው የሚሄደው። እንኳን በእሳቸው ላይ በእንስሳ ላይ የሚጨክን ሰው አይመስለኝም። እኔ የማውቀው ጉድ የለኝም። የኔን ታንኳ የሚሰርቀኝ የግዮኑ ቆሌ ተጠናውቶት ካልሆነ በቀር አያደርገውም። ይሄ ግምቴ ነው። አላየሁም። እንዴ በዱላ መትቼው 'እ - እ - እ' ብሎ ዝም ሲል ልቤ መልሶ ተንቦጫቦጨ። ለዚህም ይቅር እንዲለኝ ለምኑልኝ!" ብሎ ወደ ይበልጣል ሰገደ።

ይበልጣል የተደበደበውን፣ የተበደለውንና የተሰቃየውን ከተዘራ አፍ ሲሰማ እንባው ከቁጥጥሩ ውጭ ሆኖ መፍሰስ ጀመረ። 'ከእንግዲህ እንኳን በደሌ



ተስማልኝ እንጂ ቢፈልጉ በስቅላትም ይቅጡኝ። መቼም ፍርድ ማጣመም ልማዳቸው ነው፤ ፍርዳቸውን ይገምድሉብኝ' አለ በልቡ።

አቃቤ ሕጉ ንዴት አፍንጫውን አቅልቶት ብድግ ብሎ "ተቃውሞ ክቡ- ፍርድ ቤት!" አለ። "ለሂደቱ አስፈላጊ ያልሆኑ ቃላት ከጉዳያችን ው- ስለሆኑ እንዲቆሙ በድጋሚ እጠይቃለሁ ክቡር ፍርድ ቤት!" ሰ ተቃውሞውን አሰምቶ ተቀመጠ።

"ለውሳኔው ቅንነትና ፍትህነት ከሁሉም ቃላት የተወሰነ መረጃ ማግ አስፈላጊ ስለሆነ ምስክሮቹ ሳይሸማቀቁ ቃላቸውን እንዲሰጡ እጠይቃለ አለ ጠበቃ ተበጀ ከመቅፅበት። ይግባኝ ባዩ ይበልጣል ተበጀ እ ሸንጡን ገትሮ ሲከራከርለት እግዚአብሔር ከሰማይ የላከለት መ መሰለው።

ዳኛው ለተቃውሞው ምላሽ ሰጡ። "የፍርድ ቤቱን ሰዓት ከመቆጠብ ምስክሮች አላስፈላጊ ቃላትን በማስወገድ ያለ ምንም መ የሚያውቁትን ብቻ ለፍርድ ቤቱ እንዲያስረዱ እጠይቃለሁ።"

እንደገና ብድግ አለና "ተቃውሞ ክቡር ፍርድ ቤት! ምስክሩ ሙሉ መሆን አለመሆናቸውም ግምት ውስጥ ይግባልኝ።" ሲል አቃ ጠየቀ።

"ምስክሬ አቶ ተዘራ ቁሜ ከጤነኛ ሰው አመለካከት ውጪ ያሳዩ የለም ክቡር ፍርድ ቤት። ጥያቄዬን ጨርሻለሁ።" ጠበቃ ተበጀ በ መንፈስ ምስክሩን አመስግኖ ተቀመጠ።
"አቃቤ ህግ መስቀለኛ ጥያቄ ካለህ እንድታቀርብ እጠይቃለሁ ዳኛው ወደ አቃቤ ህጉ ተመለከቱ።
"አመሰግናለሁ ክቡር ፍርድ ቤት!" በማለት አቃቤ ህጉ ተነሳ በመስቀለኛ ጥያቄ ያዋክበው ጀመር። "አቶ ተዘራ! ... ቅድም ስ ሰዓት እንዳልያዝክና መቁጠርም እንደማትችል ገልፀህ ነበር። :

"ምንም አላውቅም፡፡ በበነጋታው አባ ሰባጋዲስ ጠፉ ሲባል ሰማሁ፡፡ እንደሁሉም ሰው አዘንኩ፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከነወይዘሮ መርጊያሽ ቤት አስማቸው ተገኘ ተብሎ ሰው ሲሰበሰብ አብሬ ተሰበሰብኩ፡፡ አቶ ይበልጣል አጥንታቸውን ተሸክሞ ሲደበደብ አየሁ፡፡"

"ማነው የደበደበው?!" ሲል ጠየቀ አቶ ተበጀ ለዚህ ጥያቄ አፅንኦት መስጠት ፈልጎ፡፡

"ሊቀ መንበር አዳምጠው፡፡ በዱላ፣ በጠመንጃ ሰደፍ እየመታው በአፉ በአፍንጫው ደሙ ሲዥረገረግ ነበር፡፡ አልዋሽም እኔም በያዝኩት ብትር ዘብጬዋለሁ፡፡ ያን ቀን ያልመታው ሰው የለም፡፡ ትልቁ ትንሹ ሲደበድበው ነው የዋለ፡፡ አለመሞቱ ገርሞኛል፡፡ እኔ ብሆን ገና ሰው ሲመጣ ነበር የምሞተው፡፡ በእውነት እሱ ዘጠኝ ነፍስ ነው መሰለኝ የያዘው፡፡"

"አንተ ለምን መታሃው?"

"አባ ሰባጋዲስኮ ደግ ናቸው፡፡ ንፍሮ ይሰጡኛል፡፡ ሲርበኝ ያበሉኛል፡፡ አንተ ልጅ ጠላ መጠጣት ይቅርብህ ሽልንግ ስታገኝ እንጀራ በሽሮ ብላ፡፡ አትስከር፡፡ ሲርብህ ከኔ-ና (ጽዕ!) ይሉኝ ነበር፡፡" ብሎ ከልቡ አዘነ፡፡

"አቶ ይበልጣል በግድያው አስበት ብለህ ታምናለህ?"

"አየዋ ይበልጣል በእውነት ከሆነ አናከብረውም፡፡ ትንሽ ትልቁ 'አንባባው!' ሲለው ሳቅ ብሎ አንገቱን ደፍቶ ነው የሚሄደው፡፡ እንኳን በእሳቸው ላይ በእንስሳ ላይ የሚጨክን ሰው አይመስለኝም፡፡ እኔ የማውቀው ጉድ የለኝም፡፡ የኔን ታንኪ የሚሰርቀኝ የግሮኑ ቆሌ ተጠናውቶት ካልሆነ በቀር አይደርገውም፡፡ ይሄ ግምቱ ነው፡፡ አላየሁም፡፡ አንዴ በዱላ መትቼው 'እ - እ - እ' ብሎ ዝም ሲል ልቤ መልሶ ተንቦጫቦጨ፡፡ ለዚህም ይቅር እንዲለኝ ለምኑልኝ!" ብሎ ወደ ይበልጣል ሰገደ፡፡

ይበልጣል የተደበደበውን፣ የተበደለውንና የተሰቃየውን ከተዘራ አፍ ሲሰማ እንባው ከቁጥጥሩ ውጭ ሆኖ መፍሰስ ጀመረ፡፡ 'ከእንግዲህ እንኳን በደሌ



ተሰማልኝ እንጂ ቢፈልጉ በስቅላትም ይቅጡኝ፡፡ መቼም ፍርድ ማጣመም ልማዳቸው ነው፤ ፍርዳቸውን ይገምድሉብኛ አለ በልቡ፡፡

አቃቤ ሕግ ንዴት አፍንጫውን አቅልቶት ብድግ ብሎ "ተቃውሞ ክቡር ፍርድ ቤት!" አለ፡፡ "ለሂደቱ አስፈላጊ ያልሆነ ቃላት ከጉዳያችን ውጭ ስለሆነ እንዲቆሙ በድጋሚ እጠይቃለሁ ክቡር ፍርድ ቤት!" ሲል ተቃውሞውን አሰምቶ ተቀመጠ፡፡

"ለውሳኔው ቅንነትና ፍትህነት ከሁሉም ቃላት የተወሰነ መረጃ ማግኘቱ አስፈላጊ ስለሆነ ምስክሮቼ ሳይሸማቀቁ ቃላቸውን እንዲሰጡ እጠይቃለሁ!" አለ ጠበቃ ተበጀ ከመቅዐበት፡፡ ይግባኝ ባዩ ይበልጣል ተበጀ እንዲያ ሸንጡን ገትሮ ሲከራከርለት እግዚአብሔር ከሰማይ የላከለት መልአክ መሰለው፡፡

ዳኛው ለተቃውሞው ምላሽ ሰጡ፡፡ "የፍርድ ቤቱን ሰዓት ከመቆጠብ አንፃር ምስክሮች አላስፈላጊ ቃላትን በማስወገድ ያለ ምንም መሸማቀቅ የሚያውቁትን ብቻ ለፍርድ ቤቱ እንዲያስረዱ እጠይቃለሁ፡፡"

እንደገና ብድግ አለና "ተቃውሞ ክቡር ፍርድ ቤት! ምስክሩ ሙሉ ጤነኛ መሆን አለመሆናቸውም ግምት ውስጥ ይግባልኝ፡፡" ሲል አቃቤ ሕግ ጠየቀ፡፡

"ምስክሬ አቶ ተዘራ ቁሜ ከጤነኛ ሰው አመለካከት ውጪ ያሳዩት ጠባይ የለም ክቡር ፍርድ ቤት፡፡ ጥያቄዬን ጨርሻለሁ፡፡" ጠበቃ ተበጀ በአሸናፊነት መንፈስ ምስክሩን አመስግኖ ተቀመጠ፡፡

"አቃቤ ህግ መስቀለኛ ጥያቄ ካለህ እንድታቀርብ እጠይቃለሁ፡፡" ሲሉ ዳኛው ወደ አቃቤ ህጉ ተመለከቱ፡፡

"አመሰግናለሁ ክቡር ፍርድ ቤት!" በማለት አቃቤ ህጉ ተነሳና ተዘራን በመስቀለኛ ጥያቄ ያዋክበው ጀመር፡፡ "አቶ ተዘራ! ... ቅድም ስትመሰክር ሰዓት እንዳልያዝክና መቁጠርም እንደማትችል ገልፀህ ነበር፡፡ ታዲያ አባ

ሰቢጋዲስ አንተ ወደ ቤት ከሄድክ በኋላ በሌላ ታሽጎ ተመልሰክ እንደመጣክስ?"

"እንደተለመደው ደንገዝገዝ ሲል ሁሉም ባለታንኪ ታንኪውን ፍር አለደው ወደ ቤቱ ይገባል፡፡ እንዲያውም ከባለታንኪዎች ሁሉ በመጨረሻ ወደ ቤት የገባሁት እኔ ነበርኩ፡፡"

"ከገዳው ወጥተው ሲሄዱ ይነጋገሩ ነበር ብለሃል፡፡ እንዲያው የጠብ የሚመስል የቃላት ልውውጥ ሰምተሃል?" ኢዮብ ሆነ ቀጠለ፡፡

"እረ በፍጹም! አባ ሰቢጋዲስ ድምፃቸውን ከፍ አርገው የሚነጋገሩት ልማድ የላቸውም፡፡ እንዲህ ከሩቅ ከቅርብም በውል አይሰሙም፡፡" ሲል ተዘራ አስረግጦ ተናገረ፡፡

"የይግባኝ ባይ ጠበቃ ድጋሚ 'ጥያቄ አለህ?' ሲሉ ዳኛው ጠየቁ፡፡

"የለኝም ክቡር ፍርድ ቤት!" ጠበቃ ተበጀ ለዳኛው ለተወረወረለት ጥያቄ ምላሽ ሰጠ፡፡ በማስከተልም ሁለተኛ ምስክሩን እንዲያቀርብ ጠየቁ፡፡

ሥነ-ሥርዓት አስከባሪው ወደ ውጭ ወጣ ብሎ የሁለተኛዋን ምስክር ስም ተጣራ፡፡ መስከረም ሳታስበው ስሟ ስለተጠራ ስውነቷን አለበትረበ እንደያዛት ነዘራት፡፡ ምን ማለት እንዳለባት ስታስበውና ስትከልሰው የነበረው የሀሳብ ካብ ሁሉ ተናናደባት፡፡ ጫን ጫን እየተነፈሰች ገባች፡፡ የሁሉም ዓይን ሲያርፍባት እግሯ ሽብረክ ሽብረክ አለ፡፡ ሽባ ሆነች፡፡ ዓይኗን ጨፍና ገለጠችው፡፡ ራሷን በራሷ መምከር ጀመረች፡፡ 'አይዞሽ!'

ከምስክር መሰየሚያው ወንበር ላይ ስትሆን ትንሽ መረጋጋት ጀመረች፡፡ የዚያ ሁሉ ሰው ድባ የሚመስል ዓይን ከዓይኖቿ ሲቸናከር ያንገሯግባት መሰለት፡፡ ነፍሷ በእግዚአብሔር ደጅ ለፍርድ የቀረበች መሰላት፡፡ በውስጧ ያለው የሀሳብ ውዥንብር እየለባት፡፡ ልቧ በመንታ ሀሳቦች መካከል ይዋልል ጀመር፡፡ "እናት" እና "እውነት"

የዘጠኝ ወር ቤቷ፣ አባትም እናትም ሆና፣ ደሟን አጥብታ ያሳደገቻት እናቷ ላይ አስፈርዳ ለዘለዓለም ወህኒ ቤት ልታበስብሳት ፈራች፡፡



የታሰት የወጣችው የእናቷ እንሽርት ውሃ፣ አቁሰላው የወጣችው የማህፀኗ ግድግዳ፣ ትትታው የወጣችው እትብቷ ታየት፡፡

የጨርቋ የማጠቢያትን ሰዓት፣ በምጥ ያስለቀሰቻትን እንባ፣ በጨቅላነቷ ሳትታፈን፣ ሳትጠበስ፣ አካለ ጎደሎ ሳትሆን ያሳደገቻት፣ ጠላ ሸጣ፣ ዘንቦልባ አሸሩሩ ብላ ያሳደገቻት፣ ወገቧ ላይ እየሸናች፣ እሊጋዋን እየበጠበጠች..... ያሳደገቻት እናቷ ተፈርዶባት ወህኒ ቤት ዕድሜ ልኳን ስትማቅቅ ... ራሷን ከበዳት፡፡

ሕዝቡ ከእርሷ አፍ የሚወጣውን ቃል ይጠባበቃል፡፡

"እውነት ለመመስከር፣ በሀሰት ላለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ቃል እገባለሁ፡፡" ብላ የተለመደውን መሃላ በዳኛው መሪነት ፈፀመች-መስከረም፡፡

"ወይዘሪት መስከረም!" ሲሉ ዳኛው ወደ ጥያቄያቸው ገቡ፡፡

"አቤት?"

"ከይግባኝ ባይ ጠብ፣ ዝምድና አለሽ?"

"ዝምድና አለኝ፣ የእንጀራ አባቴ ነው፡፡ ጠብ ግን የለኝም፡፡"

"የይግባኝ ባይ ጠበቃ ጥያቄዎችህን ማቅረብ ትችላለህ፡፡"

"አመሰግናለሁ ክቡር ፍርድ ቤት፡፡" ሲል ጠበቃ ተበጀ ፊቱ እንደ መስከረም አደይ እየፈካ ተነሳ፡፡

"ወይዘሪት መስከረም፣ በዚያች ምሽት የት ነበርሽ?"

"ከትምህርት ቤት ስንብቴ ከባህርዳር ተነስቼ ደብረ ማርያም" እናቴ ቤት የገባሁት በጊዜ ቢሆንም እንቅልፍ የወሰደኝ ወዲያው ነበር፡፡ ከጨለመ በኋላ አንድ የጓዕር ድምፅ ከእንቅልፌ ቀሰቀሰኝ፡፡ ባንኜ ስነቃ አባ ሰባጋዲስ በወገባቸው ዙሪያ በሚጠመጥሙት ቅናት ከምሰሶው ጋር ታስረው እንዲናገሩ ሲጠየቁ አየሁ፡፡" ብላ ዝም አለች፡፡

"ምንድን ነበር እንዲናገሩ ሲጠየቁት የነበር?" ሲል ጠበቃው ቀለል ባለ ድምፅ ጠየቃት፡፡

“እናቴ ይቅርታ! አሁን የምመሰክረው ስለእውነት ብቻ ነው!” ዕንባዋን መቆጣጠር ስላልቻለች በባይሉባዋ ትጠራርግ ጀመር። ዳኛው አስቆሟትና እንድትረጋጋ ጠየቁ።

“ተቃውሞ አለኝ ክቡር ፍርድ ቤት!” ሲል አቃቤ ህጉ ብድግ አለ። “መስካሪዋ ተገዳ ወላጅ እናቷ ላይ ልትመሰክር ስለቀረበች የምስክርነት ቃሏን እንዳትሰጥ ይከልከልልኝ።”

“እኔ ማንንም ሳያስገድደኝ ለእውነት ስል ብቻ ነው የምናገረው” ስትል መስከረም አቃቤ-ህጉን አፉን ስታስይዝ ተበጀ በኩራት ተመለከታት።

“ያየሽውን ነገር ብቻ ምንም ሳትፈሪ ተረጋግተሽ መስክሪ። ወይዘሪት መስከረም” ሲሉ ዳኛው አስቀጠሏት።

መርጊያሽ ለሁለተኛ የመከላከያ ምስክርነት ልጇ ስትጠራ በልቧ ትልቅ የደስታና የተስፋ ችቦ ተለኩሶ ነበር። አሁንም ጭራሽ አልጠፋም። ግን ፈራች። ልጇ ስታለቅስ እሷም ልታለቅስ ሞከረች። ግን ውሃ ፈልቆበት እንደማያውቅ በረሃ ዓይኗ ከሮ ዝም አለ።

“በዚያች ምሽት እናቴ መሆንሽን ተጠራጥሬ ነበር። መጥረቢያ ይዞ ‘ቅርሶቹ የተደበቁባቸውንና ታቦታቱ የት እንዳሉ ያመላክቱኝ! ቁልፉ ካሁን ሰዓት ጀምሮ በቁጥጥሬ ሥር ነው!’ እያለ ሲያስጨንቃቸው ከጎኑ ቆመሽ ነበር። እኔን ከእንቅልፌ መንቃቴን የተገነዘብሽው ግን በኋላ ነው። በፋስ ግንባራቸውን ሲፈልጣቸው መቀነትሽን ፈተሽ አፋቸው ውስጥ እንዳይጮኹ ጠቅጥቀሽ በክላሹ መትቶ እንዲጨርሳቸው ነገርሽው። እሱግን አልሰማሽም። ትንሽ ርህራሄ የላችሁም ነበር። በመጨረሻ ለጋን መነለቻ ብለሽ ከዋሸሽልኝ ትልቅ ከግድግዳው ጥግ የተቆፈረ ጉድጓድ ውስጥ አብራችሁ ስትቀብሯቸው አይቻለሁ። የናንተ ልብስ ደም ነክቶት ስለነበር አቃጠላችሁት። እኔ ራሴን ስቼ በመጮሄ ውሃ አምጥታችሁ ስትደፉብኝ በሰመመን ውስጥ ነበርኩ። ከዚያ በኋላ ያለውን አላውቅም።” ብላ ስትጨርስ መርጊያሽ በጣም ጮክ ብላ የማይሰማ ነገር እንደቅዥ በመለፍለፏ ደንብ አስከባሪው ቀርቦ ፀጥ አሰኛት።



ጠበቃው አቶ ተበጀ ይህን ያህል ነገር ይቅርና ሁለት ቃላትም ትናገራለች ብሎ ያልገመታት ልጅ እስከአሁን ለፖሊስም ሆነ ለእርሱ ያልሰጠችውን እምቅ ምስጢር በማፍሰሷ ሁሉም ግራ ተጋቡ።

“እብሪት በመጥረቢያ ይከተክታቸው የነበረው ሰው ማን ነው?” ሲል ረጋ ብሎ ጠየቃት- ተበጀ።

“መጀመሪያ አላየሁትም ነበር።” መስከረም በረጅሙ ተነፈሰች።

“ለምን?”

“በምናምንቴ ጨርቅ ፊቱን ሸፍኖ ነበር። በኋላ ግን ፊቱን ሁሉ ደም ረጭቶት ስለነበር ጨርቁንና የለበሰውን ኮትና ሱሪ አውልቆ ከቀሚሷ ጋር አቃጠለው። እኔ ራሴን ስቼ በመውደቄ ውሃ እያመጡ ሲደፉብኝ እሱ ማን እንደሆነ ለይቸዋለሁ። አስተዳዳሪው፣ ሲቀመንበር ተብዬው፣ እናቴን ለዚህ ሁሉ ወንጀል ያበቃት በግራዋ በኩል እንደሰይጣን የተቀመጠው አዳምጠው ነው።”

“ክቡር ፍርድ ቤት! ይህን የፍርድ ቤት ሥነ-ሥርዓት መጣስ እንዲያይልኝ እጠይቃለሁ።!” አቃቤ-ህጉ ተንጨረጨረ።

“እንዴውም ያንሰዋል። ሰይጣንን የማውቀው በወሬ ነው፣ አላየሁትም። ሰው ሲከተክት በአፍቅሮ - ንዋይ ቅርስ ሸጦ ሲያውም አስተዳድር፣ ሀገር ጠብቅ ተብሎ የተሾመው የሚጠብቀውን ቅርስ ሸጦ ሲጠግብ፣ ያለ ርህራሄ ሰው እንደፍልጥ ሲፈልጥ ያየሁት እሱ ሰይጣንም መባል ያንሰዋል! ሳጥናኤልስ ከክብሩ የተዋረደው ልፍጠር ብሎ በፈጣሪ ስራ በመግባቱ እንጂ የአምላክን ፍጡር የፈጣሪን እጅ ሥራ ሲያፈርስ ተገኝቶ አይደለም! ሳይማር ሳያውቅ በአፈቀላጤነት በምላስ መሾሙን አባ ሰባጋዲስ እንደተቃወሙትም ሰምቻለሁ። ይህ ሳያንሰው ያለኃጢአቱ የእናቴን ሕጋዊ ባለቤት የእሷን ልብ ግሎ በውሸት እንድትወነጅለው አድርጎ፣ እሱ መደብደብ ሲገባው በደለኛ ወንጀለኛ ያልሆነውን ንፁሁን ሰው ማንንም በአካፋና በዶማ እንዲቀጠቀጠው

Scanned with CamScanner

አደረገ። እሱ እስር ቤት ሲገባለት እናቴን ማላገጫው አደረጋት። ቀዬው ሁሉ የሚያወራው የእሱን ተከርቸምነትና የእሷን ትዳሯን ፊታ ተከርችም ማስገባት ነው። እኔም የዚህ አስፀያፊ ቤተሰብ አባል በመሆኔ አንገቴን ደፍቼ እንድሄድ ሆኛለሁ። በዚህ ላይ እኔና አሉላ የተቃውሞ ሀሳባችን አቅርበን እንድታቆም ብንነግራት አሉላን በመርዝ ገድላ ወንዝ ከተተችው..." ብላ ሳትጨርስ

"እኔ ግን አለሁ! እግዚአብሔር ይመስገን በእህቴ ትልቅ መስዋዕትነትና እርዳታ ከሞት አፍ አምልጫለሁ!" ብሎ አሉላ ከተመልካቹ ሕዝብ መሀል ቆመ። ሕግ አስከባሪው ሮጦ ሄዶ ሁለተኛ እንዳይናገር አስጠንቅቆ አስቀመጠው።

መርጊያሽና አዳምጠው ተያዩ። ያሉት በህልም ዓለም እንጂ በእውነተኛዋ እነሱ እንደልባቸው ያስሩ ይፈቱባት በነበረችው የግላቸው ዓለም ውስጥ መኖራቸውን ተጠራጠሩ።

"ከዚህ ውጭ ያየሽው ይኖራል?" በማለት ጠበቃ ተበጀ በኩራት ጠየቀ።

"ከበቂ በላይ ካልሆነ ይኖራል!" አለች ንግግሯን ስትጀምር። "ይኸው አስተዳዳሪያችን በተደጋጋሚ የሚፈፅማቸው ቅሌቶች ሳያንሱ የቀበሌው ማህተምና ሌሎች ንብረቶችን ከቤት ጥሎአቸው ይሄዳል። ጥይቶች ሳይቀሩ። ለመረጃ ይጠቅማል ብዬ የያዝኩትን ማህተም ወደዚህ ፍርድ ቤት ደብቄ በማስገባቴ ይቅርታ እጠይቃለሁ። በዚህ ማህተም የመንግሥት ንብረት የሀገር ቅርስና የወገን ሀብት ሊመዘበርበት ይችላል። እባካችሁ ካሁን በኋላ ጥንቁቅ ሰው በመብራት ተፈልጎ ይያዘው። ሌላው የቤተክርስቲያን ቁልፍ እርሱው ዘራፊ እርሱው ፈላጊ እርሱው አግኚ ሆኖ ሕዝብ ሰብስቦ ለምን እንደዚያ እንዳደረገ ባላውቅም ከህዝብ መሀል በጉትጎታ ዘመዱ ቄስ ፀሐይን አስመርጦ ቁልፍ ሰጠው። 'ዘወር አሉ እንጂ አልሸሹም' እንደሚባለው ለጥንቃቄ ከእጁ የወጣ ቢመስልም ከቄሱ ተቀብሎ ወይም አስከፍቶ ይሁን አላውቅም በሶስት ሳጥን የቤተክርስቲያን ንዋዩ



ቅድሳትና ዘመን የማይሽራቸው ቅርሶችን ቤት ውስጥ አይቼ ነበር።
በኢግዚቢትነት እንደተያዙ ሰምቻለሁ። ቢቃኝ!" ብላ በረጅሙ ተንፍሳ ዝም
አለች። ዳኛ ፈዘው እያዩ ዝም አሉ። አቃቤ ህጉም ምንም ዓይነት ቃል
ትንፍሽ አላለም። አቀቤ ህጉ ዓይኖቹን ወደነ መርጊያሽ አዞረ።

ዳኛው አቃቤ ህግ መስቀለኛ ጥያቄ እንዲያቀርብ ፈቀዱለት።
"አመሰግናለሁ! ክቡር ፍርድ ቤት!.....ወይዘሪት መስከረም ... ራስሽን ስትሸ
ባለሽበት ሰዓት ከእናትሽ ጋር የነበረው ሰው አቶ አዳምጠው እንደነበር
እንዴት ልታስተውይ ቻልሽ"
"ውሃ ደፍተውብኝ ስለነበር ትንሽ ወደ አዕምሮዬም ተመልሼ ስለነበር
የሰውየውን ማንነት ለማወቅ አላዳገተኝም።"
"ጨርሻለሁ ክቡር ፍርድ ቤት" አቃቤ ህጉ ስሜቱ ቀዝቅዞ ተቀመጠ።
"ድጋሚ ጥያቄ ከአለህ የይግባኝ ባይ ጠበቃ" ዳኛው ወደ ጠበቃ ተበጀ
ተመለከቱ።
"የለኝም። ክቡር ፍርድ ቤት!" ጠበቃ ተበጀ በቂ እንደሆነ አምኗል።
ዳኛው የፍርድ ቤቱን የማጣሪያ ጥያቄ አስከተሉ።
"ወ/ሪት መስከረም ሰውየው በምናምን ነገር ፊቱን ሸፍኖ ነበር ብለሻል
እንዴት ልትለይው ቻልሽ?"
"በኋላ ፊቱን የሸፈነበትን ጨርቅ አውልቆ ሲያቃጥል አይቼዋለሁ።" ስት
መስከረም ፈርጠም ብላ መለሰች።

ተበጀ ሶስተኛውን የመከላከያ ምስክር ለማቅረብ እንዲፈቀድለት ጠየቀ።

እማሆይ ጦቢያ ከቆረቡ ከፀደቁ በኋላ ከዓለማዊ ፍርድ ፊት መቆ
ባይወዱትም ግድ ስለሆነባቸው ከደብረ ማርያም አንስተው ፍርድ
ድረስ መጥተዋል። ከውጭ ቀስ እያሉ ተራምደው ገብተው
መሰየሚያው መንበር ላይ ሆኑ። መሀላውንም ፈጸሙ።

"ስለአባ ስባጋዲስ ግድያ ያዩትንና ያወቁትን ለፍርድ ቤቱ አስረዱ።"
ጠበቃው በአክብሮት ጠየቃቸው። ድምፁን ዘለግ አርጉ።

"ስመሆኑ እርሳቸው በጠፉበት ሌሊት ይብልጣል የት ነበረና? እ? በነጋታው የአቡዬ ፀበል ስለነበራቸው ከድግሱ የመርጊያሽን ዘመዶች ሲጠሩ ወደ ደጋው ሄዶ ነበር። እኔ በዚያ ምሽት አሳት ልጭር ወደ ቤት ብሄድ በቀን ሲገቡ ስላየሁ ተጠራጠርኩ። ሳስተውል እርሳቸው ናቸው። እርሳቸው ወደ ቤት ከመግባታቸው በፊት በአጥሩ ሾልኮ ሲገባ አዳምጠውን አይቸዋለሁ። በኋላ ከፊታቸው መጥረቢያ ይዞ 'ቁልፉን ይስጡኝ፣ ታቦታቱ የት እንደተቀበሩ አመላክቱኝ' እያለ ሲያናዝዛቸው ሰማሁ። ፊቱ ግን ተሸፍኗል። እኔ የአዳምጠው ድምፅ ይቅርና የመንደሩን ሰው ድምፅ እለያለሁ። ድምፁ የአዳምጠው ነው። 'አበስኩ ገበርኩ' ከዚህ በላይ ግን አላውቅም። መስከረሜ ታማ መጥታ ራሷን ስታ ስለነበር ከኔ ቤት ተኝታ ድናለች። በኋላም አሉላ ከሞት ተርፎ ከቤቱ ድኖ ጠፍቷል። አሁን ግን በዓይኔ አየሁት። ወይ ጉድ እቴ! ይህን ያህል መከራ ከማይ እድሜዬን ቢያሳጥረው ምናለበት እናተ ሆዬ..." ብለው ሳይጨርሱ ጠበቃው "ጨርሻለሁ!" ብሎ በደስታ ፈገግ አለ።

"አቃቤ ህግ መስቀለኛ ጥያቄ አለህ? ማስማት ትችላለህ"
"አመሰግናለሁ። በድምፅ ብቻ እንጂ በዓይኖት አላዩትም ሁለተኛውን ግለሰብ ታዲያ እንዴት አቶ አዳምጠው መሆኑን እርግጠኛ ስመሆን ቻሉ? በዛ ላይ ጆሮዎትን ያከራክረዎታል አይደለም?"
"ወደ ቤት በአጥር ሾልኮ ሲገባ አይቼዋለሁ ደግሞም አስተዳዳሪያችን ስለሆነ ድምጹን በደንብ ለየዋለሁ ጆሮየም ቢሆን አያከራክረኝም። የዓለምን ነገር ክፉ በጎውን ለመስማት ስል ያከራክረኛል እላቸዋለሁ። አትሰማም እያሉ ሰዎች እኔ ጥግ ሆነው ስለ እኔ የሚያንሾካሽኩትን ሁሉ እሰማለሁ። በዚህም አጥብቄ ስለ ሰዎች ጠባይና ሰዎች ስለ እኔ ያላቸውን ምልከታ ተምሬበታለሁ። ይህችን ዘዴ ያስተማሩኝ አያቴ ናቸው። ከዚህ በኋላ ግን የተማርኩት ይበቃኛል። ስለ ራሴም ከበቂ በላይ ተምሬ ጠግቤአለሁ። ደብረ ማርያም እንግዲህ እርምህን አውጣ። ያልከኝን ሁሉ ሰምቻለሁ።



እንዳያውም ጆሮዬ ቶቅ ነው።" አዳራሹ በጉምጉምታ ተዋጠ። የሳቀም አልታጣም። ዳኛው በመዶሻቸው ጠረጴዛውን ደልቀው ፀጥ አሰኙት። አቃቤ ህጉ "ጨርሻለሁ" ብሎ ተቀመጠ። ዳኛውና የይግባኝ ባይ ጠበቃ የሚያነሷቸው ጥያቄዎችም አልነበሩም።

በመጨረሻ አቃቤ ሕጉ ለሁሉም ምስክሮች በደንቡ መሠረት የሚቀርበውን መስቀለኛ ጥያቄ የለኝም በማለቱ ምስክሮች ተሰናበቱ።

ዳኛው መነፅራቸውን ረዥም አፍንጫቸው ላይ አስተካክለው "በቀረበው ይግባኝ ላይ ቀደም ሲል የታች ፍርድ ቤት የወሰነውን ውሳኔና በዚህ ፍርድ ቤት የቀረቡትን አዳዲስ የመከላከያ ማስረጃዎች አድምጠናል። ወደ ውሳኔ ከማምራታችን በፊት አቃቤ ህግ የምትለው ነገር ካለ።" ሲሉ ዕድል ሰጡ።

አቃቤ ህጉም ዳኛውን እጅ ነስቶ "በመጀመሪያ ፍርድ ቤት አቃቤ ህግ ያቀረበው ማስረጃ እንደሚያመክተው የአሁን ይግባኝ ባይ አቶ ይብልጣልን እጅ ከፍንጅ አገኘኋቸው ብሎ ክስ መመስረቱን፣ ያለ ተጨማሪ ማስረጃና በአቶ ይብልጣል በኩልም መከላከያ ማጣት ምክንያት የእድሜ ልክ ጽኑ እስራት መወሰኑ ይታወሳል። ሆኖም አሁን የመጡት የመከላከያ ምስክሮች እንዳስረዱት ከሆነ ደግሞ ጥፋተኝነቱ ወደ ሌላ አካል እየተላለፈ በመሆኑ ተጨማሪ ቀጠሮ ተሰጥቶ በተነሱት ሀሳቦች ላይ ምርመራዬን አጣርቼ እንድቀርብ ይፈቀድልኝ" ብሎ ጠየቀ።
"የይግባኝ ባይ ጠበቃ የምትለው ነገር አለ?" ሲሉ ዳኛው ጠየቁ።

ስፊ የማስታወሻ ደብተር በያዘው ጠበቃ ላይ የሁሉም ዓይን አፈጠጠ። ዳኛውን እጅ ነስቶ ንግግሩን ቀጠለ።

"አቃቤ ሕጉ፣ ከአሁን በፊት ውሳኔ ሲሰጥ ከምንም ተነስተው ያቀረቡት እንቶፈንቶ ክስና ዘግናኝ የመፋረጃ ሀሳብ እውነቱን ሳላወቁ ይበል አሰኝቶ ነበር። ዛሬ ግን እውነት ራሷ ከተደበቀችበት ወጥታ በሁላችን ጆሮ ተሰማች። ከወንጀሉ አስከፊነት ይልቅ የውንጀላው ዘግናኝነት ይበልጣል።

የተጣለባቸው ሰው፣ አደራ እምነት በመንግሥት ተብለው አስተዳዳሪ ውስጥ በመሬት በባዕዳን በላይ ከምንም ቅርስ፣ የወገን የሀገር በልተው፣ ወርቅ ሰጥተው አመድ ሳይበቃ መመዝበሩ ሀብታችን የተዳፈነው ሁሉ ይህ ሲሸጥ፣ ጥቅሙ ለግል ሀብታችን አንጡራ ባዕዳን ለሚወስዱብን ባዘጋጃቸው ጭምር ቤቱን ፍርድ ሸጉጦ ውስጥ በንፁሃን ራሱን ሳያንስ ማቅረብ ለሕግ በአግባቡ እንኳን ቢሆን ወንጀለኛ አሳሳተ። አፈሙሴዎቹ ማስረጃ በህኪም አድርሶበት ድብደባ ከባድ ዘግናኝና ላይ በአካሉ ሲቻል ሆነዋል።ባ ውጭ ከጥቅም እጆቹ ሁለት ይበልጣል አቶ ተከሳሽ መሠረት የለውም። እጅ የሚጎርስበት ቆርሶ እንኳ እህል ይበልጣል አቶ ከእንግዲህ ከዚህም ተደረገበት። ሙከራ የመግደል ውስጥ ቤት በማረሚያ ሳያንስ ይህ ሁሉ እነዚህን ተደረገ። ሙከራ የግድያ ላይ ልጁ ባለው ጠባቂ ባድማ ሌላ የመፋረጃ ሕጉን የአቃቤ አስገብቶ ውስጥ ግንዛቤ ቤቱ ፍርድ ክቡር ሁሉ ጉዳት ለደረሰበት ባሻገር ከመልቀቅ በነፃ ተከሳሹን በማነጻጸር ሀሳብም ላይ በተጠርጣሪዎቹ በመወሰን እንዲከፈለው ካሣውንም የህይወት በትህትና እንዲሰጥልኝ ውሳኔ የፍርድ የሆነ ርቱዕ ትክክለኛውና እጠይቃለሁ!" በማለት ንግግሩን ፈፀመ።

ይበልጣል እጆቹን ወደ ላይ ዘርግቶ ፈጣሪውን ሲያመሰግን ቢል አቅም አጠረው። እነዛ የጣና ሐይቅን የቀዘፉ ጠንካራ ክንዶቹ መንቀሳቀስ አቃታቸው። የፍትሕ ጮራ በዛ ትንሽ አዳራሽ ፈንጥቆ ተፈርዶለት ሲወጣ ተጠባበቀ።

"ለትክክለኛ ፍትህ ሲባልና አዲስ የተያዙትን ጭብጦች ከሁለቱም ወገን ከማጣራት አንፃር ተለዋጭ ቀጠሮ ያስፈልገናል።" ዳኛው መደሻቸውን አነሱ።



# ፴፩

የፍርድ ቤቱ የውሳኔ ቀን እስኪደርስ መላ የደብረ ማርያም ህዝብ ለመቁነጥነጥ ላይ ነው፡፡

የአዳምጠው ተከርቸምነት ጉድ ማስባሉ ዘብጥያ በመውረዱ ተተክቷል፡፡ በተለይም የቄስ ፀሐይ ነገር አገሩን አስገርሟል፡፡ መርጊያሽ የመንደሩ ሴቶች አፍ ማላወሻ ሆናለች፡፡ የእማሆይ ጠቢያ ነገር ግን ትንግርት ሆኖ ነው የሰነበተ፡፡
"ይገርማል! እስካሁን ያማናቸውን ሁሉ ለካስ ሲሰሙን ነበር፡፡ ወይ ትንግርት!" ይላል አንዱ፡፡

"ስለራስ ካወቁ አይቀር እንዲህ ነው! ግን እንዴት አስቻላቸው? ይህን ያህል ዘመን ክፉ በጎ እየሰማ ዝም ማለት የሚችል ጆሮ ማን አለው?" ይላል ሌላው።

የመስከረም በእናቷ ላይ መመስከርም ጉድ ሲያስብል ነበር የሰነበተ። ዘውዱ በበኩሉ "ከተልባ ጋር ያለህ ሰሊጥ፣ አብረህ ተወቀጥ" የሚለውን ብሂል ተርቶ የደረሰበት ጠፍቷል። 'ወይ እንደ ወንድሞቼ እኔም ዘብጥያ እወርዳለሁ ወይም መስከረም በአስገድዶ መድፈር ትከሰኝና እሥር ቤት እበሰብሳለሁ' ብሎ ፈርቶ ይሆናል ስትል መስከረም አስባለች፡፡

ሰሞኑን አሉላና መስከረም የሚያብሰለስሉት የፍርዱን ጉዳይ ነው፡፡ "እነ አዳምጠው እንደለመዱት በገንዘብ ዳኞችን ደልለው ነፃ ይወጡ ይሆን?" ትላለች መስከረም አልፎ አልፎ፡፡

"መሞከራቸውማ የት ይቀራል! ሆኖም የደነገጡ ይመስለኛል፡፡ የደብረ ማርያም ህዝብም ቢመለሱ በመጥረጊያ እንደ አይጥ የሚያባርራቸው ይመስለኛል፡፡" ይላታል አሉላ፡፡ "ይህም ቢሆን ሁሉ ነገር ገና ውሉ አልታወቀም፡፡ ዳኛው የመጨረሻውን ውሳኔ ሰጥተው ጠረጴዛውን በዶሻቸው እስኪወግሩ ማንም በምንም እርግጠኛ መሆን አይችልም፡፡"

ፀሐይ በጣና ምስራቃዊ ገመገሞች ልትጠልቅ ስታዘቀዝቅ፣ አሉላ፣ አባ ሰባጋዲስ ዙትር ይቆሙባት ከነበረችው አለት ላይ ቆሞ ይመለከታት ጀመር፡፡

ጀምበሯን ሲመለከት ቆይቶ "ገፀ አባ ሰባጋዲስ"ን ገልጦ ያነብ ጀመር ካቆመበት፡፡

"ዓባይ እንደዘንዶ ቁልቁል ሲጥመለመል እኔና እሷን ማዶና ማዶ የሁለት ዓለም ሰዎች እንዳደረገን ቢያውቅ ኖሮ ወዲያውኑ በደረቀ ነበር፡፡ እኔ ወዲህ ማዶ መቁለጭለጬን ቀጠልኩ፡፡ እሷም ከወዲያ ማዶ ዓይኖቿን እንደተከለችብኝ ናት፡፡ 'ስ ስ ስ ስ ስ ...' ብዬ ስሟን ልጠይቃት ስል አፌ ተሳሰረብኝ፡፡ የወንዙ ፏፏቴ እንኳን በዚህ አቅሜ ጎሮሮዬ እስኪሰነጠቅ ብጮህ እንኳ የሚያደማምጥ አይደለም፡፡ የእሷ ድምጽ ግን ወደ እኔ መጣ፡፡ ዝማሬ የሚመስል ድምፅ፡፡
'መዋኘት አትችልም እንዴ?' የሚል ስርቅርቅ ድምጿ ነበር የተሰማኝ፡፡ የገደል ማሚቶው ደጋግሞ ድምጿን አሰማኝ፡፡ 'መዋኘት አትችልም እንዴ? ... መዋኘት አትችልም እንዴ? ... መዋኘት ...' ማሚቶዎች ድምጿን አላመጡት፡፡ 'ምን ማለቷ ነው?' ስል አሰብኩ፡፡ 'በዋና እንገናኝ ማለቷ ነዋ!' ህሊናዬ መለሰልኝ፡፡ 'እኔ ውስጥ ያለው ምትሀት እሷም ውስጥ ተፈጥሯል ማለት ነው?' ስል እንደገና ራሴን ጠየኩት፡፡ 'በደንብ እንጂ!' እንደገና ህሊናዬ መለሰልኝ፡፡
'እችላለሁ!' ስል ድምፄን ዝግ አድርጌ መለስኩላት መንተፍረቴን፡፡ የኔንም ድምጽ ተራሮች ተቀባበሉት፤ የገደል ማሚቶዎች አልጎመጎሙት፡፡ 'እችላለሁ! እችላለሁ! እችላለሁ! ... እችላለሁ! እችላለሁ! እች ...' ውሃ



መቅጃዋን ስታወርድ አየኋት፡፡ ቀሚሷን ስታወልቅ ማመን አቃተኝ፡፡ አበባ የመሰለ ሰውነቷን የምሽቷ ጀምበር ጨረሮች ተበተኑበት፡፡ እኔም ልብሴን አውልቄ ፈረሰኛውን ተክሎ ወደሚጋልበው ወንዝ ተጠጋሁ፡፡

ምንም ሌላ ቃል ሳትናገረኝ ቁልቁል በኃይለኛ ፍጥነት ወደሚጥመለመለው ውሃ ሙላት ገብታ እጆቿን ማወናጨፍ ጀመረች፡፡ እኔም ዘልዬ ተደረገምኩ፡፡ ከወዲያ ወዲህ ያላጋኝ ጀመር፡፡ ጥቂት ኳፍጨ ቀና ስል ከላይ የውሃው ሙላት ግድግዳ መስሎ ቁልቁል ሲምዘገዘግ ታየኝ፡፡ የዛፍ ቅርንጫፎችን ከመጤፍ ሳይቆጥር ከፊት ለፊት እየነዳ ሳያችን ላይ ሊከነበል እየተቃረበ ነው፡፡ ከአንገቴ ቀና ብዬ በዓይኖቼ ፈለኳት፡፡ ወደ እኔ እየገሰገሰች ነው፡፡ ኃይለኛ ሙላት ከወዲያ ወዲህ ያላትማታል፡፡

'እምልጪ!' ስል ጮህኩ፡፡ 'እምልጪ! እምልጪ!' የሚመጣውን ግድግዳ የመሰለ ውሃ ሙላት በዓይኔ አሳየኋት፡፡ እሷ ግን ወደ ኋላ አልተመለሰችም፡፡ እንኳን ልትመለስ ወደ ኋላዋ እንኳ ዞራ አልተመለከተችም፡፡ እኔም ወደ እሷ እሷም ወደኔ እንዛግጥ ጀመር፤ ለረጅም ደቂቃዎች ከታላቁ ወንዝ ጋር ትግላችን ቀጠለ፡፡

ግድግዳ የመሰለው ውሃ ሙላት ዓይኔ ጥግ ደረሰ፡፡ ትንፋሽ አጠረኝ፡፡ በማላውቀው የፍርሃት ኃይል ወደ እሷ ገሰገስኩ፡፡

እጄ ክንዷን ለመያዝ አልታደለም፡፡ ጣቶቼ ጣቶቿን ሲነኩ ተሰይተው ሙጫ ሲቀራቸው ዓይኖቿ ዓይኖቼን እየተማፀኑ፤ እያየኋት እያየችኝ ሁሉ ነገር ጨላለመ፡፡ ግድግዳ መስሎ የመጣው መዓት ቁልቁል ደፈቀን፡፡ የተቀራረቡ ጣቶቻችን ወዲያና ወዲህ ሲነጣጠሉ ትዝ ይለኛል፡፡ ሄደች፡፡ ቁልቁል ወደ ማልደርሰበት፡፡

በማላውቀው ሁኔታ ከማላቀው ቀየ ሰዎች ደረቴን ተጭነው ውሃ ባፌ ቡልቅ እያለ ሲወጣ ነቃሁ፡፡ ከአያሌ ሰዓታት በኋላ እሷን ውሃ እንደበላት እኔ እንደተረፍኩ ተነገረኝ፡፡ እስከሬኗን ዘመዶቿ

እንደወሰዱትም አረዱኝ፡፡ እነማን ዘመዶቿ እንደሆኑም አላወቅኩም፡፡ ምናለ አስከሬኗን እንኳ መልሼ ባየሁት? ያቺ የዓባይ ዳር አበባ እያየኋት ጠወለገች፡፡ ከዛ ወዲያ ወደ ትውልድ መንደሬ አልተመለስኩም፡፡ እግሬ በመራኝ እንጓዝ ጀመር፡፡ እንዲህ ነው የምነናዬ አጀማመር፡፡" አሉላ የመጽሐፉን ገፅ ዘግቶ አለቱ ላይ በማያውቀው ስሜት ተቀመጠ፡፡ የጀምበሯ ግማሽ አካል በተራራዎች ገመገም መሃል ገብቷል፡፡



# ፴፪

በፍርድ ቤቱ አዳራሽ ውስጥ ጉምጉምታ ይስገመገማል፡፡

"ባለፈው አዳምጠው፣ መርጊያሽና ቄስ ፀሐይ እዚህ ችሎት ቀርበው ሲቀለጨለጩ ነበርክ፡፡"
"በደንብ እንጂ፡፡ መከላከያ አቅርቡ ተብለው አናቀርብም ያሉ ጊዜ?!"
"እጡ እኮ! ለነሱ ተከላካይ ምስክር ከየት ይመጣል?"
"ኧረ ለመሆኑ?!"
"እህ!?"
"አቃቤ ህግ ክስ በነአዳምጠው ላይ ከመሠረተ ለምን ይበልጣልን ፍርድ ቤቱ በነፃ አይለቀውም?"

"ጉዳዩ በደንብ ሳይጣራ? የማይሆነውን ጃል?... ይህ እኮ ከባድ ሀገራዊ ጉዳይ እኮ ነው፡፡ እውነት ከተደበቀችበት ሳትወጣ ማንስ ቢለቀቅ ሀገሬው በጀ ይላል? ... እውነት እንደጮራ ሳትፈነድቅ ማን ሊለቀቅ?"

ሶስቱ ዳኞች ወደ አዳራሹ ሲገቡ ጉምጉምታው ጋብ አለ፡፡ ህዝቡ ቆሞ ተቀበላቸው፡፡ ሲቀመጥም ዓይኖች ሁሉ ዳኞች ላይ እንደተቸናከሩ ነበሩ፡፡

የከሳሽ ተከሳሽ ልቦች ዳንኪራ ይረግጡ ጀመር፡፡ ረጅም ፀጥታ ሰፈነ፡፡ የመሃል ዳኛው ግራና ቀኝ ሲያተቶከቱኩ ቆይተው ጎሮሮአቸውን ጠራረጉ፡፡ ቅንድቦች ሽቅብ ወደ ግንባር ተሸመጠጡ፡፡ የዓይን ሽፋሽፍቶች ተቀነበቡ፡፡

Scanned with CamScanner

"… እ … የጥፋተኝነት ውሳኔ ለመወሰን፣ አቃቤ ህግ የቀረቡትን የመከላከያ ማስረጃዎች እንዲያጣራ ውሳኔ ሰጥተን መለያየታችን ይታወሳል፡፡ በመሆኑም አቃቤ ህግ ያጣራውን ያቀርብ ዘንድ እጠይቃለሁ፡፡"

አቃቤ ህጉ በዝግታ ዓይኖቹን ማስታወሻው ላይ ሳይነቅል ተነሳ፡፡

"… የፖሊስ ምርመራ መዝገቦችንና የመከላከያ ማስረጃዎችን ስንመረምር ቆይተናል፡፡ ይግባኝ ባይ አቶ ይበልጣል በቀረቡበት ማስረጃዎች መሠራት ወንጀሉን አለመፈፀሙንና ከዚህም ጋር በተያያዘ በሌሎች ተጠርጣሪዎች በነአቶ አዳምጠው ላይ አቃቤ ህግ ክስ መሥርቶ፣ መከላከያ እንዲያቀርቡ ክቡር ፍርድ ቤቱ ጠይቆ አለማቅረባቸውም ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ በዚህ ወንጀል ላይ የሚሰጠውን ፍርድ እንጠባበቃለን፡፡" አቃቤ ህጉ ተቀመጠ፡፡

ዳኛው የፍርድ ውሳኔ ለመስጠት ሲዘጋጁ አዳራሹ ፀጥታ ነገሠበት፡፡ የሁሉም ዓይኖች ከዳኛው አፍ ላይ አነጣጠሩ፡፡ የተከራካሪ ልቦች አታሞአቸውን ደለቁ፡፡ የመሃል ዳኛው ፋይሉን አስተካክለው በግራና በቀኝ ካሉ ዳኞች ጋር ሲያንሾከሹኩ ቆይተው መናገር ጀመሩ፡፡

"የቀረበውን ይግባኝ ፍርድ ቤቱ ሲመረምርና ሲከታተል እንዲሁም ሕጋዊ ክርክሩን ሲያዳምጥ ቆይቷል፡፡ ማስረጃዎችም ቀርበዋል፡፡ ከመሠረታዊው ክስ በመነሳት ከሕግ አኳያ ጉዳዩን አጣርቶ ፍትህ ሳያጎል ፍርድ ሳይጣመም የሚከተለውን የፍርድ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡" ተመልካቹ ሁሉ አፉን ከፈተ፡፡ ዳኛው ጥቂት ጥሞና አደረጉ፡፡

"ተከሳሽ አቶ አዳምጠው ካደረገው የቅርስ ዘረፋ፣ የግድያ ሙከራና የነፍስ ግድያ ወንጀል በተጨማሪ ወንጀሉን በሌላ ላይ ጭኖ ፍርድንና ፍርድ ቤቱን ከማሳሳቱ አንፃር እንዲሁም የሰውየውን የሕግ ባለቤት በማማገጥና



በቅሌት መያዝ አንፃር ፍርድ ቤቱ የሞት ቅጣት ወስኖበታል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ ወይዘሮ መርጊያሽ ለወንጀሉ አባሪ ተባባሪ በመሆን፣ በሁለት የግድያ ሙከራና ሌሎችንም ተዛማጅ ወንጀሎች በመፈፀሟ የዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ተወስኖባታል፡፡" ዳኛው ትንፋሽ ወስደው ቀጠሉ፡፡

"አቶ ይበልጣል በነፃ ከመለቀቁም በተጨማሪ ስልሳ ሺህ ብር የካሣ ክፍያ እንዲከፈለው በዛሬው ዕለት ክቡር ፍርድ ቤቱ ወስኖ ፋይሉ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት እንዲመለስ ፍርድ ቤቱ አዟል፡፡ የፍርዱም ግልባጭ ለማረሚያ ቤት እንዲላክና አቶ ይበልጣል እንዲፈታ ትዕዛዝ ሰጥተናል፡፡" ብለው ፋይሉን ዘግተው ጠረጴዛቸውን በመዶሻቸው ደለቁት፡፡

አሉላና መስከረም ወደ ይበልጣል ተሽቀዳደሙ፡፡ ይበልጣል የሲቃ ዕንባ ተናነቀው፡፡ የፍርድ ቤቱ አዳራሽ ድብልቅልቁ ወጣ፡፡ እንደ ሐምሌ ሰማይ ያጉረመርም ገባ፡፡

ከደብረ ማርያም ቀበሌ የመጡ ሽማግሌዎች አሉላን ከበቡት፡፡ ምንም አልተናገሩትም፡፡ የማጭድ ቅርፅ ያለውን ቁልፍ ለአሉላ ሊያስረክቡ ዘረጉለት፡፡ "አታቅማማ! … ይህን ቁልፍ ከአንተ በቀር የሚረከብ አይኖርም ህዝብ ወክሎን ነው አመጣጣችን፡፡" አሉላ መስከረምንና ሽማግሌዎችን አፈራርቆ ተመለከተ፡፡ ወዝ በጠገበ ወፍራም ማተብ የታሰረውን ማጭዴ ቁልፍም ተመለከተ፡፡ ደንግዞ ቆመ፡፡ ግራ ገባው፡፡ መስከረምን እንደገና ተመለከታት፡፡ እሷም ግራ ተጋብታለች፡፡ ወደ ቁልፉ እንደገና አየ፡፡ የአባ ሰባጋዲስ አደራ በአእምሮው አቃጨለ፡፡ በተከርቸሙ የፈረሰው ትዳርና የተወሳሰበው የአባቱ ህይወት በዓይነ ህሊናው ታየው፡፡ በውስጡ ግን እንዲህ ሲል አሰበ፡፡ 'ህገሬም ብዙ ተከርቸሞች እንዲሁ ተከርችመውባታል፡፡' በመጨረሻም ወደ ቁልፉ ተመለከተ፡፡ እጁንም ሰደደ፡፡

ከግርግሩ ፈንጠር ብሎ ገፀ ሰባጋዲስን ገልጦ ለማንበብ ተቻኮለ፡፡ በእጁ ከጨበጠው ቁልፍ በላይ የሚያስፈልገው የሽማግሌው ማስታወሻ

Scanned with CamScanner

እንደሆነ ተገነዘበ፡፡ የሰባጋዲስን መጽሐፍ በመመርመር የሚከፍተው ዋሻ ያጨቃቸው ቅርሶች ለዓይነ ህሊናው ቀረቡ፡፡ እድሜውን ሁሉ እንደ እርሳቸው ከመጻሕፍት ገፆች ጋር እንደትኳን ተጣብቆ ለመኖር ወሰነ፡፡ ህይወቱንም እንደርሳቸው ለዝምታ፣ ለአርምሞ፣ ለተመስጦ ... ለመስጠት ቆረጠ፡፡ 'ይከብድ ይሆናል! ነገር ግን ...አንዳንዴ እኛ ብቻ የምንሸከመው ሸክም አለ፤ ለጥቂት አካላት ብቻ ግዴታ የሆነ አደራ አለ....እንቢ የማይባል፡፡ ወፍራም ጫንቃ ያለው ብቻ የሚችለው፡፡' ሲል ራሱን አሳመነው፡፡ እርሳቸው እንደሚያደርጉትም ጠዋት የምትወጣውን ፀሐይ ለመቀበል ማታ የምትጠልቀውን ጀምበርም ለመሸኘት አሰበ፡፡ ለማለዳ ሰማይ እጁን ሊዘረጋ......በሌሊት ጨረቃ ከዕንቅልፉ ሊነቃ፡፡

# ይስማዕከ ወርቁ














ISBN-978-99944-843-4-7

ዋጋ 160 ብር